# ህያውነት

ኦሾ



@shuktus_books

(The Courage Of Living
Dangerously)

@shuktus_books

# ድፍረት

ደፋር ካልሆናችሁ እውነተኛ ልትሆኑ አትችሉም ፤

ደፋር ካልሆናችሁ አፍቃሪ አትችሉም ፤

ደፋር ካልሆናችሁ የምታምኑ ልትሆኑ አትችሉም ፤

ደፋር ካልሆናችሁ እውነትን ልትመረምሩ አትችሉም ፤

ስለዚህ ከሁሉም ነገር በፊት ድፍረት ይቀድማል፡፡

ኦሾ

## ማውጫ

### መቅድም


- በፍፁም እርግጠኛ የሆነ ሕይወት የለም ! ---------------------------------------- 5

1.ድፍረት ምንድነው ? ---------------------------------------- 8

- ድፍረት ከማይታወቅ ነገር ጋር መጋፈጥና
  -እውነትን መቀበል ነው ---------------------------------------- 10
- የድፍረት መንገድ (ታኦ) -
  -ለመሸነፍ ዝግጁ የሆነ ማንም አያሸንፈው ---------------------------------------- 11
- የልብ መንገድ -
  -ብሬ ምንም ሳይሆን ወደ ነገ የሚደረግ ጉዞ ነው ---------------------------------------- 15
- የብልሆት መንገድ -
  -አዕምሮ ሲጠፋ ነው ምስጢር የሚገባው ---------------------------------------- 24
- የማመን መንገድ -
  -የተከተሉት ማመን፣ እምነት ይሆናል ---------------------------------------- 30
- የየዋሀነት መንገድ -
  -የዋህ ከሆናችሁ ድፍረት አያስፈልጋችሁም ---------------------------------------- 38

2.እንግዳው በራችሁን ሲያንኳኳ ክፈቱለት ---------------------------------------- 53

- የራስ ኩራት ሞት፣ የማንነት ውልደት ነው ---------------------------------------- 54
- በፍቅር መደፈር -
  -ፍርሃትን ፍራ፣ እጦት ማጣት ነው ---------------------------------------- 62
- ፍቅር ግንኙነት ሳይሆን የመሆን ሁኔታ ነው ---------------------------------------- 74







- ወሰን አልባ ዓለም
  -የሚያበስላችሁ የፍቅር እሳት ብቻ ነው ---------------------------------------- 81
- ፍቅር ተዓምር ፤ አስቸጋሪም ሳይሆን ተፈጥሮዊ ነው ---------------------------------------- 85

3.ከህዝብ መሀል ውጡ ---------------------------------------- 91

- ልታውቁት የምትችሉት መታጣት ያለበትን ነው ---------------------------------------- 92
- የቴቄሮች ፖለቲካዊ አስተሳሰብ -
  -የሌሎችን ድጋፍ የሚሹት የሌሎችን አመለካከት የያዙ ብቻ ናቸው ---------------------------------------- 97
- እግዚአብሔር ሰው ሳይሆን ስሜት ነው ስለዚህ
  ውስጣዊ ስሜታችሁን አድምጡ ---------------------------------------- 100
- በዓለም ላይ ታላቁ ፍርሃት ያለው በሌሎች
  አመለካከቶች ውስጥ ነው ---------------------------------------- 104
- ነፃነት - ከነፃነት - ለ -
  -ማንም ከምንም ነገር ኃላፊነት ነፃ አይደለም ---------------------------------------- 106
- ቀናው ፊታችሁን አግኙ -
  -ፈሪ ለመሆን ድፍረት የሌለው እሱ ጀግና ነው ---------------------------------------- 109

4.አደጋ ውስጥ በመኖር የሚገኝ ደስታ ---------------------------------------- 114

- ህያው የምትሆኑት በአደጋ ውስጥ ብቻ ነው ---------------------------------------- 115
- ምንም ብታደርጉ ህይወት ምስጢር ናት ---------------------------------------- 121
- ከየትኛውም ስፍራ ባሻገር የሚታይ ሌላ ስፍራ አለ ---------------------------------------- 123
- ህይወት ሁልጊዜ አይጠብቃችሁም ---------------------------------------- 124
- የመጨረሻው ድፍረት መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ የለውም ---------------------------------------- 129

5.ድፍረትን ፍለጋ—148

- በተመስጦ የማሰላሰል ዘዴዎችና ልምምዶች የተሰጡ ምላሾች - ማንኛውም የታጎተ ነገር ፀፀትን ይፈጥራል—149
- መፍራት ማለት ፍርሃትን መቃረን ነው —151

  የተቀበልነው ፍርሃት ነፃነት ነው —154
- ራስን ማጋለጥ ማለት ባዶነትን ማጋለጥ ነው —159
- የመሰላቸት ስሜት የሚሰማን የተሰጠንን ስርዓት ተከትለን ስለምንኖር ነው —164
- በተመስጦ ማሰላሰል ለባዶነት ፍራቻ —169
- በተመስጦ ማሰላሰል የቀድሞ የፍርሃት ስርዓቶችን ለማሟሟት —171
- በተመስጦ ማሰላሰል ለማመን —173
- በተመስጦ ማሰላሰል ፍርሃትን ወደ ፍቅር ለመቀየር —174
- የመጨረሻው ጥያቄ- ፈሪሀ እግዚአብሔር —177
- ስለ ደራሲው —191





# መቅድም

## በፍጹም እርግጠኛ የሆነ ህይወት የለም!

## ጥርጣሬ ሳይሆን መሻት ብላችሁ ጥሩት፡፡

## ስጋት ሳይሆን ነፃነት ብላችሁ ጥሩት፡፡

ይህን የነፃነት ቀኖና ለሰጣችሁ አልደልም፡ ቀኖና እርግጠኛ ያደርጋል፡፡ በስወደፊቱም ተስፋ ለሰጣችሁ አልደልም፡ የወደፊት ተስፋ ስጋት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ እኔ የምፈልገው ንቁና ጠንቃቃ እንድትሆኑ ነው፡ ስጋት፣ ጥርጣሬ እና አደጋ ከሞላበት ህይወት ጋር አብራችሁ እንድትኖሩ ነው፡፡

ይህን የምታገኙት አንድ የሆነ እርግጠኛ ነገር፣ አንድ የሆነ እምነት ፍለጋ፣ የሆነ የምትጠብቁት፣ የምትተማመኑበት ነገር በመሻታችሁ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ይህን የምታደርጉት ስለፈራችሁ ነው፡፡ ያለ ምንም ንቃት አውቀት መኖር የምትችሉበት አንድ ውብ እስር ቤት እየፈለጋችሁ ነው፡፡

እኔ ግን የበለጠ ስጋት እንዲያድርባችሁ፣ የበለጠ እርግጠኛ እንዳትሆኑ እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም ህይወት እንዲያ ናት፡፡የበለጠ ጥርጣሬ እና አደጋ ሲኖር ይህን መቋቋሚያ ብቸኛው መንገድ ንቃት ይሆናል፡፡ ሕይወት እንደ አንድ ሜካኒካዊ ሂደት እርግጠኛ አይደለችም፣ የማይታሰበ ማስጠራት የሚገለጥባት ናት፡፡ አሁን ምን ሊከሰት እንደሚችል ማንም የሚያውቅ የለም፡፡ በሰባተኛው ሰማይ ይኖራል የሚባለው እግዚአብሄር ምን ሊከሰት እንደሚችል ወይም ምን እንደሚመጣ አስቀድሞ የሚያውቅ ከሆነ፣ ሕይወት የይምሰል ነች ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ነገር ቀድሞ የተሳለ፣ ሁሉም ነገር አስቀድሞ ልክ ፈንታው የሚታወቅ ይሆናል፡፡ መጪው ጊዜ ክፍት ከሆነ ግን ቀጥሎ ምን ሊከሰት እንደሚችል እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

እግዚአብሔር ቀጥሎ የሚከሰተውን ነገር የሚያውቅ ከሆነ ሀይወት ሙት እና ሜካኒካዊ ሂደት ናት ማለት ነው፡፡ እናም ነፃነት አይኖርም፡፡ ሀይወት ደግሞ እንዴት ያለ ነፃነት ትኖራለች? ሁሉም ነገር ቀድሞ የሚታወቅ ከሆነ ክብር እና ታላቅነት አይኖሩም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ እናንተ ልክ እንደ ሮቦት ናችሁ ማለት ነው፡፡

በፍፁም፣ እርግጠኛ የሆነ ሀይወት የለም፡፡ መልዕክቱ ይህ ነው፡፡ እርግጠኛ ሀይወት ከሞት የበለጠ አስከፊ ነውና እርግጠኛ የሆነ ምንም ነገር የለም፡፡ ሀይወት በጥርጣሬ እና ባልታሰቡ ነገሮች የተሞላች ናት፡፡ ውበቷም ይህ ነው! 'አሁን እርግጠኛ ነኝ' ብላችሁ መናገር አትችሉም፡፡ እርግጠኛ ነኝ ባላችሁ ጊዜ ሞታችሁን አውጃችኋል፤ሀይወት ከአንድ ሺ አንድ ጥርጣሬዎች ጋር ጉዞዋን ትቀጥላለች፡፡ ይህ ነው ነፃነቷ፡፡ ይህን ስጋት ነው፡ ብላችሁ አትጥሩት፡፡

አስምሮ ነፃነትን ለምን "ስጋት" ብሎ እንደሚጠራው አውቃለሁ፡፡ ለጥቂት ወራት ወይም አመታት በእስር ቤት ኖራችሁ ታውቃላችሁ? ለጥቂት ዓመታት በእስር ቤት ኖራችሁ የምታውቁ ከሆነ እስረኛው ከእስር የመፈቻው ቀን ሲቃረብ ስለወደፊቱ እርግጠኛ ያለመሆን ስሜት እንደሚሰማው ታውቃላችሁ፡፡ እስር ቤት ውስጥ ሁሉም ነገር እርግጠኛ ነው፡ ሁሉም ነገር አንድ አይነትና ተደጋጋሚ ነው፡፡ ምግቡ ይሰጠዋል፣ ጥበቃ ይደረግለታል፣ በሚቀጥለው ቀን ሊራብ አይችልም፣ ምግብ ላይኖር ይችላል፣ የሚል ፍርሃት የለበትም - ሁሉም ነገር እርግጠኛ ነው፡፡ ታዲያ ከዚያ ሁሉ ዓመት እስር በኋላ መፈቻው ቀን ሲቃረብ እራሱን "አሁን ልትፈታ ነው" ይለዋል፡፡ ይኸን ጊዜ መርበትበት ይጀምራል፡፡ ከእስር ቤት ቅጥር ውጪ ጥርጣሬዎች ይኖራሉና፤በነጻነት መኖሩ ግድ ይሆናልና፣ መመንኘት፣ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

ነፃነት ፍርሃትን ይፈጥራል፡፡ ሰዎች ስለ ነፃነት ቢያወሩም ፈሪዎች ናቸው፡፡ አንድ ሰው ደግሞ ነፃነትን የሚፈራ ከሆነ ገና ሰው አልሆነም ማለት ነው፡፡ እኔ ነፃነት እሰጣችኋለሁ፤ነገር ግን ስጋት የሌለበት ሀይወት አይደለም የምሰጣችሁ፡፡ እውቀት ሳይሆን ግንዛቤን እሰጣችኋለሁ፡፡ እውቀት እርግጠኛ እንድትሆኑ ያደርጋችኋልና፡፡...አንድ እግዚአብሄር አለ፣ ገነትና ሲኦል አለ ፤ እነዚህ መልካም እነዚያ ደግሞ መጥፎ ምግባሮች ናቸው፣ ሃጢአት ከሰራችሁ ሲኦል ትወርዳላችሁ፣ እኔ መልካም የምላቸውን ከሰራችሁ ገነት ትገባላችሁ... ...ብዙ አንድ ቀድሞ የተዘጋጀ ቀመር የምሰጣችሁ ከሆነ-





አለቀ! እርግጠኛ ትሆናላችሁ! ለዛም ነው ሰዎች ነፃነትን ሸሽተው አንድ ቋሚ ቀመር ፍለጋ የአንድ የሆነ ሀይማኖት ተከታይ መሆን የሚመርጡት፡፡እናንተ ግን እርግጠኛ በሆነ ነገር ላይ ጥገኛ አትሁኑ፡፡ ሀይወት በተፈጥሮዋ እርግጠኛ አይደለችም፡፡ ብልህ ሰው ደግሞ ሁሌጊዜ እርግጠኛ አይሆንም- ምክንያቱም ሕይወት የምክንያትና ውጤት ሰንሰለት አይደለችም፡፡

ይህ እርግጠኛ ላለመሆን የሚደረግ ዝግጅት ድፍረት ነው፤ ይህ እርግጠኛ ላለመሆን የሚደረግ ዝግጅት እምነት ነው፡፡ ብልህ ሰው ምንም አይነት ሁኔታ ቢከሰት ንቁ ሆኖ የሚቀበልና በሙሉ ልቡ ምላሽ የሚሰጥ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ምን እንደሚከሰት 'ይህ እና ያ ይከሰታል' ብሎ ያውቃል ማለት አይደለም፡፡ ሀይወት ሳይንስ አይደለችም፣ የምክንያት እና የውጤት ሰንሰለትም አይደለችም፡፡ ውሃን በአንድ መቶ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ሙቀት ቢያፈሉት ይተናል- ይህ እውነት ነው፡፡ በእውነተኛው ሀይወት ውስጥ ግን እንደዚህ አይነት እርግጠኝነት የለም፡፡

እያንዳንዱ ሰው አንድ ያልታወቀ ነገር ነው፡፡ ቀድሞ መገመት፣ ቀድሞ መተንበይ ፈፅሞ አይቻልም፡፡ ሰው በንቃት እና በግንዛቤ ውስጥ መኖር አለበት፡፡

ይህን ጽሁፍ የምታነቡት እውቀት ፍለጋ ነው፤ ጥገኛ የምትሆኑበት ቀመር ትፈልጋላችሁ፡፡ እኔ ደግሞ ይህን አልሰጣችሁም፡፡ እንዲያውም ካላችሁ እነጥቃችኋለሁ ቀስ በቀስ እርግጠኝነታችሁን አጠፋለሁ፣ ቀስ በቀስ ተጠራጣሪ አደርጋችኋለሁ፣ ቀስ በቀስ ስጋት አሳድርባችኋለሁ፡፡ መደረግ ያለበት ብቸኛው ነገር ይህ ነው-አንድ ሊቅ ማድረግ የሚኖርበት ብቸኛው ነገር ይህ ነው! - እናንተን በምሉዕ ነፃነት ውስጥ ማስቀመጥ፡፡ ውስን ባልሆነ፣ ሁሉም አማራጮች ክፍት በሆኑበት ምሉዕ ነፃነት ውስጥ ..... ንቁ መሆን አለባችሁ - የሚሆን ምንም የለም፡፡

ይህንን ነው ግንዛቤ የምለው፡፡ ግንዛቤ ካላችሁ ስጋት የሀይወታችሁ አካል ይሆናል - ይህ ደግሞ ሀይወትን ነፃ እና ማቆሚያ የሌላቸው አስደናቂ ነገሮች መከሰቻ ያደርጋታልና ጥሩ ነው፡፡ ማንም ቢሆን ምን እንደሚከሰት አያውቅም፡፡ እያንዳንዱ ክስተት ሁሌጊዜ እንድትደነቁ ያደርጋችኋል፡፡ ይህንን እንደጥርጣሬ ሳይሆን መኖት ብላችሁ ጥሩት፣ ስጋት ሳይሆን ነፃነት ብላችሁ ሰይሙት፡፡



# የአዲስ ሕይወት ፋና

# 1

## ድፍረት ምንድነው?



በመሰረቱ ድፍረት ማለት የማይታወቀውን ለማወቅ ሲባል የሚታወቀውን፣ ያልተለመደውን ለማየት ሲባል የተለመደውን፣ የማይመቸውን ለማየት ሲባል የሚመቸውን፣ የማይታወቀውን ዕጣ - ፈንታ ለማየት ሲባል አክብሮታዊ ሰግደትን መተው ነው፡፡ አንድ ሰው ይሳካለት ወይም አይሳካለት ምንም አያውቅም፡፡ ቁማር እንደመጫወት አይነት ነው፡፡ ቁማር ተጫዋቾቹ ግን ህይወት ምን እንደሆነች ያውቃሉ፡፡

@shuktus_books

# ድፍረት ከማይታወቅ ነገር ጋር የመጋፈጥን እውነት መቀበል ነው

ድፍረት ማለት ፍርሃቶችን ሁሉ ጥሶ ወደማይታወቀው ዓለም መግባት ነው። ድፍረት ማለት ፈሪ አለመሆን ማለት አይደለም። ፈሪ አለመሆን የሚከሰው ደበሎ ደፋር እየሆናችሁ ስትመጡ ነው። የድፍረት መጨረሻው ፈሪ አለመሆን ነው። ድፍረት ፍፁም ሲሆን አለመፍራት ይሆናል። ይሁን እንጂ በፈሪና በደፋር ሰው መሃል ብዙ ልዩነት የለም። ብቸኛው ልዩነታቸው ፈሪው ፍርሃቶቹን ማድመጡና መከተሉ፤ ደፋሩ ደግሞ ፍርሃቶቹን አስወግዶ ትቶውን ወደፊት መቀጠሉ ነው። ደፋር ሰው ፍርሃቶቹን ሁሉ ጥሶ ወደማይታወቀው ዓለም ይገባል። ፍርሃቶቹ እዚያ እንዳሉ ያውቃል።

ልክ እንደ ኮሎምበስ በባህሩ ላይ ወዳልሰፈረ ባህር ስትሄዱ የሚከተተውን አታውቁምና እጅትን ትፈራላችሁ። የደህንነት ወሰንን አለፋችሁ ማለት ነው። አንድ ነገር ከመጉደል በቀር ፍፁም ተመቻችታችኋል። ድፍረት፤ የምትሄዱት ወደማይታወቅ ስፍራ በመሆን ትፈራላችሁ። ልባችሁ በፍጥነት መምታት ትጀምራለች። በድጋሚ ምስሉ ህያው ትሆናላችሁ። ከማይታወቀው ነገር ጋር የመጋፈጣችሁን ነገር ተቀብላችሁታልና የማንነታችሁ እያንዳንዱ ቅንጣት ህያው ይሆናል።

ፍርሃትን በሙሉ ተቋቁሞ ከማይታወቅ ነገር ጋር የመጋፈጥን እውነት መቀበል ድፍረት ነው። ፍርሃቶች ይኖራሉ። ነገር ግን ፈተናዎቹን ለመቀበል ደጋግማችሁ ዝግጁ በሆናችሁ ቁጥር ፍርሃቶቹ ቀስ በቀስ ይጠፋሉ። የማይታወቀው ነገር የሚፈጥረው ደስታ፣ ከማይታወቀው ነገር ጋር የተከሰተው ታላቅ ሃሴት ጠንካራ ያደርጋችኋል፤ የማትናወጡ እንድትሆኑ ያስችላችኋል፤ ብልህነታችሁን ስለ ያደርገዋል። ለመጀመሪያ ጊዜ ህይወት አሰልቺ ሳትሆን ብዙ አስደናቂ ነገሮች የሚከሰቱባት እንደሆነች መገንዘብ ትጀምራላችሁ። በመቀጠል ፍርሃቶቻችሁ ቀስ በቀስ ይጠፋሉ፤ ከዚያም አንድ አስደናቂ ነገር መፈለጋችሁን ትቀጥሉበታላችሁ።





በመሰረቱ ድፍረት ማለት የማይታወቀውን ለማየት ሲባል የሚታወቀውን፣ ያልተለመደውን ለማየት ሲባል የተለመደውን፣ የማይመቸውን ለማየት ሲባል የሚመቸውን፣ የማይታወቀውን ልፋ - ፈንታ ለማየት ሲባል አዝብርታዊ ስንደትን መተው ነው። አንድ ሰው ይሳካለት ወይም አይሳካለት ምንም አያውቅም። ቁማር እንደመጫወት አይነት ነው። ቁማር ተጫዋቾቹ ግን ህይወት ምን እንደሆነች ያውቃሉ።

# የድፍረት መንገድ (ታኦ)

## ለመሸነፍ ዝግጁ የሆነ ማንም አያሸንፈውም

ህይወት የእናንተን በምክንያት የተደገፈ ሃሳብ አታዳምጥም፤ ምንም ሳትረበሽ በራሷ መንገድ ነው የምትጓዘው። ስለዚህ ህይወትን ሊታደምጧት ይገባል። ህይወት ስለ እናንተ ምክንያታዊ ሃሳብ ግድ ስለሌላት አታደምጣችሁም።

ወደ ህይወት ውስጥ ስትገቡ ምን ታያላችሁ? አንድ ታላቅ ማዕበል ይነሳ እና ትላልቅ ዛፎች ይወድቃሉ። እንደ ቻርለስ ዳርዊን እምነት ከሆነ ዛፎች ጠንካሮች፣ ሃይለኞች እና ብቁዎች ስለሆኑ በህይወት መቆየት ይችሉባቸዋል። ሰስት ሺ ዓመት ያለውን የሰስት ሺ ዓመት እድሜ ባለፀጋ የሆነውን የጥንት ዛፍ ተመልከቱት። የዛፉ መኖር በራሱ ጥንካሬ ከመፍጠሩ በተጨማሪ የጥንካሬ እና የሃይለኛነት ስሜት ይፈጥራል። ከመሬት በታች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ስሮች ጠልቀው በመቀመጥ ዛፉ በሃይል እንዲቆም አስችለውታል። በእርግጥ ዛፉ ይታገላል - መሸነፍ መገዛት አይፈልግምና - ይሁን እንጂ ከማዕበል በኋላ ወድቋል፣ ሞቷል፣ ህይወቱን አጥቷል፣ ያ ሁሉ ጥንካሬው ጠፍቷል። ማዕበሉ እጅግ ሃይለኛ ነበር - ማዕበል ምንጊዜም ኃይለኛ ነው። ማዕበል ሲመጣ አንድ ጊዜ ተሰብስቦ ሲሆን ዛፍ ደግሞ ብቸኛ ወይም አንዱ ነው።

ከዚያም ትናንሽ እፅዋት እና ተራ ሳሮች ይመጣሉ - ሀይለኛ ነፋስ በመጣ ጊዜ ሳሮች ስለሚያጎነብሱ ነፋሱ ሳይጎዳቸው ያልፋል። ሲበዛ በደንብ

ቢያስተኛቸው(ቢለሽልሻቸው) ነው፡፡ በሳሩ ላይ ተከማችቶ የነበረው ቆሻሻ በሙሉ ተጠራርጐ ይሄዳል፤ አውሎ ነፋሱ በደንብ ያጥበዋል፡፡ አውሎ ነፋሱ ካለፈ በኋላ ትናንሽቹ እፅዋት እና ሳሮች ከፍ ብለው መደነስ ይጀምራሉ፡፡ ሳር እምብዛም ስር እለው ስለማይባል አንድ ህፃን በቀላሉ ሊነቅለው ይችላል፡፡ አውሎ ነፋሱ ግን ድል ተመትቷል፡፡ ምንድነው የተከሰተው?

ሳሩ የተከተለው የታኦን፣ የላኦ ዙን መንገድ ነው፡፡ግዙፉ ዛፍ ደግሞ የቻርልስ ዳርዊንን፡፡ ግዙፉ ዛፍ በጣም ምክንያታዊ ነው፤ለመታገል፣ ጥንካሬውን ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ጥንካሬያችሁን ለማሳየት ከሞከራችሁ ትሸነፋላችሁ፡፡ ሁሉም ሂትለሮች፣ ናፖሊዮኖች፣ አሌክሳንደሮች...... ትላልቅና፣ ጠንካራ ዛፎች ናቸው፡፡ ሁሉም ይሸነፋሉ፡፡ ላኦዙዎች ደግሞ ልክ እንደ ትናንሽ እፅዋት ናቸው፣ ሁሌጊዜ ለመሸነፍ ዝግጁ ስለሆኑ ማንም ሊያሸንፋቸው አይችልም፡፡ "ተሸንፌያለሁ" የሚልን ሰው እንዴት ልታሸንፉት ትችላላችሁ? "ጌታዬ! ድልዎን ያጣጥሙ፡፡ እኔ የተሸነፍኩ ነኝና ሌላ ችግር መፍጠሩ አስፈላጊ አይደለም፡፡" የሚላችሁን ሰው እንዴት ታሸንፉታላችሁ? ከአንድ ላኦ ዙ ፊት የቆመ አሌክሳንደር ከንቱ እንደሆነ ይሰማዋል፣ ምንም ማድረግ አይችልም፡፡ እንዲህ ነው የሆነው፣ በትክክል እንዲህ ነው የሆነው ........

በአሌክሳንደር ዘመን፣ አሌክሳንደር ህንድ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ዳንዳሚስ የሚባል ረቂቅ ሰው ይኖር ነበር፡፡ የአሌክሳንደር ጓደኞች ከህንድ ሲመለስ አንድ ሳንያሲን (ደቀ - መዝሙር) ይዞ እንዲመጣላቸው ነግረውት ነበር፡፡

እሱ ግን በጦርነት፣ በትግል እና በፍልሚያ ውስጥ ስለነበር ለጥቂት ጊዜ ያሉትን ዘንግቶ ነበር፡፡ የተባለውን ረስቶ ወደ ሃገሩ ሲመለስ ከህንድ ድንበር ላይ እንደደረሰ ድንገት ትውስ አለው፡፡ የመጨረሻዋን ድንበር እያለፈ ሳለ ወታደሮቹ ወደ መንደሯ ዘልቀው እዚህ አካባቢ ሳንያሲን ይኖር እንደሆን እንዲጠይቁ አዘዛቸው፡፡ የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ዳንዳሚስም በመንደሯ ውስጥ ከወንዙ ዳርቻ ነበር፡፡ ሰዎቹም ወታደሮቹን "በትክክለኛው ወቅት ነው የመጣችሁት፡፡ ብዙ ሳንያሲኖች አሉ፡፡ ሆኖም እውነተኛው ሳንያሲን እምብዛም አይገኝም፡፡ ዛሬ ግን እዚህ ነው ያለው፡፡ ሄዳችሁ ልትጎበኙት ትችላላችሁ" አሏቸው፡፡





አሌክሳንደር ሳቀ፡፡ "እኔ እዚህ የመጣሁት ድርሻ ለመሰብሰብ አይደለም፡፡ ወታደሮቹ ሄደው ያመጡታል፡፡ እኔ ደግሞ ወደ ሃገሬ መዲና እወስደዋለሁ" አለ፡፡

ነዋሪዎቹም "እንዲህ ቀላል አይሆንላችሁም ......" ሲሉ መለሱለት፡፡

አሌክሳንደር የሰማውን ማመን አልቻለም - ምን ችግር ሊፈጠር ይችላል? ታላላቅ ነገስታትን ድል ነስቷል፤ ታዲያ አንድ ለማኝ ሳንያሲን ምን ያስቸግረዋል?

ወታደሮቹ ከወንዙ ዳር እርቃኑን ወደቆመው ዳንዳሚስ ሄዱ፡፡ "ታላቁ አሌክሳንደር ወደ ሃገሩ አብረኸው እንድትሄድ ይፈልጋል፡፡ የፈለግኸው ነገር በሙሉ ይሟላልሃል፡፡ የተከበረ እንግዳው ትሆናለህ፡፡" አሉት፡፡

ራቁቱን የቆመው ረቂቅ መንፈስ ሳቀ፡፡ "ወደ አለቃችሁ ሂዱና ራሱን ታላቅ ብሎ የሚጠራ ሁሉ ታላቅ እንደማይሆን ንገሩት፡፡ ደግሞም እኔን ማንም የትም አይወስደኝም - ሳንያሲን እንደ ደመና የትም ቢሆን በሙሉ ነፃነት ነው የሚጓዘው፡፡ እኔ የማንም ባሪያ አይደለሁም፡፡"

"መቼም ስለ አሌክሳንደር ሳትሰማ አልቀረህም" አሉት፡፡ "በጣም አደገኛ ሰው ነው፡፡ እንቢ ካልከው አያዳምጥህም፣ ጭንቅላትህን ቆርጦ ነው የሚቀጥለው፡፡"

ወታደሮቹ ወደ አሌክሳንደር በመመለስ፣ "ረቂቅ፣ የሚያበራ፣ አንድ የሆነ የማያጋጥም ነገር ዙሪያውን የከበበው ነው፡፡ ራቁቱን ቢሆንም እርቃኑን መሆኑ አያታውቅህም - በኋላ ነው ትውስ የሚልህ፡፡ በጣም ሃይለኛ በመሆኑ መላውን እለም ያስረሳሃል፡፡ እንደ ማግኔት የመሳብ ሃይል አለው፡፡ ዙሪያውን ታላቅ ፀጥታ ከብቦታል፡፡ አካባቢው በሙሉ በሰውየው ውስጥ ደስታ እንዳለ ይመሰክራሉ፡፡ የሚታይ ሰው ነው፤ ግን ማንም ሊወስደው እንደማይችልና የማንም ባሪያ ሊሆን እንደማይችል ተናግሯልና ይዞ ምልኪን ችግር ይጠብቀዋል" ሲሉት አሌክሳንደር ሁኔታውን ለማየት መሄድ ነበረበት፡፡

አሌክሳንደር ጐራዴውን በእጁ ይዞ ሄደ፡፡ ዳንዳሚስ እሱንም በድጋሚ ሳቀና "ጐራዴህን አስቀምጠው፣ እዚህ ምንም አያጠቅምህም፡፡ ወደ ሰገባው

መለሰው፡፡ አካሌን ብትቆርጠው እንኳን እኔ ከሄድኩ ቆይቻለሁ፡፡ ጭራሹ ሊቆርጠኝ አይችልምና አስተምሮሐል፡፡ ሀገን እንተው" አለው፡፡

አሌክሳንደር ለመጀመሪያ ጊዜ ለሌላ ሰው ትዕዛዝ ተገዢ ሊሆን ተገደደ፡፡ ሰውየው ከፊት በመቆሙ ምክንያት ብቻ ማንነቱን ረሳ፡፡ ጎራዴውን ወደ ሰገባው መለሰና "እንደዚህ አይነት ቆንጆ ሰው አይቼ አላውቅም" አለ፡፡ ወደ ጦር ሰፈሩ ከተመለሰ በኋላም ጭምትን ሰው መግደል አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህን ሰው መግደል ምንም ትርጉም የለውም፡፡ የሚታገለን ሰው መግደል ትርጉም ይኖረው ይሆናል፤ ለመሞት ዝግጁ የሆነና <ይኸውልህ ጭንቅላቴ፤ ቆርጠህ ልትወስድ ትችላለህ> የሚልን ሰው ግን መግደል አይቻልም አላቸው፡፡

እርግጥም ዳንዳሚስ እንዲህ ብሎ ነበር፡ "ይኸውልህ ጭንቅላቴ፡ ቆርጠህ ልትወስድ ትችላለህ፡፡ ጭንቅላቴ ከተቆረጠ በኋላ አሸዋው ላይ ሲወድቅ እንደምታየው እኔም አየዋለሁ፤ ምክንያቱም እኔ አካሌን አይደለሁም፡፡ እኔ ምስክር ነኝ፡፡"

አሌክሳንደር አምሳሉን ወዳሉት ጓደኞቹ እንደተመለሰ እንዲህ አላቸው፡፡ "ለመጣላችሁ የምችላቸው ሳንያሲዎች ነበሩ፤ ግን በእርግጥ እውነተኛ ሳንያሲን አይደሉም፡፡ እነሱን ስፈልግ አንድ ረቂቅ ሰው አጋጠመኝ - በእርግጥ እምብዛም እንደማይገኝ የሰማችሁት ትክክል ነው፡፡ እሱ ሞትን አይፈራምና ማንም ሊያስገድደው አይችልም፡፡ ሰው ደግሞ ሞትን ካልፈራ እንዴት ሊታስገድዱት ትችላላችሁ"

ፍርሃታችሁ ነው ተገዢ የሚያደርጋችሁ፤ ፍርሃታችሁ! መፍራት ስታቆሙ ተገዢ መሆናችሁ ያበቃል፡፡ ሰዎች እናንተን ተገዢ ከማድረጋቸው በፊት ተገዢ እንድትሆኑ የሚያስገድዳቸው የእናንተ የራሳችሁ ፍርሃት ነው፡፡

ፍርሃት የሌለበት ሰው ማንንም ካለመፍራቱ በተጨማሪ ማንም ሊያስፈራራው አይችልም፤ ፍርሃቱ ከነድራሹ ጠፍቷልና፡፡







# የልብ መንገድ

## ዛሬ ምንም ሳይሆን ወደ ነገ የሚደረግ ጉዞ ነው

ድፍረት የሚለው ቃል በጣም የሚስብ ነው፡፡ ድፍረት (በእንግሊዝኛ Courage) የሚለው ቃል ኮር (Cor) ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ሲሆን "ልብ" የሚል ትርጉምም አለው፡፡ ድክመቶች፣ ድክመቶች ብቻ በጭንቅላት ውስጥ ይኖራሉ፤ ፍርሃት ስለሚደላቸውም በዙሪያቸው የምክንያት አጥር ይገነባሉ፡፡ ስለሚፈሩ በሃይማኖት፣ በፅንሰ - ሃሳቦች፣ በቃላት፣ በንድፈ-ሃሳቦች በሮቻቸውንና መስኮቶቻቸውን በሙሉ ዘግግተው ከበሮቹና መስኮቶቹ ጀርባ ይደበቃሉ፡፡

የልብ መንገድ የድፍረት መንገድ ነው፡፡ በስጋት ውስጥ መኖር ነው፤ በፍቅርና በእምነት ወስጥ መኖር ነው፤ በማይታወቀው ውስጥ መጓዝ ነው፡፡ ትናንትናን ረስቶ ነገን መከተል ነው፡፡ ድፍረት በአደገኛ መንገድ ላይ መጓዝ ነው፡፡ ህይወት አደገኛ ናት፡፡ ፈሪዎች ብቻ ናቸው ይህን አደጋ የማይጋፈጡት ሙታን ስለሆኑ፡፡ ህያው፣ በእርግጥም ህያው የሆነ ሰው ሁልጊዜ ወደማይታወቀው ይገባል፡፡ እዚያ አደጋ ቢኖርም አደጋውን

ይጋፈጣል። ልብ ደግሞ ይህን አደጋ ለመጋፈጥ ሁልጊዜ ዝግጁ ነው። ልብ ቁማርተኛ ነው። ጭንቅላት ነጋዴ ነው። ጭንቅላት ሁልጊዜም ያሰላል፣ ብልጥ ነው። ልብ ግን አያሰላም።

ድፍረት (Courage) የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ማራኪ እና በጣም የሚስብ ነው። በልብ ውስጥ መኖር ማለት ትርጉም ማግኘት ነው። ባለቅኔ ልብ ውስጥ ይኖራል። ቀስ በቀስም በልቡ ውስጥ የማይታወቀውን ድምፅ ማድመጥ ይጀምራል። ጭንቅላት ማድመጥ አይችልም፣ ከማይታወቀው እጅግ የራቀ ነው። ጭንቅላት በሚታወቁ ነገሮች የተሞላ ነው።

***ልብ ቁማርተኛ ነው፤ ጭንቅላት ነጋዴ ነው፤ ጭንቅላት ሁልጊዜ ያሰላል - ብልጥ ነው፤ ልብ ግን አያሰላም፤ ጭንቅላት ስላለፈው ጊዜ ሲያስብ፣ ልብ ስለወደፊቱ ያልማል።***

አዕምሮ ምንድነው? የምታውቁት ነገር በሙሉ በአዕምሯችሁ ውስጥ ነው። ያ ደግሞ የትናንት፣ የሞተ፣ ያለፈ ነው። አዕምሮ ምንም ሳይሆን ያለፈ ነገር የተከማቸበት ትውስታ ነው። ልብ የነገ ነው፣ ልብ ሁልጊዜ በተስፋ የተሞላ ነው፣ ልብ ሁልጊዜ ወደፊት አንድ ቦታ ላይ ነው። ጭንቅላት ስላለፈው ጊዜ ሲያስብ ልብ ስለወደፊቱ ያልማል።

የወደፊቱ ጊዜ ገና የሚመጣ ነው፣ የወደፊቱ ጊዜ ገና የሚሆን ነው። የወደፊቱ ጊዜ ምርጫ አለው - ይመጣል፣ እየመጣ ነው። በእያንዳንዱ ቅፅበት ነገ ዛሬ ሊሆን እየቀረበ ነው፣ ዛሬ ደግሞ ወደ ትናንት እየተጠጋ ነው። ትናንት አማራጭ የለውም፣ ጥቅም ላይ ውሏል። ርቃችሁት መጥታችኋል - ያለፈ፣ የሞተ ነገር ነው። መጪው ጊዜ እንደ በር ነው፣ እየመጣ፣ ሁልጊዜ እየደረሰ፣ ከዛሬ ጋር እየተቃረበ ነው። እናንተ ሁልጊዜ በጉዞ ላይ ናችሁ። ዛሬ ምንም ሳይሆን ወደ ነገ የሚደረግ ጉዞ ነው። እርምጃችሁ ነው - ወደፊት የሚወስዳችሁ እርምጃ።

እውነት ብዙ ደስታ እና አያሌ በረከት ያመጣልና በዓለም የሚኖር በሙሉ እውነት መሆን ይፈልጋል - ከቶስ ውሸት መሆን ለምን ያስፈልጋል? ውስጣችሁን በጥልቀት ለመመልከት ድፍረት ሊኖራችሁ ይገባል። ለምን ትፈራላችሁ? አለም ምን ሊታደርጋችሁ ትችላለች? ሰዎች ይስ ሊሳቁባችሁ ይችላሉ - ሳቅ ሁልጊዜም መድሃኒት፣ ጤና ነው። ሰዎች እናንተ





እብድ እንደሆናችሁ ሊያስቡ ይችላሉ ..... ግን እነሱ እብድ ናችሁ ስላሏችሁ ብቻ እብድ አትሆኑም።

በደስታችሁ፣ በሀዘናችሁ፣ በእንቅስቃሴያችሁ እውነተኛ ከሆናችሁ ውሎ አድሮ ሃሳባችሁን የሚረዱላችሁ፣ በእናንተ መንገድ የሚጓዙ ሰዎች ማግኘታችሁ የማይቀር ነው። እኔ ራሴ መንገዴን ስጀምረው ብቻዬን ነበርኩ። ዛሬ ግን መንገዴን የሚከተሉ ሰዎች በዝተው ጉዞዬ አለማቀፍ ሆኗል! እኔ ማንንም ወደ መንገዴ አላጋበዝኩም፣ ልቤ የፈቀደውን አደረግሁ እንጂ።

የእኔ ሃላፊነት የልቤን እንጂ በአለም የሚኖርን የማንንም ትዕዛዝ ማድመጥ አይደለም። የእናንተም ሃላፊነት ራሳችሁን ብቻ ማድመጥ ነው። ራስን መቃወም ራስን ማጥፋት፣ ራስን መግደል ነውና ራሳችሁን አትቃወሙት። ታዲያ ጥቅሙ ምንድነው? ሰዎች ቢያከብሯችሁ፣ ሩህሩህ፣ የተከበረ፣ የተሞገሰ ሰው እንደሆናችሁ ቢያስቡ እንኳን እነዚህ ሁሉ ነገሮች ማንነታችሁን አያድሱትም፤ ህይወትንና የማያልቅ ውበቷን በጥልቀት እንድትመረምሩ አያደርጓችሁም።

ከእናንተ በፊት ስንት ሚሊዮን ሰዎች በዚህች ምድር ላይ ኖረዋል? ስማቸውን እንኳን አታውቁትም፣ የእነሱ መኖር አለመኖር ምንም ለውጥ አያመጣም። ቅዱሳን ነበሩ፣ ሃጢአተኞች ነበሩ፣ በጣም የተከበሩ ነበሩ፣ ብዙ አይነት ጠቢባንና እብዶች ነበሩ፣ እነዚያ ሁሉ ግን ዛሬ የሉም - አንዳቸውም እንኳን በዚህች ምድር አልቀሩም።

ብቸኛው ትኩረታችሁ ሞት አካላችሁን፣ አዕምሮአችሁን በሚያጠፋው ጊዜ ከእናንተ ጋር የሚሄዱትን እነዚያን ባህሪያት መንከባከብና መጠበቅ ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም ብቸኛ ጓደኞቻችሁ እነዚህ ባህሪያት ናቸው፣ እውነተኛ ዋጋዎች እነሱ ብቻ ናቸው። እነዚህን ያገኙ ብቻ ይኖራሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ እንደሚኖሩ ያስመስላሉ።

*በአንድ ጨለማ ምሽት አንድ የኪጂዚ ሰው የቡሊል ፈንክልለስታይንን በር ያንኳኳል። ቡሊል በሩን ከፈተ። የኪጂዚው ሰው "ቡሊል ፈንክልለስታይን እዚህ ነው የሚኖረው?" በማለት ይጠይቃል።*

*"አይደለም" ብሎ መለሰ ቡሊል የነተበ ፒጃማውን እንደለበሰ።*

*"አይደለም? ታዲያ አንተ ማነህ?"*

ቸሲል ፈገዝሊስታይን፡፡"

ይህን ጊዜ የክርስቲያኑ ሰው በጣም ተናዶ የሲልን መሬት ላይ ይፈጠፍጠውና "እዚህ አለናርም ነው ያለከው?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡

የሲልም "ይህን ኦር ነው ኦር ብለህ የምትጠራው?" ሲል ይመልስለታል፡፡

መኖር ብቻውን ኑሮ አይደለም፡፡ ህይወታችሁን ተመልከቱት፡፡ የተባረከ ነው? የህያውነት ምልክት የሆነ ስጦታ እንደሆነ ያለ ይሰማችኋል? ይህን ህይወት ደጋግማችሁ ልትኖሩት ትፈልጋላችሁ?

ማንንም አታድምጡ ፡ የልባችሁን አድምጡ እንጂ፡፡ እኔ ይህን እመክራለሁ፡ በደንብ አድምጡ፣በንቃት አድምጡ፡ እንዲያ ካደረጋችሁ ፈጽሞ አትሳሳቱም፡፡ ልባችሁን ካዳመጣችሁ ሃሳባችሁ አይከፋፈልም፡፡ ልባችሁን በማድመጣችሁም የትኛው ነው ትክክል? የትኛው ነው ስህተት?' ብላችሁ ሳታስቡ በትክክለኛው አቅጣጫ መንገዱ ትጀምራላችሁ፡፡

ጠቅላላው የሕይወት ስብዕና ጥበብ ሌብነት በተንቃቂብንነት እና በደንብ በማድመጥ ሚስጥር ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ተከተሉት፤ በሄደበት ሂዱ፡፡ አዎ አንዳንድ ጊዜ ወደ አደጋ ይወስዳችኋል፡፡ነገር ግን እነዚያ አደጋዎች በሳል እንደሚያደርጋችሁ አትርሱ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በመንፈስ ይወስዳችኋል፡፡ነገር ግን እነዚያ የመንፈስ ጉዞዎች የብስለታችሁ አካል መሆናቸውን አትዘንጉ፡፡ ብዙ ጊዜ እየወደቃችሁ ትነሳላችሁ፡ ምክንያቱም ጥንካሬ የሚገኘው በመውደቅ እና በመነሳት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ነው የምትኖሩት ጠንካራዎች መሆን የምትችሉት፡፡

ከውጪ የሚጫኑባችሁን ህጎች አትከተሏቸው፡፡ በግድ የተጫነ ህግ ትክክል ሊሆን አይችልም ፡ ህጎቹ የተፈጠሩት እናንተን ለመምራት በፈለጉ ሰዎች ነው፤ አዎ፤ቡድሃን፣ ኢየሱስን፣ ክሪሽናን፣ መሐመድን የመሳሰሉ ጥልቅ አስተውሎት የነበራቸው ታላላቅ ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ሰዎች ለዓለም ህግን ሳይሆን ፍቅርን ነው የሰጡት፡፡ ይሁን እንጂ ደቀመዛሙርቶቻቸው ተሰብስበው ህግ ማርቀቃቸው አልቀረም፡፡ አንድ ጊዜ አሊቃው ከሄደ፣ መብራቱ ከጠፋ በኋላ በጨለማ ውስጥ ስለሚወድቁ የተወሰኑ ህጎች ተገኘ





ይሆናሉ፡፡ ምክንያቱም የሚያዩት ብርሃን የለም፡፡ ይሄን ጊዜ የህግ ጥገኛ ይሆናሉ፡፡

ኢየሱስ ተግባሩ ሁሉ የልቡ ሹክሹክታ ነፀብራቅ ነበር፡፡ ተከታዮቹ ደግሞ የልባቸውን ምት የሚያደምጡ አይደሉም፡፡ አስመሳዮች ናቸው፡፡ባስመሰሉ ጊዜ ሰብዕናቸውን እየተሳደቡ፣ እግዚአብሔርን እየተሳደቡ ነው፡፡ እናንተ ግን ፍፁም አስመሳይ አትሁኑ፤ ሁሌጊዜ እውነተኛ ሁኑ፡፡ የካርቦን ቅጂ አትሁኑ፡፡ ይሁን እንጂ በመላው ዓለም እየተከሰተ ያለው ይህ ነው- የካርቦን ቅጂዎች!

እውነተኛ ከሆናችሁ ህይወት እንደ ዳንስ ትሆንላችኋለች ፡ እናንተም እውነተኛ ትሆናላችሁ፡፡ ለምሳሌ በክሪሽና እና በቡድሃ መካከል ያለውን ልዩነት አስታውሱ፡፡ ክሪሽና ቡድሃን የተከተለው ቢሆን ኖሮ በዓለም ምርጥ ከሆኑ ሰዎች አንዱን እናጣ ነበር፡፡ ወይም ቡድሃ ክሪሽናን ተከትሎ ቢሆን ኖሮ ምስኪን ፍጡር ይሆን ነበር፡፡ ቡድሃ ዋሽንቱን እየተጫወተ እስኪ አስቡት! - ዋሽንት ተጫዋች ቢሆን ብዙዎችን ከእንቅልፋቸው በቀሰቀሳቸው ነበር፡፡ ቡድሃን ሲደንስ አስቡት በጣም አስቸጋሪ እና የሚያስመስል ነበር!

በክሪሽና በኩል ያለው ሁኔታም ተመሳሳይ ነው፡፡ ዋሽንት ሳይዝ ከዛፍ ስር የተሰራ አክሊል ሳይደፋ፤ የተዋቡ ልብሶች ሳይለብስ ልክ እንደ ለማኝ እየዞረ ሲለምን፤ አስፈላ የሚደንስ ሰው ሳይኖር፣ ምንም አይነት ዘፈን ሳይኖር ከአንድ የዛፍ ጥላ ስር ምስኪን እና የተጎሳቆለ መስሎ ተቀምጦ አስቡት፡፡ ቡድሃ ቡድሃ ነው፤ክሪሽና ክሪሽና ነው፡ እናንተም ቤት የገዛ ራሳችሁን ናችሁ፡፡ ከማንም በምንም አታንሱም፡፡ ራሳችሁን አክብሩ፤ ውስጣዊ ድምፃችሁን አክብሩና ተከተሉት፡፡

ይህ መንገድ ሁሌጊዜ በትክክለኛው አቅጣጫ ይወስዳችኋል ብዬ ዋስትና እየሰጣችሁ እንዳልሆነ አስታውሱ፡፡ አንድ ሰው ትክክለኛውን በር ለማግኘት ብዙ የተሳሳቱ በሮችን ማንኳኳት ስላለበት ይህ ብዙውን ጊዜ በተሳሳተው መንገድ ይወስዳችኋል፡፡ እውነታው ይህ ነው፡፡ በድንገት ትክክለኛውን በር ካገኛችሁት እንኳን ትክክለኛው በር ላይ መሆናችሁን አታውቁም፡፡ስለዚህ በጥልቅ እምነት ውስጥ የሚገኙን ምንም ሃይል የለም፤ ሁሉም ጥረቶቻችሁ እድገታችሁን ከጫፍ ያደርሱታል፡፡

ስለዚህ አታመንቱ፡፡እሳሳታለሁ ብላችሁ አትፍሩ፡፡አንዱ ችግር ይህ ነው፡፡ ሰዎች እንዳይሳሳቱ ስለተነገራቸው አመንቺ፣ ፈሪ፣ ስህተት እንዳይሰሩ

የሚጠነቀቁ ሆነዋል፡፡ አንድ የሆነ የተሳሳተ ነገር ይገጥመኛል ብለው ስለሚያስቡ መንቀሳቀስ ያቅታቸዋል፡፡ ስለዚህም እንደድጥኝ የማይንቀሳቀሱ ይሆናሉ፡፡ .

አንድን ስህተት በድጋሚ እንዳትሰሩ እያሰባችሁ በተቻላችሁ መጠን ብዙ ስህተቶች ስሩ፡፡ ይህን ካደረጋችሁ ታድጋላችሁ፡፡ ይህ በመንፈስ የመንሳፈፍ ነፃነታችሁ አካል ነው፡፡ ወደ ሲኖራችሁ የሚችለው በዚህ መልኩ ነው፤ አለበለዚያ እንደ ሊሎቹ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ወላዋይ ትሆናላችሁ፡፡

"ይህ ትክክል ነው፤ ይህ ስህተት ነው" ተብሎ የተነገራችሁን በሙሉ እርሱት፡፡ ህይወት ቋሚ ህግ የላትም፡፡ ዛሬ ትክክል የሆነ ነገር ነገ ስህተት ሊሆን ይችላል፤ ዛሬ ስህተት የተባለው ነገር ነገ ትክክለኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ህይወት እንዲህ ብላ ልትመደብ አትችልም፡፡ "ይህ ትክክል ነው፤ ይህ ደግሞ ስህተት ነው" ብሎ በቀላሉ መመደብ አይቻልም፡፡ ህይወት በውስጧቸው ምን እንደያዙ በትክክል እንደሚታወቅ-ምልክት እንደተደረገባቸው የተማሚ ብልቃጦች አይደለችም፡፡ ህይወት ምስጢር ናት፤ አንድ ጊዜ ሁሉም ነገር ትክክል ሆኖ ይገጥማል፤ ሌላ ጊዜ ደራሽ ውሃ መጥቶ የጠበቀው ይላላና ትክክል የነበረው ስህተት ይሆናል፡፡

ትክክለኛ ስንል ምን ማለታችን ነው? ከህልውና ጋር ህብር ያለው ትክክለኛነት ማለታችን ነው፡፡ ከህልውና ጋር ህብር የሌለው ደግሞ ስህተት ነው፡፡ በእያንዳንዱ ቅፅበት በአዲስ መንፈስ ውሳኔ ማሳለፍ ስለሚኖርባችሁ በእያንዳንዱ ቅፅበት ንቁ መሆን አለባችሁ፡፡ ትክክለኛና ስህተት ለሆኑ ነገሮች ቀድመው በተዘጋጁ መልሶች ላይ ጥገኛ መሆን የለባችሁም፡፡ ደደብ የሆኑ ብቻ ናቸው ቀድመው በተዘጋጁ መልሶች ላይ ጥገኛ የሚሆኑት - ምክንያቱም ብልህ መሆን አይፈልጉም፡፡ በእርግጥም ብልህ መሆን አስፈላጊያቸው አይደለም፡፡

**ትክክለኛ ስንል ከህልውና ጋር ህብር ያለው ትክክለኛነት ማለታችን ነው፡፡ ከህልውና ጋር ህብር የሌለው ደግሞ ስህተት ነው፡፡ በእያንዳንዱ ቅፅበት በአዲስ መንፈስ ውሳኔ ማሳለፍ ስለሚኖርባችሁ በእያንዳንዱ ቅፅበት ንቁ መሆን አለባችሁ፡፡ ትክክለኛና ስህተት ለሆኑ ነገሮች ቀድመው**





**በተዘጋጁ መልሶች ላይ ጥገኛ መሆን የለባችሁም፡፡ ደደብ የሆኑ ብቻ ናቸው ቀድመው በተዘጋጁ መልሶች ላይ ጥገኛ የሚሆኑት - ምክንያቱም ብልህ መሆን አይፈልጉም፡፡አያስፈልጋቸውምም፡፡**

እናንተ የቱ ትክክል፤ የቱ ስህተት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡፡ ዝርዝሩ በጣም ረዥም አይደለም በቀላሉ ልታስታውሱት ትችላላችሁ፡፡ አስርቱ ትዕዛዛት - በጣም ቀላል! - የቱ ትክክል፤ የቱ ስህተት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡፡ ህይወት ግን መለወጧን ትቀጥላለች፡፡ ሙሴ ተመልሶ የሚመጣ ቢሆን እነዚያን አስር ትዕዛዛት ይሰጣችኋል ብዬ አላስብም - ደግሞም አይችልም፡፡ ከሶስት ሺ ዓመታት በኋላ እንዴት እነዚያን ትዕዛዛት ሊሰጣችሁ ይችላል? ዓለም ተቀይራለች፤ ስለዚህ አንድ አዲስ ነገር መፍጠር ይኖርበታል፡፡

የእኔ ግንዛቤ ይህ ነው፡፡ ትዕዛዛት ወደሰው ሊተላለፉ ችግር ይፈጥራሉ - ምክንያቱም የተላለፉበት ጊዜ ያረጀ፤ ያረጀ ነው፡፡ ህይወት በፍጥነት ነው የምትጓዘው፤ ቋሚ ሳትሆን ተንቀሳቃሽ ናት፤ የቆመች ኩሬ ሳትሆን የምትፈስ ጅረት ናት፡፡ ሁለት ተከታታይ ቅፅበታት በፍፁም አንድ አይሆኑም፡፡ ስለዚህ አሁን ትክክል የሆነ ነገር ነገ ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡

ስለዚህ ምን መደረግ አለበት? ሰዎች ከሚለወጠው ህይወት ጋር እንዴት መኖር እንደሚችሉ ማንቃት ብቸኛው መንገድ ነው፡፡

## የዜን ታሪክ፡-

ሁለት ተቀናቃኝ ቤተ-መቅደሶች ነበሩ፡፡ የሁለቱ ቤተ-መቅደሶች የበላይ አለቆች እርስ በርስ የሚቃረኑ በመሆናቸው ለተከታዮቻቸው ወደ ተቀናቃኛቸው ቤተ-መቅደስ እንዳይሄዱ ይሰብኩ ነበር፡፡

ሁለቱም ካህናት እቃ የሚያመጡላቸው እና የሚላላኩቸው ሁለት ልጆች ነበሯቸው፡፡ የአንደኛው ቤተ-መቅደስ ቄስ ተላላኪ ልጃቸውን ይጠሩና "የዚያን ሰውዬ ልጅ እንዳታናግረው፡፡ እነዚህ ሰዎች አደገኞች ናቸው" ይሉታል፡፡

ሁለቱ ልጆች ግን ትናንሽ ልጆች ነበሩ፡፡ አንድ ዕለት መንገድ ላይ ይገናኙና ከአንደኛው ቤተ-መቅደስ የመጣው ልጅ ለሌላኛውን "የት እየሄድክ ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል፡፡

ሌላኛውም "ነፋስ ወደ ወሰደኝ" ሲል ይመልስለታል፡፡ በቤተ-መቅደሱ የታላቁን የዜን ነገሮች ተምሯልና ነው "ነፋስ ወደወሰደኝ" ያለው፡፡ ትልቅ ንግግር ንፁህ ታኦ!

የመጀመሪያው ልጅ ግን በጣም ስለፈራ እና የጥፋተኝነት ስሜት ስለተሰማው ምን ብሎ መመለስ እንዳለበት ቸገረው፡፡ ተስፋ ቆርጦ፣ ተበሳጭቶ እና የጥፋተኝነት ስሜት እየተሰማው "አለቃዬ ከእነዚህ ሰዎች ጋር እንዳትነጋገር ብለውኛል፡፡ እነዚህ ሰዎች አደገኞች ናቸው፡፡ አሁን ይሄን መልስ ምን ይሉታል? በመልስ አሳፍረኛል፡፡" አለ፡፡

ወደ አለቃው እንደተመለሰም የተከሰተውን ሁሉ ነገራቸው፡፡ "ልጁን ስላናገርኩት ይቅርታ፡፡ እርስዎ ትክክል ነበሩ፣ እነዚያ ሰዎች ጉራ ናቸው፡፡ ይህን መልስ አሁን ምን ይሉታል? ‹የት እየሄድክ ነው?› በማለት ተገቢና የተለመደ ጥያቄ አቀረብኩለት፡፡ እሱም እንደእኔ ወደ ገበያ እየሄደ እንደሆነ አውቅ ነበር፡፡ እሱ ግን ‹ነፋስ ወደወሰደኝ› ብሎ መለሰልኝ፡፡"

አለቃውም "አስጠንቅቄህ ነበር፣ አንተ ግን አትሰማም፡፡" አሉት፡፡ "አሁን አድምጠኝ፡፡ ነገ እዚያው ቦታ ሄደህ ትቆማለህ፡፡ እሱ አጠገብህ ሲደርስም ‹የት እየሄድክ ነው?›ብለህ ትጠይቀዋለህ፡፡ እሱም ‹ነፋስ ወደወሰደኝ› ብሎ ይመልስልሃል፡፡ ይሄን ጊዜ አንተ ትንሽ ፍልስፍናዊ በሆነ አነጋገር ‹ምንም እግሮች ባይኖሩህስ?› ትለዋለህ - ነፍስ አካል ስለሌላት ነፋስ የትም ሊወስዳት አይችልም፡፡"

ልጁ ፍፁም ዝግጁ ሊሆን በማሰብ ሌሊቱን በሙሉ የነገረውን ሲያብሰለስል አሳለፈ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ማልዶ በመነሳት እዚያው ቦታ ላይ ሄዶ ቆመ፡፡ ልጁም በዚያው ሰዓት መጣ፡፡ እውነተኛ ፍልስፍና ምን እንደሆነ ሊያሳየው ነውና በጣም ደስ አለው፡፡ እናም "የት እየሄድክ ነው?" ሲል ጠየቀውና መልሱን ይጠብቅ ያዘ ___

ልጁ ግን "ገበያ አትክልት ልገዛ እየሄድኩ ነው" አለው፡፡ ይሄን ጊዜ ታዲያ ጠያቂው ልጅ ያጠናውን ፍልስፍና ምን ያድርገው?





ህይወት እንዲህ ናት፡፡ ተዘጋጅታችሁ፣ ተሰናድታችሁ ልትጠብቋት አትችሉም፡፡ ውበቷም ይህ ነው፣ ምትሃቷም ይህ ነው፡፡ ምንም ሳታሳውቃችሁ አንዳች ነገር ይዛ ከች ትልባችኋለች፡፡ አይን ካላችሁ በእያንዳንዱ ቅፅበት አዲስ ነገር እንደሚከሰት እና ቀድሞ የተዘጋጀ ምላሽም እርባና ቢስ እንደሆነ መመልከት ትችላላችሁ፡፡



# የብልህነት መንገድ

# እዕምሮ ሲጠፋ ምስጢር ይገባል

***እውነት የሚባለውን ግኝት ለማግኘት ዝግጁ የሆነ ሰው ብዙ ስህተቶችን ለመስራትም ዝግጁ መሆን አለበት፡፡***

ብልህነት ሀያውነትና ቀጣይነት ነው፣ ግልፅነትና ተጋላጭነት ነው፣ አለመከፋፈልና ያለምንም መደምደሚያ በድፍረት መስራት ነው፡፡ እንዴት ድፍረት ሊባል ቻለ? ድፍረት ነው የተባለው አንድ መደምደሚያ ላይ ተመርኩዛችሁ አንድ ነገር ስትፈፅሙ መደምደሚያው ይጠብቃችኋል፣መደምደሚያው ከለላ፣ ደህንነት ይሰጣችኋል፡፡ በደንብ ታውቁታላችሁ፣ እንዴት ማድረግ እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ፣ ይህን ለመፈፀምም ብቁ ትሆናላችሁ፡፡ ያለ መደምደሚያ መፈፀም ግን በንፅህና መፈፀም ነው፡፡ ማስተማመኛ የለም፣ ልትሳሳቱ ትችላላችሁ፣በመንፈስ ልትንሳፈፉ ትችላላችሁ፡፡

እውነት የሚባለውን ግኝት ለማግኘት ዝግጁ የሆነ ሰው ብዙ ስህተቶችን ለመስራትም ዝግጁ መሆን አለበት፣ አደጋ መጋፈጥ መቻል አለበት፡፡ አንድ ሰው በመንፈስ ሊጓዝ ይችላል፡፡ የሚደርሰው ግን በዚህ መንገድ ነው፡፡ በመንፈስ ብዙ የተጓዘ እንዴት አለመንሳፈፍ እንደሚችል ያውቃል፡፡ አንድ ሰው ብዙ ስህተት በመስራት ስህተት ምን እንደሆነና እንዴት ስህተት አለመስራት እንደሚችል ያውቃል፡፡ ስህተት ምን እንደሆነ ያወቀ ደግሞ ወደ እውነት ይበልጥ ይቀርባል፡፡ ይህ በሌላ ላይ ጥገኛ ሳትሆኑ በግላችሁ የምትፈልጉት ነገር ነው፡፡

የተወለዳችሁት እዕምሮ-የለሽ ሆናችሁ ነው ፡፡ እስኪ ወደ ልባችሁ ይበልጥ ጠልቃችሁ ግቡ፣ ምክንያቱም በዚህ መንገድ ነው በሩ የሚከፈተው፡፡ የተወለዳችሁት እዕምሮ የለሽ ሆናችሁ ከሆነ እዕምሮ ማህበራዊ እንደማለት ነው፡፡ ተፈጥሯዊ ሳይሆን ተኮትኩቶ የሚገኝ ነው፣ ከበላያችሁ ተሰብስቦ የተቀመጠ ነው፡፡ ነፃ ስለሆናችሁ ከዚያ ልትወጡ ትችላላችሁ፡፡ አንድ ሰው





ከተፈጥሮ ውጪ መሆን ባይችልም በተወሰነ ጊዜ በማንኛውም ቅፅበት ከሰው ሰራሽ አጥር መውጣት ይችላል፡፡

ሀያውነት ከማሰብ ይቀድማል፡፡ ስለዚህ ሀያውነት የአእምሮ ሁኔታ ሳይሆን ከዚያ የዘለለ ነው ማለት ነው፡፡ ማሰብ ሳይሆን መሆን፣ መሰረታዊውን ነገር ማወቂያ መንገድ ነው፡፡ ሳይንስ ማለት ማሰብ ነው፣ ፍልስፍና ማለት ማሰብ ነው፣ ሃይማኖት ማለት ማሰብ ነው፡፡ ሃይማኖታዊነት ግን ማሰብ ማለት አይደለም፡፡ ሃይማኖታዊ አቀራረብ ያለማሰብ አቀራረብ ነው፡፡ ወደ እውነት የሚያቀርብ የጠለቀ መንገድ ነው፡፡ መሰናክሎችን በሙሉ ያስወግዳል፣ ነፃ ያደርጋችኋል፣ ወደ ህይወት መፍሰስ ትጀምራላችሁ፡፡ ነጠል ብላችሁ የምትመለከቱ እንደሆናችሁ አታስቡም፡፡ ገለልተኛ፣ ባይተዋር፣ የሩቅ ተመልካች እንደሆናችሁም አይሰማችሁም፡፡ ከእውነት ጋር ትገናኛላችሁ፣ ትታገላላችሁ፣ ትዋሃዳላችሁ፡፡

**ሀያውነት ከማሰብ ይቀድማል፤ ሀያውነት የአእምሮ ሁኔታ ሳይሆን ከዚያ የዘለለ ነው፡፡ ማሰብ ሳይሆን መሆን፣ መሰረታዊውን ነገር ማወቂያ መንገድ ነው፡፡**

ሌላም አይነት እውቀት አለ፡፡ በእርግጥ "እውቀት" ተብሎ ሊጠራ አይችልም፡፡ ከእውቀት ይልቅ ወደ ፍቅር ይቀርባል፡፡ እውቀት የሚለው ቃል በበቂ ሁኔታ አይገልፀውም፡፡ ፍቅር የሚለው ቃል የበለጠ በበቂ ሁኔታ ይገልፀዋል፡፡

በሰው ልጅ የንቃት ታሪክ ውስጥ ቀድሞ ብቅ ያለው እስማት ነበር፡፡ እስማት የሳይንስ እና የሃይማኖት ድብልቅ ነው፡፡ እስማት ከአእምሮ የሆነና ከአእምሮ ያልሆነ ሁኔታ ቅልቅል ነው፡፡ ስለዚህም ከእስማት ፍልስፍና ይፈልቃል፣ ከፍልስፍና ሳይንስ ይመነጫል፡፡ እስማት ከአእምሮ የሆነም፣ ከአእምሮ ያልሆነም ሁኔታ ነው፡፡ ፍልስፍና ከአእምሮ ብቻ ነው፡፡ አእምሮ እና ሙከራ ሲደመሩ ሳይንስን ይሰጣሉ፡፡ ሃይማኖታዊነት ከአእምሮ ያልሆነ ሁኔታ ነው፡፡

**ፍልስፍና ከአእምሮ ብቻ ነው፡፡ አእምሮ እና ሙከራ ሲደመሩ ሳይንስን ይሰጣሉ፡፡ ሃይማኖታዊነት ከአእምሮ ያልሆነ ሁኔታ ነው፡፡**

ሃይማኖታዊነት እና ሳይንስ ወደ እውነታ የሚወስዱ ሁለት መንገዶች ናቸው፡፡ ሳይንስ በሁለተኛው መንገድ የሚገባ ነው፤ ሃይማኖተኛነት ቀጥተኛ ነው፡፡ ሳይንስ ቀጥተኛ ያልሆነ አቀራረብን ይጠቀማል፤ ሃይማኖተኛነት ቀጥተኛ አቀራረብ ነው፡፡ ሳይንስ ዙሪያውን ይዞራል፤ ሃይማኖተኝነት በቀጥታ ወደ እውነታው ልብ ይገባል፡፡

ቀጥሎ ተጨማሪ ነገሮችን እንመልከት .... ማሰብ ሲባል ስለሚታወቁ ነገሮች ብቻ ነው የሚያስበው፡ የታኘከውን ነው የሚያኝከው፡፡ ማሰብ እውነት ሊሆን አይችልም፡፡ ስለማይታወቅ ነገር እንዴት ሊታሰቡ ትችላላችሁ? የፈለገ ነገር ብታስቡ ስለሚታወቅ ነገር ነው የምታስቡት፡፡ ቢበዛ ማሰብ አዲስ ጥምረቶችን ሊፈጥር ይችል ይሆናል፡፡ ከወርቅ የተሰራ በሰማይ የሚበር ፈረስ ልታስቡ ትችላላችሁ፡፡ ይህ ግን አዲስ አይደለም፡፡ በሰማይ የሚበሩ አዕዋፋትን ታውቃላችሁ፤ ወርቅ ታውቃላችሁ፤ ፈረስ ታውቃላችሁ፤ ስለዚህም ከማጣመር ውጪ ምንም አላደረጋችሁም፡፡ ማሰብ ቢበዛ አዲስ ጥምረት ቢፈጥር እንጂ የማይታወቀውን አያውቅም፡፡ የማይታወቀው ከዚህ በላይ ነው፡፡ ስለዚህ ማሰብ እውቀትን ደጋግሞ በመጨመር ተሰበት ውስጥ የሚሄድ ነው ማለት ነው፡፡ የታኘከውን ያኝካል፡፡ ማሰብ ዋና ነገር አይደለም፡፡

**ማሰብ ስለሚታወቁ ነገሮች ብቻ ነው የሚያስበው፡፡ የታኘከውን ነው የሚያኝከው፡፡ ማሰብ እውነት ሊሆን አይችልም፡፡ ማሰብ ቢበዛ አዲስ ጥምረት ቢፈጥር እንጂ የማይታወቀውን አያውቅም፡፡**

እውነት ላይ መድረስ ያለ ማንም እጋዥነት እውነታ ላይ መድረስ፡ እናንተ የመጀመሪያው ሰው የሆናችሁ ያህል እውነታ ላይ መድረስ ነፃ መውጣት ነው፡፡ አዲስነቱ ነፃ ያወጣል፡፡

እውነት እምነት ሳይሆን ልምድ ነው፡፡ እውነት በጥናት አይገኝም፤ እውነት መጋፈጥን ይጠይቃል፡፡ ስለፍቅር የሚያጠና ሰው የተራሮችን ካርታ ተመልክቶ ስለሂማሊያ እንደሚያጠና ሰው ነው፡፡ ካርታው ተራራ አይደለም! በካርታው ማመን ከጀመራችሁ ተራራውን እያጣችሁት ትሄዳላችሁ፡፡ ከካርታው ጋር ይበልጥ በተቀራረባችሁ ቁጥር ተራራው ከፊት ለፊታችሁ ቢሆንም ሊታዩት አትችሉም፡፡





ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ ተራራው ከፊት ለፊታችሁ ቢሆንም እያሳጣችሁ በካርታዎች የተሞላ ናችሁ - የተራራው ካርታዎች፤ በተለያዩ አሳሾች የተዘጋጁ አንድ አይነት ተራራ የሚያሳዩ ካርታዎች- አንዱ ተራራው ላይ የወጣው በሰሜን በኩል ይሆናል፤ ሌላኛው ደግሞ በምስራቅ አቅጣጫ፡፡ አሳሾቹ የተለያዩ ካርታዎችን ሰርተዋል፡፡ ቅዱስ ቁርዓን፤ መፅሃፍ ቅዱስ፤ ጊታ - የአንድ እውነት የተለያዩ ካርታዎች ናቸው፡፡ እናንተ ግን በካርታዎቹ የተሞላችሁ ናችሁ፡፡ ከክብደታቸው ተጭናችኋል፡፡ አንድ ጋት እንኳን መንቀሳቀስ አትችሉም፡፡ በጠዋት ፀሃይ ጫፉ ላይ የሚገኘው የበረዶ ግግር እንደወርቅ የሚያብረቀርቀውን ከፊታችሁ የቆመውን ተራራ ማየት አትችሉም፡፡ እሱን የምታዩበት አይን የላችሁም፡፡

ሚዛናዊ ያልሆነ አይን እውር ነው፡፡ በመደምደሚያዎች የተሞላ ልብም ሙት ነው፡፡ እጅግ ብዙ ቅድመ - ግምቶች ስለሞላችሁ ብልህነታችሁ ስሌቱን፤ ውበቱን፤ ክብደቱን ያጣላችሁት ይሆናል፡፡ ህያው መሆን ግን ፍፁም የተለየ ነገር ነው፡፡

## ሳይንስ ማለት ስለ እውነታዎች ፍፁም እርግጠኛ መሆን ነው

ስለ እውነታዎች በጣም እርግጠኛ ስትሆን ሚስጥሩ አይታያችሁም፡፡ይበልጥ እርግጠኛ በሆናችሁ ቁጥር ሚስጥሩ እየጠፋባችሁ ይሄዳል፡፡ ሚስጥር የተወሰነ ድብቅነትን ይጠይቃል፡፡ ሚስጥር እርግጠኛ ያልሆነ አንድ ነገር ይፈልጋል፡፡ ሳይንስ እውነታ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ሚስጥር ደግሞ እውነታ ላይ ሳይሆን ህልውና ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡

እውነታ የህልውና አካል ነው - አንድ ትንሽ አካል፡፡ ስለ አካላት ማጥናት ቀላል ነውና ሳይንስም ስለ አካላት ያጠናል፡፡ ትንንሽ ስለሆኑ ልትቆጣጠሯቸው ትችላላችሁ፤ አይበልጧችሁም፡፡በእጆቻችሁ ልትጨብጧቸው ትችላላችሁ፡፡ ልትለያዩዋቸው፣ ልትመዝኗቸው ትችላላችሁ፡፡ ስለባህሪያቸው፣ መጠናቸው፣ አማራጮቻቸው እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን በዚህ ሂደት ውስጥ ሚስጥር ይሞታል፡፡ ሳይንስ የሚስጥር ገዳይ ነው፡፡ሚስጥሩን መፍታት ከፈለጋችሁ ፍፁም በተለየ አቅጣጫ በሌላ በር መግባት ይኖርባችኋል፡፡ የአእምሮ አቅጣጫ የሳይንስ አቅጣጫ ነው፡፡ የተመስጦ አቅጣጫ፣ የተዓምር፣ የሚስጥር አቅጣጫ ነው፡፡

ተመስጥዖ ሁሉን ነገር ያልተወሰነ፣ ያልተደመደመ ያደርጋል፡፡ ተመስጥዖ ካርታ ወደሌለው፣ ወዳልተወቀው ይወስዳችኋል፡፡ ተመስጥዖ ቀስ በቀስ ተመልካችና እይታ ውስጥ የሚገባው ነገር አንድ ወደሆኑበት ወህድ ነገር ይወስዳችኋል፡፡ አሁን በሳይንስ ይህን ማድረግ አይቻልም፡፡ በሳይንስ ተመልካቹ ተመልካች መሆን አለበት፣ የሚታየው ነገርም የሚታይ ነገር መሆን ይኖርበታል፡፡ በሁለቱ መካከል ቀጣይነት ያለው የጠራ ልዩነት ይኖራል፡፡ ለአንዲት ቅፅበት እንኳን ራሳችሁን አትረሱም፡፡ለአንዲት ቅፅበት እንኳን በምታዩት ነገር አትሳቡም፣ ከምታዩት ነገር ጋር አትዋሃዱም፣ የምታዩትን ነገር አታፈቅሩም፡፡ ገለል ማለት፣ መተዛዘነ ፍቅም ግዴለሽ መሆን ይኖርባችኋል፡፡ ያ ግዴለሽነት ደግሞ ሚስጥሩን ይገድለዋል፡፡

በእርግጥ ሚስጥሩን ማወቅ የምትፈልጉት ከሆነ በማንነታችሁ ውስጥ አዲስ በር መክፈት ይኖርባችኋል፡፡ ሳይንቲስት መሆናችሁን አቁሙ ማለቴ አይደለም፡፡ ሳይንስ ቀሪ ሥራ ይሆንባችኋል እያልኩ እንጂ፡፡ በቤተ-ሙከራ ውስጥ ሳይንቲስት ሁኑ፣ ከቤተ-ሙከራው በወጣችሁ ጊዜ ግን ስለ ሳይንስ የምታውቁትን በሙሉ እርሱ፡፡ ከዚያም ሳይንሳዊ ባልሆነ መንገድ የአዕዋፋቱን ዝማሬ አድምጡ! ሳይንሳዊ ባልሆነ መንገድ አበቦችን ተመልከቱ! ምክንያቱም አንድን ጽጌረዳ አበባ በሳይንሳዊ መንገድ ስትመለከቱ የምታዩት ነገር ፈፅሞ ይለወጥባችኋል፡፡ሳይንቲስቶች አንድ ገጣሚ አበባውን በሚያይበት አይን አያዩትም፡፡

ልምዱ በሎጂክ ላይ የመሰረተ አይደለም፡፡ ልምዱ በሰውየው ላይ፣ በልምዱ ጥራት ላይ የተወሰነ ነው፡፡

### አንድ አበባ ስትመለከቱ አበባ ሁኑ፣ በአበባው ዙሪያ ደንሱ

አንድ ዘፈን ዝፈኑ፡፡ ነፋሱ ቀዝቃዛ እና ደረቅ ነው፣ ፀሃይዋ ሞቃት ናት፣ አበባው እየፈካ ነው፡፡ አበባው ከነፋሱ ጋር እየደነሰ፣ እየተደሰተ፣ ዘፈን እየዘፈነ፣ የምስጋና መዝሙር እያቀረበ ነው፡፡ አብራችሁ ደስታውን ተቋደሱት! ችላ ማለታችሁን፣ መንጠላችሁን፣ ተጨባጭ ነገር መፈለጋችሁን ተውት፡፡ ሳይንሳዊ አመለካከታችሁን በሙሉ አስወግዱ፡፡ በመጠኑ ፍሰሱ፣ ቅለሉ፣ ወህድ ሁኑ፡፡ ከአበባው ጋር በልባችሁ ተነጋገሩ፣ አበባው





በማንነታችሁ ውስጥ ይሰረፃል፡፡ ወደ ራሳችሁ ጋብዙት- እንግዳችሁ ነው! ያን ጊዜ ከሚስጥሩ በመጠኑ ትቋደሳላችሁ፡፡

ይህ ወደ ሚስጥሩ የሚወስዳችሁ አንድ እርምጃ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ለቅፅበት ያህል ተሳታፊ ከሆናችሁ ቁልፉን አውቃችሁታል፣ የመጨረሻውን ደረጃ ማስተር አውቃችሁታል ማለት ነው፡፡ ከዚያም በምታደርጉት ነገር ሁሉ ተሳታፊ ሁኑ፡፡ ሜካኒካዊ በሆነ መንገድ ሳይሆን እንዲሁ ተራመዱ፣ ዝም ብላችሁ መመልከት ሳይሆን ሁኑት፡፡ ስትደንሱ ቴክኒካዊ በሆነ መንገድ አይሁን፣ ቴክኒክ እዚህ ቦታ የለውም፡፡ ቴክኒካዊ በሆነ ሁኔታ ትክክል ብትሆኑም ጠቀሜታውን ደስታ ሊታጡት ትችላላችሁ፡፡ ከዳንሱ ጋር ተዋሃዱ፣ ዳንሰኛውን ረስታችሁ ዳንሱን ሁኑ፡፡

ይህ አይነቱ ውህደት በህይወታችሁ ውስጥ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ መከሰት ሲጀምር፣ በአካባቢያችሁ የመጥፋት፣ ምንም የመሆን፣ ራስን የመርሳት ነገር ሲጀምር ........ እናንተ ሳትሆኑ አበባው እዚያ ሲገኝ፣ እናንተ ሳትሆኑ ቀስተ-ደመናው እዚያ ሲገኝ፣እናንተ ሳትሆኑ ደመናው በውስጥም በውጭም ሲንሳፈፍ ..... በውስጣችሁ ፀጥታ ሲሰፍን - ከንፁህ ፀጥታ፣ ያልተነካ ፀጥታ፣ከምክንያት፣ ከሃሳብ፣ከስሜት ካልታወከ ፀጥታ በስተቀር በውስጣችሁ ምንም ሳይኖር ሲቀር ..........ያን ጊዜ በተመስጥዖ ውስጥ ናችሁ ማለት ነው፡፡ አእምሮአችሁ ጠፍቷል፡፡ አዕምሮ ሲጠፋ ደግሞ ሚስጥር ይገባል፡፡



# የማመን መንገድ

## የተኮተኮተ ማመን፣ እምነት ይሆናል

**አንድ ሰው ምንም ጥያቄ ሳያነሳ ህይወትን የሚመለከታት ከሆነና በድፍረት፣ ያለ ፍራቻ በቀላሉ የሚገባባት ከሆነ አዕምሮው በስሏል ማለት ነው፡፡**

ማመን ከሁሉም የበለጠ ብልህነት ነው፡፡ ሰዎች ለምንድነው የማያምኑትን የራሳቸውን ብልህነት ስለማያምኑ፤ ምናልባት እንታለል ይሆናል ብለው ስለሚፈሩ፣ ስለሚፈሩ ይጠራጠራሉ፡፡ ጥርጣሬ ከፍርሃት ነው የሚመነጨው፡፡ ጥርጣሬ በብልህነታችሁ ውስጥ ሲጎድል ሲኖር የሚፈጠር ነው፡፡ ለማመንም ሆነ ወደ ማመን ለመግባት ልብ - ሙሉነት አይኖራችሁም፡፡ ማመን ትልቅ ብልህነት፣ ድፍረትና ጥንካሬ ይጠይቃል፡፡ ወደ ማመን ለመግባት ትልቅ ልብ ያስፈልጋል፡፡ በቂ ብልህነት ከሌላችሁ ራሳችሁን በጥርጣሬ ትከላከላላችሁ፡፡

ብልህነት ካላችሁ የሚታተው ዓለም በሙሉ ቢጠፋ እንኳን በማይታወቀው ውስጥ ተፈጥሯታችሁ መቀመጥ እንደምትችሉ ስለምታውቁ ወደማይታወቀው ለመሄድ ዝግጁ ናችሁ፡፡ በማይታወቀው ውስጥ ኑሯችሁን መቀለስ ትችላላችሁ፡፡ ብልህነታችሁን ታምናላችሁ፡፡ ጥርጣሬ አጥር ሆኖ ቢቆምም ብልህነት ራሱን ከፍተት ያደርጋል - ምክንያቱም ቸፈለገው ነገር ቢከሰት በበቂ ሁኔታ እመከተዋለሁ፣ እታገለዋለሁ" ብሎ ያምናልና ነው፡፡ የማይደረባ አዕምሮ በራሱ አይተማመንም፡፡ በመደምደሚያ የተሞላ እውቀት የማይደረባ ነው፡፡

ብልህነት ግን ንቃት ነው፡፡ ክፍተት ነው፤ በመደምደሚያ የተሞላ አይደለም፡፡ ልክ እንደ ሀገን ገደሀ፣ የዋህ ሆኖ ይወጣል፡፡

ህይወትን ለመገንዘብ አትሞክሩ፤ ህይወትን ኑሯት እንጂ! ፍቅርን ለመገንዘብ ከመሞከር ይልቅ ራሱን ፍቅርን ሁኑ፡፡ ይህን ካደረጋችሁ እውቀት ከተግባር እንደሚመነጭ ታውቃላችሁ፡፡ እውቀት ሚስጥርን





እንደማያጠፋ፣ ብዙ ባወቃችሁ ቁጥር ብዙ የሚታወቅ ነገር እንደቀራችሁ ታውቃላችሁ፡፡

ህይወት ችግር አይደለችም፡፡ ህይወትን እንደ ችግር መመልከት የተሳሳተ መንገድ እንደመያዝ ነው፡፡ ህይወት መኖር፣ መፈተር፣ መሆን ያለባት ሚስጥር ናት፡፡

በእርግጥ ሁልጊዜ ማብራሪያ የሚፈልግ አዕምሮ ፈሪ አዕምሮ ነው፡፡ በጣም ስለሚፈራም ሁሉም ነገር እንዲብራራለት ይፈልጋል፡፡ ማብራሪያ ካልተሰጠው በቀር ወደ አንድ ነገር አይገባም፡፡ ገለፃ ከተደረገለት ግን ወሰኑን ያውቀው ያህል ይሰማዋል፡፡ መልክዓ ምድሩን በሚያውቀው በካርታው፣ በመለያና መልክ በተጠረዘ መመሪያው፣ በጊዜ ሰሌዳው ታግዞ መጓዝ ይችላል፡፡ ያለምንም ካርታ፣ ያለምንም መመሪያ ወደማያውቀው ድንበር ለመሻገር ዝግጁ አይደለም፡፡ ህይወት ግን እንዲያ ናት፡፡ ህይወት ሁልጊዜም በለውጥ ላይ ናትና ምንም አይነት ካርታ አያስፈልጋትም፡፡ እያንዳንዱ ቅፅበት አሁን ነው፡፡ ከዚያ በታች ምንም አርጌ ነገር እንደሌለ እንግራችኋለሁ፣ ሁሉም ነገር አዲስ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ፍፁም በሆነ እንቅስቃሴ ውስጥ ነው፡፡ ቋሚው ነገር ለውጡ ብቻ ነው፤ ለውጡ ብቻ ነው የማይለወጠው፡፡

ሁሉን ነገር ስለሚለውጥ ካርታ አይኖራችሁም፤ ካርታው ዝግጁ በሆነ ቅፅበት ጊዜው ያለፈበት ይሆናል፡፡ ካርታው ዝግጁ በሆነበት ቅፅበት ጥቅም አልባ ይሆናል፡፡ ህይወት ምዝዋሯን ቀይራለች፡፡ ህይወት አዲስ ጨዋታ መጫወት ጀምራለች፡፡ ህይወት የምትለካ አይደለችምና በካርታ ልትከተሏት አትችሉም፤ መመሪያ መጻሀፍት የሚያገለግሉት ለቋሚ ነገሮች ነውና ህይወትን በመመሪያ መፃህፍት ማግኘት አይቻልም፡፡ ህይወት የረጋች አይደለችም - ሁሌም በእንቅስቃሴ ላይ፣ ሁሌም በሂደት ውስጥ ናት፡፡ ካርታ ልታወጡላት አትችሉም፡፡ የምትለካ ሳትሆን የማትለካ ሚስጥር ናት፡፡ ስለዚህ ማብራሪያ አትጠይቁ፡፡

ይህንንም የአዕምሮ ብስለት ብዬ እጠራዋለሁ፡፡ አንድ ሰው ምንም ጥያቄ ሳያነሳ ህይወትን የሚመለከታት ከሆነና በድፍረት፣ ያለፍራቻ በቀላሉ የሚገባባት ከሆነ አእምሮው በስሏል ማለት ነው፡፡

## ዓለም በሃሰተኛ ሃይማኖተኞች የተሞላች ናት

አብያተ ክርስቲያናት፣ ቤተ-መቅደሶች፣ ጉሩ ድዋራስ፣ መስጊዶች በሃይማኖተኛ ሰዎች የተሞሉ ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ ግን አለም ሃይማኖት የለሽ መሆኗ አይታያችሁም? ብዙ ሃይማኖተኛ ሰዎች ቢኖሩም አለም ግን ሃይማኖት የለሽ ናት ፡፡ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? እያንዳንዱ ሰው ሃይማኖተኛ ቢሆን ጠቅላላው ግን ኢ-ሃይማኖተኛ(መዓይም) ነው፡፡ ሰዎች እምነትን "ትተኩተው" አልምተዋል፡፡ እምነት ልምድ መሆኑ ቀርቷል፡፡ ሰዎች እንዲያምኑ ተምረዋል፣ ሰዎች እንዲያውቁ ትምህርት ተሰጥቷቸዋል - እዚህ ጋር ነው ስብዕና የጠፋው፡፡

ከልጅነታችሁ ጀምሮ እንድታምኑ ተምራችኋል፡፡ የሁሉም ሰው አዕምሮ በእግዚአብሄር፣ በነፍስ፣ በዚህ፣ በዚያ እንዲያምን ተደርጓል፡፡ አሁን ያ እምነት ወደ አጥንታችሁ ዘልቋል፣ ከደማችሁ ጋር ተዋህዷል፣ ግን ያው እምነት ነው ባታውቁትም፡፡ ካላወቃችሁ ደግሞ ነፃ አትወጡም፡፡ እውቀት ነፃ ያወጣል፣ ማወቅ ብቻ ነው ነፃ የሚያደርገው፡፡ ሁሉም እምነቶች የውሰት ናቸው- ሌሎች የሰጡዋችሁ፡፡ እናንተ ያበቀላችኋቸው አይደሉም፡፡ ታዲያ እንዴት አድርጐ ነው የውሰት ዕቃ ወደ እውነተኛው፣ ፍፁም እውነተኛ ወደሆነው የሚመራችሁ? ከሌሎች የተቀበላችሁትን በሙሉ ጣሉት፡፡ ሰርቃችሁ፣ ለፍታችሁ ሳይሆን በስርቆት ባገኛችሁት ንዋይ ሃብታም ከመሆን ለማኝ መሆን ይሻላል ፡፡ በውሰት ዕቃ፣ በባህል፣ በውርስ ሀብታም ከመሆን ይልቅ አለመሆን ይሻላል፡፡ የሌላ ከመሆን ለማኝ መሆን ይሻላል፡፡ ድህነት እውነት ነውና በውስጡ ሃብት አለው፡፡ የእናንተ የእምነት ሀብታምነት ደግሞ በጣም ድህነት ነው፡፡ እነዚያ እምነቶች በጣም ጥልቅ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ቢበዛ ቆዳን አልፈው ቢገቡ ነው፡፡ ትንሽ ብትፍቁት አለማመን ብቅ ይላል፡፡

በእግዚአብሄር ታምናላችሁ፡፡ አንድ ነገር አልሳካ ሲላችሁ ግን ወዲያውኑ አለማመን ውስጥ ትገባላችሁ፡፡ "አላምንም፣ በእግዚአብሄር አላምንም!" ትላላችሁ፡፡ በእግዚአብሄር ስታምኑ ብትቆዩም፣ የምትወዷቸው ሰዎች በሞት ሲለዩዋቸው አለማመናችሁ ብቅ ይላል፡፡ በእግዚአብሄር እያመናችሁ የምትወዷቸው ሰዎች ስለሞቱ ብቻ እምነታችሁ ጠፋ ማለት ነው? ይህ





ብዙም ዋጋ የለውም፡፡ እምነት ሊጠፋ አይችልም - እንዴ ከተተከለ "ግንም ሊያጠፋው አይችልም፡፡ ማንም፣ ምንም ነገር ሊያጠፋው አይችልም፡፡

ስለዚህ በማመን እና በእምነት መካከል ብዙ ልዩነት እንዳለ አስተውሉ፡፡ ማመን ግላዊ ሲሆን እምነት ማህበራዊ ነው፡፡ ማመን በውስጣችሁ የምታሳድጉት ነገር ነው፣ እምነት ግን ማንም ሁኑ ማን የሚጫንባችሁ፣ የትም ብትሄዱ አብሮዋችሁ የሚሄድ ነው፡፡ ስለዚህ እምነቶቻችሁን አራግፉ፡፡ እርግጥ እምነትን ስትተው ጥርጣሬ ይፈጠራል፣ ፍርሃትም ይኖራል፡፡ እያንዳንዱ እምነት ጥርጣሬን በውስጣችሁ የሆነ ቦታ ላይ ይደብቀዋል፡፡ ግን ስለ እሱ አትጨነቁ፣ እንዲያውም ያ ጥርጣሬ እንዲወጣ አድርጉት፡፡ ከመንጋቱ በፊት ይጨልማል፡፡ እያንዳንዱ ሰው በጥርጣሬ ውስጥ ማለፍ አለበት፡፡ መንገዱ ረጅም፣ ምሽቱም ጨለማ ነው፡፡ ከረጅሙ ጉዞ እና ከምሽቱ ጨለማ በኋላ ግን ጉህ ይቀዳል፡፡ ያን ጊዜ ሁሉም ነገር ዋጋ እንዳለው ትገነዘባላችሁ፡፡ ማመን "ሊኮተኮት" አይችልም - ለመኮትኮትም አትሞክሩ፡፡ የሰው ዘር በሙሉ ይህን ሲያደርግ ነው እየሞከረ ያለው፡፡ የተኮተኮተ ማመን እምነት ይሆናል፡፡ በውስጣችሁ ያለውን ማመን አውጡት እንጂ አትኮትኩቱት፡፡ ወደ ማንነታችሁ ዝለቁና አውጡት፡፡

**ማመን ግላዊ ሲሆን እምነት ማህበራዊ ነው፡፡ ማመን በውስጣችሁ የምታሳድጉት ነገር ነው፣ እምነት ግን ማንም ሁኑ ማን የሚጫንባችሁ፣ የትም ብትሄዱ አብሮአችሁ የሚሄድ ነው፡፡**

አሁን ወደማይታወቀው ሂያጅ ስለሆናችሁ መመራመራችሁ ማመን ያስፈልገዋል፡፡ ከተለመደው እና ከባህላዊው ርቃችሁ ልትሄዱ ነውና ማመንና ድፍረት ያስፈልጋችኋል፡፡ ከአብዛኛው ሰው እየራቃችሁ ነው፡፡ ወደ ክፍቱ ውቅያኖስ ልታመሩ ስለሆነ ሊላኛው ባህር ከነመኖሩም አታውቁም፡፡

ለማመን ሳላዘጋጃችሁ በፊት ወደ ምርምሩ ውስጥ አላስገባችሁም፡፡ እርስ በርሱ የሚጣረስ ቢመስልም ሌላ ምን ማድረግ እችላለሁ? - ህይወት እንደሁ እንዲህ ናት፡፡ በትልቁ የሚያምን ሰው ነው በትልቁ መጠራጠር፣ በትልቁ መመራመር የሚችለው፡፡

በጥቂቱ የሚያምን ሰው በጥቂቱ ነው የሚጠራጠረው፡፡ ማመን የማይችል ሰው እንደሚጠራጠር ማስመሰል ብቻ ነው የሚችለው፡፡ በጥልቀት መጠራጠር አይችልም፡፡ ጥልቀቱ በእምነት የሚመጣ ነው - ደግሞም አደጋ ነው፡፡ እናንተን ካርታ ወዳልወጣለት ባህር ከመላኬ በፊት ብቻችሁን ለምትጓዙበት ግዙፍ ጉዞ ሳዘጋጃችሁ ይገባል፡፡ወደ ጀልባዋ ለመሬችሁ እችላለሁ ገና በመጀመሪያ ስለ ማመን ውበት፡ ስለልብ መንገድ አስደሳችነት ልታውቁ ይገባል፡፡ ከዚያ ወደ ከፍተኛ የእውነት ውቅያኖስ በሄዳችሁ ጊዜ ብርታት የሚሆናችሁን ድፍረት ታገኛላችሁ፡፡ የፈለገው ነገር ቢከሰት በውስጣችሁ በቂ እምነት ይኖራችኋል፡፡

እስኪ በደንብ አስተውሉ፡፡ የገዛ ራሳችሁን ካላመናችሁ ሌላውን እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ? ፍፁም የማይቻል ነገር ነው፡፡ ራሳችሁን የምትጠራጠሩ ከሆነ እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ? የምታምኑት እናንተ ናችሁ፡፡ ራሳችሁን ካላመናችሁ ደግሞ እምነታችሁን እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ? እውቀት ወደ ብልህነት ከመለወጡ በፊት ልብ መከፈቱ የግድ ያስፈልጋል፡፡ በእውቀት እና በብልህነት መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው፡፡

ብልህነት በልብ ያለ እውቀት ነው፡፡ ልብ እንዴት ማመን እንዳለበት ያውቃል፡ እውቀት ደግሞ እንዴት መፈለግና መመራመር እንዳለበት ያውቃል፡፡

አንድ ጥንታዊ የምስራቃውያን ታሪክ አለ፡፡ እንዲህ ይላል፦

ሁለት ለማኞች ከአንድ መንደር ወጣ ብለው ይኖሩ ነበር፡፡ አንደኛው አይነስውር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እግሮቹ ተቆርጠዋል፡፡

አንድ ቀን እነዚህ ለማኞች የሚኖሩበት በመንደሩ አቅራቢያ የሚገኘው ደን በእሳት ይያያዛል፡፡ በእርግጥ ሰዎቹ ከአንድ ህዝብ የሚለምኑ፡ በአንድ ሙያ የተሰማሩ ተተናታኞች ነበሩ ፡፡ እንዳቸው በሌላኛቸው ይበሳጫሉ፡፡ ወዳጆች ሳይሆኑ ጠላቶች ናቸው፡፡

በአንድ ሙያ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ወዳጆች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ጥያቄው የውድድር፡ የደንበኞች ነውና በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ የአንድን ሰው ደንበኛ ልትቀሙ ትችላላችሁ፡፡ ለማኞች ደንበኞቻቸውን ይለያሉ፡ "ይህ የእኔ ደንበኛ ነው፡፡ እታስቸግረው" ይባባላሉ፡፡ እናንተ የየትኛው ለማኝ ደንበኛ





እንደሆናችሁ፡ የእናንተ ለማኝ የትኛው እንደሆን ባታውቁም አንድ በመንገድ ዳር የሚለምን ለማኝ የራሱ አድርጉአችኋል፡፡ ታማኙና ፍልሚያውን አሸንፎ ይሆናል -አሁን እናንተ የእሱ ናችሁ፡፡

በዩኒቨርሲቲው አካባቢ የማየው አንድ ለማኝ ነበር፡፡ አንድ ቀን ገበያ ውስጥ አገኘሁት፡፡ ወጣቶች ቸር ናቸውና ከዩኒቨርሲቲው አካባቢ አይጠፉም፡ በእድሜ የገፉት የበሰለ ንፉግና ፈሪ ናቸው፡፡ ሞት እየቀረባቸው ነውና አሁን የሚተማመኑበት ብቸኛው ድጋፋቸው ገንዘባቸው ነው፡፡ ገንዘብ ካላቸው ሌሎች ሊረዷቸው ይችላሉ፡፡ ገንዘብ የሌላቸው ከሆኑ ልጆቻቸው እንኳን አይጨነቁላቸውም፡፡ ወጣቶች አባካኝ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ወጣቶች ስለሆኑ ያባከኑትን እንደገና ሊያገኙት ይችላሉ፡ ህይወት እዚያ አለች፡ ረዥም ህይወት ከፊታቸው ይጠብቃቸዋል፡፡

አንድ የሀገር ተማሪ ዩኒቨርስቲ የሚገባው ሃብታም ቤተሰቦች ያሉት ከሆነ ነበርና ለማኙም ሃብታም ነበር፡፡ ሃብት የሌለው ተማሪ መታገል ይጠበቅበታል፡፡ ጥቂት ድሃ ተማሪዎች እዚያ የሚገቡ ቢሆንም ህይወታቸው በስቃይ የተሞላች ናት፡፡ እኔም ከድሃ ቤተሰብ የተገኘሁ ነኝ፡፡ ምሽቱን በሙሉ የአንድ ጋዜጣ አርታኢ ሆኜ እሰራና ቀን ሲሆን ወደ ዩኒቨርሲቲ እሄዳለሁ፡፡ ለብዙ ዓመታት በቀን ከሶስት ወይም ከአራት ሰዓታት በላይ አልተኛም ነበር - እሱንም በቀንና ማታ ጊዜ ሳገኝ የማደርገው ነው፡፡

እናም ይህ ለማኝ በጣም ጠንካራ ነበር፡፡ በሩ ክፍት ቢሆንም ማንም ለማኝ ወደ ዩኒቨርስቲው መንገድ መግባት አይችልም፡፡ ሁሉም ሰው ዩኒቨርስቲው የማን እንደሆን ያውቃል - የዚያ ለማኝ ነው! አንድ ቀን በሽማግሌው ፋንታ አንድ ወጣት አየሁ፡፡ "ምን ተከሰተ? ሽማግሌውስ?" ስል ጠየቅኩት፡፡

"እማቴ ናቸው፡፡ ዩኒቨርሲቲውን በስጦታ መልክ ሰጥተውኛል" አለኝ፡፡ ዩኒቨርስቲው ግን የባለቤትነት ለውጥ መደረጉን አያውቅም፡፡ አሁን ባለቤቱ ተቀይሯል፡፡ "ልጃቸውን ነው ያገባሁት" አለኝ ወጣቱ፡፡

ሕንድ ውስጥ አንድ ሰው ሲያገባ የጥሎሽ ይሰጣል፡፡ እናንተ ልጅቷን ማግባት ብቻ አይደለም፡፡ አማታችሁ ሀብት ያላቸው ከሆኑ መኪና ወይም አንድ አነስተኛ ቤት ይሰጡዋችኋል፡፡ የሌላቸው ከሆኑ ቢያንስ ሞተር

ሳይከል ይሰጡዋችኋል፡፡ ይህ ባይኖራችሁ እንኳን ብስክሌት፣ ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን ወይም ትንሽ ገንዘብ ሊሰጡዋችሁ የግድ ነው፡፡ በእርግጥ ሃብታም ከሆኑ ውጪ እንደትሄዱ፣ እንድትማሩ፣ ሃኪም፣ መሃንዲስ እንድትሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቹላችኋል- ይከፍሉላችኋል፡፡

የዚህ ሰማኝ ቤት ልጅ በማግባቷ ወጣቱ እንደ ጥሎሽ ይህ ዩኒቨርሲቲ በጠቅላላ ተሰጥቶታል፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ይህ መንገድ እና ይህ ዩኒቨርሲቲ የእኔ ናቸው፡፡ እማቴም ደንበኞቼ እነማን እንደሆኑ አሳይተውኛል" አለኝ፡፡

ሽማግሌውንም በገበያ ውስጥ አገኘሁትና "ግሩም ጥሎሽ በመስጠት መልካም አድርገሃል" አልኩ፡፡

"አዎ" አለኝ፡፡ "ያለቺኝ አንዲት ልጅ ናት፡፡ ለእማቹ አንድ ነገር ማድረግ ነበረብኝ፡፡ ምርጥ የመሰመኛ ስፍራ ነው የሰጠሁት፡፡ አሁን ገበያውን ለመቆጣጠር እየሞከርኩ ነው፡፡ እዚህ ብዙ ደንበኞች ያሏቸው ቀደምት ለማኞች ስላሉ ፉክክሩ ጠንካራ ነው፡፡ ግን ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም፡፡ እወጣዋለሁ፣ የተወሰኑትን ከዚህ አባርራቸዋለሁ፡፡"

በእርግጥም ይህን አድርጉታል፡፡

እናም ደኑ በእሳት በተያያዘ ጊዜ ሁለቱ ለማኞች ለትንሽ ጊዜ ያህል ሲጣሉ ቆዩ፡፡ ጠላቶች ቢሆኑም ጉዳዩ አስቸኳይ ነበር፡፡ አይነ-ስውሩ እግር ለሌለው ሰው "ብቸኛው መንገድ አንተ ትከሻዎቼ ላይ ተቀምጠህ እግሮቼን ትጠቀማለህ፡፡ እኔ ደግሞ አይኖችህን እጠቀማለሁ፡፡ ራሳችንን የምናድንበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው" አለው፡፡

ሁኔታው ግልፅ ነበር፡፡ ምንም ችግር የለም፡፡ እግር የሌለው ሰው ብቻውን በእሳት ስለተያያዘ ሊያቋርጠው አይችልም፡፡ ትንሽ መንቀሳቀስ ቢችልም ይህ ምንም አይጠቅመውም፡፡ አንድ በፍጥነት መውጫ መንገድ ያስፈልጋል፡፡ አይነ-ስውሩም ቢሆን ብቻውን መውጣት እንደማይችል ገብቶታል፡፡ እሳቱ የት እንዳለ፣ መንገዱ በየት አቅጣጫ እንደሆነ፣ የትኞቹ ዛፎች እንደተቃጠሉና እንዳልተቃጠሉ አያውቅም፡፡ አይነ-ስውር በመሆኑ ሊጠፋ ይችላል፡፡ ሁለቱም ግን ብልሆች ነበሩ፤ ጠላትነታቸውን አቁመው ወዳጅ መሆን በመቻላቸው ህይወታቸውን አተረፉ፡፡





## ህይወት ትርጉም አልባ መስላ የታየቻቸው በታወረ አይናቸው ብርሃን ማየት ስለሞከሩ ነው፡፡ ይህ የማይቻል ነገር ነው፡፡

ይህ የምስራቃውያን አፈ-ታሪክ ነው፡፡ ገፀ-ባህሪያቱ ብልህነታችሁን እና ልባችሁን ይወክላሉ፡፡ ታሪኩ የለማኞቹ ሳይሆን የእናንተ ነው፡፡ የምናወራው ስለተቃጠለው ደን ሳይሆን ስለ እናንተ ነው - ምክንያቱም ሁላችንም በእሳት ተያይዘናል፡፡ በየደቂቃው እየተቃጠልን፣ እየተሰቃየን፣ እየተጐዳን እና እየተገደልን ነው፡፡ ብልህነታችሁ ብቻውን እውር ነው፡፡ እግሮች ስላሉት በፍጥነት ሊሮጥ፣ በፍጥነት ሊንቀሳቀስ ቢችልም አይነ-ስውር በመሆኑ ትክክለኛውን አቅጣጫ መለየት አይችልም፡፡ መንገዳገድ፣ መውደቅ፣ መሰናከል፣ ራሱን መጉዳት እና የህይወትን ጣዕም ማጣት የዘወትር ልማዱ ይሆናል፡፡ በመላው ዓለም የሚገኙ ምሁራን "ህይወት ትርጉም አልባ ናት" የሚሉት ለዚያ ነው፡፡ ህይወት ትርጉም አልባ መስላ የታየቻቸው በታወረ አይናቸው ብርሃን ማየት ስለሞከሩ ነው፡፡ ይህ የማይቻል ነገር ነው፡፡

የሚያይ፣ የሚሰማ ግን እግር የሌለው፣ መሮጥ የማይችል ልብ በውስጣችሁ አለ፡፡ እዚያው ሆኖ እየመታ፣ ይጠባበቃል ..... አንድ ቀን ብልህነት ይገባውና የልብን አይን መጠቀም ይፈልግ ይሆናል፡፡

ማመን የሚለውን ቃል ስጠራ የልብን አይኖች ማለቴ ነው፡፡ጥርጣሬ ስል የብልህነትዎን እግሮች ማለቴ ነው፡፡

ሁለቱም በአንድነት ከእሳቱ ሊወጡ ይችላሉ፤ ይህ ከሆነ ምንም ችግር የለም፡፡ ነገር ግን ብልህነት ልብን በትከሻው መሸከም ይኖርበታል፤ እንዲያ መሆንም አለበት፡፡ ልብ አይኖች እንጂ እግሮች የሉትም፤ ብልህነት ልብን እያደመጠ መንገዱን ሊከተለው ይገባል፡፡

በልብ ውስጥ ያለ ሊቅነት ብልሀ ይሆናል፡፡ ይህ ለውጥ ነው ምሉዕ የሆነ ለውጥ፡፡ ከዚያም ሰውየው ምሁር ብቻ ሳይሆን ብልሀ ይሆናል፡፡

ልብና ብልህነት ሲገናኙ ጥበብ ይፈልቃል፡፡ የልብ ምታችሁንና የማሰብ ችሎታችሁን አጣምራችሁ አንድ ሀብር መፍጠር ከቻላችሁ መላውን ሚስጥር፣ የሚስጥራቱን ሁሉ መክፈቻ ቁልፍ በእጃችሁ አስገባችሁ ማለት ነው፡፡



# የየዋህነት መንገድ

## የዋህ ከሆናችሁ ድፍረት አያስፈልጋችሁም

***ግንዛቤ ያለው ሰው በእያንዳንዱ ያለፈ ቅፅበት እየሞተ ወደፊት ደጋግሞ ይወለዳል፡፡ አሁን የቆመበት ጊዜ የዳግም ውልደት፣ የትንሳኤ፣ የለውጥ ጊዜው ነው፡፡***

ዋናው ቁምነገር ድፍረት ሳይሆን የተወቀው ሙት፣ ያልታወቀውን ደግሞ ህያው መሆን ነው፡፡ ወደታወቀው መጠጋት ወደ አስከሬን እንደመጠጋት ነው፡፡ ከዚህ ጥገኝነት ለመላቀቅ ድፍረት አይጠይቅም፡፡ በእርግጥ በአንድ አስከሬን ለመተማመን ድፍረት ይጠይቃል፡፡ የለመዳችሁት፣ የኖራችሁበት፣ የሰጣችሁን ነገር ማወቅ ይገባችኋል፡፡ የት ደርሳችኋል? አሁንም ድረስ ባዶ አይደላችሁም ወይ? መከፋታችሁ፣ ተስፋ መቁረጣችሁ፣ ጣዕም አልባነታችሁ ጥልቅና ከፍተኛ አይደለም ወይ? ይህ ሁሉ ሆኖ ግን እውነቱን በመደበቅ እና ውሸት በመፍጠር ቀጥላችሁበታል፡፡





ጥያቄው ይህ ነው- ትናንት የምታውቁት ነገር ሁሉ ያለፈ መሆኑን በግልፅ ማየት፡፡ ትናንት የምታውቁት የመቃብር አካል ሆኗል፡፡ የምትፈልጉት መቃብር መውረድ ነው ወይስ መኖር? ጥያቄው የዛሬ ብቻ አይደለም፣ ነገና ከነገ ወዲያም ተመሳሳይ ጥያቄ ይነሳል፡፡ ከህይወታችሁ ሜዳ ስትደርሱም ይህ ጥያቄ ይኖራል፡፡

የፈለገ መረጃ፣ እውቀት፣ ልምድ ብታጠራቅሙም በመረመራችኋቸው ጊዜ አብራችሁ ትጠፋላችሁ፡፡ እነዚያን ባዶ ቃላት፣ ያን ሙት ሸክም መሸከም ማለተ ህይወታችሁን ቸማጥፋት፣ ህይወታችሁን መጨቆን፣ ራሳችሁን ህያው ከመሆን መግታት፣ በእያንዳንዱ ቅፅበት ከምትጠብቁት የደስታ ህይወት ራሳችሁን ማስወጣት ማለት ነው፡፡

ግንዛቤ ያለው ሰው በእያንዳንዱ ያለፈ ቅፅበት እየሞተ ወደፊት ደጋግሞ ይወለዳል፡፡ አሁን የቆመበት ጊዜ የዳግም ውልደት፣ የትንሳኤ፣ የለውጥ ጊዜው ነው፡፡ የመጀመሪያው ጉዳይ ድፍረት ሳይሆን ግንዛቤ ነው፡፡ ምን ምን እንደሆነ በግልፅ የማወቅ ጉዳይ ነው፡፡

ሁለተኛው ነገር የድፍረት ጥያቄ ቢኖር እንኳን ማንም ሊሰጣችሁ አለመቻሉ ነው፡፡ እንደ ስጦታ የሚሰጥ ነገር አይደለም፡፡ አብራችሁት የምትወለዱት እንጂ አብራችሁት የምታድጉት፣ የምታረጋግጡት አይደለም፡፡

የዋህነት ድፍረት እና ግልፅነት ነው፡፡ የዋህ ከሆናችሁ ድፍረት አያስፈልጋችሁም፡፡ ከየዋህነት በላይ ግልፅነት የለምና ሌላ ግልፅነት መጠበቁ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ስለዚህ ዋናው ነገር የአንድ ሰውን የዋህነት እንዴት መጠበቅ ይቻላል የሚለው ነው፡፡

የዋህነት የሚገኝ ነገር አይደለም፣ በትምህርት እንኳን የሚገኝ አይደለም፡፡ እንደ ስነ-ስዕል፣ ሙዚቃ፣ ስነ-ግጥም ወይም ስነ-ልሁፍ አይነት ዝንባሌም አይደለም፣ የዋህነት እንዲያ አይደለም፡፡ የዋህነት ልክ እንደ መተንፈስ አብራችሁት የምትወለዱት ነው፡፡

የዋህነት በማንኛውም ሰው ተፈጥሮ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ማንም የዋህ ሳይሆን አልተወለደም፡፡

እንድ ሰው የዋህ ሳይሆን እንዴትስ ይወለዳል? ውልደት ማለት ምንም እንዳልተጻፈበት ነጭ ወረቀት ሆኖ ወደዚህ ዓለም መምጣት ማለት ነው፡፡ የትናንት ሳይሆን የነገ ታሪክ ነው ያላችሁ፡፡ ይህ ነው የየዋህነት ትርጉም፡፡ ስለዚህ ሁሉንም የየዋህነት ትርጉሞች ማወቁ መልካም ነው፡፡

የመጀመሪያ ትርጉም፡- ትናንት ሳይሆን ነገ ማለት ነው፡፡

ትናንት ትዝታ፣ ልምድ፣ ግምት ይሰጣችኋልና የዛባ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ጉበዝ ቢያደርጉዋችሁም ግልፅ አያደርጉዋችሁም፣ ብልጥ ቢያደርጉዋችሁም ብልህ አያደርጊዋችሁም፡፡ በዓለም ስኬታማ ሊያደርጊዋችሁ ይችሉ ይሆናል፤ በውስጣችሁ ግን ትወድቃላችሁ፡፡ በዓለም የምታገኙት ስኬት በሙሉ በውስጣችሁ ከሚደርስባችሁ ውድቀት ጋር ሲነፃፀር ሚዛን የሚያነሳ አይደለም፡፡ በመጨረሻ ብቻችሁን የምትቀሩት ከውስጣዊ ማንነታችሁ ጋር ነው፡፡ ሁሉም ይጠፋል፤ ክብራችሁ፣ ሃይላችሁ፣ ስማችሁ፣ ዝናችሁ- ሁሉም እንደ ጥላ ይሰወራል፡፡

በመጨረሻ የሚቀረው በመጀመሪያ ያስገባችሁት ነው፡፡ ከዚህ ዓለም መውሰድ የምትችሉት የወሰዳችሁትን ያህል ብቻ ነው፡፡

ሕንድ ውስጥ ዓለምን በአንድ የባቡር ጣቢያ ውስጥ እንዳለ መጠበቂያ ክፍል የመመሰል ጥበብ አለ፤ ዓለም መኖሪያ ቤት አይደለችም፡፡ በመጠባበቢያ ቤት ውስጥ የሚገኘው ነገር በሙሉ የእናንተ አይደለም- የቤት እቃዎቹ፣ በግድግዳዎቹ ላይ የተሰቀሉት ስዕሎች .... ትጠቀሙባችኋላችሁ - ስዕሎቹን ትመለከቷቸዋላችሁ፤ በወንበሮቹ ላይ ትቀመጣላችሁ፣ አልጋ ላይ ታርፋላችሁ- ነገር ግን እንዱም እንኳን የእናንተ የግላችሁ አይደለም፡፡ እዚህ የምትቆዩት ለጥቂት ደቂቃዎች ወይም ቢበዛ ለጥቂት ሰዓታት ቡሆን ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ትሄዳላችሁ፡፡

አዎ፤ ወደ መጠባበቂያው ክፍል ያስገባችሁትን በሙሉ ይዛችሁ ትወጣላችሁ፤ የእናንተ ነውና፡፡ ታድያ ወደዚህ ዓለም ምንድነው ያመጣችሁት? ዓለም በእርግጥም የመጠባበቂያ ክፍል ናት፡፡ ቆይታችሁ በሰኮንዶችና በደቂቃዎች፣ በሰዓታት፣ በቀናት ብቻ ሳይሆን በዓመታትም ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ለሰባት ሰዓታት ጠበቃችሁ፣ ለሰባ ዓመታት ምን ልዩነት አለው?





ሰባ ዓመት ሲሞላችሁ በመጠባበቂያ ክፍያ ውስጥ እንዳላችሁ ትዘነጉት ይሆናል፡፡ ምናልባትም ቤቱ የእናንተ እንደሆነ፣ እናንተ የገነባችሁት እንደሆነ ማሰብ ትጀምሩ ይሆናል፡፡ በመጠባበቂያ ክፍሉ ውስጥ ስማችሁን ማስፈርም ትጀምሩ ይሆናል፡፡

ብዙውን ጊዜ ጉዞ ስለማደርግ በመታጠቢያ ቤቶች ስማቸውን የሚፅፉ ብዙ ሰዎች እንዳሉ ለማየት ችያለሁ፡፡ ሰዎች በመጠባበቂያ ክፍላቸው ውስጥ በሚገኙ ቁሳቁሶች ላይ ስማቸውን ያስፍራሉ፡፡ ነገሩ ዋጋ ቢስ ቢሆንም በዓለም የሚደረገው ይህ ነው፡፡

በጥንታዊ የጀይና ቅዱሳን መፃህፍት ውስጥ ሰፍሮ የሚገኝ አንድ በጣም ጠቃሚ ታሪክ አለ፡፡ ህንድ ውስጥ አንድ ሰው የመላው ዓለም ንጉስ መሆን ከቻለ ቻክራቫርቲን ተብሎ እንደሚጠራ ይታመናል፡፡ "ቻክራ" የሚለው ቃል "ጎማ" የሚል ትርጓሜ አለው፡፡ በጥንታዊት ህንድ ውስጥ አላስፈላጊ ውጊያንና ሁከትን ለማስወገድ የሚጠቅም መላ ነበር፤ ከፍተኛ ዋጋ ያለው፣ በውብና ጠንካራ ፈረሶች የሚጎተት አንድ ወርቃማ ሰረገላ ከአንድ ግዛት ወደ አንዱ ይጓዛል፡፡ ሌላኛው ግዛት ምንም ሳይቃወም ሰረገላውን የሚያሳልፈው ከሆነ ግዛቱ የሰረገላውን ባለቤት የበላይ እንደሆነ ተቀብሎታል ማለት ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ፍልሚያ የሚባል ነገር አያስፈልግም፡፡

በዚህ መንገድ ሰረገላው ይጓዛል፡፡ ሰረገላው በሀገሮቹ እንዲቆም ከተደረገ ጦርነት ይነሳል፡፡ ሰረገላው የትም ቦታ እንቅፋት ካላጋጠመው የንጉሱ የበላይነት ያለምንም ጦርነት ይረጋገጣል፡፡ ቻክራቫርቲን ይሆናል - ጎማዎቹ ማንም ሳይነካቸው የሚሽከረከሩ፡፡ ሁሉም ነገስታት ቻክራቫርቲን የመሆን ምኞት ነበራቸው፡፡

ታላቁ አሌክሳንደር ከነበረው ሃይል በላይ እንደሚያስፈልጋችሁ እርግጥ ነው፡፡ ሰረገላችሁን ለመላክ ብቻ ...... ከፍተኛ ሃይል ያስፈልጋችኋል፡፡ ሰረገላው እንቅፋት የሚገጥመው ከሆነ ግዙፍ ጦርነት እንደሚኖር ፍፁም የሆነ እርግጠኝነት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ማለት ሰውየው የታወቀ ስለሆነ ሌሎቹን ማሸነፍ ከቻለ እናንተንም ከማሸነፍ የሚያግደው ነገር አይኖርም፡፡

ይሁን እንጂ በጣም ዘመናዊና ተምሳሌተዊ መንገድ ነው፡፡ ጥቃት መፈፀም፣ ግድያ መጀመር አስፈላጊ አይደለም - አንድ ምሳሌያዊ ምልክት

ብቻ፡፡ እናም የንጉሱን ባንዲራ የለበሰው ሰረገላ ሲያልፍ ሊላኛው ንጉስ መቃወም አስፈላጊ ካልመሰለው ማለትም ጦርነቱ ሽንፈት፡ አላስፈላጊ ሁከትና መውደቅ ከመሰለው ሰረገላውን ተቀብሎ የክብሩማዋን እበቦች ይበትንበታል፡፡

እንደ ሶቭየት ህብረትና አሜሪካ ያሉ ሃገራት ከሚጠቀሙበት በጁ የበለጠ የሰለጠነ ይመስላል፡፡ አንድ ውብ ሰረገላ ትልካላችሁ - ነገር ግን ይህ ማለት በጥንካሬያችሁ እርግጠኛ መሆን ይኖርባችኋል፡ ለራሳችሁ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም፡፡ ይሄን ጊዜ ነው ምልክቱ የሚጠቅመው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ንጉስ አንድ ቀን ቻክራቫርቲን የመሆን ምኞት ነበረው ማለት ነው፡፡

ታሪክ ላይ እንደተገለፀው አንድ ሰው ቻክራቫርቲን ሆኗል - ይህ የሚሆነው ደግሞ በሺ ዓመታት አንዴ ነው፡፡ ታላቁ አሌክሳንደር እንኳን የአለም ገዢ ለመሆን አልቻለም፣ ብዙ ግዛቶች ይቀሩት ነበር፡፡ ሲሞትም ገና የሰላሳ ሰስት ዓመት ወጣት ነበር፡፡ አለምን መግዛት የሚችልበት ጊዜ አልነበረውም፡፡ በእርግጥ መላውን ዓለምም የሚታወቅ አልነበረም! ከፊሉ አለም አልታወቀም ነበር፡ የታወቀውም ቢሆን አልተገዛም ነበር፡፡ አሁን ታሪኩን የምነግራችሁ ሰው ቻክራቫርቲን ለመሆን በቅቶ ነበር፡፡

አንድ ቻክራቫርቲን በሺ ዓመታት አንዴ የሚገኝ በመሆኑ እንደ ብርቅ የሚታይ ነው፡፡ እናም አንድ ቻክራቫርቲን በሞተ ጊዜ ወደ ገነት ተወስዶ መልካም አቀባበል ከተደረገለት በኋላ አንድ ልዩ ቦታ ይሰጠዋል ይባላል፡፡

በጃይና አፈ - ታሪክ መሰረት ገነት ውስጥ የሂማሊያን ተራራ የሚያስተካክል ተራራ አለ፡፡ የሂማሊያ ተራራ ከድንጋይ፡ ከአፈር እና ከበረዶ የተገነባ ነው፡፡ በገነት የሚገኘው ሂማሊያ የሚስተካከል ተራራ ሱሚሩ ይባላል፡፡ ሱሚሩ ማለት ግዙፉ ተራራ የሚል ትርጉም አለው፤ ከእሱ የሚበልጥ ወይም የሚሻል ሊላ የለም፡፡ ሙሉ በሙሉ ወርቅ ነው፡ በድንጋይ ፋንታ በአልማዞች፣ በከበሩ ድንጋዮች እና ሊሎች ያጌጠ ነው፡፡

አንድ ቻክራቫርቲን ሲሞት ስሙን እንዲቀርፅ ወደ ሱሚሩ ተራራ ይወሰዳል፡፡ ይህ ለማንም የሚሰጥ እድል አይደለም፤ በሺ ዓመታት አንዴ የሚከሰት ነው፡፡ እርግጥ ነው ይህ ሰው ስሙን በሱሚሩ ላይ ለመፃፍ ተራራው የእርሱ በመሆኑ በጣም ተደስቶ ነበር - መዝገቡ የታላላቆች ስም





የሰፈረበት እና የሚሰፍርበት ነውና፡፡ ይህ ንጉስ ደግሞ ከታላላቆች ጐን ሊሰለፍ ነው፡፡

የበሩ ጠባቂ ስሙን የሚቀርፅባቸውን መሳሪያዎች ሰጠው፡፡ ንጉሱ እሱ ከመሞቱ በፊት ያለ እሱ አንኖርም ብለው ራሳቸውን ያጠፉትን ሰዎች ይዟቸው ሊሄድ ፈልጓል፡፡ ሚስቱ፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፡ የጦር አለቃው፡ እነዚህ ሁሉ አብረውት ሊሆኑ ስላሰቡ ራሳቸውን አጥፍተዋል፡፡

ንጉሱ የበር ጠባቂው ሰዎቹን እንዲያስገባቸውና ስሙን ሲቀርፁ እንዲመለከቱት ፈልጓል፡፡ ማንም ሳያየው ብቻውን ሄዶ ስሙን ቢፅፍ ምን ዋጋ አለው? መላው ዓለም ቢመለከተው ደስታው የላቀ ይሆን ነበር፡፡

"ሙያዬን የማውቅ ሰው ነኝና ምክሬን ቢያደምጡ የተሻለ ይሆናል" አለ የበር ጠባቂው፡፡ "አባቴ የበር ጠባቂ ነበር፡ የእሱም አባት የበር ጠባቂ ነበር፡፡ ለዘመናት የሱሚሩ ተራራ ዘቦች ሆነን ኖረናል፡፡ ምክሬን አድምጡ፡ ይዘዋቸው ከሄዱ በኋላ ይፀፀታሉ፡፡"

ንጉሱ ባይገባውም ምክሩንም ችላ ሊለው አልቻለም ምክንያቱም ሰውየው እሱን ከልክሎ ምን ሊጠቀም ይችላል?

"ፅሁፍዎን እንዲያዩልዎ ከፈለጉ በመጀመሪያ ስምዎን ሄደው ይቅረፁ፤ ከዚያ በኋላ ከፈለጉ ሊወስዷቸው ይችላሉ፡፡ እርግጥ አሁን ቢወስዷቸውም ቅሬታ የለኝም፤ ነገር ግን ይህን መወሰን ካልቻሉ ወይም ሃሳብዎን ሊለውጡ የማችሉበት ምንም መንገድ ከሌለ ..... አብረዎት ይሆናሉ፡፡ ብቻዎትን ቢሄዱ ግን የተሻለ ነው፡፡"

ሃሳቡ በጣም ጥሩ ነው፡፡ "ጥሩ ነው፡፡ ብቻዬን ሄጄ ስሜን እቀርፅና ተመልሼ መጥቼ ሁሉንም እጠራችዋለሁ" አለ ንጉሱ፡፡

"እኔም በዚህ እስማማለሁ" አለ የበር ጠባቂው፡፡

ንጉሱ ወደ ተራራው ሲወጣ ሱሚሩን ከሺ ፀሃያት ስር ሲያብረቀርቅ ተመለከተው - ገነት ውስጥ አንድ ብቻ ፀሃይ አይደለም ያለችው - በሺ ከሚቆጠሩት ፀሃያት ባሻገር ከሂማሊያ የማበልጥ አንድ ግዙፍ ወረቃማ ተራራ አለ፡፡ ሂማሊያ ሁለት ሺ ማይል ያህል ርዝመት አለው! ተራራው እጅግ ስለሚያንፀባርቅ አይኖቹን መክፈት አቃተው ከዚያም ትክክለኛውን

ስፍራ ይፈልግ ገባ፡፡ በጣም ጨነቀው፡፡ ምንም ቦታ የለም፡ ተራራው በሙሉ በስሞች ተሸፍኗል፡፡

ዓይኖቹን ማመን አቃተው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ማን እንደሆነ ታወቀው፡፡ እስካሁን ድረስ በሺ ዓመታት እንዴ ከሚፈጠሩት ሃያል ሰዎች መሃል አንዱ እንደሆነ ያስብ ነበር፡፡ ጊዜ ዘላለማዊ ነው፡ አንድ ሺ ዓመታት ምንም ለውጥ አያመጡም፡፡ ብዙ ቻክራቫርቲኖች ተፈጥረዋል፡፡ በዚያ ግዙፍ ተራራ ላይ ትንሽዬ ስሙን የሚፅፍበት ስፍራ እስኪያጣ ድረስ፡፡

ተመልሶ መጣ፡፡ የበር ጠባቂው ሚስቱን፡ የጦር አለቃውን፡ ጠቅላላ ሚኒስትሩን እና የልብ ጓደኞቹን ይሆ እንዳይሄድ የመከረው ትክክል እንደነበር ገባው፡፡ ሁኔታውን አለማየታቸው ጥሩ ነው፡፡ አሁንም ድረስ ንጉሳቸው ተራ ሰው እንዳልሆነ ያስባሉና፡፡

የበር ጠባቂውን ጠጋ አደረገውና "ምንም ቦታ የለም!" አለው፡፡

"እፀኑም ለዚህ ነው የነገርኩዎት" አለ የበር ጠባቂው፡፡ "የተወሰኑትን ስሞች ሰርዘው የእርስዎን ስም ማስፈር ይችላሉ፡፡ እስከዛሬ ድረስ እንዲህ ሲደረግ ነው የቆየው፡፡ ህይወቴን ሙሉ እንግዲህ ሲደረግ አይቻለሁ፡፡ አባቴም ይህ እንደሚደረግ ነግሮኝ ነበር፡፡ አያቶም ሆነ ሌሎች የቤተሰቤ አባላት ሱሚሩ ባዶ ሆኖ ወይም መፃፊያ ቦታ ኖሮት አይተው አያውቁም………"

"አንድ ቻክራቫርቲን ሲመጣ ጥቂት ስሞችን ይሰርዝና የራሱን ስም ያስፍራል፡፡ ስለዚህ የቻክራቫርቲኖች ስም በሙሉ እዚህ አለ ማለት አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ ተሰርዞ፡ ብዙ ጊዜ ተፅፎበታል፡፡ እርስዎ ስራዎን ይስሩ፡፡ ከዚያ ከፈለጉ ወዳጆችዎን ማስገባት ይችላሉ፡፡"

"በፍፁም፡ ላላያቸው አልፈልግም" አለ ንጉሱ፡፡ "ስሜንም መፃፍ አልፈልግም፡፡ ምንስ ጥቅም አለው? - አንድ ቀን አንዱ ይመጣና ይሰርዘዋል …."

"መላ ሕይወቴ ትርጉም የለሽ ሆኗል፡፡ ይህ በግንት የሚገኘው የመርቅ ተራራ ነበር - ብቸኛ ተስፋዬ፡፡ ስሜን እዚህ ላይ ለማስፈር ምኞት ነበረኝ፡፡ ለዚህ ነበር የኖርኩት፡ ህይወቴን የገነባሁት ለዚህ ነበር፡ ይህን ክብር ለማግኘት መላውን አለም ለመጨረስ዗ዝግጁ ነበርኩ፡፡ አሁን





እንደነገርኩኝ ከሆነ ማንም ሰው ስሜን ሰርዞ የእሱን ስም ሊፅፍ ይችላል፡፡ መፃፉ ምን ትርፍ አለው? ስሜን አልፅፍም፡፡"

የበሩ ጠባቂ ሳቀ፡፡

"ምን ያስቅሃል?" አለ ንጉሱ፡፡

"ይህንንም ከአያቶቼ መስማቴ ይገርማል - ቻክራቫርቲኖች መጥተው ይህን ታሪክ ከሰሙ በኋላ ስማቸውን ሳይፅፉ ይመለሳሉ ብለው ነግረውኝ ነበር፡፡ እርስዎ አዲስ አይደሉም፡፡ ትንሽ ብልሀት ያለው እንዲህ ነው የሚያደርገው" ሲል መለሰ፡ የበር ጠባቂው፡፡

እናስ ከዚህ ዓለም ምን ታገኛላችሁ? ከእናንተ ጋር ምን ይዛችሁ ትሄዳላችሁ? ስማችሁን፡ ክብራችሁን፡ ሞገሳችሁን? ገንዘባችሁን፡ ሃይላችሁን- ምኞታችሁን? የትምህርት ልድላችሁን? ምንም የምትወስዱት ነገር የለም፡፡ ሁሉም ነገር እዚህ ቀሪ ነው፡፡ ያን ጊዜ ይህ ሁሉ ነገር የራሳችሁ እንዳልሆነ፡ የባለቤትነት ሃሳባችሁ የተሳሳተ እንደሆነ ትገነዘባላችሁ፡፡ በዚያ የባለቤት ስሜትም አስተሳሰባችሁ ተዛብቷል፡፡

ይህን ንብረት ከፍ ለማድረግ - ብዙ ገንዘብ እንዲኖራችሁ፡ ሃይለኛ እንድትሆኑ፡ ብዙ መሬቶችን ለመውረር - ራሳችሁ ትክክል እንዳልሆናችሁ የሚመስክሩላችሁን ተግባራት ፈፅማችኋል፡፡ ስትዋሹ፡ እምነት ስታፈርሱ ነበር፡፡ መቶ ጊዜ ስትለዋወጡ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ እንኳን ለራሳችሁም ሆነ ለሌላው እውነተኛ አልነበራችሁም፡ ልትሆኑም አልቻላችሁም፡፡ ሃሰተኛ፡ ውሸታም፡ አስመሳይ መሆን ነበረባችሁ፡ ምክንያቱም በዓለም ስኬታማ የምትሆኑት በዚህ መንገድ ነው፡፡ እውነተኛነት አይጠቅማችሁም፡ ታማኝነት አይረዳችሁም፡ ሃቀኝነት አይረባችሁም፡፡

ያለ ንብረት፡ ስኬት እና ዝና እናንተ ማን ናችሁ? አታውቁትም፡፡ እናንተ ስማችሁን፡ ዝናችሁን፡ ክብራችሁን፡ ሃይላችሁን ናችሁ፡፡ ከዚህ በላይ ማን ልትሆኑ ትችላላችሁ? እናም ይህ ሁሉ ንብረት የእናንተ መለያ ይሆናል፡፡ ሃሰተኛ የባለቤትነት ስሜት ይሰጣችኋል፡፡ የራስ ክብራችሁን ይጨምረዋል፡፡

የራስ ክብት (ለራሳችሁ የምትሰጡት ከፍተኛ እመለካከትን) ሚስጥር የሆነ ነገር አይደለም፡ በጣም ቀላል ክስተት ነው፡፡ ማን እንደሆናችሁ

አተውቱም፡፡ ማንነትን ሳያውቁ ደግሞ መኖር አይቻልም፡፡ እኔ ማን እንደሆንኩ ካላወቅኩ እዚህ ምን እሰራለሁ? ስለዚህ የማደርገው ነገር በሙሉ ትርጉም አልባ ይሆናል ማለት ነው፡፡ የመጀመሪያው ተዳጋው ነገር ማንነትን ማወቅ ነው፡፡ ይሄን ካወቅኩ ምናልባት ተፈጥሮዬን ምሉዕ የማያደርግ፡ የሚያስደስተኝ፡ ወደ ቤት (ወደ ግዛ ተፈጥሮዬ) የሚመልሰኝ ነገር ማድረግ እችላለሁ፡፡

ማን እንደሆንኩ ካላወቅኩ ግን ተፈጥሮዬጋ መድረስ፡ መምራት የምፈልግበት ስፍራ እንዴት ልደርስ እችላለሁ? ወዲያ ወዲህ ልሮጥ እችላለሁ፤ ግን "አሁን ደርሻለሁ፡ ስፈልገው የነበረው ቦታ ይሄ ነው" ማለት የምችልበት ደረጃ ላይ አልደርስም፡፡

ማንነታችሁን ስላላወቃችሁ በምትኩ ሃሰተኛ መታወቂያ አስፈልጓችኋል፡፡ ንብረቶቻችሁ ያን ሃሰተኛ ማንነት ያጐናፅፏችኋል፡፡

ወደዚህ ዓለም ስትመጡ የዋህ ተመልካች ነበራችሁ፡፡ ሁሉም ሰው ይህን የንቃት ባህርይ ይዞ ነው የሚመጣው፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ከዓለም ጋር ትዋዋላላችሁ፡፡ አለም ብዙ የምትሰጣችሁ ነገር አላት፤ እናንተ ግን አንድ ነገር ብቻ ነው ያላችሁ - ቅንነታችሁ፡ ለራሳችሁ ያላችሁ ክብር፡፡ ከአንድ ነገር ነው ልትለቱ ትችላላችሁ፡ የዋህነት፡ ብልህነት፡ እውነተኝነት አንድ ነገር ብቻ ነው ያላችሁ፡፡

አንድ ህፃን ደግሞ በዙሪያው ያለውን ነገር በሙሉ ማወቅ ይፈልጋል፡፡ ይህንንም፡ ያንንም ማግኘት ይፈልጋል፤ ይህ የሰው ተፈጥሮ ነው፡፡ አንድ ገና የተወለደ ህፃን እንኳን አንድ ነገር ለመያዝ ሲሞክር ማየት ይቻላል፤ እጆቹ አንድ ነገር መጨበጥ ይፈልጋሉ፡፡ ጉዞውን ጀምሯል ማለት ነው፡፡

በጉዞው ውስጥ ያለምንም ክፍያ ከዚህ አለም ምንም ነገር አያገኝምና ራሱን ያጣል፤ ራሱን ይከፍላል፡፡ ህፃኑ የሸጠው ነገር ዋጋ ያለው መሆኑን፡ መላው ዓለም በአንድ ጐን፡ ቅንነቱ ደግሞ በሌላ ጐን ቢመዘኑ የእሱ ቅንነት ሚዛን እንደሚደፋና ዋጋ እንዳለው አያውቅም፡፡ ምስኪኑ ህፃን ይህን የሚያውቅበት ምንም መንገድ የለም፡፡ ችግሩ ይህ ነው፡ ምክንያቱም ያገኘውን ነገር ያገኘው በቀላሉ ነው፡ እንደ ስጦታ ነው የተቀበለው፡፡

ይህን ግልፅ የሚያደርግ አንድ ታሪክ ልንገራችሁ፡-





አንድ በጣም ሃብታም የሆነ ሰው የስኬቶች ሁሉ መጨረሻ ከሆነው የተስፋ መቁረጥ አፋፍ ላይ ይደርሳል፡፡ እንደ ስኬት ቶሎ የሚወድቅ ነገር የለም፡፡ እንዲ ከተሳካላችሁ ዓለም፡ ህዝቡ፡ ማህበረሰቡ ኢታልሉአችኋል ማለት ነው፡፡ ሰውየው ሃብት ቢኖረውም የአዕምሮ ሰላም አልነበረውም፡፡ ስለዚህም ይህን የአእምሮ ሰላም ፍለጋ ጀመረ፡፡

አሜሪካ ውስጥ እየተከሰተ ያለው ይህ ነው፡፡ ከሌላው ዓለም በበለጠ አሜሪካውያን የአእምሮ ሰላምን ፍለጋ ላይ ናቸው፡፡ ህንድ ውስጥ የአእምሮ ሰላሙን የሚፈልግ ሰው አላጋጠመኝም፡፡ በትድግያ የሆድ ሰላም መገኘት አለበትና - የአእምሮ ሰላም ሩቅ ነው፡፡ ሆድና አእምሮ በብዙ ማይሎች የተራራቁ ናቸው፡፡

አሜሪካ ውስጥ ሁሉም ሰው የአእምሮ ሰላም ፍለጋ ላይ ነው፡፡ በእርግጥ ሰላማችሁን የምትፈልጉ ከሆነ ህዝቡም ሊሰጣችሁ ዝግጁ ነው፡፡ ይህ ቀላል የኢኮኖሚክስ ህግ ነው፤ ፍጆታ ሲኖር አቅርቦት ይኖራል፡፡ የምትፈልጉት ነገር በእርግጥ ትፈልጉታላችሁ? የሚለው ጥያቄ ለውጥ አያመጣም፡፡ ሰውም ለሚሰጣችሁ ነገር አይጨነቅም - ሃሰተኛ ማስታወቂያ ይሁን ፕሮፖጋንዳ ወይም አንድ ጠቃሚ ነገር ግድ የለውም፡፡

ይህ ፍጆታ ሲኖር አቅርቦት ይኖራል የሚል ቀላል መርህ የሚያውቁ ብልህ ሰዎች አንድ እርምጃ ወደፊት ተራምደዋል፡፡ "ፍጆታ እስኪመጣ ድረስ መጠበቅ አያስፈልግም፤ ፍጆታን መፍጠር ይቻላል" ይላሉ፡፡ ይህ ነው የማስታወቂያ ጥበብ፡ ፍጆታን መፍጠር፡፡

ማስታወቂያውን ከማንበባችሁ በፊት ዕቃው እንደሚያስፈልጋችሁ፡ ከፍጆታዎቻችሁ እንዱ መሆን እንዳለበት አይሰማችሁም ነበር፡፡ ማስታወቂያውን ከተመለከታችሁ በኋላ ግን በድንገት "ወይ አምላኬ፡ እስከዛሬ ተጉድቼ ነበር ለካ! ይህ እቃ መኖሩን የማላውቅ ቂል ነበርኩ" ትላላችሁ፡፡

አንድ ሰው አንድ ነገር ከማምረቱ ሶስት፡ አራት ዓመታት በፊት እንኳን ሳይተር ማስተዋወቅ ይጀምራል፡፡ ዕቃው ቀድሞ ወደ ገበያ የማይወጣው ፍላጎቱ መጀመሪያ በሰው አእምሮ ውስጥ እንዲቀረፅ ነው፡፡ የፍጆታው ፍላጎት እንዴ በሰው አእምሮ ውስጥ ካደረ ያን ጊዜ አቅርቦቱ ዝግጁ ይሆናል፡፡

ስለዚህ በመጀመሪያ የፍጆታ ፍላጎትን መፍጠር አለባችሁ፡፡ ከተሳካላችሁ በኋላ ግን የአእምሮ ሰላም ለማግኘት ፍላጎት አይጠበቅባችሁም፡፡ ሲሳካላችሁ የአእምሮ ሰላማችሁን በሙሉ ጠራርጉ ይወስድባችኋል፡፡ በህይወታችሁ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ፣ ሰላማችሁን፣ ፀጥታችሁን፣ ደስታችሁን፣ ፍቅራችሁን ይቀማችኋል፡፡ ጠቃሚ የሆነውን ነገር በሙሉ በመንጠቁ ይገፋበታል፡፡ በመጨረሻም እጃችሁ ባዶ ይሆናል፤ ጠቃሚ የሆነውን ነገር በሙሉ ታጣላችሁ፡፡ ያን ጊዜ በድንገት የአእምሮ ሰላም እንደሚያስፈልጋችሁ ታምናላችሁ፡፡

ይህን ጊዜ ስለ አእምሮ፣ ስለ ሰላም ምንም የማያውቁ አትራቢዎች ብቅ ይላሉ፡፡ ጆሹዋ ሊብማን የተባለ የአይሁድ መምህር የጻፈውን "የአእምሮ ሰላም" የተባ መፅሃፍ አንድ ወትት አንብቤ ነበር፡፡ መፅሃፉን ጨርሼ አንብቤዋለሁ፤ ነገር ግን ሰውየው ስለ ሰላምም ሆነ ስለ አእምሮ ምንም የሚያውቀው ነገር ያለ አልመሰለኝም፡፡ ትኩረቱ ንግዱ ላይ ነው፡፡ ግን ስለ አእምሮ ሰላም ምንም ሳያውቅ አንድ ጥሩ ስራ ሰርቷል፡፡

የአእምሮ ሰላሙን የፈለገ ሰው ውስዮ አድር የጆሹዋ ሊብማንን መፅሃፍ መፈለጉ አልቀረምና በአለም ላይ በሽያጭ ቀዳሚ ከሆኑት በሃፍት መሃል አንዷ ለመሆን በቃ፡፡ ሲፅፍም አሳምሮ ነው፤ መሳጭና ውብ ፅሁፍ መፃፍ ይችልበታል፤ ፅሁፎቹ ቀፅፅና የማሳደር ሃይል አላቸው፡፡ መፅሃፉን ካነበባችሁ በኋላ ግን የአእምሮ ሰላማችሁ እንደራቃችሁ ይቆያል፤ ወይም የባሰ ይርቃችሃል፡፡

ሰላምና አእምሮ ምን እንደሆኑ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው የአእምሮ ሰላም የሚል መፅሃፍ አይፅፍም፣ ምክንያቱም አእምሮ የሰላም መረበሽ፣ የእረፍት ማጣት ምንጭ ነውና፡፡ ሰላም የሚኖረው ያለ አእምሮ ነው፡፡ ስለዚህ የአእምሮ ሰላም የሚባል ነገር የለም፡፡ አእምሮ ካለ ሰላም አይኖርም፤ ሰላም ካለ አዕምሮ አይኖርም፡፡ ነገር ግን "ያለ አዕምሮ ሰላም" የሚል መፅሃፍ ብትፅፉ የሚገዛችሁ አይኖርም፡፡ እኔ ራሴ ይህን ሳስብ ነበር ..... ግን እንዲህ በሚል ርዕስ ያወጣሁትን መፅሃፍ የሚገዛኝ አይኖርም የሚል ሃሳብ መጣብኝ፡፡ እውነቱ ይህ ቢሆንም ለአንባቢዎቹ ስሜት አይሰጣቸውም፡፡





ህፃኑ በራሱ ላይ ምን እንዲመጣ አያውቅም፡፡ ይህም ሃብቱም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነበር፡፡ በዓለም ላይ የማገኘው ሃብት በሙሉ ቢኖረውም የአዕምሮ ሰላሙን ፍለጋ ላይ ነው፡፡ ከአንዱ አዋቂ ወደ ሌላኛው እየሄደ ታላላቅ የሚባሉ ምክሮችን ቢቀበልም ምክሮቹ መፍትሄ ሊያመጡለት አልቻሉም፡፡

በእርግጥ ምክር የሚሰጡም፣ የሚቀበሉም ቂሎች ናቸው፡፡ ብልሆች በዓለም ላይ ለሰው ልጅ በነፃ የተሰጠው እና ለማንም ተለይቶ ያልተሰጠው ምክር እንደሆነ ስለሚያውቁ ምክር ሊሰጡዋችሁ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ደግሞም ምን አስጨነቃቸው?

ብልህ ሰው ምክሩን ከመስጠቱ በፊት ያዘጋጃችኋል፡፡ ሳትዘጋጁ ምክሩን አይለግሳችሁም፡፡ እናንተን ለማዘጋጀት፣ መሬቱን ለማለሰለስ ዓመታት ሊፈጅ ይችላል፡፡ ከዚህ በኋላ ዘሩ ይዘራል፡፡ ዘሮቹን በድንጋዮች እና በቋጥኞች ላይ ዘርቶ ዘሩን የሚያባክን ቂል ነው፡፡

እነዚህ ሁሉ አዋቂዎች ምክር ቢለግሱትም አንዱ እንኳን አልጠቀመውም፡፡ በመጨረሻ በመንደሩ ነዋሪዎች እንደ ደደብ የሚቆጠር አንድ ሰው በመንገድ አቁሞ "ጊዜህን እያባከንክ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ አዋቂዎች አይደሉም፤ በደንብ አውቃቸዋለሁ፡፡ እኔን ደደብ ነህ ስለሚሉኝ አያምኑኝም፡፡ አንተም ላታምነኝ ትችላለህ፤ ነገር ግን አንድ አዋቂ አውቃለሁ :.........."

"የአእምሮ ሰላም ፍለጋ ከቆኝ እየጣርክ እንደሆነ በማየቴ ወደ ትክክለኛው ሰው ብመራህ መልካም መሆኑን አስቤያለሁ፡፡ እኔ ደደብ ስለሆንኩ ማንም ምክር ጠይቆኝ፣ እኔም ምክር ሰጥቼ አላውቅም፡፡ የእንተን ሃዘንና ስቃይ ማየት ግን ከብዶኛል፡፡ ለባም ነው ያናገርኩህ፡፡ ከጐረቤት መንደር ወደሚገኘው ሰው ብትሄድ የተሻለ ነው" አለው፡፡

ሐብታሙ ሰው ምንም ሳያመነታ በውድ አልማዞች የተሞላ ትልቅ ከረጢቱን በአንድ ውብ ፈረስ ላይ አስጭኖ ወደ ሰውየው ገሰገሰ፡፡ ይህን አዋቂ ሱፊዎች ሙላ ናስሩዲን ብለው ይጠሩታል፡፡

"የአዕምሮ ሰላሜን እንዳገኝ ልትረዳኝ ትችላለህ?" በማለት ሙላውን ጠየቀው፡፡

"እርዳታ? እረ እሰጥሃለሁ፡፡"

"በጣም እንግዳ ነገር ነው" ሲል አሰበ፡ ሃብታሙ ሰው፡፡ "በመጀመሪያ የደደቡን መክር ሰማሁ፡፡ ተስፋ ቆርጬ ስለነበር ምክሩን ሰምቼ እዚህ መጣሁ፡፡ እዚህ ደግሞ የባሰ ደደብ ገጠመኝ፡፡ <እሰጥሃለሁ> ይለኛል እንዴ?"

"ልትሰጠኝ ትችላለህ?" አለ ሃብታሙ፡፡ "ሁሉም አዋቂዎች ዘንድ ሄጃለሁ፡፡ እነሱም ይህ አድርግ፣ ያን አድርግ፣ ራስህን በስነ-ምግባር አንፅ፣ እርዳታ ስጥ፣ ድሆችን እርዳ፣ ሆስፒታሎች ክፈት፣ በዚህ ሂድ፣ በዚያ ሂድ እያሉ ምክር ሰጥተውኛል፡፡ እነዚህን ሁሉ አድርጌያለሁ፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም እንኳን የፈየዱልኝ ነገር የለም፡፡ እንደውም ችግሬን አባሰብኝ እንጂ፡፡ አንተ ደግሞ <እሰጥሃለሁ> ትለኛለህ?"

"በጣም ቀላል ነው፡፡ አሁን ከፈረሱ ውረድ" አለው ሙላው፡፡ ከረጢቱን እንደያዘ ከፈረሱ ወረደ፡፡ ከዚያም ሙላት፡ "ወደ ደረትህ አስጠግተህ የያዝከው ምንድነው?" ሲል ጠየቀው፡፡

"እነዚህ ውድ አልማዞች ናቸው፡፡ ሰላምን ከሰጠኸኝ ይህን ከረጢት እሰጥሀለሁ" አለው፡፡ ይህን ብሎ እንደጨረሰ በድንገት ምን እንደተከሰተ ሳይታወቀው ሙላው ከረጢቱን ቀምቶት ሮጠ!

ሃብታሙ ሰው በድንጋጤ ደርቆ ቀረ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት እንኳን ግራ ገባው፡፡ ከዚያም ተከትሎት ሮጠ፡፡ ነገር ግን ሙላ መንደሩን ልቅም አድርጎ ስለሚያውቀው መንገድ እያሳበረ በሃይል ሮጠበት፡፡ ሃብታሙ ሰው በህይወቱ ሮጦ ካለማወቁም በተጨማሪ ሰውነቱ ወፍራም ነው ...... መጮህ፣ መንጫነጭ፣ መንፋረቅ ጀመረ፡፡ እንባው ይረግፍ ጀመር፡፡ "አታለለኝ! ህይወቴን በሙሉ ለፍቼ ያጠራቀምኩት ጥሪት በሙሉ ተወሰደ!" ብሎ ጮኸ፡፡

ሰዎች እየተከተሉ ሳቁበት፡፡ "ሁላችሁም ደደቦች ናችሁ እንዴ? ከተማው በሙሉ ደደብ ነው እንዴ? እኔ ተዘርፌ ራቁቴን ቀርቻለሁ፣ እናንተ ሌባውን በመያዝ ፋንታ ትስቁብኛላችሁ" አላቸው፡፡

"ሌባ አይደለም፡፡ በጣም አዋቂ ሰው ነው" አሉት፡፡

"ከእኔ መንደር ያለው ደደብ ነው እዚህ ችግር ውስጥ የከተተኝ! አለ ሃብታሙ ሰው፡፡ እያባበሉም ቢሆን ሙላን መከተሉን አልተወም፡፡ ሙላ





ሮጦ ፈረሱ ከቆመበት ስፍራ ተመልሶ መጣ፡፡ ከረጢቱን ያዞ ከዛፉ ስር እንደተቀመጠ ሃብታሙ ሰው እየጮኸና እያለቀሰ ደረሰ፡፡ "እንካ ከረጢትህን" አለው ሙላ፡፡ ሃብታሙ ሰው ከረጢቱን ተቀብሎ ወደ ደረቱ አስጠጋው፡፡ "ምን ተሰማህ? ትንሽ የእዕምሮ ሰላም አገኘህ?" አለው ሙላ፡፡

"አዎ አሁን ሰላም ይሰማኛል፡፡ በጣም የምትገርም ሰው ነህ፡፡ ዘዴዎችህም የሚገርሙ ናቸው" ሲል መለሰ ሃብታሙ ሰው፡፡

"ምንም አዲስ ዘዴዎች አይደሉም - ቀላል ስሌቶች ናቸው፡፡ ያለህን በሙሉ በስጦታ ያገኘኸው ነው፡፡ ይህን እንድታጣው አጋጣሚው ሊፈጠርልህ ይገባል፤ ይሄን ጊዜ ያጣኸው ነገር ወዲያውኑ ይገባሃል፡፡ ምንም አዲስ ነገር አላገኘህም፡፡ የእዕምሮ ሰላም ሳይኖርህ የያዝከውን ከረጢት ነው አሁንም የያዝከው፡፡ አሁን ከረጢትህን ወደ ልብህ አስጠግተህ ይዘሃል፡፡ ሰዎች ሁሉ ምን አይነት ሰላማዊ፣ ፍሁም አዋቂ ሰው እንደሆንክ ይገነዘባሉ! አሁን ወደቤትህ ሂድ፡፡ ሰውም አታስቸግር" አለ ሙላ፡፡

የህፃኑም ችግር ይሄ ነው፡፡ በየዋህነት ስለመጣ የዋህነቱን ሊቀበልም ሆነ ሊሰጥ ዝግጁ ነው፡፡ ቆሻሻውን ነገር ሁሉ ሊቀበል፣ ድፍረቱን ደግሞ ሊሰጥ ዝግጁ ነው፡፡ አሻንጉሊቶችን ሊቀበል (ለነገሩ በዚህ ዓለም ከአሻንጉሊት በቀር ምን አለ?) ግልፅነቱን ሊሰጥ ዝግጁ ነው፡፡ አሻንጉሊቶቹ ሲተሙ ግን ያጣው ነገር ምን እንደሆነ ይገነዘባል፡፡ ራሱ ነው ያጣቸው፡፡

በተሻለ ዓለም የሚኖሩ ቤተሰቦች ከልጆቻቸው ይማራሉ፡፡ እናንተ ግን ልታስተምርዋቸው ችኩላችኋል፡፡ ማንም ከእነሱ ሊማር የፈለገ አይመስልም፡፡ እነሱ ብዙ ሊያስተምሩዋችሁ የሚችሏቸው ነገሮች አሏቸው እናንተ ግን ምንም ልታስተምሯቸው የምትችሉ ነገር የላችሁም፡፡

በእድሜ ትልቅ ስለሆናችሁና ሃይል ስላላችሁ ብቻ ምን እንደሆናችሁ፣ የት እንደደረሳችሁ፣ በዓለም ያላችሁ ቦታ የት እንደሆነ ሳታውቁ እናንተን እንዲመስሉ ታስተምሯቸዋላችሁ፡፡ እናንተ ደሃ ናችሁ፣ ታዲያ ልጆችሁም እንደ እናንተ ደሃ እንዲሆን ትፈልጋላችሁ?

ግን ማንም ሰው እንዲህ አያስብም፡፡ ይህ ቢሆንማ ሰዎች ከህፃናት ልጆቻቸው በተማሩ ነበር፡፡ ህፃናት አዲስ መጤዎች በመሆናቸው ከሌላኛው

ዓለም ያመጡት ብዙ ነገር ይናገሩችኋል፡፡ የማህፀን ዐዋቂ፣ የጥንቱ ፍጥረት ርጋታ አብሯቸው አለ፡፡

ስለዚህ በማይታወቀው ማመን እንዳለባችሁ ሁሌጊዜ አስታውሱ፡፡ የሚታወቀው አእምሮ ነው፡፡ የማይታወቀው አዕምሮ ሊሆን አይችልም፣ ሌላ ነገር ሊሆን ቢችልም አእምሮ ሊሆን ግን አይችልም፡፡ አንድ በእርግጠኝነት የሚታወቀው ነገር አእምሮ የሚታወቁ ነገሮች ክምችት መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ መንታ መንገድ ላይ ደርሳችሁ አእምሮአችሁ "በዚህኛው ሂዱ፣ ይህን መንገድ አውቀዋለሁ" ቢላችሁ እሱ አዕምሮአችሁ ነው፡፡ ራሳችሁን ብታዳምጡ ግን በማይታወቀው መንገድ ትሄዱ ነበር፡፡ ማንነት ሁልጊዜም ጀብደኛ ነው፡፡ አእምሮ በጣም ወግ አጥባቂ፣ በጣም ግትር ነው፡፡ ብዙ እንቅፋት በሌለበት መንገድ ደጋግሞ መጓዝ ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ ሁሌጊዜ የማይታወቀውን አድምጡ፡፡ ወደማይታወቀው ለመሄድም ድፍረታችሁን አሰባስቡ፡፡

ወደ ዕጣ ፈንታችሁ ለመግባት ድፍረት፣ ፍርሃት አልባ መሆን ያስፈልጋል፡፡ በፍርሃት የተሞሉ ሰዎች ከታወቀው መሻገር አይቻላቸውም፡፡ የታወቀው ምቾት፣ እርግጠኝነት፣ ጠንቃቃነትን ይሰጣል - ምክንያቱም የታወቀ ነውና፡፡ ፍፁም የሆነ ንቃት ያለው ሰው ይህን እንዴት መቋቋም እንዳለበት ያውቃል፡፡ - መንቃት አያስፈልግም፣ በዚህ መልኩ ነው ከሚታወቀው ጋር መስማማት የሚቻለው፡፡

የታወቀውን ድንበር ባለፋችሁ ቅፅበት ምንም ስለማታውቁ ፍርሃት ይነሳል፡፡ ምን ማድረግ እና ምን አለማድረግ እንዳለባችሁ አታውቁም፡፡ አሁን ስለ ራሳችሁ እርግጠኛ መሆናችሁን ታቆማላችሁ፡፡ ሰዎችን ከሚታወቀው ጋር እንዲጣበቁ የሚያደርጋቸው ፍርሃት ነው፡፡ ሰው እንደ ከሚታወቀው ጋር ከተጣበቀ ሙት ነው፡፡

ህይወትን ከአደጋ ጋር መኖር ብቻ ነው የሚቻለው - ህይወትን የመኖሪያ ሌላ መንገድ የለም፡፡ ህይወት የምትበለፅገው፣ የምትጐለምሰው በአደጋ ነው፡፡ አንድ ሰው የሚታወቀውን ለማይታወቀው በመሰዋት ጀብደኛ መሆን አለበት፡፡ አንዴ የነፃነትን እና የፍርሃት አልባነትን ደስታ ያጣጣመ ሰው አይፀፀትም፣ ምክንያቱም ምቹ ኑሮ መኖር እንዴት እንደሆነ ያውቃልና፡፡ የህይወትን ችቦ ሁለት ጫፎች መለኮስ እንዴት እንደሆነ ያውቃል፡፡ ከጠቅላላው የማይረባ ህይወት ይልቅ ይህን የተጐናፀፈች አንዲት ጠንካራ ቅፅበት ትበልጣለች፡፡





# እንግዳው በራችሁን ሲያንኳኳ ክፈቱለት!

# 2

## ያልታወቀ እንግዳ

**እንግዳው ያልታወቀ ነው፡፡ ጓደኛችሁ፣ ጠላታችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ማን ያውቃል? ይህን ማወቅ አይቻልም! ፍርሃትን አስወግዶ እንዲገባ በመፍቀድ ብቻ ነው ማወቅ የሚቻለው፡፡**

@shuktus_books

# የራስን ኩራት ሞት፣ የማንነት ውልደት ነው!

እንግዳው ከእናንተ የሚወጣ ሳይሆን ከውጭ የሚመጣ ነው፡፡ የእናንተ አካል አይደለም፡፡ ያለፈ ህይወታችሁ የቆመ ነው፡፡ አዲስ ደግሞ በፍርሃታችሁ ሳቢያ ከእናንተ ጋር አልተገናኘም፡፡ የኖራችሁት በአንድ መንገድ ነው፤ ከእምነታችሁ ውጪ ምቹ ህይወት ፈጥራችኋል፡፡ ያን ጊዜ አንድ እንግዳ ነገር በራችሁን ያንኳኳል፡፡ አሁን ያለፈ ህይወታችሁ አካሄድ ይታወካል፡፡ አዲሱ እንግዳ እንዲገባ ከፈቀዳችሁለት ፍፁም እንደበፊቱ አትሆኑም፤ አዲሱ ይቀይራችኋል፡፡

በርግጥ ሁኔታው አደጋ አለው - ከአዲሱ ጋር የት እንደምትሄዱ አታውቁምና፡፡ አሮጌው የታወ ነው - ለረዥም ጊዜ አብራችሁት ኖራችኋል፤ ተላምዳችሁታል፡፡ አዲሱ ግን አይታወቅም፡፡ ጓደኛችሁ፣ ጠላታችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ማን ያውቃል? ይህን ማወቅ አይቻልም፤ ፍርሃትን አስወግዶ እንዲገባ በመፍቀድ ብቻ ነው ማወቅ የሚቻለው፡፡

አሮጌው የፈለጋችሁትን ሁሉ እስከሁን አልሰጣችሁምና አዲሱን አልቀበልም ማለትም አትችሉም፡፡ አሮጌው ቃል የገባላችሁ ቢሆንም ቃሉን አልጠበቀም፡፡ አሮጌው የሚታወቅ ቢሆንም አስቸጋሪ ነው፡፡ አዲሱ ግን የማይመች ቢሆን እንኳ አስደሳች ነገር ሊያመጣላችሁ የሚችልበት አጋጣሚ አለ፡፡ ስለዚህ ልትቀበሉትም፣ ልታገሉትም አትችሉም፡፡ ይህን ማድረግ ባለመቻላችሁም ትሸበራላችሁ፤ ትንቀጠቀጣላችሁ፤ በውስጣችሁ ጭንቀት ይፈጠራል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ክስተቱ ተፈጥሯዊ ነው፤ ምንም ስህተት የለበትም፡፡ ሁልጊዜም እንዲህ ነው የሆነው፤ ሁልጊዜም የሚሆነው እንዲህ ነው፡፡

የአዲሱን አቀራረብ ለመረዳት ሞክሩ፡፡ ማንም ሰው በአሮጌው አይረካምና አዲስ ነገር ይፈልጋል፡፡ ማንም ሰው ያለፈውን ስለሚያውቀው ምንም ይሁን ምን አይረካበትም፡፡ ድግምግሞሽ፣ አሰልቺ እና አንድ አይነት ሆኖ ይታየዋል፡፡ ስለዚህም ሊያስወግደው ይፈልጋል፡፡ አዲስ ነገር ማየት፣ ማወቅ ይፈልጋል፡፡ አዲስ መሆን ብትፈልጉም እንግዳው በሩን ሲያንኳኳ





ወደኋላ ታፈገፍጋላችሁ፤ በአሮጌአችሁ ውስጥ ትሸሸጋላችሁ፡፡ ይህ ማመንታት ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ እንዴት አዲስ መሆን እንችላለን? ሁሉም ሰው አዲስ መሆን ይፈልጋል፡፡ አዲስ ለመሆን ደግሞ ተራ ድፍረት ሳይሆን የለየ ድፍረት ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች ማደግ ስላቆሙ ዓለም በፈሪዎች የተሞላች ሆናለች፡፡ ፈሪ ከሆናችሁ እንዴት ልታድጉ ትችላላችሁ? አዲስ አጋጣሚ ባገኛችሁ ቁጥር ወደኋላ ተፈገፍጋላችሁ፤ አይናችሁን ትጨፍናላችሁ፡፡ ታዲያ እንዴት ታድጋላችሁ? እንዴት ራሳችሁን ልትሆኑ ትችላላችሁ? አትሆኑም፤ በማስመሰል ብቻ ትኖራላችሁ፡፡

ማደግ ስለማትችሉም መተኪያ እድገት ትፈልጋላችሁ፡፡ እናንተ ማደግ ባትችሉም ተቀማጭ ገንዘባችሁ ያድጋል - ይህ ምትክ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ድፍረት አያስፈልግም፤ ከፍርሃታችሁ ጋር ስምም ሆኖ የተጣጣመ ነውና፡፡ በባንክ የተቀመጠ ገንዘባችሁ ሲያድግ፣ እናንተ ራሳችሁ እያደጋችሁ እንደሆነ ይሰማችኋል፡፡ የበለጠ የተከበረ ትሆናላችሁ፡፡ ስምና ዝናችሁ ከፍ ሲል እያደጋችሁ ይመስላችኋል፤ ግን ራሳችሁን እያታለላችሁ ነው፡፡ ስማችሁም ሆነ ዝናችሁ እናንተ አይደለም፡፡ ተቀማጭ ገንዘባችሁም ማንነታችሁ አይደለም፡፡ እናም ስለሚናወጠው ማንነታችሁ ካሰባችሁና ማደግ ከፈለጋችሁ ፍርሃታችሁን በሙሉ ልታስወግዱ ይገባል፡፡

ለመሆን እንዴት አዲስ መሆን እንችላለን?

አዲስነት ከሀልውና የሚመጣ ነው፡፡ አዕምሮ ሁልጊዜም አሮጌ ነው፤ አዕምሮ አዲስ ሆኖ አያውቅም፤ የትናንት ክምችት ነው፡፡ አዲስነት ከሩቅ የሚመጣ ነው፡፡ ከእግዚአብሄር የሚሰጥ ስጦታ ነው፤ ከሩቅ የሚመጣ የሩቅ ነው፡፡

የማይታወቀው፣ የማይታወቀው፣ ከሩቅ እውስጣችሁ ዘልቆ ገብቷል፡፡ ወደ ውስጣችሁ ዘልቆ የገባውም ራሳችሁን ጠርቅማችሁ ስላላያችሁት ነው፡፡ እናንተ የሩቁን ብትረሱትም እሱ ግን አልረሳችሁም፡፡ ልጅ እናቱን ይረሳ ይሆናል፤ እናት ግን ልጇን አትረሳም፡፡ አንዴ አካል ‹‹የተለየሁ ነኝ›› ብሎ ማሰብ ጀምሮ ይሆናል፤ መላው አካል ግን እንዳልተለየ ያውቃል፡፡ መላው እናንተነታችሁ ውስጥ ነው ያለው፡፡ አሁንም ከእናንተ ጋር ነው፡፡ ለዚያም ነው ባትጋብዙትም አዲሱ መምጣቱን የማያቆመው፡፡ በየቀኑ፣ በየምሽቱ

ይወጣል፣ በአንድ ሺ አንድ መንገዶች ይወጣል። የምታዩበት አይን ካላችሁ ሳያቋርጥ እንደሚመጣ ትገነዘባላችሁ።

ሕያውነት አላያችሁ ላይ እየፈሰሰ ቢሆንም እናንተ ግን በትናንት ታጥራችኋል። ልክ በመቃብር እንዳላችሁ ስሜት አልባ ሆናችኋል። ፈሪ በመሆናችሁ ባቢያ ስሜታችሁን አጥንታችኋል። ስሜታዊ መሆን ማለት አዲሱ ይሰማችኋል - የአዲሱ ስሜት፣ የአዲሱ ፍትር ተሰምቶዋችሁ የት እንደምትሄዱ ሳታውቁ ወደማይታወቀው ትሄዳላችሁ ማለት ነው።

አዕምሮአችሁ ሃሳቡ መጥፎ እንደሆን፣ አሮጌውን ጥሎ መሄድ ምክንያታዊ እንዳልሆነ ያስባል። እግዚአብሄር ግን ሁልጊዜ አዲስ ነው። ለዛም ነው ለእግዚአብሄር ያለፈ ወይም መጪውን ጊዜ የሚያመላክት ግስ የማንጠቀመው። "እግዚአብሄር ነበር" ወይም "እግዚአብሄር ይሆናል" አንልም። "እግዚአብሄር" የሚለውን ብቻ ነው የምንጠቀመው። ሁልጊዜም አዲስ እና ትኩስ ነውና። እናንተ ውስጥም አለ።

ወደ ህይወታችሁ የሚመጣ አዲስ ነገር በሙሉ የእግዚአብሄር መልእክት እንደሆነ አትርሱ። ከተቀበላችሁት ሃይማኖተኛ ናችሁ ማለት ነው። ካልተቀበላችሁት ሃይማኖት የለሽ ናችሁ። የሰው ልጅ አዲሱን ለመቀበል ትንሽ ዘና ማለት፣ ትንሽ ክፈት ማለት አለበት። አምላክ ወደ ውስጣችሁ እንዲገባ መንገድ ስጡት።

ይህ ነው የፀሎት ወይም የተመስጦ ምሉዕ ትርጓሜ - ክፍት ሁኑ፣ እሺ በሉ፣ "ግባ" በሉት። "እስካሁን ስጠብቅህ ነበር። አሁን ስለመጣህ አመሰግናለሁ" በሉት። ሁልጊዜም አዲሱን በታላቅ ደስታ ተቀበሉት። አንዳንድ ጊዜ አዲሱ ምቾት ባይሰጣችሁ እንኳን ዋጋ እንዳለው ተገንዘቡ። አንዳንድ ጊዜ አዲሱ ትንሽ ችግር ውስጥ ቢከታችሁም እንኳን ዋጋ እንዳለው ተገንዘቡ፣ ምክንያቱም አንድ ሰው የሚያድገው በችግሮች ውስጥ፣ የሚማረው ከስህተቶቹ ነውና። አዲሱ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ይፈጥርባችኋል። ለዛም ነው አሮጌውን የመረጣችሁት - እሱ ምንም ችግር አይፈጥርባችሁም። እሱ መፅናኛ፣ መሸሸጊያ ነው።

አዲሱን በጥልቀት እና ሙሉ በሙሉ ስትቀበሉት ብቻ ነው የሚለውጣችሁ። አዲሱ እናንተ ጉትጎታችሁ የምታመጡት አይደለም፣ ራሱ መጥቶ በህይወታችሁ ውስጥ ይገባል። እናንተ ደግሞ ልትቀበሉት ወይም



ህያውነት እኛ 2007 ዓ.ም

ላትቀበሉት ትችላላችሁ። ካልተቀበላችሁት ድንጋይ፣ የተዘጋ፣ የሞተ እንደሆናችሁ ትቀራላችሁ። ከተቀበላችሁት አበባ ትሆናላችሁ፣ ክፍት መሆን ትጀምራላችሁ .... ይህ ክፍትነት ደግሞ ድንቅ ነው።

ሌላ የመለወጫ መንገድ የለምና አዲሱ ብቻ ይለውጣችኋል። ከእናንተ እና ከጥረታችሁ ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር እንደሌለ ግን አስታውሱ። ምንም አለማድረግ መንቀሳቀስ ማቆም አይደለም፣ ያለ ፈቃድ ወይም ያለ መሪ ወይም ባለፈ ህይወት ሳይገፉ መንቀሳቀስ ነው ማለት እንጂ። አዲሱን ለማግኘት የሚደረገው ፍለጋ ተራ ፍለጋ አይደለም - ምክንያቱም የምትፈልጉት አዲስ ነው። ግን እንዴት ልትፈልጉት ትችላላችሁ? አታውቁትም፣ እስካሁን ድረስም አላገኛችሁትም። አዲሱን ለማግኘት የሚደረግ ፍለጋ አንድ ግልፅ ፍለጋ ነው የሚሆነው። ማንም አያውቀውም። አንድ ሰው ባለማወቅ መጀመር፣ እንደ ህፃናት በአጋጣሚዎች እየተደነቀ በየዋህነት መንቀሳቀስ ይኖርበታል - እነዚህ አጋጣሚዎች ደግሞ የትየለሌ ናቸው።

**አዲሱ እናንተ ጉትጎታችሁ የምታመጡት አይደለም፣ ራሱ መጥቶ በህይወታችሁ ውስጥ ይገባል። እናንተ ደግሞ ልትቀበሉት ወይም ላትቀበሉት ትችላላችሁ።**

አዲሱን ለመፍጠር ምንም ማድረግ አትችሉም፣ ምክንያቱም ይህን ስታደርጉ የአሮጌው አካል፣ የትናንት ትሆናላችሁ። ይህ ማለት ግን መንቀሳቀስ ታቆማላችሁ ማለት አይደለም። ያለ ፈቃድ ወይም ያለ መሪ ወይም ባለፈ ህይወት ሳትገፉ ነፃ ሆናችሁ መንቀሳቀስ ነው። ይህ ሂደት ተመስጦ ይባላል። ሳታቋርጡ ተንቀሳቀሱ። እያንዳንዱን ቅፅበት ወሳኝ አድርጉት።

ውሳኔአችሁን አትጫኑት - ምክንያቱም ውሳኔው ያለፈ ይሆንና አዲሱን ያጠፋዋል። ልክ እንደ ህፃን ሁኑ። በዚያ ቅፅበት ራሳችሁን እርሱ - ይሄን ጊዜ በእያንዳንዱ ቀን አዲስ ክፍተት፣ አዲስ ብርሃን፣ አዲስ ራዕይ ታገኛላችሁ። እነዚህ አዳዲስ ራዕዮች ደግሞ ይለውጡዋችኋል። አንድ ቀን ድንገት በእያንዳንዱ ቅፅበት አዲስ እንደሆናችሁ ትገነዘባላችሁ። አሮጌው ከእናንተ መለጠፉን፣ በዙሪያችሁ ማንዣበቡን ያቆማል። እንደ ጤዛ ትኩስ እና ወጣት ትሆናላችሁ።

ይህ ነው የትንሳኤ እውነተኛ ትርጉም፡፡ ይህን ከተገነዘባችሁ ከስኑ. ልቡናችሁ ትውስታ ነፃ ትሆናላችሁ፡፡ ትውስታ የሞተ ነገር ነው፡፡ ትውስታ እውነት አይደለም፤ደግሞም አይሆንም- ምክንያቱም እውነት ሁልጊዜ ህያው ነው፤ እውነት ህይወት ነው፡፡ ትውስታ አሁን የሌለ እውነት ነው፤ በማስታወስ ዓለም እንደመኖር ነው፡፡ እኛ በውስጡ አለን፡፡ የእኛ እስር ቤታችን ነው፡፡ ትውስታ "እኔ" የተባለውን ተራራ፣ የራስ ኩራት፣ እኔነት ይፈጥራል፡፡ ይህ ሃሰተኛ ማዕረግ "እኔ፡" ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ ሞትን ይፈራል - ለዛም ነው አዲሱን የምትፈሩት፡፡

እናንተ ራሳችሁ ሳትሆኑ ይሄ "እኔ" የተባለ ነገር ነው የሚፈራው፡፡ ማንነት አይፈራም፡፡ የራስ ኩራት ግን ይፈራል - ሞትን በጣም ይፈራዋልና፡፡ ሰው ሰራሽና በፈቃድ የሚገኝ ነው፡፡ ስለዚህ በማንኛውም ጊዜ ሊፈራርስ ይችላል፡፡ አዲስ ሲመጣ ፍርሃት ይኖራል፡ የራስ ኩራት ስለሚፈራ ይፈራርሳል፡፡ ራስን አደራጅቶ እንደ አንድ ቢቆይም አዲሱ ሲመጣ ይበታተናል፡፡ ለዛም ነው አዲሱን በደስታ የማትቀበሉት፡፡ የራስ ኩራት የራሱን ሞት በደስታ አይቀበልም - የራሱን ሞት እንዴት በደስታ አይቀበልም - የራሱን ሞት እንዴት በደስታ ሊቀበል ይችላል?

የራስ ኩራታችህ እንዳልተጫናችሁ እርግጠኛ እስካልሆናችሁ ድረስ አዲሱን መቀበል አትችሉም፡፡ የራስ ኩራታችሁ ያለፈ ትውስታችሁ ከመሆን በቀር ምንም እንዳልሆነ - ማለትም እናንተ ትውስታችሁን እንዳልሆናችሁ፣ ትውስታ ልክ እንደ ባዮኮምፒዩተር እንደሆነ ከተገነዘባችሁ ....... ትውስት ሳይሆን ንቃተ- ህሊና ናችሁ ማለት ነው፡፡ ትውስታ በንቃተ- ህሊና ውስጥ ያለ አንድ ነገር ነው፡፡ እናንተ ንቃተ-ህሊና ናችሁ፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው በመንገድ ላይ ሲራመድ ታያላችሁ እንበል፡፡ ፊቱን ብታውቁትም ስሙ ይጠፋባችኋል፡፡ እናንተ ትውስታ ብትሆኑ ኖሮ ስሙንም ማስታወስ ነበረባችሁ፡፡ "ፊቱ ትዝ ይለኛል፤ ስሙ ግን ጠፋኝ" ትላላችሁ፡፡ እናም ወደ ትውስታችሁ ውስጥ በጥልቀት ትመለከታላችሁ፡፡ ይሄን ጊዜ ስሙ ብልጭ ይልላችሁና "አዎን፣ አገኘሁት" ትላላችሁ ትውስታ ቀርፃችሁ ያስቀመጣችሁት ነገር ነው፡፡ እናንተ ግን ወደተቀመጠው ነገር የምትመለከቱ እንጂ ትውስታውን ራሱን አይደላችሁም፡፡





ብዙውን ጊዜ ለማስታወስ በተጨነቃችሁ ልክ ለማስታወስ ይቸግራችኋል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት በማንነታችሁ ላይ የሚደርሰው ውጥረት ትውስታዊ መረጃውን ወደ እናንተ እንዳይለቀው ስለሚያግደው ነው፡፡ የአንዱን ሰው ስም ለማስታወስ ብትሞክሩም፣ አፋችሁ ላይ ያለ ቢሆንም አይመጣላችሁም፡፡ እንደምታውቁት ታውቃላችሁ፣ ስሙ ግን አይመጣላችሁም፡፡

ይህ እንግዳ ነገር ነው፡፡ እናንተ ትውስታ ከሆናችሁ እንዳታስታውሱ የሚከለክላችሁ ማነው? ደግሞስ ለምንድነው ትውስ የማይላችሁ? "አውቀዋለሁ፣ ግን አልመጣልኝም" የሚለው ማነው?

ትውስትችሁ እናንተን አይደለም፡፡ እናንተ ንቃተ-ህሊና ናችሁ፡፡ ትውስታ አንድ አካል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ትውስታ የራስ ኩራት፣ የህይወት ሃይልም ነው፡፡ ትውስታ እርጌ ከመሆኑ ባሻገር አዲሱን ይፈራል፤ አዲስ ያውከዋል፤ ለመዋሃድም አስቸጋሪ ይሆንበታል፡፡ አዲሱ ምናልባት ችግር ይፈጥርበት ይሆናል - ምክንያቱም ራሳችሁን መለወጥና ማስተካከል ይኖርባችሁ ይኖናል፡፡ ይህም ከባድ ይመስላል፡፡

አንድ ሰው አዲስ ለመሆን ራሱን ከራስ ኩራቱ መሸሽግ ይኖርበታል፡፡ አንዴ ከራስ ኩራታችህ ከተሸሸጋችሁ በኋላ ቢኖር ወይም ቢሞት ግድ አይኖራችሁም፡፡ በእርግጥ ይኑርም፣ ይሙትም እንደሞተ ታውቃላችሁ፡፡ ልክ እንደ መሳሪያ ነው፡፡ ትጠቀሙበታላችሁ እንጂ አይጠቀምባችሁም፡፡ የራስ ኩራት በፈቃድ የሚገኝ ነውና ሞትን ይፈራል፡፡ ከማንነት አይልቅም፣ ሊልቅም አይችልም - ምክንያቱም ማንነት ህይወት ነው፡፡ ህይወት ደግሞ እንዴት ሞትን ይፈራል? ህይወት ሞትን አያውቀውም፡፡ የራስ ኩራት የሚመነጨው በፈቃድ ከሚገኘው፣ ከሰው ሰራሹ፣ እንደ ነገሩ ከተቀመጠው፣ ከሃሰተኛው፣ ከውሸቱ ነው፡፡ የራስ ኩራት ሞት ነው ሰውን ህያው የሚያደርገው፡፡ የራስ ኩራት ሞት የማንነት ውልደት ነው፡፡

አዲሱ ከአምላክ የተላከ መላዕክተኛ፣ ከአምላክ የተላከ መልዕክት ነው፡፡ ወንጌል ነው! እናም አዲሱን አድምጡት፣ ከአዲሱ ጋር ተጓዙ፡፡ እንደፈራችሁ አውቃለሁ፡፡ ይሁንና ፍርሃታችሁን ገለል አድርጋችሁ ከአዲሱ ጋር ሂዱ፡፡ እንግዲህ ካደረጋችሁ ህይወታችሁ አድጉና በለፀጉ አንድ ቀን የተሸሸገ ውበታችሁን ማውጣት ትችላላችሁ፡፡

ድፍረት በማጣታችን ምክንያት ብቻ በህይወታችን ብዙ ነገሮችን እናጣለን፡፡ የሆነ ነገር ለማግኘት ከድፍረት በቀር ሌላ ጥረት አያስፈልግም፡፡ እናንተ ወደ ነገሮቹ ከመሄድ ይልቅ ነገሮቹ ወደ እናንተ መምጣት ይጀምራሉ .... ቢያንስ በውስጠኛው ዓለም ይህ ነው፡፡

ለእኔ ደስተኛ መሆን ትልቁ ድፍረት ነው፡፡ አሰቃቂ መሆን በጣም ፈሪ መሆን ነው፡፡ በእርግጥ አስቸጋሪ ለመሆን ምንም ማድረግ አያስፈልግም፡፡ ማንም ፈሪ፡ ማንም ቂል ይህን ማድረግ ይችላል፡ ማንም ሰው መጥፎ መሆን ይችላል፡፡ ደስተኛ ለመሆን ግን ትልቅ ድፍረት ያስፈልጋል፡፡

"ደስተኛ ለመሆን ምንድነው የሚያስፈልገው? ሁሉም ሰው ደስተኛ መሆን ይፈልጋል" እንላለን፡፡ ይህ ግን ሙሉ በሙሉ የተሳሳተ ነው፡፡ ሰው ብዙውን ጊዜ ደስተኛ መሆን አይፈልግም - የሚናገረው ግን ሌላ ነው፡፡ ይሁንና ሰው ብዙውን ጊዜ ደስተኛ ለመሆን ዝግጁ አይደለም - ብዙ ጥረቱን የሚያባክነው መጥፎ ለመሆን ነው፡፡ ደስተኛ አለመሆን ይፈልጋል .... ደስተኛ ባመሆኑም ደስተኛ ነው፡፡

ብዙ ነገሮች ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለባቸው - አለበለዚያ ከመጥፎነት ወጥመድ መውጣት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያ እናንተን ከዚያ ይዛ ያቆያችሁ የለም፡ ራሳችሁ ናችሁ በዚያ የስቃይ እስር ቤት ውስጥ የገባችሁት፡፡ ማንም ማንንም አልያዘም፡፡ ከዚያ መውጣት የፈለገ ሰው ወዲያውኑ መውጣት ይችላል፡፡ ማንም ሃላፊነት የለበትም፡፡ አንድ ሰው መጥፎ ከሆነ ሃላፊነት አለበት፡፡ መጥፎ ሰው ግን ይህን ሃላፊነቱን አይቀበልም - ለዛም ነው መጥፎ ሆኖ የቀረው "አንድ የሆነ ነገር መጥፎ እያደረገኝ ነው" ይላል፡፡

**ሰው ብዙውን ጊዜ ደስተኛ መሆን አይፈልግም - ብዙውን ጊዜ ደስተኛ ለመሆን ዝግጁ አይደለም - ብዙ ጥረቱን የሚያባክነው መጥፎ ለመሆን ነው፡፡ ደስተኛ አለመሆን ይፈልጋል ..... ደስተኛ ባመሆኑም ደስተኛ ነው፡፡**

አንድ የሆነ ነገር መጥፎ ያደረጋችሁ ከሆነ ምን ማድረግ ትችላላችሁ? ራሳችሁን መጥፎ ያደረጋችሁ ከሆነ አንድ ነገር መደረግ ይቻላል ... በፍጥነት አንድ ነገር ማድረግ ይቻላል፡፡ ስለዚህ መጥፎ ለመሆንና





ላለመሆን ያለው አማራጭ በእጃችሁ ነው ማለት ነው፡፡ እናም ሰዎች ሃላፊነታቸውን እንዳንዴ ወደ ሚስቶቻቸው፡ ባሎቻቸው፡ ቤተሰቦቻቸው፡ የተለያዩ ሁኔታዎች፡ ልጅነታቸው፡ እናታቸው፡ አባታቸው፡ ..... ማህበረሰቡ፡ ታሪክ፡ እድል፡ እግዚአብሄር ይወረውራሉ፡፡ ስሞቹ የተለያዩ ቢሆኑም ጨዋታው ተመሳሳይ ነው፡፡

አንድ ሰው፡ ሰው የሚሆነው ሃላፊነቱን በሙሉ ሲቀበል ነው - ለሁሉም ነገር ሃላፊው እሱ ነው፡፡ ይህ ነው የመጀመሪያውና ታላቁ ድፍረት፡፡ እዕምሮ ደጋግሞ "ሃላፊነቱ ያንተ ከሆነ ለምን ፈጠርከው?" ስለሚል ይህን ለመቀበል ከባድ ይሆናል፡፡ ይህን ለመሸከም ሌሎች ሃላፊነት እንዳለባቸው እንናገራለን፡፡ "ምን ማድረግ እችላለሁ?" ረዳት የሌለኝ ተጠቂ ነኝ! ከእኔ በሚበልጡ ሃይሎች ወዲያ ወዲህ እየተወረወርኩ ነው፡፡ ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ ስለዚህ ቢበዛ መጥፎ በመሆኔ መጮህና የበለጠ መጥፎ መሆን ነው የምችለው" እንላለን ይህን ስትለማመዱት እያደገባችሁ ይሄዳል፡፡ ከዚያም ይጠልቅባችኋል፡ ትሰጥሙበታላችሁ፡፡

ማንም፡ የትኛውም ሃይል ምንም እያደረገባችሁ አይደለም፡፡ እናንተና እናንተ ብቻ ናችሁ፡፡ ይህ የካርማ ፍልስፍና ነው፡፡ ካርማ ማለት ስራ ነው፡፡ እናንተ እንዳደረጋችሁት ሁሉ አለማድረግም ትችላላችሁ፡፡ መዘግየት አስፈላጊ አይደለም፡ ጊዜ መፍጀት አያስፈልግም - ዘልላችሁ መውጣት ትችላላችሁ!

ይሁን እንጂ ተላምደነዋል፡፡ መጥፎ ካልሆንን ብቸኝነት ይሰማናል፡ የቅርብ ጓደኞችንን እናጣለን፡፡ የትም የሚከተለን ጥላችን ሆኗል፡፡ ሌላ ሰው አጠገባችን ባይኖር እንኳን ቢያንስ መጥፎነታችን አብሮን አለ - ተጋብተነዋል፡፡ ጋብቻውም ብዙ የቆየ ነው፡ ከመጥፎነት ጋር ከተሳሰርን ብዙ ዓመታት ቆይተናል፡፡

አሁን ጋብቻው የመፍረሻው ቀን ደርሷል፡፡ እኔ ታላቁ ድፍረት የምለው ከሰው ልጅ እዕምሮ የጥንት ጓደኛና ልማድ መጥፎነት መላቀቅ ነው፡፡



# በፍቅር መድፈር - ፍርሃትን ፍራቻ፣ እጦትን ማጣት ነው

***ፍርሃት ምንም ሳይሆን የፍቅር እጦት ነው፡፡ ፍርሃትን እርሱና በፍቅር አድ ነገር አድርጉ፡፡ በደንብ ካፈቀራችሁ ፍርሃት ይጠፋል፡፡***

በጥልቀት ካፈቀራችሁ ፍርሃት ድራሹ ይጠፋል፡፡ ፍርሃት እጦት፣ አሉታዊ ነገር ነው፡፡ ይህንን በጥልቀት ልትገነዘቡት ይገባል፡፡ ይህን ግንዛቤ ካልጨበጣችሁ የፍርሃትን ባህርይ ልትረዱ አትችሉም፡፡ ፍርሃት እንደጨለማ ነው፡፡ ጨለማ የሌለ ቢሆንም ያለ ይመስላል፡፡ ጨለማ የብርሃን እጦት ነው፡፡ ብርሃን ግን አለ፤ ብርሃኑን ካስወገዳችሁት - ጨለማው ብቅ ይላል፡፡

ጨለማ የለም፤ ጨለማን መግፈፍ አትችሉም፤ የፈለጋችሁትን ነገር ብታደርጉ ጨለማን ማስወገድ አትችሉም፤ ልታመጡት ወይም ልትወረውሩት አትችሉም፡፡ ጨለማን አንድ ነገር ማድረግ ከፈለጋችሁ ብርሃንን መጠቀም ይኖርባችኋል፤ ምክንያቱም አንድ ነገር ማድረግ የምትችሉት ህያው የሆነን ነገር ነው፡፡ መብራቱ ሲጠፋት ጨለማ





ይሆናል፤ መብራቱን ስታበሩት ጨለማ አይኖርም - በብርሃን አንድ ነገር ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ ጨለማን ግን ምንም ማድረግ አትችሉም፡፡

ፍርሃት ጨለማ ነው፤ የፍቅር እጦት ነው፡፡ ምንም ልታደርጉት አትችሉም፡፡ ልታስወግዱት ብዙ በጣራችሁ ቁጥር የበለጠ ፈሪ ትሆናላችሁ፡ ምክንያቱም የበለጠ የማይቻል ይሆንባችኋል፡ችግሩ ይበልጥ ውስብስብ ይሆናል፡፡ ጨለማን ከታገላችሁት ትሸነፋላችሁ፡፡ ጉራዴ ይዛችሁ ጨለማን ልትገድሉት ብትሞክሩ ትርፉ ድካም ብቻ ነው፡፡ በመጨረሻም አዕምሮ "ጨለማ ሃይለኛ ስለሆነ ነው የተሸነፍኩት" ይላል፡፡

ይሄን ጊዜ ነው ምክንያታዊ አስተሳሰብ ስህተት የሚሆነው፡፡ ሁኔታው ፍፁም ስነ-አመክኖያዊ ነው - ከጨለማ ጋር ታግላችሁ ልታሸንፉ ወይም ልታጠፉት ካልቻላችሁ "ጨለማ በጣም፣ በጣም ሃይለኛ ነው፡፡ እኔ ከእሱ ጋር ስነፃፀር ደካማ ነኝ" ብሎ ማሰብ ትክክለኛ አስተሳሰብ ነው፡፡ እውነታው ግን የተለየ ነው፡፡ እናንተ ሳትሆኑ ጨለማው ነው - ደካማ፡፡ በእርግጥ ጨለማው እዚያ ስለሌለ ነው ልታሸንፉት ያልቻላችሁት፡፡ የሌለን ነገር እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?

ከፍርሃት ጋር አትታገሉ፤ አለበለዚያ የበለጠ ፈሪ ትሆናላችሁ፡፡ አዲስ ፍርሃት በውስጣችሁ ይገባል፡፡ ፍርሃትን መፍራት ነው በጣም አደገኛው ነገር፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርሃት እጦት ነው፡፡ ሁለተኛው ነገር ፍርሃትን ፍራቻ፣ እጦትን ማጣት ነው፡፡ ከዚያም ወደ እብደት ታመራላችሁ!

ፍርሃት ምንም ሳይሆን የፍቅር እጦት ነው፡፡ ፍርሃትን እርሱትና በፍቅር አንድ ነገር አድርጉ፡፡ በደንብ ካፈቀራችሁ ፍርሃት ይጠፋል፤ በጥልቀት ካፈቀራችሁ ፍርሃት ድራሹ ይጠፋል፡፡

ለአንዲት ቅፅበት እንኳን አንድን ሰው አፍቅራችሁ ፈርታችሁ ታውቃላችሁ? ሁለት ሰዎች ተገናኝተው በጥልቅ ፍቅር ከወደቁ - ለአንዲት ቅፅበት እንኳን ቢሆን - በመሃላቸው ፍርሃት አይኖርም፡፡ መብራት በርቶ ጨለማ ሳይኖር እንደ ሚስጥራዊ ቁልፍ አለ - ፍቅር፡፡

በህያውነታችሁ ውስጥ ፍርሃት እንዳለ ከተሰማችሁ የበለጠ አፍቅሩ፡፡ በፍቅር ድፈሩ፤ ደፋር ሁኑ፤ የፍቅር ጀብደኛ ሁኑ፡፡ ያለምንም ትድመ

ሁኔታ የበለጠ አፍቅሩ፤ የበለጠ ባፈተራችሁ ቁጥር ፍርሃታችሁም የዚያኑ ያህል ይቀንሳል፡፡

ፍቅር ስል ከፆታ እስከ ሳማዲ ያሉትን እርከኖች ማለቴ ነው፡፡ በጥልቀት አፍቅሩ፡፡

በፆታዊ ግንኙነት በጥልቀት ካፈቀራችሁ ከእካላችሁ ብዙ ፍርሃት ይወገዳል፡፡ ሰውነታችሁ በፍርሃት የሚንቀጠቀጥ ከሆነ የፆት ፍርሃት አለባችሁ ማለት ነው፤ ከዚህ በፊት በጥልቅ የፆታዊ ግንኙነት ውስጥ አልነበራችሁም፡፡ አካላችሁ ሲንቀጠቀጥ ሰውነታችሁ አልተረጋጋም ማለት ነው፡፡

በጥልቀት አፍቅሩ - ወሲባዊ እርካታ ፍርሃታችሁን በሙሉ ጠራርጐ ያጠፋባችኋል፡፡ ፍርሃታችሁ ተጠራርጐ ይጠፋል ማለት ደፋር ትሆናላችሁ ማለተ አይደለም፡፡ ደፋሮች የፈሪዎች ግልባጮች ናቸው፡፡ ፍርሃት በሙሉ ተጠራርጐ ይጠፋል ስል ፍርሃትም፤ ድፍረትም አይኖሩም ማለቴ ነው፡፡

- ሁለት አይነት ፍርሃቶች አሉ፡፡

ደፋር የምትሉዋቸውን ሰዎች ተመልከቷቸው፡፡ በውስጣቸው ጥልቅ የሆነ ፍርሃት እንዳለባቸው ትገነዘባላችሁ፤ ከውጭ ሽፋን አበጅተው ነው ደፋር የመሰሉት፤ ድፍረት ፍርሃት አልባነት አይደለም፡፡ ድፍረት ጥሩ መከላከያ፤ ከለላ፤ ጥሩር ያለው ፍርሃት ነው፡፡

ፍርሃት ሲጠፋ ፍርሃት አልባ ትሆናላችሁ፡፡ ፍርሃት የሌለበት ሰው በማንም ላይ ፍርሃትን አይለቅም፤ ሌላም ሰው ፍርሃት እንዲያሳድርበት አይፈቅድም፡፡

**ፍርሃታችሁ ተጠራርጐ ይጠፋል ማለት ደፋር ትሆናላችሁ ማለት አይደለም፡፡ ደፋሮች የፈሪዎች ግልባጮች ናቸው፡፡ ፍርሃት በሙሉ ተጠራርጐ ይጠፋል ስል ፍርሃትም፤ ድፍረትም አይኖሩም ማለት ነው፡፡**

ጥልቅ የሆነ ወሲባዊ እርካታ አካልን ያረጋጋል፡፡ ሰውነት ምሉእነት ስለሚሰማው በጣም፤ በጣም ጥልቅ የሆነ ጤንነት በእካላችሁ ይሰራጫል፡፡





ሁለተኛው ደረጃ ፍቅር ነው፡፡ ሰውን ያለ ገደብ አፍቅሩ በአዕምሮአችሁ ውስጥ እንድ የሚገድባችሁ ነገር ካለ ማፍቀር አትችሉም፡፡ እነዚያ ሁኔታዎች እንቅፋት ይሆኑባችኋል፡፡ ፍቅር አስፈላጊያችሁ ከሆነ ስለ ሁኔታዎቹ ለምን ትጨነቃላችሁ? ያለ ገደብ በጥልቀት ማፍቀር በጣም አስፈላጊ ነው - በምላሹ ምንም አትጠይቁ ሰዎችን በመውደድ ምክንያት ብቻ ፍርሃት አልባነትን ማዳበር ከቻላችሁ ለደስታችሁ ስትሉ ብቻ ታፈቅራላችሁ?

ተራ ሰዎች ሁኔታዎቻቸው ሲሟሉላቸው ብቻ ያፈቅራሉ፡፡ "እንዲህ ከሆንክ ብቻ ነው የማፈቅርህ" ይላሉ፡፡ እናት ልጅዋን "ዐባየኛ ከሆንክ ብቻ እወድሃለሁ" ትለዋለች፡፡ ሚስት ባሏን "እንዲህ ከሆንክ አፈቅርሃለሁ" ትለዋለች፡፡ ሁሉም ሰው ቅድመ - ሁኔታ ሲያስቀምጥ ፍቅር ይጠፋል፡፡

ፍቅር ወሰን የሌለው ሰማይ ነው! ልታጠቡት፤ ልትወስኑት አትችሉም፡፡ ቤታችሁ ውስጥ ንፁህ አየር እስገብታችሁ መስኮቶቻችሁንና በሮቻችሁን ብትቆላልፉ ብዙም ሳይቆይ የትመቀ ይሆናል፡፡ ፍቅር የሚመጣው በነፃነት ነው፡፡ ያን ንፁህ አየር ወደቤታችሁ እስገብታችሁ እንደቆለፋችሁበት ወዲያውኑ ሁሉም ነገር የታመተ፤ ቆሻሻ ይሆናል፡፡

ይህ የጠቅላላ ሰው ችግር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሰዎች በፍቅር ሲወድቁ ሁኔታዎችን ስለማይደረድሩ ሁሉም ነገር መልካም ይመስላል፡፡ የተፈቀሩት ሰዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይቀራረባሉ፡፡ ከተረጋጉ በኋላ፤ ፍቅር መስጣጠት ከጀመሩ በኋላ፤ ቅድመ - ሁኔታዎች ይመጣሉ፡፡ ፍቅር የገበያ ዕቃ ይመስል "ይህን ካልመሰልክ፤ እንዲህ ካልሆንሽ" ይባባላሉ፡፡

በሙሉ ልባችሁ ካላፈቀራችሁ እየተደራደራችሁ ነው፡፡ ለላኛውን ሰው የሆነ ነገር ካላደረግክልኝ እያላችሁ እያስገደዳችሁ ነው፡፡ ይህ ቅድመ ሁኔታችሁን ካልተሟላ ፍቅራችሁን ትከዳላችሁ፡፡ አሁን እያፈቀራችሁ ሳይሆን ፍቅራችሁን እንደ መቅጫ፤ እንደማስገደጃ እየተጠቀማችሁበት ነው፡፡ ፍቅር ተቀባይ ወይም ፍቅር ሰጪ ብትሆኑም በሁለቱም መንገድ ፍቅር መጨረሻ አይደለም፡፡

ያገባችሁ ከሆነ ለሚስታችሁ ስጦታ ይዛችሁላት ትሄዳላችሁ - ያኔን ጊዜ ደስ ብሏት እያቀፈች ትስማችኋለች፡፡ ወደ ቤታችሁ የሆነ ነገር ይዛችሁ ካልገባችሁ ግን መራራት ይፈጠራል፡፡ እንኳን ልትስማችሁ አጠገባችሁ አትደርስም፡፡ እንደዚህ አይነት ነገር ስታደርጉ ፍቅር ለሌሎች ብቻ ሳይሆን

ለእናንተም ጠቃሚ እንደሆነ ዘንግታችኋል ማለት ነው፡፡ ፍቅር የሚጠቅመዉ አፍቃሪዎችን ነው፤ የተፈቀሩትንም ይጠቅማል፡፡

ሰዎች ወደ እኔ ይመጡና "ጓደኛዬ አያፈቅረኝም" ይላሉ፡፡ "እኔ አላፈቅረውም" ብሎ የሚመጣ የለም፡፡ ፍቅር ማስገደጃ ሆኗል፡፡ "ጓደኛዬ አያፈቅረኝም፡፡" ስለሌላው እርሱ! ፍቅር እጅግ ድንቅ ክስተት ነው፡፡ ስታፈቅሩ ደስተኛ ትሆናላችሁ፡፡

ብዙ ባፈቀራችሁ መጠን ደስተኛ መሆናችሁም በዚያው ልክ ይጨምራል፡፡ ፍቅራችሁ ባነሰ ቁጥር ሌሎች እንዲያፈቅሯችሁ ትጠብቃላችሁ፤ ደስተኛነታችሁ ይቀንሳል፤ የበለጠ ውስን ትሆናላችሁ፤ የራስ ኩራታችሁ ጥገኛ ትሆናላችሁ፡፡ ስሜታችሁ የሚነካ ሰው ትሆናላችሁ - እንዴ ሊያፈቅራችሁ ቢጠጋችሁ እንኳን መገለል፤ መተው ይደርስብኛል ብላችሁ ስለምትፈሩ ስጋት ያድርባችኋል፡፡

ማንም አያፈቅረኝም የሚል ሃሳብ በውስጣችሁ ተሰንቅሯል፡፡ ይህቺ ሴት እንዴት ነው አእምሮአችሁን የምትለውጠው? ልታፈቅራችሁ እየሞከረች ይሆን? በውሸት ቀርባ ልታታልላችሁ ይሆን? በዚህም አሳሳች ሰው መሆን አለባት፡ ብላችሁ ታስቡና ራሳችሁን ትከላከላላችሁ፡፡ ምንም ሰው እንዲያፈቅራችሁ አትፈቅዱም፤ እናንተም ማንንም አታፈቅሩም፡፡ ፍርሃት ያድርባችኋል፤ ብቸኝነት ይሰማችኋል፡፡ ከማንም ሳትገናኙ ብቸኛ ትሆናላችሁ፡፡

ታዲያ ፍርሃት ምንድነው? ፍርሃት ከህልውና ጋር ባመገናኘት የሚፈጠር ስሜት ነው፡፡ ፍርሃትን ከህልውና ጋር ባለመገናኘት የሚፈጠር ሁኔታ ብለን ልንፈታው እንችላለን፡፡ ቤት ውስጥ ብቻችሁን የምታለቅሱ ህፃን ናችሁ፡፡ አባትና እናትን ጨምሮ መላው ቤተሰብ ወደ ቲያትር ቤት ሄደዋል፡፡ ህፃኑ በአልጋው ላይ ተኝቶ ያለቅሳል፡፡ ግንኙነት የለም፤ ጠባቂ የለም፤ የሚረዳ የለም - ብቸኝነት! ሰፊ ብቸኝነት ብቻ፡፡ ይህ ነው የፍርሃት ሁኔታ፡፡

ይህ ሁሉ የማሆነው ፍቅርን እንዳትፈቅዱት ሆናችሁ ስላደጋችሁ ነው፡፡ መላው የሰው ልጅ ለፍቅር ሳይሆን ለሌሎች ነገሮች የሰለጠነ ነው፡፡ መግደል ተምረናል፡፡ የጦር ሰራዊቶች ለዓመታት የመግደል ስልጠና ይወስዳሉ! እንዴት ማስላት እንዳለብን ተምረናል፡፡ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ሌሎች





እንዳያታልሉን፤ እኛ ግን ሌሎችን እንድናታልል ያስተምሩናል፡፡ በነፃነት ማፍቀር እንዴት እንደሆነ ግን አልተማርንም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ማህበረሰቡ ፍቅርን ይከለክላል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው እንዲያፈቅሩ አይፈልጉም፤ እናቶች፡ አባቶች ይህን አይፈቅዱም፡፡ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚሆናቸውን ፍቅረኛ ቢመርጡ ደስ ይላቸዋል፡፡

ለምን? አንድ ወጣት አንዲት ሴት ሲያፈቅር ከቤተሰቡ ይርቃል፤ የራሱን አዲስ በተሰብ ይመሰርታል፡፡ ከአሮጌው ቤተሰብ ጋር ይተናተናል ... "አሁን ልሄድ ነው፤ የራሴን ቤት እመሰርታለሁ" ይላል፡፡ እናም የራሱን ሴት ይመርጣል፡፡ አባት፡ እናት ምንም አያገባቸውም፡፡ ሙሉ በሙሉ የተገለሉ ይመስላል፡፡

እነሱ ግን ራሳቸው ቢመርጡ ደስ ይላቸዋል፡፡ "ቤትህን ስራ፤ ነገር ግን የእኛም እጅ ይኑርበት፡፡ በፍቅር አትውደቅ - በፍቅር ስትወድቅ ፍቅርህን አለም ያውቀዋል" ይሉታል፡፡ በቤተሰብ ምርጫ የተደረገ ጋብቻ ከሆነ ግን ማህበራዊ ጉዳይ ይሆናል፡፡ ይሄኔ በፍቅር ውስጥ አይደላችሁም፡፡ ሚስታችሁ ወይ ባላችሁ መላው አለማችሁ አይሆኑም፡፡ ስለዚህ የቤተሰብ ጋብቻ ሲቀጥል ቤተሰብም ይቀጥላል፡፡ የፍቅር ጋብቻ እውን ሲሆን ግን ቤተሰብ ይጠፋል፡፡

**መላው የሰው ልጅ ለፍቅር ሳይሆን ለሌሎች ነገሮች የሰለጠነ ነው፡፡ እንዴት ማስላት እንዳለብን ተምረናል፡፡ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ሌሎች እንዳያታልሉን፤ እኛ ግን ሌሎችን እንድናታልል ያስተምሩናል፡፡ በነፃነት ማፍቀር እንዴት እንደሆነ ግና አልተማርንም፡፡**

በምዕራቡ ዓለም ቤተሰብ እየጠፋ ነው፡፡ አሁን ለምን የቤተሰብ ጋብቻ እንደሚፈፀም ይገባችኋል፤ ቤተሰብ መኖር ይፈልጋል፡፡ የሚጠፋ ከሆነ፡ የፍቅር ዕድላችሁ የጠፋ ከሆነ ያለው አማራጭ ለበተሰባችሁ መስዋዕት መሆን ነው፡፡ ጋብቻው የበተሰብ ከሆነ ጥንድ ቤተሰብ ይመሰረታል ማለት ነው፡፡ ከዚያም በአንድ ቤተሰብ ውስጥ በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ይኖራሉ - ጋብቻው የቤተሰብ ከሆነ፡፡ ልጁ ሌላ ሴት፤ ልጅቷ ሌላ ወንድ ካፈቀሩ ግን ለራሳቸው ዓለም ይሆናሉ፡፡ ብቻቸውን መሆን፡ የግል ነፃነታቸው እንዲጠበቅ ይፈልጋሉ፡፡ በመቶ በሚቆጠሩ አጎቶች፤ አክስቶች፤ የአክስት አክስቶች ....

መከበብ አይፈልጉም:: የራሳቸውን ዓለም መገንባት ነው የሚፈልጉት:: ይህ ሁሉ ነገር ይረብሻቸዋል::

ቤተሰብ የፍቅር ጠላት ነው:: ቤተሰብ የፍቅር ምንጭ ነው ሲባል ሰምታችሁ ይሆናል፤ ነገር ግን ቤተሰብ የፍቅር ጠላት እንደሆነ እነግራችኋለሁ:: ቤተሰብ ሀያው የሆነው ፍቅርን ገድሎ፣ ፍቅርን አግልሎ ነው::

አንድ ሰው በጥልቅ ፍቅር ውስጥ ሲወድቅ ለመያዝ ያስቸግራልና ማህበረሰቡ ፍቅርን አይፈቅድም:: ወደ ጦርነት ልትልኩት ስትፈልጉ "እኔ እዚህ ደስተኛ ነኝ! የት ነው የምትልኩኝ? ከቤተሰባቸው ጋር በደስታ የሚኖሩትን ሰዎች ለምንድነው የምገድለው? ተቃርኖ የለብንም፤ የፍላጐት ግጭት የለብንም ......." ይላችኋል::

ወጣቱ ትውልድ በጥልቀት ወደ ፍቅር ውስጥ መግባቱን ከቀጠለ ወደ ጦርነት የሚሄድ ብዙ ሰው ስለማይገኝ ጦርነት ይጠፋል:: ስታፈቅሩ የህይወትን ጣዕም ትቀምሳላችሁ:: ሞትንና ግድያን ትጠላላችሁ:: ካላፈቀራችሁ የህይወትን ጣዕም አትቀምሱም፣ ሞትን ትወዳላችሁ::

ፍርሃት ይገድላል፤ ፍርሃት መግደል ይፈልጋል፤ ፍርሃት አጥፊ ነው:: ፍቅር ሃይል ይፈጥራል:: ስታፈቅሩ መፍጠር ትፈልጋላችሁ - ዘፈን መዝፈን፣ ስዕል መሳል፣ ግጥም መግጠም ያሰኛችኋል:: አንድ ሳንጃ ወድራችሁ፣ አንድ የአቶም ቦምብ ይዛችሁ ፍፁም የማታውቁትን፣ ምንም ያላደረጋችሁን ሰዎች ለመግደል አትገሰግሱም::

ዓለም ከጦርነት ነፃ የምትሆነው ፍቅር ዳግም ወደ ዓለም ስትመለስ ነው:: ፖለቲከኞች ማፍቀር አይፈልጉም፤ ማህበረሰቡ እናንተ እንድታፈቅሩ አይፈልግም፤ ቤተሰብ እንድታፈቅሩ አይፈቅድላችሁም:: ባንፃሩ ሁሉም የፍቅር ኃይላችሁን እንድትቆጣጠሩ ይፈልጋሉ - ምክንያቱም ያላችሁ በቸኛው ሃይል እሱ ነውና፤ ለዛም ነው ፍርሃት የኖረው::

ፍርሃታችሁን በሙሉ ወዲያ አሽቀንጥራችሁ ፍቅራችሁን ጨምሩ - ስታፈቅሩ ደግሞ ያለ ገደብ ይሁን:: ስታፈቅሩ ለሌላኛው ወገን አንድ ነገር እንዳደረጋችሁ አይሰማችሁ፤ የምታደርጉት ለራሳችሁ ነው፤ ብታፈቅሩ የምትጠቀሙት እናንተ ናችሁ:: ስለዚህ አታመንቱ፣ ሌሎች ሲወዱኝ እወዳቸዋለሁ አትበሉ:: ዋናው ነጥብ ይህ አይደለም::





ራሳችሁን የምትወዱ ሁኑ:: ፍቅር ራስ ወዳድ ነው:: ሰዎችን አፍቅሩ - ይህን ካደረጋችሁ ምሉዕ ትሆናላችሁ፣ የተባረካችሁ ትሆናላችሁ::

ፍቅር ጥልቅ ሲሆን ፍርሃት ይጠፋል፣ ፍቅር ብርሃን ነው፣ ፍርሃት ደግሞ ጨለማ::

አሁን ሶስተኛው የፍቅር እርከን ይመጣል - ፀሎት አብያተ- ክርስቲያናት፣ ሃይማኖቶች፣ ድርጅቶች .... ፀሎት እንድታደርጉ ያስተምሩዋችኋል:: ፀሎት ግን የምትማሩት ነገር አይደለም:: በዚህም ፀሎት እንዳታደርጉ እየከለከሉዋችሁ ነው:: ከህፃንነታችሁ ጀምሮ እንዴት መፀለይ እንዳለባችሁ የተማራችሁ ከሆነ አንድ ውብ ነገር አምልጧችኋል ማለት ነው - ፀሎት ሁልጊዜ የሚፈጠር ቀጣይ ክስተት ነውና::

አንድ የምወደውን ታሪክ ልንገራችሁ እወዳለሁ:: ሊዮ ቶልስቶይ የፃፈው አጭር ታሪክ ነው:: በጥንታዊቷ ሩሲያ በአንድ አካባቢ አንድ ሃይቅ ነበር:: በአካባቢው በነበሩ ሶስት ቅዱሳን ሳቢያም ሃይቁ ዝነኛ ለመሆን በቅቶ ነበር:: የከተማው ነዋሪ በሙሉ ወደ አካባቢው መሳብ ጀመረ:: በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ሶስቱን ቅዱሳን ለማየት ወደ ሃይቁ ይተምሙ ያዙ::

በዚህ ክስተት የሃገሪቱ ሊቀ ጳጳስ ፈሩ:: ምንድነው የተፈጠረው? ሲሉ አሰቡ:: እነዚህ "ቅዱሳን" የሚያታወቁ ከመሆናቸው በተጨማሪ በተክርስቲያኒቱ ሹመቱን አልሰጠቻቸውም:: ታድያ ማነው ቅዱስ ያደረጋቸው? ጳጳሳት ይህን ጅል ተግባር ሲፈፅሙ ቆይተዋል - ሹመት መስጠት:: "ይህ ሰው ቅዱስ ነው" በማለት:: ሹመት በመስጠት አንድን ሰው ቅዱስ ማድረግ የሚቻል ይመስል!

ሰው ግን መጉረፉን አላቋረጠም:: ብዙ ተዓምር እየተፈጠረ መሆኑ በሰፊው ተወርቷልና:: ስለዚህም ካህኑ ወደ ስፍራው ለመሄድ ተነሱ:: የሀይቁ አለቃ አንድ ጀልባ ይዘው እነዚያ ሶስት ምስኪኖች ወደሚገኙበት ደሴት አቀኑ:: ሰዎቹ እጅግ ድሆች ቢሆኑም በጣም ደስተኞች ነበሩ - ምክንያቱም ያላቸው አንድ ድህነት ብቻ ነበር:: ድህነት ደግሞ ማፍቀር የሚችል ልብ ነበር:: ድሆች ቢሆኑም ሃብታም ነበሩ - ከማንም የላቁ ሃብታሞች::

ከአንድ የዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠው ይስቃሉ፤ ይደሰታሉ፤ ይቦርቃሉ:: የካህኑን መምጣት ሲመለከቱ ሰጥ ብለው እጅ ነሱ:: "እዚህ ምን ትሰራላችሁ? ታላላቅ ቅዱሳን እንደሆናችሁ ይወራል:: የሆነስ ሆነና እንዴት መፀለይ እንዳለባችሁ

ታውቃላችሁ?" በማለት ቄሱ ጠየቋቸው፡፡ ካህኑ ይህን ጥያቄ ያነሱት ሰዎቹ ያልተማሩና ትንሽ ደነዝ የሆነ ስለመሰሏቸው ነው - ደስተኞች፤ ግን ደግሞ ቂሎች፡፡

ሰዎቹ እርስ በርሳቸው ተያዩና "ይቅርታ ጌታዬ ደንቆሮዎች ስለሆንን የቤተ ክርስቲያኒቱን ፀሎት አናውቀውም፡፡ ነገር ግን የራሳችንን ፀሎት ፈጥረናል . እዚህ የፈጠርነው ፀሎት ነው፡፡ የማይቃወሙት ከሆነ ልናሳይዎት ዝግጁ ነን" አሉ፡፡

"ፀሎታችሁን አሳዩኝ" አሉ ቄሱ፡፡

ሰዎቹም እንዲህ አሉ፡፡ "ብዙ አሰበን ነበር - ነገር ግን ቃላት አሳቢዎች አይደለንም፡፡ እኛ ቂሎች እና መሃይማን ነን፡፡ ስለዚህም አንድ ፀሎት ማድረግ እንዳለብን አሰብን፡፡ በክርስትና እግዚአብሄር ሰላሴ እንደሆነ፤ ሶስት እንደሆነ ነው የሚታመነው - አብ፤ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ፡፡ እኛም ሶስት ነን፡፡ ስለዚህ እንዲህ የሚል ፀሎት ፈጠርን፡፡ <አንተ ሶስት ነህ፤ እኛም ሶስት ነን፤ ምህረትህ በእኛ ላይ ይሁን፡፡>"

ቄሱ ከፉኛ ተቆጡ፤ ተበሳጩ፡፡ "ምን የማይረባ ነገር ነው እንደዚህ አይነት ፀሎት ሰምተን አናውቅም፡፡ ሁለተኛ እንዳትሉት! በዚህ መንገድ ቅዱሳን ልትሆኑ አትችሉም፡፡ ደደቦች ናችሁ!" አሏቸው፡፡

ይሄን ጊዜ ሰዎቹ በቄሱ እግር ስር ተደፍተው "እውነተኛውን ፀሎት ያስተምሩን" አሏቸው፡፡

እናም የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ - ክርስቲያንን ዋና ፀሎት ነገሯቸው፡፡ ፀሎቱ ረዥም፤ ውስብስብ፤ ረጋ ዥምም ቃላት ያሉት እና አስቸጋሪ ነው፡፡ ሶስቱ ሰዎች እርስ በርሳቸው ተያዩ - የማይመስል ነገር፡፡ የመንግስተ ሰማያት በር ለእነሱ የተዘጋ ይመስላል፡፡ "ፀሎቱ ረዥም በመሆኑና እኛም መሃይማን በመሆናችን እባክዎ እንደጌ ይድገሙልን" ሲሉ ጠየቋቸው፡፡ ቄሱም ደግመው ነገሯቸው፡፡

"እባክዎን ጌታዬ፤ አንዴ ይድገሙልን፡፡ እንረሳውና ሌላ ስህተት ልንሰራ እንችላለን አሏቸው ሰዎቹ፡፡ ቄሱ ደገሙላቸው፡፡ ሰዎቹ ከልባቸው አመሰገኗቸው፡፡ ቄሱ እነዚያን ቂል ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን የመለሱ መሰሏቸው ደስ ተሰኙ፡፡





እናም ቄሱ ጀልባቸውን ይዘው መመለስ ጀመሩ፡፡ በሃይቁ መሃል እንደደረሱ ግን አይናቸውን ማመን አቃታቸው - እነዚህ ሶስት ሰዎች፤ እነዚያ ሶስት ጅሎች፤ በውሃ ላይ እየሮጡ ነው! "ይቆዩን ..... አንዴ ይድገሙልን .... ረሳነው!" እያሏቸው ነው፡፡

ፍፁም የማይታመን ነገር! ቄሱ በሰዎቹ እግር ላይ ተደፉና "ይቅር በሉኝ፡፡ ያ የለመዳችሁት ፀሎታችሁን ቀጥሉበት" አሉ፡፡

ሶስተኛው የፍቅር ሃይል ፀሎት ነው፡፡ ሃይማኖቶች ግን አጥፍተውታል፡፡ ለእናንተ የሰጡዋችሁ ሰው ሰራሽ ፀሎቶችን ነው ፀሎት ማቆሚያ የሌለው ስሜት ነው፡፡ ፀሎት ስታደርጉ ይህን ታሪክ አስታውሱ፡፡ ፀሎታችሁ ቀጣይነት ያለው ክስተት ይሁን፡፡ ፀሎታችሁ ቀጣይ ካልሆነ ግን ሊሆን ነው? በእግዚአብሄር ፊት አስመሳይ ከሆናችሁ በማን ፊት እውነተኛ እና የተፈጥሮ ልትሆኑ ነው?

ደስ ያላችሁን ነገር ተናገሩ፡፡ ጓደኞችሁን እንደምታናግሩት ከእግዚአብሄርም ጋር ተነጋገሩ፡፡ ወግ አጥባቂ አትሁኑ፡፡ ወግ ያጠበቀ ግንኙነት ከነቀራሽ ግንኙነት አይደለም፡፡ በእግዚአብሄር ፊት ስርዓት መያዝ ተጣይነታችሁን ያሳጣችኋል፡፡

በፀሎታችሁ ውስጥ ፍቅር ይኑር፡፡ ይሄን ጊዜ ከልባችሁ ለልባችሁ መናገር ትችላላችሁ፡፡ ከዩኒቨርስ ጋር መነጋገር ውብ ነገር ነው፡፡

ግን አስተውላችኋል? ትንሽ ወጣ ያላችሁ ከሆናችሁ ሰዎች እንደ እብድ ይቆጥሩዋችኋል፡፡ ወደ አንድ ዛፍ ጠጋ ብላችሁ ብታናግሩት ሰዎች እብድ ነው፤ ወይም ናት ይሏችኋል፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ ከመስቀል ወይም ከስዕሉ ጋር ብትነጋገሩ ግን እብድ ናችሁ ብሎ የሚያስብ ሰው የለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ሃይማኖተኛ ትባላላችሁ፡፡ ወደ ቤተ መቅደስ ገብታችሁ ከድንጋይ ጋር ስትነጋገሩ የታዘዘው መንገድ ይህ ነውና ሃይማኖተኛ ትባላላችሁ፡፡

ከማንኛውም የድንጋይ ምስል ይበልጥ ህያው ከሆነው የፅጌረዳ አበባ ጋር ከማንኛውም የድንጋይ ምስል ይልቅ መለኮታዊ ከሆነው የጽጌረዳ ብትነጋገሩ፤ ከማንኛውም የድንጋይ ምስል ይልቅ መለኮታዊ ከሆነው የጽጌረዳ አበባ ጋር ብታወሩ .... የትኛውም መስቀል ስር የለውምና ከማንኛውም አበባ ጋር ብታወሩ .... የትኛውም መስቀል ስር የለውምና ከማንኛውም ዛፍ ጋር በትነጋገሩ መስቀል ይልቅ ስሮቹን በእግዚአብሄር ስር ከተተ አንድ ዛፍ ጋር በትነጋገሩ መስቀል ሙት ስለሆነ ነው የሚገድለው ሰዎች እንደ እብድ ይቆጥሩዋችኋል፡፡

.... አንድ ዛፍ ግን ስሮቹን ከመሬት ስር የዘረጋ፣ ከሰማይ ጨረሮች፣ ከከዋክብት ጋር የተገናኘ ህያው ነው። ስለዚህ ከዛፎች ጋር ተነጋገሩ። ይህን ካደረጋችሁ ከመለኮት ጋር ትነጋገራላችሁ።

ይሁን እንጂ በዚህ መንገድ ስትነጋገሩ ከታያችሁ እብድ ትባላላችሁ - ልዩነት (ለየት ማለት) እንደ እብደት ይቆጠራልና። ስርዓት መያዝ እንደ ጤነኛ ተግባር ይታያል። እውነቱ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ወደ ቤተ-መቅደስ ተግባር ይታያል። እውነቱ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው። ወደ ቤተ-መቅደስ ገብታችሁ አንድ አይነት ፀሎት ታነበንባላችሁ። ይህ ሞኝነት ነው። የልብ ገብታችሁ አንድ አይነት ፀሎት ታነበንባላችሁ። ይህ ሞኝነት ነው። የልብ ለልብ ወሬ አውሩ! ይሄን ጊዜ ፀሎታችሁ ውብ ይሆናል፤ እናንተም በውስጡ ማበብ ትጀምራላችሁ።

ፀሎት በፍቅር ውስጥ መሆን ማለት ነው - ከሁሉም ጋር በፍቅር መኖር። አንዳንድ ጊዜ በምሉዑ ትናደዱና መናገር ታቆማላችሁ፤ በጣም ቀንጆ ነው! "አልናገርም በቃ። እስካሁን አላደመጥከኝም!" ትላላችሁ። በጣም ጥሩ አድርጋችኋል። አንዳንድ ጊዜ ፀልያችሁ፡ ፀልያችሁ እምላክ ፀሎታችሁን እልሰማ ሲላችሁ ፀሎታችሁን እርግፍ አድርጋችሁ ትተውታላችሁ። በውስጡ ስለተመሰጣችሁ ነው የምትበሳጩት አንዳንድ ጊዜ በጣም ጥሩ፡ መልካም የሆነ ስሜት ይሰማችኋል። ሌላ ጊዜ ደግሞ የተገለላችሁ ይመስላችኋል። ግንኙነታችሁን ግን ህያው አድርጉት። ይሄን ጊዜ ፀሎታችሁ እውነተኛ ይሆናል። ልክ እንደ ድምፅ ማጉያ ሁልጊዜ አንድ ነገር የምትደጋግሙ ከሆነ ይህ ፀሎት አይደለም።

በጣም አገናዛቢ ስለሆነ አንድ ጠቢቃ ታሪክ ሰምቼ ነበር። ሁልጊዜ ምሽት ላይ ወደ አልጋው ይሄድና ወደ ሰማይ ቀና ብሎ "እንደሁልጊዜው" በማለት ፀልዮ እንቅልፉን ይለጥጣል። በህይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲሁ ቢፀልይም ይህንኑ ቃል ነው የሚደግመው። ልክ በህግ የተደነገገ ነገር ይመስላል። አንድን ፀሎት መደጋገሙ ጥቅሙ ምንድነው? እንደሁልጊዜውም አላችሁ ምን፣ ያው አንድ አይነት ነው።

ፀሎት ህያው ልምድ፣ የልብ ለልብ ንግግር መሆን አለበት። ፀሎቱ ከልባችሁ ከሆነ፣ እየተናገራችሁ እንደሆነ በቻ አይደለም ምላሽ እያገኛችሁ እንደሆነም ይሰማችኋል። ፀሎታችሁ ይጉለምሳል። ፀሎታችሁ ምላሽ እንዳገኘ ከተሰማችሁ ንግግሩ የሁለትዮሽ ሆኗል ማለት ነው። ብቻችሁን የምታወሩ



ከመሰላችሁ ግን እሱ ፀሎት አይደለም። ማነብነብ ብቻ ሳይሆን ማድመጥም አለባችሁ።

ምሉዑ ህያውነት ምላሽ ሊሰጣችሁ ዝግጁ እንደሆነ እነግራችኋለሁ። ልባችሁ ክፍት ከሆነ ምላሽ ታገኛላችሁ።

እንደ ፀሎት ያለ ምንም የለም። የትኛውም ፍቅር እንደፀሎት ሊሆን አይችልም፤ የትኛውም ወሲብ እንደ ፍቅር ውብ ያለመሆኑን ያህል የትኛውም ፍቅርም እንደ ፀሎት ውብ አይደለም።

ተመስጥዖ የሚባል አራተኛ ደረጃ አለ። እዚህ ንግግር ሁሉ ይቆማል። በፀጥታ ነው የምትነጋገሩት። ልብ ሙሉ ሲሆን መናገር አትችሉምና ታላቅ ይጠፋሉ። ልብ መምጠት የምትችለው በፀጥታ ውስጥ ብቻ ነው። "ሌላ" ምንም ስፍራ የላትም። ከዓለም ጋር ያላችሁ እናንተ ናችሁ። አትናገሩምም፣ አታዳምጡምም። ከዓለም ጋር፣ ከምሉዑ ጋር ያላችሁ እናንተ ናችሁ። አንድነት ተመስጦ ማለት ይህ ነው።

እነዚህ ናቸው አራቱ የፍቅር እርከኖች። በእነዚህ እርከኖች በሙሉ ፍርሃት ይጠፋል። ወሲብ በመልካም ሁኔታ ከተፈፀመ አካላዊ ፍርሃት ይጠፋል። በሺ የሚቆጠሩ አካላት እርካታ ስላላገኙ ሲረበሹ አካል አይረበሽም። ይቻለሁ።

ፍቅር ካ ፍርሃት ከአዕምሮ ይጠፋል። ውስጥም ይደሰታል። ነፃ ሀይወት ይኖራችኋል። ምንም አይነት ፍርሃትም ሆነ ቅዥት አይመጣም።

በፀሎት ጊዜ አንድ ትሆናላችሁ፣ ከምሉዕነት ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዳላችሁ ይሰማችኋልና ፀሎት ሲኖር ፍርሃት ድራሹ ይጠፋል፤ ፍርሃት ከመንፈስ ይጠፋል። ስትፀልዩ በፊት ለሞት የነበራችሁ ፍራቻ ይሰወራል።

ስትመስጡ ፍርሃት አልባነት ራሱ ይጠፋል። ፍርሃት ይጠፋል፤ ፍርሃት አልባነት ይጠፋል። ምንም አይቀርም፤ ወይም ምንም ይቀራል። ሰፊ የተንጣለለ ንፁህነት፣ የጥሀንት ያልተነካ ግንነት ይቀራል።



ትርጉም፡ ሀብታሙ ተስፋዬ

# ፍቅር ግንኙነት ሳይሆን የመሆን ሁኔታ ነው

ፍቅር ግንኙነት ሳይሆን የመሆን ሁኔታ ነው፣ ከማንም ጋር ግንኙነት የለውም፡፡ አንድ ሰው ፍቅር ውስጥ ነው ወይም አፍቅሯል ሳይሆን የሚባለው ‹እገሌ ፍቅር ነው› ነው የሚባው፡፡ በእርግጥ አንድ ሰው ፍቅር ሲሆን በፍቅር ውስጥ ነው ያለው - ነገር ግን ይህ ምርጫ ሳይሆን ውጤት ነው፡፡ ምንጩ ፍቅር መሆኑ ነው፡፡

ማን ፍቅር ሊሆን ይችላልን? ማን እንደሆኛችሁ የማታውቁ ከሆነማ ፍቅር ልትሆኑ አትችሉም፡፡ ይልቁኑ ፍርሃት ትሆናላችሁ፡፡ ፍርሃት የፍቅር ተቃራኒ ነው፡፡ ሰዎች እንደሚያስቡት የፍቅር ተቃራኒ ጥላቻ አይደለም፡፡ ጥላቻ የፍቅር ተቃራኒ ሳይሆን ፍቅር ተገልብጦ ሲቆም ነው፡፡ እውነተኛ የፍቅር ተቃራኒ ፍርሃት ነው፡፡ ፍቅር ያሰፋል፣ ፍርሃት ያጠብባል፡፡ ፍርሃት ይዘጋል፡፡ ፍቅር ይከፍታል፡፡ ፍርሃት ያጠራጥራል፣ ፍቅር ያሳምናል፡፡ ፍርሃት ብቸኛ ያደርጋል፡፡ ብቸኛ ከማድረግም አልፎ ያጠፋል፡፡ የሌለ ሰው እንዴት ብቸኛ ይሆናል? እነዚህ ዛፎች፣ አዕዋፋት፣ ደመናዎች፣ ፀሃይ፣ ከዋክብት በሙሉ እናንተ ውስጥ ናቸው፡፡ ፍቅር ማለት ውስጣዊ ቁልፋችሁን ስታውቁ ነው፡፡

ማንም ህፃን ከፍርሃት ነፃ ነው፣ ህፃናት የሚወለዱት ያለምንም ፍርሃት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ፍርሃት አልባ እንዲሆኑ ቢረዳቸውና ቢደግፋቸው ዛፎችና ተራሮች ላይ እንዲንጠለጠሉ፣ ውቅያኖሶችንና ወንዞችን እንዲያቋርጡ በረዳቸው ነበር፡፡ ማህበረሰቡ ጀብደኛ እንዲሆኑ፣ ካረጀ እምነት ይልቅ የማይታወቀውን እንዲመረምሩ ቢያደርጋቸው ኖሮ፣ ታላላቅ የህይወት አፍቃሪዎች ባደረጋቸው ነበር፡፡ ይህ ነው እውነተኛ ሃይማኖት፡፡ ከፍቅር በላይ ሃይማኖት የለም፡፡

ተመሰጡ፣ ደንሱ፣ ዝፈኑ፣ ወደ ውስጣችሁ ጠልቀችሁ ግቡ፡፡ የአዕዋፋቱን ዝማሬ በእንክሮ አድምጡ፡፡ አበቦቹን በአድናቆት ተመልከቱ፡፡ አዋቂ አትሁኑ፣ ነገሮችን አትፈርጁ አዋቂ መሆን ማለት ይህ ነው - ለእያንዳንዱ ነገር መደብ፣ ፈርጅ ማውጣት፡፡ ከሰዎች ጋር ተገናኙ፣ ከሰዎች ጋር ተቀላቀሉ፣ በተቻላችሁ መጠን ከብዙ ሰዎች ጋር ተገናኙ፡፡ እያንዳንዱ ሰው በተለያየ ሁኔታ የእግዚአብሄርን መልክ ያሳያል፡፡ ከሰዎች ተማሩ፡፡ አትፍሩ፡፡





ይህ ህይወት ጠላታችሁ አይደለም፡፡ ይህ ህልውና ይንከባከባችኋል፣ በማንኛውም መንገድ ይረዳችኋል፡፡ እመኑ - ስታምኑ አንድ ሃይል በውስጣችሁ ሲተጣጠል ይሰማችኋል፡፡ ያ ሃይል ፍቅር ነው፡፡ ያ ሃይል መልካም ስሜት የሚያጐናፅፍ ነውና መላውን ዓለም መሙላት ይፈልጋል፡፡ የተባረካችሁ እንደሆናችሁ ከተሰማችሁ መላውን ህልውና ከመባረክ ሌላ ምን ለማድረግ ታስባላችሁ?

ፍቅር መላውን ህይወት የመቀደስ ጥልቅ ፍላጐት አለው፡፡

ይህ ኬክ እንዴት ያለ ጣፋጭ ነው!

ፍቅር በብዛት የሚገኝ አይደለም፡፡ እንድን ሰው በማዕከሉ (በዋናው ፍሬ ነገሩ) ማግኘት በአንድ አብዮት ውስጥ እንደማለፍ ነው፣ ምክንያቱም አንድን ሰው በማዕከሉ ውስጥ ለማግኘት ሰውየው በእናንተ ማዕከል ውስጥ እንዲያልፍ መፍቀድ ይኖርባችኋል፡፡ መጋለጥ፣ ፍፁም መጋለጥ፣ ግልፅ መሆን ይኖርባችኋል፡፡

ሆኖም አደጋ አለው፡፡ አንድን ሰው በማዕከላዊያችሁ ውስጥ እንዲያልፍ መፍቀድ ሰውየው ምን እንደሚያደርጋችሁ አይታወቅምና አደጋ አለው፡፡ አንዴ ሚስጥሮቻችሁ ሁሉ ከታወቁ፣ የደበቃችሁት ነገር ሁሉ ይፋ ከወጣ፣ ሙሉ ለሙሉ የተጋለጠ ከሆናችሁ ሌላኛው ሰው ምን ሊያደርጋችሁ እንደሚችል ፍፁም አይታወቅም፡፡ በዚህም ፍርሃት እዚያ ስላለ ግልፅ አንሆንም፡፡

በመርካታችን ብቻ ፍቅር እንደተከሰተ እናስባለን፡፡ ዳርቻዎቻችን ሲገናኙ እኛ የተገናኘን ይመስለናል፡፡ ግን አይደለም፡፡ እናንተ ዳርቻችሁ አይደላችሁም፡፡ ዳርቻችሁ እናንተ የምትጨርሱበት ወሰን፣ እናንተን የከበባችሁ አጥር ነው፡፡ እናንተ አይደላችሁም! ዳርቻችሁን እናንተ የምትጨርሱበትና ዓለም የሚጀምርበት ነው፡፡

ለብዙ ዓመታት አብረው የኖሩ ባልና ሚስት እንኳን በእርካታ ብቻ የሚኖሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ምናልባት እርስ በርስ ላይተዋወቁ ይችላሉ፡፡ ከአንድ ሰው ጋር ብዙ ሲኖሩ ማዕከላቸው እንደሌለ ታወቀ ይዘንጋሉ፡፡

ስለዚህ ትውውቅን ከፍቅር ጋር አንድ አድርጋችሁ አትውሰዱት፡፡ ፍቅር ልትሰሩ፣ በወሲብ ልትገናኙ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ወሲብ ራሱ ጠርዝ ነው፡፡

ማዕከላት ካልተገናኙ ወሲብ የአካላት ግንኙነት ብቻ ይሆናል፡፡ የአካላት ግንኙነት ደግሞ የእናንተ ግንኙነት ነው ማለት አይደለም፡፡ ወሲብም አካላዊ መላመድ ነው - መላመድ ብቻ፡፡ ፍርሃት ከሌለባችሁ፣ ፈሪ ካልሆናችሁ ብቻ ነው አንድ ሰው ወደማዕከላችሁ እንዲገባ መፍቀድ የምትችሉት፡፡

ሁለት አይነት ኑሮዎች አሉ፡፡ አንደኛው በፍርሃት የሚመራ ሲሆን፣ ሁለተኛው በፍቅር የሚመራ ነው፡፡ ፍርሃት መር የሆነ ኑሮ ወደ ጥልቅ ግንኙነት አይመራችሁም፡፡ ፈሪ ስለምትሆኑ ሌላኛው ወገን ወደ ማዕከላችሁ ሰርስሮ መግባት አይችልም፡፡ በተወሰነ ደረጃ ታስገቡትና ግድግዳው መጥቶ ሲጋርደው ሁሉም ነገር ይቆማል፡፡

በፍቅር የሚመራ ሰው የወደፊቱን የማይፈራ፣ ውጤቱ ወይም ተከትሎት የሚመጣው ነገር የማያስፈራው፣ እዚህና አሁን የሚኖር ነው፡፡ ውጤቱ አያስጨንቃችሁ፣ ይህን የሚያስብ በፍርሃት የሚመራ አዕምሮ ነው፡፡ የሚከሰተው ነገር አያሳስባችሁ፡፡ ሙሉ በሙሉ እዚህ ሁኑ፡፡ አታስሉ፡፡ በፍርሃት የሚመራ ሰው ግን ሁልጊዜ ያሰላል፣ ያቅዳል፣ ያመቻቻል፣ አስቀድሞ መከላከያ ያበጃል፡፡ መላ ህይወቱ በዚህ መንገድ ይባክናል፡፡

ስለ አንድ ሽማግሌ የዜን መነኩሴ የሰማሁት ታሪክ አለ፡፡

የመነኩሴው መሞቻ ቀን ተቃርቧል፡፡ የመጨረሻዋ ዕለት መጥታለች፡፡ የዛን ዕለት ምሽት እንደሚሞቱ ይፋ አደረጉ፡፡ ስለዚህም ተከታዮቻቸው፣ ደቀመዛሙርቶቻቸው፣ ወዳጆቻቸው መጉረፍ ጀመሩ፡፡ የሚወዷቸው ሁሉ ከዚያም፣ ከዚህም መጥተው ተሰበሰቡ፡፡

ከጥንት ደቀ-መዛሙርቶቻቸው አንዲ አለቃቸው ሊሞቱ እንደሆነ ሲሰሙ ወደ ገበያ ገሰገሱ፡፡ አንድ ሰው መንገድ ላይ አግኝቶ "አለቃችን በጉጂቸው ውስጥ ሊሞቱ ነው፡፡ እርስዎ ወደ ገበያ የሚሄዱት ለምንድነው?" ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡

ሽማግሌው መነኩሴም "አለቃዬ አንድ የሚወዱት ኬክ አለ፡፡ እሱን ልገዛላቸው ነው" ሲሉ መለሱለት፡፡

ኬኩን ማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም እንደምንም ምሽቱን አገኙና ወደ ጉጆው ይዘው ገሰገሱ፡፡





ሁሉም ስጋት አድሮባቸዋል - ሽማግሌው አለቃ አንድ ነገር የሚጠባበቁ ይመስላሉ፡፡ ደቀ-መዛሙራቸው እንደደረሱ "እሺ፣ መጣህ፡፡ ኬኩ የታለ?" አሏቸው፡፡ ደቀ-መዝሙሩ አለቃቸው ስለ ኬኩ በመጠየቃቸው ደስ እያላቸው አውጥተው ሰጧቸው፡፡

በሞት አፋፍ ላይ የሚገኙት አለቃ ኬኩን በእጃቸው ተቀበሉ፣ እጆቻቸው ግን እየተንቀጠቀጡ አልነበረም፡፡ እድሜያቸው በጣም የገፋ ቢሆንም እጆቻቸው አልተንቀጠቀጡም፡፡ ከተሰበሰቡት መሃል አንዱ፣ "ሽማግሌ ከመሆንዎ በተጨማሪ በሞት አፋፍ ላይ ነዎት፡፡ የመጨረሻ ትንፋሽዎ ሊወጣ ነው፡፡ ግን እጅዎ አይንቀጠቀጥም" አላቸው፡፡

"ስለማልፈራ አልንቀጠቀጥም" አሉ መነኩሴው፡፡ "አካሌ ቢያረጅም እኔ ወጣት ነኝ፡፡ አካሌ ቢሞት እንኳን ወጣትነቱ አብሮኝ ይኖራል፡፡"

ከዚያም ከኬኩ ገመጡለት፡፡ "የመጨረሻ መልዕክትዎ ምንድነው? አሁን ይለዩናል፡፡ ምን ይመክሩናል?" አላቸው አንዱ፡፡

መነኩሴው ፈገግ አሉና "ይህ ኬክ እንዴት ያለ ጣፋጭ ነው!" አሉ፡፡

እዚህና አሁን የሚኖሩ እንዲህ ያሉ ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ ኬክ እንዴት ያለ ጣፋጭ ነው! ሞት እንኳን አልረበሻቸውም፡፡ የሚቀጥለው ቅፅበት ትርጉም የሌለው ነው፡፡ ይህቺ ቅፅበት፣ ይህ ኬክ እንዴት ያለ ጣፋጭ ነው! በዚህ ቅፅበት፣ አሁን ባው ቅፅበት ውስጥ መሆን ከቻላችሁ ብቻ ነው ማፍቀር የምትችሉት፡፡

ፍቅር እምብዛም የማይገኝ አበባ ነው፡፡ ብቅ የሚለው አንዳንድ ጊዜ ነው፡፡ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች አፈቀርን ብለው የውሸት ኑሮ ይኖራሉ፡፡ እንደሚያፈቅሩ ያምናሉ፡፡ ከእምነት የዘለለ ግን አይደለም፡፡

ፍቅር ብርቅዬ አበባ ነው፡፡ ብቅ የሚለው አልፎ አልፎ ነው፡፡ የሚከሰተው ፍርሃት ሳይኖር ሲቀር ነው፡፡ ይህም ማለት ፍቅር የሚከሰተው በጣም መንፈሳዊ ሃይማኖተኛ ለሆነ ሰው ነው፡፡ ሁሉም ወሲብን፣ መላመድን ሊያገኝ ይችላሉ፡፡ ፍቅርን ግን ሁሉም አያገኙትም፡፡

ካልፈራችሁ፣ የምትደብቁት ነገር ከሌለ፣ ግልፅ ልትሆኑና ድንበሮቹን ሁሉ ልትጥሱ ትችላላችሁ፡፡ ያን ጊዜ ሌሎቹን ወደ ውስጣችሁ ማስገባት ትችላላችሁ፡፡

ሌሎች ወደ ውስጣችሁ እንዲገቡ ስትፈቅዱ እነሱም በተራቸው ወደ ውስጣቸው እንድትገቡ ይፈቅዱላችኋል፡፡ ሌሎችን ወደ እናንተ እንዲገቡ ስትፈቅዱ እምነት ይፈጠራል፡፡ እናንተ መፍራት ስታቆሙ ሊላኛው ወገንም አይፈራም፡፡

በፍቅራችሁ ውስጥ ሁልጊዜም ፍርሃት ይኖራል፡፡ ባል ሚስቱን፣ ሚስት ባሏን ይፈራሉ፡፡ ፍቅረኞች ሁልጊዜ ይፈራሉ፡፡ ይህ ፍቅር አይደለም፡፡ ይህ የሁለት ፈሪ ሰዎች ትግል፣ ሽሚያ፣ ቁጥጥር ሜና፣ ይዞታ ሊሆን ይችላል - ፍቅር ግን አይደለም፡፡

ፍቅር እንዲመጣ የምትፈቅዱ ከሆነ ፀሎት፣ ተመስጦ፣ ቤተክርስቲያን፣ ቤተመቅደስ አያስፈልጉም፡፡ ማፍቀር ከቻላችሁ እግዚአብሄርን ሙሉ በሙሉ ልትረሱት ትችላላችሁ - ምክንያቱም በፍቅር ሁሉም ነገር ይሆንላችኋል፡ ተመስጦ፣ ፀሎት፣ እግዚአብሄር ሁሉም ነገር፡፡

ይሁን እንጂ ፍቅር አስቸጋሪ ነው - ፍርሃት መወገድ አለበትና፡፡ መፍራታችሁ እና የምታጡት ነገር አለመኖሩ የሚገርም ነገር ነው፡፡

ረቂቁ ካቢር እንዲህ ይላል፡- "ሰዎችን ተመለከትኳቸው ... በጣም ፈሪዎች ናቸው፡፡ ግን ለምን እንደሚፈሩ አላወቅኩም- ምክንያቱም ምንም የሚያጡት ነገር የለም፡፡ ራቁቱን ሆኖ ገላውን ለመታጠብ ወደ ወንዝ መውረድ እንደሚፈራ ሰው ናቸው - ልብሶቼን የት አደርጋቸው ይሆን? በማለት እንደሚፈራ ሰው፡፡"

እናንተ ያላችሁበት ሁኔታም ይህን የማመስል ነው - እርቃናችሁን፣ ምንም ልብስ ሳትደርቡ ግን ስለ ልብሳችሁ ትጨነቃላችሁ፡፡

ምን የምታጡት ነገር አለ? ምንም፡፡ ይህ ገላችሁ በሞት ይወሰዳል፡፡ በሞት ከመወሰዱ በፊት ግን ፍቅር ስጡት፡፡ ያላችሁ ነገር በሙሉ ይወሰዳል፡፡ ታዲያ ከመወሰዱ በፊት ለምን አታካፍሉትም? የራስ የማድረግ ብቸኛው መንገድ ይህ ነው፡፡ ማካፈል እና መስጠት ከቻላችሁ ታላት ናችሁ፡፡





እስከዘላለሙ ልታቆዩት የምትችሉት ምንም ነገር የለም. ሁሉም ነገር ይወሰዳል፡፡ ሞት ሁሉንም ነገር ያጠፋዋል፡፡

በትክክል እየተከታተላችሁኝ ከሆነ፣ ትግሉ በሞትና በፍቅር መካከል መሆኑን ትገነዘባላችሁ፡፡ ከሰጣችሁ ሞት የለም፡፡ ሁሉንም ነገር ከመጠቃችሁ በፊት አስቀድማችሁ ብትሰጡ ሞት የሚባል አይኖርም፡፡

**ይህ ገላችሁ በሞት ይወሰዳል፡፡ በሞት ከመወሰዱ በፊት ግን ፍቅር ስጡት፡፡ ያላችሁ ነገር በሙሉ ይወሰዳል፡፡ ታዲያ ከመወሰዱ በፊት ለምን አታካፍሉትም? ከሰጣችሁ ሞት የለም፡፡ ሁሉንም ነገር ከመነጠቃችሁ በፊት አስቀድማችሁ ብትሰጡ ሞት የሚባል አይኖርም፡፡**

አፍቃሪ ሞት አያውቅም፡፡ ያላፈቀረ ግን በእያንዳንዱ ቅፅበት ይሞታል- ምክንያቱም በእያንዳንዱ ቅፅበት አንድ ነገር ይነጠቃልና፡፡ በእያንዳንዱ ቅፅበት አካሉን ያጣል፣ ምትም ይኖራል፤ ሁሉም ነገር ይጠፋል፡፡

ፍርሃትን ምን አመጣው? ለምን ትፈራላችሁ? ምንም እንኳን ስለ እናንተ ሁሉሙ ነገር የማታውቅ ቢሆንም፣ እናንተም እንደ ክፍት መፅሃፍ ብትሆኑም ለምን ትፈራላችሁ? ለምን በፍርሃት ትኑዳላችሁ? ማህበረሰቡ ራሳችሁን መደበቅ፣ መከላከል እንዳለባችሁ፣ ሁልጊዜ ታጋይ እንድትሆኑ፣ ሁሉም ሰው ጠላታችሁ፣ ባላንጣችሁ እንደሆነ የመከራችሁ ሁሉ የተሳሳተ ነው፡፡

ማንም ጠላታችሁ አይደለም! አንድ ሰው ባላንጣችሁ እንደሆነ ብታስቡም እንኳን እርሱ ጠላታችሁ አይደለም፣ ምክንያቱም ሁሉም ሰው ስለራሱ እንጂ ስለ እናንተ አይጨነቅም፡፡ ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም፡፡ እውነተኛ ግንኙነት ከመፈጠሩ በፊት ይህ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት - ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም፡፡

ተመሰጡበት፡፡ ከዚያም ሊላኛው ወደ ውስጣችሁ እንዲገባ አድርጉ፤ ጋብዙት፡፡ የትም ቦታ መሰናክል አትፍጠሩ፤ እንደ መንገድ ክፍት ሁኑ፡፡ ቁልፍ፣ በር፣ የተዘጋ በር አይኑራችሁ፡፡ እንዲህ ከደረጋችሁ ፍቅር ይኖራል፡፡

ሁለት ማዕከላት ሲገናኙ ፍቅር ይኖራል፡፡ ልክ ሃይድሮጅን እና ኦክስጂን ተዋህደው ውሃን እንደሚፈጥሩ፣ ፍቅርም እንድ የአልኬሚካል ክስተት ነው፡፡ ሃይድሮጅን እና ኦክስጂን ሊኖራችሁ ይችላል፡፡ የእነዚህ መኖር ግን ጥማችሁን አይቆርጥላችሁም፡፡ የፈለገ ያህል ኦክስጂን፣ የፈለገ ያህል ሃይድሮጅን ቢኖራችሁም ጥማችሁ አይረካም፡፡

ሁለት ማዕከላት ሲገናኙ አዲስ ነገር ይፈጠራል፡፡ ይህ አዲስ ነገር ፍቅር ነው፡፡ እሱም ልክ እንደ ውሃ ነው - የብዙዎችን ጥም የሚያረካ፡፡ ወዲያውኑ ትረካላችሁ፡፡ ይህ የፍቅር ምልክት ነው፤ ሁሉንም ነገር ያገኛችሁ ያህል ትረካላችሁ፡፡ አሁን የቀረ ነገር የለም፤ ከግባችሁ ደርሳችኋል፡፡ ሌላ ግብ የለም፡፡ መዳረሻችሁ ተሟልቷል፤ ዘሩ አበባ ሆኗል፤ አብቧል፡፡ ጥልቅ እርካታ የማታይ የፍቅር ምልክት ነው፡፡ አንድ ሰው ፍቅር ሲይዘው በሃይል ይረካል፡፡ ፍቅር የማይታይ ቢሆንም እርካታው፣ በዙሪያው የሚገኘው ፍሰት ... ትንፋሹ፣ እንቅስቃሴው፣ ማንነቱ፤ ሁሉቱ ይታያሉ፡፡

ፍቅር ፍላጐት አልባ እንደሚያደርግ ስነግራችሁ ልትገረሙ ትችሉ ይሆናል፡፡ ፍላጐት የሚመጣው ካለመርካት ነው፡፡ ስለሌላችሁ ነው የምትፈልጉት፡፡ የምትፈልጉት ያን ነገር ብታገኙት እንደምትረኩ ስለምታስቡ ነው፡፡ ፍላጐት ካለመርካት የሚመጣ ነው፡፡

ፍቅር ሲኖርና ሁለቱ ማዕከላት ተዋህደው አንድ ሲሆኑ አንድ አዲስ የአልኬሚካል ባህርይ ይፈጠራል - እርካታ፡፡ መላው ህልውና የቆ ይመስላል - የማይንቀሳቀስ፡፡ ያለው ጊዜ አሁን ብቻ ነው፡፡ ያኔን ጊዜ፣ "ይህ ልክ እንዴት ያለ ጣፋጭ ነው!" ትላላችሁ፡፡ በፍቅር ላለ ሰው ሞት ምንም ማለት አይደለም፡፡







# ወሰን አልባ ዓለም

## የሚያበስላችሁ የፍቅር እሳት ብቻ ነው

ፍቅር ወሰን ወደሌለው፣ መዳረሻ ወደሌለው ዓለም የሚያስገባ በር ነው፡፡ ፍቅር መጀመያ እንጂ መዳረሻ የለውም፣ ይጀምራል እንጂ አያበቃም፡፡

አንድ ነገር አስታውሱ፣ አእምሮ ጣልቃ እየገባ ፍቅር ወሰን አልባ እንዳይሆን፣ ስፍራውን እንዳይጠቀም እንቅፋት ይሆንበታል፡፡ ማንነታችሁ የፍቅር ማደጊያ፣ መብቀያ ስፍራ ነው፡፡ አዕምሮ ሰውየውን ሲቆጣጠረው ፍቅር ይጠፋል፡፡ አእምሮ ስግብግብ ነው፤ አእምሮ መርዘኛ ነው፡፡ ወደ ፍቅር መግባት የፈለገ ሰው አእምሮውን ሊተው ይገባዋል፡፡ አንድ ሰው የለ አእምሮ ጣልቃ ገብነት ሊኖር ይገባዋል፡፡ አእምሮ በቦታው ጥሩ ነው፡፡ በገበያ ውስጥ ቡፈለግም በፍቅር አይፈለግም፡፡ ገንዘብ ለማካበት ልትፈልጉት ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ወደ ውስጣችሁ ስትገቡ አትፈልጉትም፡፡ የሂሳብ ስሌት ሲኖር አዕምሮ ያስፈልጋል፤ ተመስጦ ሲፈለግ ግን አያስፈልግም፡፡ ስለዚህ አዕምሮ ለውጪኛው ዓለም መጠቀሚያ፣ መገልገያ ነው፡፡ የውስጠኛው አይፈልገውም፡፡ እናም የበለጠ አፍቃሪ ሁኑ .... ያለ ቅድመ - ሁኔታ የመታፈቅሩ፣ ፍቅር ሁኑ፡፡ በር ሁኑ - አፍቃሪ ሁኑ፡፡

አዕዋፋትና ዛፎች፣ መሬት እና ከዋክብት፣ ወንዶችና ሴቶች ... ሁሉም ይህ ይገባቸዋል፡፡ ጥቂርና ነጭ፣ መላው ዩኒቨርስ የሚግባባበት አንድ ቋንቋ አለ - ፍቅር፡፡ ስለዚህም ይህን ቋንቋ ሁኑ፡፡ እንዴ ፍቅር ከሆናችሁ ወሰን የሌለው አንድ አዲስ ዓለም ይከፈትላችኋል፡፡

አእምሮ ሰዎች ዘግ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነገር ነው፡፡ አእምሮ በፍርሃት የሚኖር ስለሆነ ክፍትነትን (ግልፅነትን) ይፈራል፡፡ ሰው ፍርሃትን የማይፈራ በሆነ ቁጥር በአእምሮ መጠቀሙን ይቀንሳል፡፡ የበለጠ ፈሪ ሲሆን አእምሮውን በይበልጥ ይጠቀማል፡፡

ስትፈሩ፣ አንድ ነገር ሲያስጨንቃችሁ፣ ሲረብሻችሁ አእምሮአችሁን ስራ እንደሚበዛበት አስተውላችሁ ይሆናል፡፡ አንድ ነገር ሲያስጨንቃችሁ

እእምሮአችሁ በሃይል ይሰራል፡፡ ሳትጨነቁ ስትተሩ ግን እእምሮአችሁ ሰፊ ይፈታል፡፡

**ሰው ፍርሃትን የማይፈራ በሆነ ቁጥር በእእምሮ መቀሙን ይቀንሳል፡፡ የበለጠ ፈሪ ሲሆን እእምሮውን በይበልጥ ይጠቀማል፡፡**

ሁሉም ነገር መልካም ሲሆን፣ ፍርሃት ሲጠፋ፣ እእምሮ ወደኋላ ይቀራል፡፡ ነገሮች ሲበላሹ እእምሮ ከፊት ይቀድምና መሪ ይሆናል፡፡ በአደጋ ጊዜ መሪ ይሆናል፡፡ እእምሮ ልክ እንደ ፖለቲከኞች ነው፡፡ አዶልፍ ሂትለር "ማይን ካምፕ" በተባለው ግለ-ታሪኩ ላይ እንደገለፀው፣ መሪ ሆኖ ለመቆየት ሃገሪቱን በፍርሃት መያዝ ያስፈልጋል፡፡ የጎረቤት ሃገራት ጥቃት ሊፈፅሙ እንደሆነ፣ ጥቃት ሊፈፅሙ ያቀዱ ሃገራት እንዳሉ በመናገር ህዝቡ እንዲፈራ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሰዎቹ ዘና እንዲሉ አታድርጓቸው፣ ምክንያቱም ሲረጋጉ ስለ ፖለቲከኞቻቸው አይጨነቁም፡፡ ሰዎች ሲመቻቸው ፖለቲከኞች ይረሳሉ፡፡ ፖለቲከኛው ሃይለኛ እንዲሆን ህዝቡ ሁልጊዜ ፈሪ ሊሆን ይገባል፡፡

ጦርነት ሲኖር ፖለቲከኞች ታላላቅ ሰዎች ይሆናሉ፡፡ ቸርችል፣ ሂትለር፣ ስታሊን፣ ማኦ .... እነዚህ ሁሉ የጦርነት ውጤቶች ናቸው፡፡ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ባይኖር ኖሮ ዊንስተን ቸርችል፣ ሂትለር እና ስታሊን አይኖሩም ነበር፡፡ ጦርነት ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤ ሰዎች ጨቋኝ እና መሪዎች እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ የእእምሮ ሰላምም ተመሳሳይ ነው፡፡

ተመስጦ ምንም ሳይሆን የእእምሮን ሚና ለማሳነስ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡ ስትመሰጡ አትፈሩም፣ በጣም እፍታሪ፣ በጣም ሰላማዊ ትሆናላችሁ፣ በሚከሰተው ነገር ሁሉ ትረካላችሁ፡፡ እእምሮ የሚሰው ይጠፋዋል፡፡ ይበልጥ ስትመሰጡ እእምሮ እጅግ ወደኋላ ይቀራል፡፡

አንድ ቀን እእምሮአችሁ ሙሉ በሙሉ ወደኋላ ይቀርና እናንተ መላውን ዓለም ትሆናላችሁ፡፡ በሰውነታችሁ፣ በምንም ነገር ውሱን አትሆኑም፣ ንፁህ ስፍራ ትሆናላችሁ፡፡ ይህ ነው እግዚአብሄር፡፡ እግዚአብሄር ንፁህ ስፍራ ነው፡፡

ፍቅር ወደ ንፁህ ስፍራ የሚወስድ መንገድ ነው፡፡ ፍቅር መንገድ ሲሆን እግዚአብሄር መድረሻ ነው፡፡





**ተመስጦ ምንም ሳይሆን የእእምሮን ሚና ለማሳነስ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡**

ፍርሃት ያለባቸው ሰዎች ከፍተኛ የፍቅር አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ ፍርሃት የፍቅር አሉታዊ ጎን ነው፡፡ ፍቅር እንዳይንሸራሸር ከተከለከለ ፍርሃት ይሆናል፤ ፍቅር እንዲተላለፍ ከተፈቀደለት ፍርሃት ይጠፋል፡፡ ለዛም ነው ፍቅር ሲኖር ፍርሃት የሚጠፋው፡፡ እንድን ሰው ስታፈቅሩ ወዲያው ፍርሃታችሁ ይጠፋል፡፡ እፍቃሪዎች የማይፈሩ ብቸኛ ሰዎች ናቸው፤ ሞት እንኳ ቢሆን ችግር አይፈጥርባቸውም፡፡ ፍቅረኞች በፀጥታ እና ሳይፈሩ የሚሞቱ ብቸኛ ሰዎች ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ የበለጠ ባፈቀራችሁ ቁጥር የበለጠ ፍርሃት ይሰማችኋል፡፡ ሴቶች የበለጠ የፍቅር አቅም ስላላቸው ከወንዶች ይልቅ የበለጠ ፍርሃት ይሰማቸዋል፡፡ በዚህች ዓለም ፍቅርን የምትወጡበት አጋጣሚ እጅግ እናሳ በመሆኑ ከእናንተ ጋር እንዳለ ይኖራል፡፡ እቅም ሲከማች በተግራሪ እትጣጣ ይሆራል፡፡ ትናት ሊሆን ይችላል፤ የእእንት ስሜት ሊፈጠር ይችላል፤ ይህም የፍርሃት አካል ነው፡፡ ጥላቻም ሊሆን ይችላል፤ ይህም የፍርሃት አካል ነው፡፡ ስለዚህ የበለጠ እፍቃሪ ሁኑ፡፡ ያለምንም ገደብ እፍቅሩ፤ በተቻላችሁ መጠን በብዙ መንገድ እፍቅሩ እንድ ሰው በሚሊየን መንገዶች ማፍቀር ይችላልና፡፡

አንድ ሰው በመንገድ የሚያልፍን መንገደኛ ሊያፈቅር ይችላል፡፡ የፍቅር ስሜት ተሰምቶት በእንዱ መንገድ ሊሄድ ይችላል፡፡ መነጋገር እንኳን ላያስፈልግ ይችላል፤ መግባባት እያስፈልግም፡፡ ስሜቱን ተከትሎ መንገዱ ይችላል፡፡ አንድ ሰው ድንጋይ ሊያፈቅር ይችላል፤ አንድ ሰው ዛፎችን፣ ሰማይን፣ ከዋክብቱን ሊያፈቅር ይችላል፤ አንድ ሰው ጓደኛውን፣ ባለቤቱን፣ ልጆቹን፣ አባቱን፣ እናቱን ሊያፈቅር ይችላል፤ አንድ ሰው በሚሊየን መንገዶች ሊያፈቅር ይችላል፡፡

የማይፈራ ሁሉ ደፋር አይደለም፡፡ የማይፈራን ሁሉ ደፋር ማለት አይቻልም፡፡ እንድን ማሽን ስላልፈራ ብቻ ደፋር ልትሉት አትችሉም፡፡ ደፋርነት በፍርሃት ውቅያኖስ ላይ የሚገኝ ደሴት ነው፡፡ ፍርሃት ቢኖርም ሰውየው አደጋውን ይጋፈጣል- ይህ ነው ጀግንነት፡፡ አንዱ ቢንቀጠቀጥ፣ ወደ ጨለማ መግባት ቢፈራም፣ ሌላው ደፍሮ ይገባበታል፡፡ ራሱን አሸንፎ መንገዱ

ነው - ጀግንነት፡፡ ይህ ግን አለመፍራት አይደለም፡፡ በፍርሃት የተሞላ ቢሆንም ፍርሃትን ተቋቁሞ መጓዝ ነው- ጀግንነት፡፡

ወደ ፍቅር ውስጥ ስትገቡ ትልቁ ጥያቄ ይነሳል፡፡ ፍቅር ማለት ለሌላው መሞት ነውና ፍርሃት ነፍሳችሁን ጠፍንጐ ይይዛታል፡፡ ከተራው ሞት የጠነከረ ሞት፡፡ በተራው ሞት አካል ብቻ ነው የሚሞተው፡ በፍቅር ሞት ግን የራስ ኩራትም (እኔነትም) ይሞታል፡፡ ለማፍቀር ወኔ ያስፈልጋል - ፍርሃትን በጣጥሶ የማለፍ ወኔ፡፡

አደጋው በበዛ መን የማደግ እጋጣሚም ይጨምራል - ስለዚህ ለሰው ልጅ ዕድገት ከፍቅር የበለጠ ጠቃሚ የሆነ ምንም ነገር የለም፡፡ ማፍቀርን የሚፈሩ ህፃን፡ ያልበሰሉ ሆነው ይቀራሉ፡፡ የሚያበስላችሁ የፍቅር እሳት ብቻ ነው፡፡







# ፍቅር ቀላልም፣ አስቸጋሪም ሳይሆን ተፈጥሯዊ ብቻ ነው

# ፍቅር ሲኖር ወሰኖች አይኖሩም፣

ፍቅር የንቃተ-ህሊና ተፈጥሯዊ ሁኔታ ነው፡፡ ቀላልም አስቸጋሪም አይደለም፡ ቃላት በደንብ አይገልፁትም፡፡ ጥረት ባለመሆኑ ቀላልም፡ ከባድም አይደለም፡፡ ልክ እንደ ትንፋሽ ነው! ልክ እንደ ልብ ምታችሁ፡ ልክ በሰውነታችሁ ውስጥ እንደሚመላለሰው ደም ነው፡፡

ፍቅር ማንነታችሁ ነው .... ያ ፍቅር ግን የማይቻል ሆኗል፡፡ ማህበረሰቡ ፍቅር አይፈቅደውም፡፡ ማህበረሰቡ በሚደረድራቸው ምክንያቶች ሳቢያ ፍቅር የማይቻል ይሆናል፤ ብቸኛው እማራጭ ጥላቻ ይሆናል፡፡ ጥላቻ ቀላል ቢሆንም ፍቅር አስቸጋሪ ከመሆኑ በተጨማ የማይቻል ይሆናል፡፡ የሰው ልጅ ተዛብቷል፡፡ የሰው ልጅ አስተድሞ ባይዛባኖሮ ወደ ባርነት አይወርድም ነበር፡፡ ፖለቲከኞች እና ካህናት ለዘመናት በተንኮልና ሴራ ውስጥ ተዘፍቀው ኖረዋል፡፡ የሰው ልጅን ወደ ባሪያነት ለውጠውታል፡፡ ተቃዋሚ የመሆን እጋጣሚን በሙሉ አጥፍተውታል - ፍቅር ደግሞ የልብን እንጂ የሌላን የማይደግም አማፂ ነው፡፡

ፍቅር እንድ ፍፁም ግለሰብ ስለሚያደርጋችሁ አደገኛ ነው፡፡ ሀገርና ቤተ ክርስቲያንን ደግሞ ፍፁም ግለሰቦችን አይፈልጉም፡፡ ነጠላ ሰዎችን ሳይሆን መንጋውን ነው የሚፈልጉት፡፡ ነፍሶቻቸው ደግሞ ሳይጠኑ የተጉዱ ሰው መሳይ ሰዎችን ብቻ ነው የሚፈልጉት፡፡

ሰውን ማጥፊያው ምርጡ መንገድ ፍቅሩን ማጥፋት ነው፡፡ ሰው ፍቅር ካለው በጥላቻ ነው፡፡ የተለያዩ ሃገራት አይኖሩም፡፡ የተለያዩ ሃገራት ያሉት በጥላቻ ነው፡፡ ህንዳውያን ፓኪስታናውያንን ይጠላሉ፤ ፓኪስታናውያን ህንዳውያንን ይጠላሉ - ለዛም ነው ሁለት ሃገራት የሆኑት፡፡ ፍቅር ሲኖር ወሰኖች አይኖሩም፡፡ ፍቅር ቢኖር ኖሮ ማን ክርስቲያን፡ ማን አይሁድ ይሆን ነበር? ፍቅር ሲኖር ሃይማኖቶችም ይጠፋሉ፡፡

ፍቅር ቢኖር ኖሮ ማን ወደ ቤተ መቅደስ ይሄድ ነበር? ለምንስ ይሄዳል? ፍቅር ስለጠፋ ነው እግዚአብሄርን የምትፈልጉት፡፡ ፍቅር የጠፋባችሁ ፍቅር ምትክ ነው፡፡ ደስተኛ ባለመሆናችሁ፣ ሰላማዊ ባለመሆናችሁ፣ ሃሴት ስለራቃችሁ እግዚአብሄርን ትፈልጋላችሁ - አለበለዚያ ለምን ይጨንቃችኋል፣ ማን ግድ አለው? ህይወታችሁ ደስታ ከሆነ እግዚአብሄር እዚያ አለ፡፡ አፍቃሪ ልብ በእግዚአብሄር የተሞላች ናት፡፡ ሌላ ፍለጋ ማድረግ፣ ሌላ ፀሎት ማድረግ፣ ወደ ቤተ-መቅደስ መሄድ፣ ወደ ካህን መሄድ አያስፈልግም፡፡

**ሰውን ማጥፊያው ምርጡ መንገድ ፍቅሩን ማጥፋት ነው፡፡ ሰው ፍቅር ካለው የተያዩ ሃገራት አይኖሩም፡፡ የተለያዩ ሃገራት ያሉት በጥላቻ ነው፡፡**

ካህናት እና ፖለቲከኞች የሰው ልጅ ጠላቶች ናቸው፡፡ ፖለቲከኛ አካላችሁን፣ ካህኑ ደግሞ ነፍሳችሁን ለመግዛት ሴራ ይጠነስሳሉ፡፡ አሁንም ሚስጥሩ አንድ ነው - ፍቅርን ማጥፋት፡፡ ስለዚህ ሰው ባዶነት፣ መናኝነት፣ ትርጉም አልባ ሀልውና ነው፡፡ ሰውን የፈለገ ነገር ብታደርጉት ማንም አይቃወምም፣ ማንም ለማመፅ ድፍረት አይኖረውም፡፡

ፍቅር ድፍረት ይሰጣል፣ ፍቅር ፍርሃትን ያጠፋል - ጨቋኞች የእናንተ ፍርሃት ጥገኛ ናቸው፡፡ አንድ ሺ አንድ ፍርሃት ይፈጥሩባችኋል፡፡ ስለዚህ በፍርሃት ትከበባላችሁ፣ ሥነ - ልቡናችሁ በፍርሃት ይሞላል፣ በውስጣችሁ ትሸበራላችሁ፡፡ ፊታችሁ አንድ አይነት ገፅታ ብቻ ነው ያለው፣ ውስጣችሁ ግን በፍርሃት ድርብርብ የተሞላ ነው፡፡

በፍርሃት የተሞላ ሰው ምርጫው ጥላቻ ብቻ ነው - ጥላቻ ተፈጥሯዊ የፍርሃት ውጤት ነው፡፡ በፍርሃት የተሞላ ሰው በብስጭት የተሞላ፣ ከህይወት የወጣ ነው፡፡ በፍርሃት የተሞላ ሰው ማረፊያው ሞት ይመስላል፡፡ ፈሪ ሰው ከህይወት በተግራሪ ራሱን የሚያጠፋ ነው፡፡ ህይወት አደገኛ ትሆንበታለች፡፡ ለመኖር ማፍቀር ያስፈልጋል፡፡ ስጋ ለመኖር መተንፈስ እንደሚያስፈልገው፣ ለነፍስም ፍቅር ያስፈልጋታል፡፡ ፍቅር ደግሞ ከፉኛ ተበክሏል፡፡

የፍቅር ሃይላችሁን በከላችሁ በውስጣችሁ መከፋፈል ፈጥረዋችኋል፣ ውስጣችሁን ለሁለት ከፍላችሁታል፡፡ የርስ በርስ ግጭት ፈጥረውባችኋል፡፡ ሁልጊዜም በግጭት ላይ ናችሁ፡፡ በዚህ ግጭት ሃይላችሁ ተሟጥጧል፡፡





ስለዚህም ህይወታችሁ ደስታ የራቀው ሆኗል፡፡ በሃይል የተሞላ ሳይሆን የደነዘዘ፣ ጣዕም የሌለው፣ ብልህነት የሌለው ህይወት ሆኗል፡፡

ፍቅር ብልህነትን ይሰለጥላል፣ ፍርሃት ደግሞ ያደነዱማል፡፡ ብልህ መሆን ማን ይፈልጋል? ስልጣን ላይ ያሉ ይህን አይፈልጉም፡፡ እናንተ ብልህ እንድትሆኑስ እንዴት ሊፈልጉ ይችላሉ? ብልህ ከሆናችሁ አትዳቸውን፣ ጨዋታቸውን ትነቁባቸዋላችሁ፡፡ ስለዚህ መሃይም እና የማይረባ እንድትሆኑ ይፈልጋል፡፡ ስራን በተመለከተ ውጤታማ እንድትሆኑ ይፈልጋሉ፣ ብልህ እንድትሆኑ ግን አይፈልጉም፡፡ በዝቅተኛ አቅማችሁ እንድትኖሩ ነው የሚፈልጉት፡፡

የሳይንስ ተማራማሪዎች እንደሚናገሩት የሰው ልጅ በመላ የህይወት ዘመኑ የአቅሙን አምስት በመቶ ብቻ ነው የሚጠቀመው፡፡ ቀሪው ሰው አምስት በመቶውን ከተጠቀመ ልዩ የሆነ ሰውስ? አልበርት አንስታይን፣ ሞዛርት፣ ቤትሆቨን? ተመራማሪዎቹ እንደሚሉት በጣም ከፍተኛ ተሰጥኦ ያላቸው እንኳን ከአስር በመቶ በላይ አይጠቀሙም፡፡ እና የላቀ ችሎታ አላቸው የምንላቸው እንኳን አስራ አምስት በመቶውን ብቻ ነው የሚጠቀሙት፡፡

ሁሉም ሰው የአቅሙን መቶ በመቶ የሚጠቀም ቢሆን ይህች ዓለም ምን እንደምትመስል አስቡ .... ማያታት በምድር ቀንተው ምነው ምድር ላይ በተወለድን ይሉ ነበር፡፡ ምድር ገነት ትሆን ነበር፡፡ አሁን ግን ሲዖል ናት፡፡

የሰው ልጅ ብቻውን ቢተው፣ ሳይበከል ቢቀር ..... ፍቅር ቀላል፣ በጣም ቀላል ይሆን ነበር፣ ምንም ችግር አይኖርም፡፡ ቁልቁል እንደሚወርድ ውሃ ወይም ሽቅብ እንደሚወጣ ትነት፣ እንደሚያብቡ ዛፎች፣ እንደ ዘማሪ አዕዋፋት ይሆን ነበር፡፡ ተፈጥሯዊና ህያው ይሆናል!

ነገር ግን የሰው ልጅ ብቻውን አልተተወም፡፡ አንድ ህፃን ሲወለድ ጨቋኞች በልለው ሃይሉን ያደቁታል፣ ሃይሉን ያዘቡታል፣ መኖር ያለበትን ያህል ሳይሆን የውሸት ህይወት እየኖረ እንደሆነ እንዳያውቅ፣ እየኖረ ያለው በእውነተኛ ነፍሱ እንደሆነ እንዲያገነዘብ ያደርጉታል፡፡ ለዛም ነው በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች በዚህ ስቃይ ውስጥ የገቡት - እነዚህ ሰዎች እንደተሰናከሉ፣ ራሳቸውን እንዳልሆኑ፣ አንድ የተሳሳተ ነገር እንዳለ .... ይሰማቸዋል፡፡

ህፃኑ እንዲያድግ ቢፈቀድለት፣ በተፈጥሯዊ መንገድ እንዲያድግ ቢረዳ፣ ፍቅር ቀላል ይሆናል፡፡ ህፃኑ ከተፈጥሮ ጋር፣ ከራሱ ጋር በህብር እንዲኖር እርዳታ ቢደረግለት፣ ህፃኑ በየአቅጣጫው ቢደገፍ፣ እንክብካቤ ቢደረግለት፣ ተፈጥሯዊና ራሱን እንዲሆን ቢበረታታ፣ በውስጡ ብርሃን ቢበራለት ፍቅር ቀላል ይሆናል፡፡ በቀላሉ አፍቃሪ ይሆናል!

ይሄን ጥላቻ የማይቻል ይሆናል - ምክንያቱም አንድ ሰው ከመጥላታችሁ በፊት በውስጣችሁ መርዝ መፍጠር ይኖርባችኋል፡፡ የሌላችሁን መስጠት አትችሉም፡፡ ልትጠሉ የምትችሉት በጥላቻ የተሞላችሁ ከሆናችሁ ብቻ ነው፡፡ በጥላቻ ለመሞላት ደግሞ በሃይል መሰቃየት የግድ ነው፡፡ በጥላቻ ተሞላችሁ ማለት በቅድሚያ ራሳችሁን እያቆሰላችሁ ነው ማለት ነው፣ ሌላውን ከማቁሰላችሁ በፊት ራሳችሁ ትቆስላላችሁ፡፡ ሌላኛው እንደውም ላይቆስል ይችላል፡፡ ግን አንድ ነገር እርግጥ ነው፡- ከመጥላታችሁ በፊት በሃይል ልትሰቃዩ የግድ ነው፡፡ ሌላኛው መገን ሊጠላችሁ፣ ሊያገላችሁ ይችላል፡፡ ሌላኛው ምናልባት ቡድሃ ይሆንና ይስቅ ይሆናል፤ ይቅር ይላችሁ ይሆናል - ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ካልሆነ ላይቆስል ይችላል፡፡ ልትረብሹት ካልቻላችሁ ሌላ ምን ልታደርጉት ትችላላችሁ? ከፊቱ አቅመ - ቢስ ትሆናላችሁ፡፡

ስለዚህ ሌላኛው ወገን መቁሰል ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን አንድ እርግጠኛ ነገር አለ፡፡ አንድን ሰው ከመጥላታችሁ በፊት የራሳችሁን ነፍስ ከፉኛ ትጎዳላችሁ፣ መርዛችሁን ከመርጨታችሁ በፊት እናንተ ልትመረዙ የግድ ነው፡፡

ጥላቻ ኢ-ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ፍቅር ጤናማ ሁኔታ ነው፣ ጥላቻ የህመም ሁኔታ ነው፡፡ ህመምም ኢ-ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ህመም የሚፈጠረው ከተፈጥሮ መንገድ ስትወጡ፣ ከህልውና ጋር ህብራችሁን ስታቋርጡ፣ ከህያውነት ጋር ህብራችሁን ስታቆሙ፣ ከውስጣችሁ ጋር ስትለያዩ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ስነ-ልቡናዊ፣ መንፈሳዊ ህመምተኛ ትሆናላችሁ፡፡ ጥላቻ የህመም ምልክት፣ ፍቅር ደግሞ የጤንነት፣ የምሉዕነት፣ የቅዱስነት ምልክት ነው፡፡

ፍቅር ከላቁ ተፈጥሯዊ ነገሮች መሃል አንዱ መሆን ነበረበት፡፡ ግን አይደለም፡፡ በተቃራኒው አስቸጋሪ፣ የማይቻል ነገር ሆኗል፡፡ ጥላቻ ግን ቀላል ሆኗል፡፡ ጥላቻን ትማራላችሁ፣ ለጥላቻ ትዘጋጃላችሁ፡፡ ሂንዱ ስትሆኑ የመሃመድ ተከታዮችን፣ ክርስቲያኖችን፣ አይሁዶችን ትጠላላችሁ፣ ክርስቲያን





ስትሆኑ ለሎቹን ሃይማኖቶች ትጠላላችሁ፡፡ ብሄርተኛ ስትሆኑ ሌሎቹን ሃገራት ትጠላላችሁ፡፡

አንድ የፍቅር መንገድ ብቻ ነው የምታውቁት - ሌሎችን መጥላት፡፡ ሌሎችን በመጥላት ለሃገራችሁ ያላችሁን ጥልቅ ፍቅር ታሳያላችሁ፣ ሌሎች አብያተ ክርስትያናትን በመጥላት ለቤተ-ክርስቲያናችሁ ያላችሁን ፍቅር ታሳያላችሁ፡፡ እውነቱን ለመናገር ችግር ውስጥ ናችሁ፡፡

እነዚህ ሃይማኖት ተብዬዎች ስለፍቅር ብዙ ያወራሉ፡፡ የሚያደርጉት ነገር ግን በአለም ላይ ጥላቻን መዝራት ነው፡፡ ክርስቲያኖች ስለ ፍቅር ብዙ ቢሰብኩም የመስቀል ጦርነቶችን ቆስቁሰዋል፤ የመሐመድ ተከታዮች ስለፍቅር ብዙ ቢያወሩም የጂሃድ (የቅዱስ) ጦርነቶችን ፈጥረዋል፣ ሂንዱዎች ስለፍቅር ብዙ ቢለፈልፉም ቅዱሳን መጻህፍቶቻቸውን በትመለከቱ በሌሎች ሃይማኖት ላይ በተቀሰሩ የጥላቻ ጦሮች ተሞልተው ታገኟቸዋላችሁ፡፡ እነና ደገሞ ይሆን ሁሉ የማይረባ ነገር እንቀበላለን! እነዚህን ነገሮች እንድንቀበል ዝግጁ ተደርገናልና፣ በዚህ መንገድ ተምረናልና ያለምንም ማመንታት እንቀበላቸዋለን፡፡ ስለዚህም በዚህ መንገድ ተፈጥሯችንን እንክዳለን፡፡

በዚህ ሁኔታ ፍቅር የተመረዘ ቢሆንም ጨርሶ አልጠፋም፡፡ መርዙ ከስርዓቱ ወጥቶ ሊጣል፣ እናንተም ልትነፁ ትችላላችሁ፡፡ ማህበረሰቡ ያጨቀባችሁን እውጥታችሁ መወርወር ትችላላችሁ፡፡ ማህበረሰቡ ያጨቀባችሁን እውጥታችሁ መወርወር ትችላላችሁ፡፡ እምነቶቻችሁን፣ ሁኔታዎቻችሁን በሙሉ ጥላችሁ ነፃ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ ነፃ ለመሆን ከወሰናችሁ ማህበረሰቡ ዘላለም ባሪያ አድርጎ ሊያቆያችሁ አይችልም፡፡

ከአረጀ መንገዳችሁ ወጥታችሁ በአዲስ መንገድ ተፈጥሯዊ የሆነ፣ ጥቅና የሌለበት፣ የደስታ ህይወት የመጀመር ጊዜያችሁ አሁን ነው፡፡ እንዲህ ካደረጋችሁ ጥላቻ የማይቻል ይሆናል፡፡ ጥላቻ ከፍቅር በተቃራኒው ጫፍ የሚኖር ነው - ህመም የጤንነት ተቃራኒ ጫፍ እንደሆነው፡፡ ስለዚህ ህመምን መምረጥ አይኖርባችሁም፡፡

**ማንም መሆን የማይፈልጉ ብቻ ማፍቀር ይችላሉ፡፡ ማንም ለመሆን ዝግጁ የሆኑ፣ ራሳቸውን ባዶ ለማድረግ የተዘጋጁ ብቻ ፍቅርን ከማዶ መቀበል ይችላሉ፡፡**

ሀመም ጤንነት የሌለው ጥቂት ነገሮች አሉት፤ እነዚያን ነገሮች አትጠቀሙባቸው። ጥላቻም ከፍቅር በላይ የሆኑ ጥቂት ነገሮች አሉት። ስለዚህም በጣም አስተዋይ መሆን አለባችሁ። የታመመ ሰው በሁሉም ዘንድ ይታዘንለታል፤ ማንም አይጎዳውም። ሁሉም ሰው ሲናገረው ተጠንቅቆ ነው። የሁሉም ሰው የትኩረት ማረፊያ ይሆናል - የቤተሰብ፣ የጓደኛ - ማሕበራዊ ሰው፤ አስፈላጊ ይሆናል። ሀመምተኛው ከዚህ ጥቅም ጋር፤ ከፍላጎቱ መሟላት ጋር የሙጥኝ ሲል ዳግም ጤነኛ መሆንን ይጠላል። ከሀመሙ ጋር ይጣበቃል። ብዙ የስነ-ልቡና ባለሙያዎች እንደሚናገሩት ብዙ ሰዎች ይህ ጥቅም እንዳይቀርባቸው ከሀመማቸው ጋር ተጣብቀው ይቀራሉ። ከሀመማቸው ጋር ብዙ ስለሚቆዩ ከሀመማቸው ጋር መሆናቸውን እንኳን ይዘነጉታል። ጤነኛ ከሆኑ ማንም አይጠጋንም ብለው ይፈራሉ።

ይህ ሙሉ በሙሉ ኢ-ሳይንሳዊ ነው። አንድ ህፃን ሲታመም እነሱን ተንከባከቡለት እንጂ ብዙ ትኩረት አታድርጉበት። ሀመምና ትኩረታችሁ ከተገናኙ አደገኛ ነው። ይህ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ያጋጥማል። አንድ ህፃን ሲታመም የመላው ቤተሰብ ማዕከል ይሆናል። አባት አጠገቡ ተቀምጦ ስለ ጤንነቱ ይጠይቀዋል፤ ሃኪሙ ይመጣል፤ ጎረቤቶቹና ወዳጆቹ መጥተው ይጠይቁታል፤ ሰዎች ስጦታ ያመጡለታል፤ ሀመምተኛው የራስ ኩራቱ ስለሚረካለት ዳግም ጤነኛ መሆን አይፈልግም። ይህ ከተከሰተ ደግሞ ከነጭራሹ ጤነኛ መሆን አይችልም፤ ምንም አይነት መድሃኒት አይፈውሰውም። ልጁ ለሀመሙ ተገዢ ይሆናል። አብዛኛው ሰው ላይ የሚከሰተው ይህ ነው።

ስትጠሉ የራስ ኩራታችሁ (ለራሳችሁ የምትሰጡት ግምት) ይረካል። ስትጠሉ የበላይነት ስሜት ስለሚሰማችሁ፤ የተለየ ስለምትሆኑ፤ ተነጥላችሁ ስለምትታዩ የራስ ኩራታችሁ በጥላቻ ውስጥ ብቻ ይኖራል። በመጥላት የተወሰነ መታወቂያ፣ ማንነት ታገኛላችሁ። የራስ ኩራት በፍቅር ይጠፋል። በፍቅር የተለየ መሆናችሁ ይቀራል - ፍቅር ከሌሎች ጋር እንድትዋሀዱ ይረዳችኋል፤ ፍቅር ያገናኛል፤ ያዋህዳል።

ከራስ ኩራታችሁ ጋር ይበልጥ የተጣበቃችሁ ስትሆኑ ጥላቻ ይቀላል፤ ፍቅር ከባድ ይሆናል። ንቁ እና ጠንቃቃ ሁኑ። ጥላቻ የራስ ኩራት ጥላ ነው። ፍቅር ትልቅ ድፍረት ይጠይቃል። የራስ ኩራትን መጣል ስለሚፈልግ ትልቅ ድፍረት ይጠይቃል። ማንም መሆን የማይፈልጉ ብቻ ማፍቀር ይችላሉ። ማንም ለመሆን ዝግጁ የሆኑ፤ ራሳቸውን ባዶ ለማድረግ የተዘጋጁ ብቻ ፍቅርን ከማዶ መቀበል ይችላሉ።





# ከህዝብ መሀል ውጡ

# 3

## ለብቻ ለመሆን መድፈር

በተመስጦ ማሰላሰል ዝም ለማለት እና ለብቻ ለመሆን መድፈር ነው። ቀስ በቀስ በራሳችሁ ላይ አዲስ ባህርይ፤ አዲስ የህያውነት መንፈስ፤ አዲስ ውበት እንዲሁም አዲስ አስተሳሰብ ሲያቆጠቁጥ ይሰማችሁ ይጀምራል። ይህ ደግሞ ከማንም የተዋሳችሁት ሳይሆን በውስጣችሁ በማደግ ላይ የሚገኝ ስሜት ነው። ስሮቹም በህይወታችሁ ውስጥ ስር ይሰዳሉ። እናም ፍርሃት ካልገባችሁ አብቦ ይፈራል።

# ልታጡት የምትችሉት መታጣት ያለበትን ብቻ ነው

ማንም ሰው ቢሆን በህይወቱ መኖር የነበረበትን አይደለም፡፡ ማህበረሰብ፣ ባህል፣ ሀይማኖት እና ትምህርት ምንም በማያውቁ ምስኪን ህፃናት ላይ የየራሳቸውን ሴራ እየጠነሰሱባቸው ይገኛሉ፡፡ ሁሉም በየራሳቸው መንገድ በህፃናቱ ህይወት ላይ ስልጣናት አሏቸው፡፡ እያንዳንዱ ህፃን ረዳት የለሽ ምስኪን ጥገኛ ነው፡፡ በመሆኑም በህፃኑ ላይ የፈለጉትን ነገር ለማድረግ የሚያግዳቸው ነገር የለም፡፡ የትኛውንም ህፃን ቢሆን በተፈጥሮው ሊደርስበት ወደሚችልበት ደረጃ እንዲያድግ አይፈቅዱለትም፡፡ እያንዳንዱ ጥረታቸው የሰው ልጆችን እንደ መገልገያነት መጠቀሚያ ማድረግ ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ደግሞስ አንድ ህፃን በገዛ ራሱ መንገድ እንዲያድግ ቢተው ሊታሰብለት አገልግሎት መዋል አለመዋሉን ማን ያውቃል? ማህበረሰቡ ኃላፊነቱን ለመውሰድ ዝግጁ አይደለም፡፡ ብቻ ህፃኑን ጨምድዶ በመያዝ በማህበረሰቡ እንደሚፈልገው አድርጎ መቅረፅ ይጀምራል፡፡

ይህ መሆኑ በተወሰነ መልኩ የህፃኑን መንፈስ ገድሎ ሀሰተኛ ማንነት ይሰጠዋል፡፡ በመሆኑም በጭራሽ የራሱ መንፈስና ተፈጥሮ አይናፍቀውም፡፡ ሀሰተኛ ማንነቱ የትክክለኛው ማንነቱ መትከ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጠቃሚቱ ይህንን ሀሰተኛ ማንነት በሰጠው በዚያ ህዝብ ውስጥ እስካለት ጊዜ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ብቻችሁን ስትሆኑ ወዲያውኑ ሀሰተኛው ማንነታችሁ ይፈረካከስ እና የተገታው እውነተኛ ማንነት እራሱን መግለፅ ይጀምራል፡፡ በዚህ የተነሳም ለብቻችሁ ለመሆን ትፈራላችሁ፡፡

ማንም ቢሆን ብቻውን መሆንን አይሻም፡፡ ሁሉም ሰው የህዝብ (የአንድ ብቻ ሳይሆን የብዙ ህዝቦች) አካል መሆንን ይፈልጋል፡፡ አንድ ሰው በሀይማኖት ጥላ ስር የሰባሰበ ህዝብ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የንቀሳቃሾሽ ክበባት አባል ነው፡፡ ደግሞም ሌሎች አባል ሊሆንባቸው የሚቻልባቸው ብዙ ትናንሽ ቡድኖች አሉ፡፡ ሀሰተኛ ማንነት ያለ ድጋፍ መቆም ስለማይችል አንድ ሰው በቀን ውስጥ ለሀያ አራት ሰአታት ድጋፍ እንዲያደርግለት ይፈልጋል፡፡ አንድ





ሰው ብቻውን ሲሆን ከመቅፅበት እንግዳ የሆነ የእብደት ስሜት ይሰማው ይጀምራል፡፡ ለብዙ አመታት የገዛ ራሳችሁን አንድ የሆነ ሰው መሆን ታምኑበት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ድንገት ለብቻችሁ በሆናችሁበት ቅፅበት ታስቡት የነበረውን አይነት ሰው አለመሆናችሁን እየተረዳችሁት ትመጣላችሁ፡፡ ይሄ ደግሞ ፍርሃትን ያጭራል፡፡ ታዲያ ማን ናችሁ?

እናም ለአመታት ይህንን ስሜታችሁን ገድባችሁት ትቆዩና .... እውነተኛው ማንነታችሁ ራሱን ለመግለፅ ጥቂት ጊዜ ይወስድበታል፡፡ በሀሰተኛው እና በእውነተኛው ማንነታችሁ መካከል ያለው ክፍተት ከአምላክ ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳላቸው በሚታመኑ መንፈሳዊያን ዘንድ <የነፍስ የጨለማ ሌሊት> ተብሎ ይጠራል፡፡ በእውነቱ ይህ ተገቢ የሆነ አገላለፅ ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ በኋላ ሀሰተኛ ማንነታችሁን (እራሳችሁን) አይደላችሁም፡፡ ገና እውነተኛው ማንነታችሁንም አልደረሳችሁበትም፡፡ በጣም ግራ ስለተጋባችሁ ማንነታችሁን አታውቁትም፡፡ በተለይም በምዕራቡ ዓለም ይህ ችግር ይበልጥ ይወሳሰባል፡፡ ምክንያቱም በተቻለ መጠን ከዉዲሁ ትክክለኛው ማንነት ላይ ለመድረስ የሚቻልበት ዘዴ አልተተየሰም፡፡ በመሆኑም <የነፍስ የጨለማ ሌሊት> ሊያጥር አልቻለም፡፡ በተመስጦ ማሰላሰልን በተመለከተ ምዕራባውያን ምንም ነገር አያውቁም፡፡ በእነሱ ዘንድ በተመስጦ ማሰላሰል ብዙም ተግባራዊ አይደረግም፡፡ በተመስጦ ማሰላሰል ማለት ለብቻ በመሆን በፀጥታ እውነተኛው ማንነት ራሱን እስኪገልፅ ድረስ መጠባበቅ ማለት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ድርጊት ሳይሆን በፀጥታ ዘና የማለት ሁኔታ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም ይሁን ምን የሰራችሁት ነገር ከሀሰተኛው ስብዕናችሁ ውስጥ ይወጣል፣ ለብዙ አመታት የፈፀማችሁት ነገር በሙሉ ወጥቶ ሂዷል፡፡ ቢቃ ያረጀ፣ ያፈጀ ልማድ ነው፡፡

እርግጥ ልማዶችን ለመተው ያስቸግራል፤ በቀላሉ የሚረሱም አይደሉም፡፡ ለብዙ አመታት በምትወዷቸውና በምታከብሩቸው ሰዎች እስገዳጅነት በሀሰተኛ ስብዕና ውስጥ እየኖራችሁ ቆይታችኋል፤ ይህ የሆነው ደግሞ ሆን ተብሎ እናንተ ላይ መጥፎ ነገር ለመፈፀም ታስቦ አይደለም፡፡ የሰዎቹ ሀሳቦች መልካም ነበሩ፡፡ ብቻ ግንዛቤያቸው ባዶ ነበር፡፡ በሀሰተኛ ስብዕና ውስጥ እንድትኖሩ ያደረጉዋችሁ ወላጆቻችሁ፣ መምህራኖቻችሁ፣ የሀይማኖት አባቶች ወይም ፖለቲከኞች ይህንን ያደረጉት ሆን ብለው ሳይሆን ሳያውቁት ነው፡፡ ምንም ይሁንና የሚሰሩትን በማያውቁ ሰዎች ዘንድ ያሉ መልካም ሀሳቦች ይሰወጣሉ፡፡ እንኳን ጥሩ የነበሩ ቢሆንም የኋላ ኋላ ወደ መርዛማነት

ለብቻችሁ በሆናችሁ ቁጥር ጥልቅ የሆነ የናፍቆት ስሜት ያድርባችኋል፡፡ ይህም የሚሆነው ሀሰተኛው ማንነታችሁ ድንገት መሰወር ስለሚጀምር ነው፡፡ በዚህም እውነተኛው ማንነታችሁ ለመግለፅ ትንሽ ጊዜ ይወስድበታል፡፡ ምክንያቱም ከብዙ አመታት በፊት ጠፍቶዎችሁ ስለበር ነው፡፡ እናንተም ታዲያ ለብዙ አመታት ተፈጥሮ የነበረው ክፍተት መጥበብ እንዳለበት ግምት ውስጥ ማስገባት አለባችሁ፡፡

"እራሴን፣ ስሜቴን፣ ንፅህናዬን፣ አእምሮዬን እንዲሁም ያለኝን ነገር በሙሉ ማጣቴ ነው" ብላችሁ ፍርሃት ያድርባችኋል፡፡ በሌሎች የተሰጣችሁ ማንነታችሁ (እራሳችሁ) ሁሉንም ነገር ስለያ፣ አእምሯችሁን ስታጡ ጨርቃችሁን በመጣል የምታብዱ መስሎ ይታያችኋል፡፡ ወዲያውንም እንደነበራችሁት ሆናችሁ ለመቆየት ስትሉ የሆነ ነገር ማድረግ ትጀምራላችሁ፡፡ ሰዎች ባይኖሩ እንኳን ሁ ያንስ የሆነ ድርጊት ይኖራል፡፡ በመሆኑም ሀሰተኛው ማንነታችሁ እንደነበር ሆኖ ይቆያል፣ መሰወር አይጀምርም፡፡

ስለዚህ ሰዎች የእረፍት ቀናትን አስቸጋሪ ሆነው ያገኟቸዋል፡፡ ለአምስት ቀናት ስራ ይሰራሉ፡፡ በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናትም እንደሚዝናኑ ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ ይሁንና የሳምንቱ የመጨሻ ቀናት በመላው አለም የባሰ የከፉ ጊዜያት ናቸው ይበልጥ አደጋዎች ይከሰታሉ፡፡ በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት ከሌላው ጊዜ በበለጠ ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው ያጠፋሉ፣ የግድያ ወንጀሎች ይበረክታሉ፣ የስርቆት እና አስገድዶ የመድፈር አጋጣሚዎችም የዚያን ያህል ቁጥራቸው ይጨምራል፡፡ ይገርማል! ...... እንግዲህ የእነዚህ ትዕይንቶች ተዋንያን የነበሩት እኒህ ሰዎች ለአምስት ቀናት በስራ ተጠምደው ሰንብተው ነበር፡፡ በእነዚህ ቀናትም ምንም ችግር አልነበረም፡፡ ነገር ግን የሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት የእረፍት ጊዜ ድንገት አማራጭ አስገኘላቸው፡፡ ይኸውም በስራ መጠመድ አሊያም መዝናናት ነው፡፡ ይሁንና መዝናናት አስፈሪ ነው፡፡ ሀሰተኛ ሰብዕና ይሰወራል፡፡ ስለዚህ ማንነት እንደነበር ለማቆየት ሲባል የማይረቡ ድርጊቶች ይፈፀማሉ፡፡ መኪኖች በጐዳናዎች ላይ ፊት እና ኋላቸው ገጥሞ በማይሎች የሚለካ ሰልፍ ሰርተው ይደረደራሉ፡፡ ሰዎች ወደ ባህር ዳርቻዎች ለመሄድ ይጣደፋሉ፡፡ የት እንደሚሄዱ ብትጠይቋቸው <ከተጨናነቀ ህዝብ ገለል ለማለት> መፈለጋቸውን ይነግሩዋችኋል፡፡ ነገር ግን





መላው ህዝብ አብሯቸው እየሄደ ነው! ታዲያ ሁሉም ፀጥተኛ የሆነ ገለልተኛ ስፍራ ለማግኘት ነው የሚሄዱት?

በመሰረቱ አቢታቸው ቢቀሩ ኖሮ የበለጠ ፀጥተኛ እና ገለልተኛ በሆነላቸው ነበር፡፡ ቂሎች ሁሉ ተሰባስበው ገለልተኛ ስፍራ ፍለጋ ገና ድሮ ሄደዋልና፡፡ ደግሞም በጥድፊያ እቅላቸውን ሰተዋልኑ፡፡ ምክንያቱም ሁለት የእረፍት ቀናት ምን አላቸው? ገና ምንንም ሳይዙት አይደል የሚያልቁት? ስለዚህ ካሰቡበት መድረስ አለባቸው፡፡ የት ለመድረስ እንዳሰቡ እንዳትጠይቁ!

ሰዎች ወደ ባህር ዳርቻዎች ለመሄድ ይጣደፋሉ፡፡ የት እንደሚሄዱ ብትጠይቋቸው ከተጨናነቀ ህዝብ ገለል ለማለት መፈለጋቸውን ይነግሩዋችኋል፡፡ ነገር ግን መላው ህዝብ አብሯቸው እየሄደ ነው! ታዲያ ሁሉም ፀጥተኛ የሆነ ገለልተኛ ስፍራ ለማግኘት ነው የሚሄዱት?

የባህር ዳርቻዎች አካባቢ ህዝቡ መጨርከቱን ታያላችሁ፡፡ መርፌ ቢጣል እንኳን ማረፊያ ቦታ የለውም፡፡ የገበያ ቦታዎች እንኳን እንዲህ በህዝብ አይሞሉናንቂም፡፡ በጣም የሚገርመው በዚህ ሁኔታ ሰዎች ፀሃይ እየሞቁ እንደሌባቸው መሆናቸው ነው፡፡ በአንዲት ትንሽ የባህር ዳርቻ ላይ አስር ሺ ገደማ የሚሆኑ ሰዎች ፀሃይ ላይ ተሰጥተው ይዝናናሉ፡፡ ታዲያ ከነዚህ ሰዎች መካከል አንዱ በዚያ የባህር ዳርቻ ላይ ከነዚያ ሰዎች ጋር በመገኘቱ ብቻ ሊዝናና አይችልም፡፡ ነገር ግን ወደ አስር ሺህ ገደማ የሚጠጉ ሌሎች ሰዎች በሁሬያው ሆነው እየተዝናኑ እንደሆነ ያውቃል፡፡ በስራ ቀናት በቢሮዎቹ ውስጥ ሆነው ስራ ይሰሩ የነበሩት፣ በመንገዶቹ ላይ ወዲያ ወዲህ ሲጣደፉ የነበሩት፣ በየገበያ ማዕከሉ ዕቃ ለመሸመት ሲተረመሱ የነበሩት፣ እነዚሁ ሰዎች ናቸው፡፡ አሁን ደግሞ እነዚያው ሰዎች በባህሩ ዳርቻ ላይ አሉ፡፡

ለሀሰተኛ ማንነት ህልውና፣ ህዝብ (ትርምስ) የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ብቻችሁን ስትሆኑ ከመቅፅበት ወፈፍ ያደርጋችኋል፡፡ እንግዲህ በተመስጦ ስለማሰብ በትንሹም ቢሆን የማወቅ አስፈላጊነት ያለው እዚህ ላይ ነው፡፡

አትጨነቁ፣ ምክንያቱም ሊሰወር የሚችለው መሰወር የሚገባው ማንነታችሁ ነው፡፡ እሱን የሙጥኝ ማለቱ ትርጉም አይኖረውም፡፡ <ለምን?> ብትሉ ፣ የእናንተ - <እናንተ>ን አይደለማ!

ሀሰተኛው ማንነታችሁ በተሰወረ ጊዜ ያለውን <እናንተ> ናችሁ፡፡ ያን ጊዜ ንፁህ፡ እውነተኛው፡ ያልተበከለው ማንነታችሁ ነፍስ ዘርቶ በታው ላይ <ጉብ> ይላል፡፡ ማንም ቢሆን "እኔ ማን ነኝ?" የሚለውን ጥያቄያችሁን መመለስ አይችልም፡፡ ይህንንም ታውቁታላችሁ፡፡

ሊሰጥ የሚችል ማንነት እውነተኛ መሆን አይችልም፡፡ እውነተኛ ማንነታችሁ ገና ድሮ በውስጣችሁ አለ፡፡ ነገር ግን ሀሰተኛው ማንነት በቅድሚያ መወሰድ አለበት፡፡

በተለየ መንገድ እንዲህ ሊባል ይችላል፡ አንድ ጌታ በእርግጠኛነት የሌሏችሁን ነገሮች ይወስድና በትክክል ያሏችሁን ነገሮች ይሰጣችኋል፡፡

በተመሰጠ ማሰላሰል፡ ዝም ለማለት እና ለብቻ ለመሆን መድፈር ነው፡፡ ቀስ በቀስ በራሳችሁ ላይ አዲስ ባህርይ፡ አዲስ የህያውነት መንፈስ፡ አዲስ ውበት እንዲሁም አዲስ አስተሳሰብ ሲያቆጠቁጥ ይሰማችሁ ይጀምራል፡፡ ይህ ደግሞ ከማንም የተዋሳችሁት ሳይሆን በውስጣችሁ በማደግ ላይ የሚገኝ ስሜት ነው፡፡ ስሮቹም በህይወታችሁ ውስጥ ስር ይሰዳሉ፡፡ እናም ፍርሃት ካልገባችሁ አበባ ያፈራል፡፡

ሀይማኖተኛ ሊሆኑ የሚችሉት ጀግናና ደፋር የሆኑ፡ ወኔ ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ቤተክርስትያን ሳሚዎች ሀይማኖተኛ ሳይሆኑ ፈሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ሀሰተኛ ማንነታቸውን የበለጠ ለማጠናከር እየሞከሩ ይገኛሉ፡፡

ከእናታችሁ ማህፀን ተወልዳችሁ በተሟላ ንቃት፡ ሀሊና እና በአስደናቂ አዕምሮን የመረዳት ችሎታ ወደ እዚህ አለም መጥታችኋል፡፡ እስቲ አንድ ትንሽ ህፃን ተመልከቱ፡፡ አይኖቹን ልብ ብላችሁ በማየት የአይኖቹን (የአስተያየቱን) አፍላት አስተውሉ፡፡ ይሄ ሁሉ ነገር በሀሰተኛ ሰብዕና ተሸፍኗል፡፡

መፍራት አያስፈልግም፡፡ ሊታጡ የምትችሉት መታጣት ያለበትን ብቻ ነው፡፡ ደግሞም የምታጡትን ነገር ከወዲሁ ማጣቱ መልካም ነው፡፡ ምክንያቱም የበለጠ በቆየ ቁጥር እየጠነከረ ይሄዳልና፡፡

> ደግሞም አንድ ሰው ስለሞት ምንም የሚያውቀው ነገር የለውም፡፡ እውነተኛ ተፈጥሯችሁን ከመገንዘባችሁ በፊት አትሙቱ፡፡

እውነተኛ ማንነታቸውን ጠብቀው ኖረው ከእውነተኛው ማንነታቸው ለመሞት የታደሉ በጣም ጥቂቶች ብቻ ናቸው፡፡ የህይወትን ዘለአለማዊነት እና የሞትን ልብወለድነት ያውቃሉና፡፡





# የቁጥሮች ፖለቲካዊ አስተሳሰብ

## የሌሎቹን ድጋፍ የሚሹት የሌሎችን አመለካከት የያዙ ብቻ ናቸው

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር በፍፁም ተመሳሳይ የሆነ ተግባር እንዲፈፅም ይጠበቅበታል፡፡ ሰዎች ትንሽ ለየት ያለ ነገር ሲያደርጉ ከመቅፅበት ለማህበረሰቡ እንግዳ እንደሆኑ ተደርገው ይታያሉ፡፡ ሰዎች ደግሞ እንግዳ የሆነ ተግባር የሚፈፅሙ ሌሎች ሰዎችን በጣም ይፈራሉ፡፡

ለዚህም ነው ሁለት ሰዎች አውቶብስ ወይም በባቡር ውስጥ አሊያም ፌርማታ ላይ ሲገናኙ ፀጥ ብለው መቀመጥ የማይችሉት፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም እንግዶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ብዙም ሳይቆዩ ይተዋወቃሉ፡፡ "ስምህን ማን ልበል? ወዴት ነው የምትሄደው? ስራህ ምንድነው?" ይባባላሉ፡፡ በዚህ መልኩ ጥቂት መረጃዎችን ከተለዋወጡ በኋላ ይረጋጋሉ፡፡ አንዳቸው እንደ ሌላኛው ሁሉ የሰው ልጅ ናቸው ለካ!

ሰዎች ያለማቋረጥ በሚመጥኑት ህዝብ መሀል መሆንን ይፈልጋሉ፡፡ ለየት ያለ ተግባር ስትፈፅሙ ወዲያውኑ መላው ህዝብ ይጠራጠራችሁና ነገሮች ይበላሻሉ፡፡ ከዚያ ግን ያውቋችሁ ሰውዉን ለማየት ይችላሉ፡፡ እራሳችሁን በፍፁም የማትቀበሉ ሰዎች ሆናችሁ መቆየታችሁን ያውቃሉ፡፡ እናም አሁን በድንገት ራሳችሁን ስትቀበሉት ያያሉ፡፡

በማህበረሰባችን ውስጥ ማንም ቢሆን የገዛ ራሱን አይቀበልም፡፡ ሁሉም የገዛ ራሱን ይኮንናል፡፡ ራስን መኮነን የህዝቡ የአኗኗር ዘዬ ነው፡፡ እራሳችሁን መቀበል ስትጀምሩ ደግሞ ከማህበረሰቡ ውስጥ ወጥታችኋል፡፡ ማህበረሰቡም ከማሰተቀፉ የወጣን ማንንም ሰው ታግሶ የመጠበቅ ልማድ የለውም፡፡ ምክንያቱም ማህበረሰቡ የሚኖረው ቁጥሮችን መሰረት አድርጎ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የቁጥሮች ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ነው፡፡ ሰዎች ብዙ ቁጥሮች ሲኖሩ ጥሩ ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ በርካታ ቁጥሮች ሰዎችን ትክክል እንደሆኑ አድርገው እንዲያስቡ ያደርጓቸዋል፡፡ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ደጋፊዎች ስላላቸው

ሊሳሳቱ አይችሉም፡፡ ብቻቸውን ሲተው ግን ትልቅ ጥርጣሬ መተስተስ ይጀምራል፡፡ ከእነሱ ጋር ማንም ሰው የለምና ትክክል ለመሆናቸው መተማመኛው ምንድን ነው?

ለዚህም ነው በዚህ አለም አንድ ግለሰብ መሆን ታላቅ ድፍረት እንደሆነ የምናገረው፡፡

**በማህበረሰባችን ውስጥ ማንም ቢሆን የገዛ ራሱን አይቀበልም፡፡ ሁሉም የገዛ ራሱን ይኮንናል፡፡ ራስን መኮነን የህዝቡ የአኗኗር ዘዬ ነው፡፡**

አንድ ግለሰብ ለመሆን ከሁሉ የላቀ ድፍረት የተሞላበት መሰረት ያስፈልጋል፡፡ "መላው አለም እኔን መቃወሙ አያስጨንቅም፡፡ ዋናው ነገር ተሞክሮዬ ተቀባይነት ማግኘቱ ነው፡፡ ምን ያህል ሰዎች ከእኔ ጋር እንደሆኑ ለማወቅ ቁጥራቸውን አልመለከትም፡፡ ትኩረት የማደርገው በተሞክሮዬ ተቀባይነት - የሌላ ሰው ቃላትን እንደበቀቀን እየደገምኩ መሆን አለመሆኔ ወይም የምናገራቸው ነገሮች ከገዛ ራሴ ተሞክሮ የመነጩ መሆን አለመሆናቸው ላይ ነው፡፡ ንግግሬ በገዛ ራሴ ተሞክሮ ውስጥ ከሆነ፣ የደሜ፣ የአጥንቴ እና የመቅኒዬ አካል ከሆነ፣ መላው አለም በአንድ ወገን ሊሆን ቢችል እንኳን፣ እኔ ትክክል ነኝ፡፡ እነሱ ግን ተሳስተዋል፡፡ ምንም የሚያስጨንቅ ነገር የለም፡፡ እኔ ትክክል መሆኔ እንዲሰማኝ የእነሱ የድጋፍ ድምፅ አያስፈልገኝም፡፡ የሌሎችን ድጋፍ የሚሹት የሌሎችን አመለካከት የያዙ ብቻ ናቸው" ብሎ ማሰብ የግድ ይሆናል፡፡

ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ የሰው ልጅ የሚኖረው በዚያ መልኩ ነው፡፡ በማስተቶ ውስጥ ያቆዩዋችሁም በዚያ መልኩ ነው፡፡ ሰዎች ከዛኑ የግድ ማዘን አለባችሁ፡፡ ከተቸገሩም መቸገር ይኖርባችኋል፡፡ እነሱ የሆኑትን ማንኛቸውንም ነገሮች መሆናችሁ ግድ ይሆናል፡፡ ልዩነት አይፈቀድም፡፡ ምክንያቱም ልዩነት የኋላ ኋላ ወደ ግለሰቦች እና ልዩ ወደመሆን ይመራልና፡፡ ማህበረሰብ ደግሞ ግለሰቦች እና ልዩ መሆንን እጅግ በጣም ይፈራል፣ ይሄም አንድ ሰው ከማህበረሰብ ጥገኝነት ተላቆ ስለ ህዝቡ ቅንጣትም እንኳን አይጨነቅም እንደማለት ነው፡፡ የእናንተ አማልክት፣ ቤተ መቅደሶቻችሁ፣ የሀይማኖት አባቶቻችሁና ቅዱሳን ፅሁፎቻችሁ በሙሉ ለዚያ ሰው ምንም ትርጉም የማይሰጡ ይሆናሉ፡፡





አሁን የገዛ ራሱ ተፈጥሮ፣ የገዛ ራሱ የህይወት ዘዬ፣ የገዛ ራሱ መንገድ አለው፡፡ በራሱም መንገድ ይኖራል፣ ይሞታል፣ ይደስታል፣ ይዘምራል፣ ይጨፍራል፣ ተችቶታልም፡፡

ደግሞም ማንም ሰው ቢሆን ከህዝብ ጋር ሆኖ ሊመቸው አይችልም፡፡ ሁሉም ለብቻው ሲሆን ነው ሊመቸው የሚችለው፡፡



# እግዚአብሔር ሰው ሳይሆን ስሜት ነው፤ ስለዚህ 'ውስጣዊ ስሜታችሁን' አድምጡ

አንድ ልጅ ያለማቋረጥ ራሱን ይፎክት ነበር:: አንድ ቀን አባቱ እየመጣ "ልጄ፡ ለምንድነው ሁልጊዜ ጭንቅላትህን የምታከው"? ሲል ይጠይቀዋል::

ልጅም "የማከው እንደሚያሳክከኝ የማውቀው እኔ ብቻ ስለሆንኩ ይመስለኛል" ብሎ መለሰ::

እንግዲህ ውስጣዊ ስሜት ይሄ ነው! እናንተ ብቻ ናችሁ የምታውቁት:: ሌላ ማንም ሰው ሊያውቀው አይችልም:: የራስ ምታት ቢይዛችሁ ህመሙን የምታውቁት እናንተ ራሳችሁ ብቻ ናችሁ:: ይህንን ደግሞ ማረጋገጥ (ለሌሎች ማሳየት) አትችሉም:: ደስ ሲላችሁም ደስታችሁን የምታውቁት እናንተ ራሳችሁ ብቻ ናችሁ:: በማስረጃ በማስደገፍ ይህንን ስሜታችሁን ለሌሎች ማረጋገጥ አትችሉም:: ደስ ሲላችሁም ደስታችሁን የምታውቁት እናንተ ራሳችሁ ብቻ ናችሁ:: በማስረጃ በማስደገፍ ይህንን ስሜታችሁን ለሌሎች ማረጋገጥ አትችሉም:: አጠገባችሁ ያለ እያንዳንዱ ሰው እንዲፈትሸው፣ እንዲሰነጣጥቀው፣ እንዲያብጠለጥለው፣ ስሜታችሁን ጠረጴዛ ላይ አድርጋችሁ ልታሳዩት አትችሉም::

በእርግጥ ውስጣዊ ስሜት በጣም ውስጣዊ በመሆኑ የስሜቱን መኖር እንኳን ቢሆን በማስረጃ አስደግፋችሁ ልታረጋግጡ አትችሉም:: ለዚህም ነው ሳይንስ ይህንን የማይቀበለው:: ይሁንና ማስተባበያው ሰብአዊ አይደለም:: ሲላው ቀርቶ ሳይንቲስቶቹም እንኳን ቢሆኑ ፍቅርን ያውቁታል:: ውስጣዊ ስሜትም አላቸው:: አንድ የሆነ ነገር አለ! ነገር ግን በአይን የሚታይ፣ በእጅ የሚዳሰስ አይደለም:: ደግሞም ለሌሎች ለማሳየት አይቻልም:: ቢሆንም ሆኖ ግን አለ::

ውስጣዊ ስሜት የራሱ የሆነ ተቀባይነት አለው:: ሆኖም በሳይንሳዊ ስልጠና የተካኑ ሰዎች በውስጣዊ ስሜታቸው ላይ ያላቸውን እምነት አጥተዋል:: የሚተማመኑትም በሌሎች ነገሮች ላይ ነው:: አንድ ሰው "በጣም ደስ ያለህ ትመስላለህ" ቢላችሁ የበለጠ ታምኑትና የደስታ ስሜት ይሰማችሁ ይጀምራል:: ሀያ ሰዎች እናንተን ለማስከፋት ቢያስቡ ሊያስከፏችሁ ይችላሉ:: በታ ቀኑን ሙሉ "በጣም የተከፋሽ ትመስያለሽ" ብለው ደጋግመው ይነግሩዋችኋል:: "በጣም ያዘንሽ ትመስያለሽ:: ምንድነው ነገሩ? ዘመድ ሞተብሻል እንዴ? ወይስ አንድ የሆነ ችግር አጋጥሞሻል?" ብለው በተደጋጋሚ ሲጠይቋችሁ መጠራጠር ትጀምራላችሁ:: ብዙ ሰዎች መከፋታችሁን እየነገሩዋችሁ ነው እና ተከፍታችሁ መሆን አለበት::

በሰዎች አመለካከት ላይ ጥገኛ ናችሁ:: የሰዎች አመለካከት ጥገኛ ሆናችሁ በመቆየታችሁ የውስጣዊ ስሜት ደብዛ ጠፍቶባችኋል:: ይህ ውስጣዊ ስሜታችሁን መልሳችሁ ማግኘት ይገባችኋል:: ምክንያቱም ውብ ነገሮች ሁሉ፣ መልካም ነገሮች በሙሉ እንዲሁም መለኮታዊ ነገሮች ጭምር ሊተወቁ የሚችሉት በውስጣዊ ስሜት ብቻ ነው::

ብሰዎች አመለካከት ጫና ስር መንበርከካችሁን አቁሙ:: ከዚያ ይልቅ ወደ ውስጥ መመልከት ጀምሩ .... ውስጣዊ ስሜታችሁ ነገሮችን እንዲነግራችሁ ፍቀዱለት:: እመኑትም:: ካመናችሁት ያድጋል:: ካመናችሁት የበለጠ አዳብራችሁ ታጠናክሩታላችሁ::

በሰዎች አመለካከት ላይ ጥገኛ ናችሁ:: የሰዎች አመለካከት ጥገኛ ሆናችሁ በመቆየታችሁ የውስጣዊ ስሜት ደብዛ ጠፍቶባችኋል:: ይህ ውስጣዊ ስሜታችሁን መልሳችሁ ማግኘት ይገባችኋል:: ምክንያቱም ውብ ነገሮች ሁሉ፣ መልካም ነገሮች በሙሉ እንዲሁም መለኮታዊ ነገሮች ጭምር ሊታወቁ የሚችሉት በውስጣዊ ስሜት ብቻ ነው::

ቪቬካናንዳ ወደ ራማክሪሽና ሄደና "እግዚአብሄር የሚባል ነገር የለም! ይህንን ደግሞ ማረጋገጥ እችላለሁ:: እግዚአብሄር የለም" አለው:: ሰውየው የምዕራባዊያንን ፍልስፍና በሚገባ የሚያውቅ ተገቢ አስተሳሰብ ያለው ተጠራጣሪ ሰው ነበር:: ራማክሪሽና ደግሞ ያልተማረ መሀይም ነበር:: እናም ራማክሪሽና "እሺ እንግዲህ አረጋግጥልኝ!" አለው::

ቪቬካናንዳ ብዙ አወራለት:: ያሉትን ማረጋገጫዎች በሙሉ አቀረበ:: ራማክሪሽናም ካዳመጠው በኋላ "ግን እኮ ውስጣዊ ስሜቱ የእግዚአብሄርን መኖር ይነግረኛል:: ደግሞም የመጨረሻው ባለስልጣን ይሄው ስሜት ነው::

እያልከው ያለኸው ነገር በሙሉ ክርክር ነው:: ለመሆኑ የአንተ ውስጣዊ ስሜት ምን ይልሀል?"

ቪቬካናንዳ ይህንን በተመለከተ ምንም ሀሳብ ስላልነበረው ትክሻዎቹን ሰበቀ:: ብዙ መፅሀፍትን አንብቧል:: ሀሳቡን የሚደግፉም ሆነ የሚያፈርሱ ማረጋገጫዎችና የመከራከሪያ ነጥቦችን ሰብስቧል:: እናም እግዚአብሄር መኖር አለመኖሩን አስመልክቶ በእነዚህ ማረጋገጫዎች መሰረት የውሳኔ ሀሳብ ላይ ለመድረስ ሞክራል:: ነገር ግን ወደ ውስጥ አልተመለከተም:: ውስጣዊ ስሜቱን ጠይቆ አያውቅም:: ይህ ደግሞ ሲበዛ አላዋቂነት ነው::

ራማክሪሽና "የመከራከሪያ ሀሳቦችህ ቆንጆ ናቸው:: በጣም ደስ ብለውኛል:: ነገር ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? አውቃለሁ! ውስጣዊ ስሜቴ የእግዚአብሄርን መኖር ይነግረኛል:: ውስጣዊ ስሜቴ እንደሚለኝ አደሰታለሁ፣ እታመማለሁ፣ ሆዴንም ያመኛል:: ዛሬ ደህና እንዳልሆንኩ ከነገረኝ ያመኛል:: ስለዚህ አሁንም የእግዚአብሄርን መኖር እየነገረኝ ነው:: ይሄ ደግሞ የክርክር ጉዳይ አይደለም አለው::

አክል አድርጎም፡ "በእርግጥ ማረጋገጫ ልሰጥ አልችልም:: ከፈለግህ ግን ላሳይህ እችላለሁ" አለ ራማክሪሽና:: ከዚያን ጊዜ በፊት እግዚአብሄርን ለማሳየት እንደሚቻል ለቪቬካናንዳ የነገረው ሰው አልነበረም:: እና ከመናገሩ በፊት ራማክሪሽና ዘሎ ብድግ አለ:: እንደ እብድ አድርጎት ነበር:: ዘለለና እግሮቹን በቪቬካናንዳ ደረት ላይ አደረጋቸው! የዚያን እንድ የሆነ ነገር ተፈጠረ:: አንድ የሆነ ሀይል ከዘለለ በኋላ ቪቬካናንዳ ለሶስት ሰአታት ያህል ራሱን ሳተ:: ነቅቶ አይኖቹን በገለ ጊዜም ፍፁም የተለየ ሰው ሆኖ ነበር::

"አሁንስ ምን ትላለህ?" አለው ራማክሪሽና:: "እግዚአብሄር አለ ወይስ የለም? ውስጣዊ ስሜትህ አሁን ምን ይላል?" ብሎ ጠየቀው:: ከዚያ በፊት በጭራሽ ተሰምቶት የማያውቅ ሰላም እና እርጋታ ሰፍኖበታል:: በውስጡ የሆነ አይነት የደስታ ስሜት፣ የሆነ የደህንነት ስሜት፣ የሆነ ከልክ ያለፈ የጤነኛነት ስሜት ነበር:: እናም እጉንብሶ እጅ በመንሳትና የራማክሪሽናን እግሮች በመንካት "አዎን፣ እግዚአብሄር አለ" በማለት ተናገረ:: እግዚአብሄር ሰው ሳይሆን የመጨረሻው የደህንነት ስሜት፣ የመጨረሻው የምቶች ስሜት፡ እንዲሁም "እኔ የዚህ አለም አካል ነኝ:: ይህ አለምም የእኔ ነው:: እዚህ ከሌላ አለም የመጣሁ ፍጡር አይደለሁም:: መጤ አይደለሁም" የሚያስብለው የመጨረሻው ስሜት ነው:: ይህ የመጨረሻው "ይህ ምሉዕነት እና እኔ የንጣጠልን አይደለምን" የሚለን ስሜት ለዘለአለም ሆኖ እንዲሆን ስትፈቅዱለት ብቻ ነው::



INFINIX HOT 8 LITE



እንደዚያ ማድረግን ጀምሩ! የተቻላችሁን ያህል እድል ስጡት:: ሁልጊዜም ከውጪ ያሉ ሃይሎችን አትመልከቱ፣ ውጫዊ አመለካከቶችንም አትመልከቱ:: ራሳችሁን ከአሁኑ በበለጠ በትንሹም ቢሆን ከጥገኝነት አላቅቁት:: የበለጠ ስሜት ይሰማችሁ:: ሀሳባችሁ ከስሜቶቻችሁ ያነሰ ይሁን::

እግዚአብሄር ሰው ሳይሆን የመጨሻው የደህንነት ስሜት፣ የመጨሻው የምቶች ስሜት፣ እንዲሁም "እኔ የዚህ ዓለም አካል ነኝ:: ይህ ዓለምም የእኔ ነው:: እዚህ ከሌላ ዓለም የመጣሁ ፍጡር አይደለሁም፣ መጤ አይደለሁም" የሚያስብለን የመጨረሻ ስሜት ነው::

ሂዱና ፅጌረዳ አበባን ተመልከቱ:: ታዲያ እንደ በቀቀን "ይህ አበባ በጣም ውብ ነው" ብላችሁ ደግማችሁ አትናገሩ:: ይሄ ምናልባት አመለካከት ሊሆን ይችላል:: ሰዎችም ይህንኑ ሲነግሩዋችሁ ቆይተዋል:: ከልጅነታችሁ ጀምሮ "ፅጌረዳ አበባ በጣም ውብ ነው" ሲባል እየሰማችሁ ነው ያደጋችሁት:: ስለዚህ ፅጌረዳ አበባ ስታዩ እንደ ኮምፒውተር "ይህ አበባ በጣም ውብ ነው" ብላችሁ እንደ በቀቀን ደጋግማችሁ ትናገራላችሁ:: በእርግጥ ግን ውብ መሆኑ ይታወቃችኋል? ይህ ውስጣዊ ስሜታችሁ ነውን? ካልሆነ ግን እንደዚህ ብላችሁ አትናገሩ::

እግዚአብሄር የሚታወቀው በውስጣዊ ስሜታችሁ በኩል ነው:: ጨረቃንም ስትመለከቱ ውስጣዊ ስሜታችሁ ካልነገራችሁ በስተቀር ውብ መሆንዋን አትናገሩ:: ይህን ስታደርጉ በአእምሯችሁ የያዛችሁት ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ ሀሳብ (ነገር) በሙሉ የተውሶ መሆኑን ታውቁና ትገረማላችሁ:: እናም በዘጠና ዘጠኝ ከመቶው የማይረባ ጥራጊ ሀሳብ ውስጥ እንድ ከመቶው ውስጣዊ ስሜታችሁ ተዘፍቋል:: ያንን አዋቂነት ወዱያ ማለትና ውስጣዊ ስሜታችሁን እንዲያገግም አድርጉት:: ስድስት የስሜት ህዋሳት አሉ:: አምስቱ ውጪያዊ ናቸው:: ስለዓለም ይነግሩዋችኋል:: አይኖች ስለ ብርሃን የሚነግሩዋችሁ ነገር አላቸው:: ያለ አይን ስለ ብርሃን ለማወቅ አትችሉም:: ጆሮዎች ስለ ድምፅ የሚነግሩዋችሁ ነገር አላቸው:: ያለ አይን ስለ ብርሃን ለማወቅ አትችሉም:: ጆሮዎች ስለ ድምፅ የሚነግሩዋችሁ ነገር ይኖራል:: ያለ ጆሮ ስለ ድምፅ የምታውቁት ነገር አይኖርም:: ስድስተኛ የስሜት ህዋስም አለ:: ይህ ውስጣዊ ስሜት ስለ እራሳችሁ እና ስለ ነገሮች ሁሉ የመጨረሻው ምንጭ የሚነግራችሁ ነገር አለ:: ይህንን ስሜት ማግኘት (መጨበጥ) አለባችሁ::

በተመስጦ ማሰላሰል ውስጣዊ ስሜትን ፈልጐ ማግኘት እንጂ ሌላ ምንም አይደለም::

# በዓለም ላይ ታላቁ ፍርሃት ያለው በሌሎች አመለካከቶች ውስጥ ነው

ህዝብን ካልፈራችሁ ከመቅሰበት በግ መሆናችሁ ያበቃል:: አንበሳም ትሆናላችሁ:: በልባችሁ ውስጥ ታላቅ ጩኸት ይነሳል:: ይህ ደግሞ የነፃነት ጩኸት ነው::

በእርግጥም ቡድሀ ይህንን የአንበሳ ጩኸት ብሎታል:: አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ፀጥታ በሚሰፍንበት ደረጃ ላይ ሲደርስ እንደ አንበሳ ይጮሃል:: ለመጀመያ ጊዜም ነፃነት ምን እንሆን ያውቃል:: ምክንያቱም አሁን የማንንም ሰው አመለካከት አይፈራም:: ሰዎች የሚሉት ነገር አያስጨንቀውም:: አዎን፣ ሰዎች ቅዱስም ሆነ እርኩስ ቢሏችሁ የሚመጣ ነገር የለም:: መላውን እናንተነታችሁን በብቸኝነት የሚዳኘው እግዚአብሄር ነው:: ደግሞም በእግዚአብሄር ዘንድ አንድ ሰው ምንም ማለት አይደለም:: እግዚአብሄር ማለት በቃ መላው ዓለም ነው::

ዋናው ጉዳይ ሰዎችን ፊት ለፊት መጋፈጥ አይደለም:: ዛፎችን፣ ወንዞችን፣ ተራሮችን፣ ከዋክብትን .... በአጠቃላይ መላውን አለም መጋፈጥ አለባችሁ:: የእኛ አለም ይህ ነው:: እኛም የእሱ አካል ነን:: አለምን መፍራት አስፈላጊ አይደለም::

የምንደብቀው ነገር ሊኖር አይገባም:: በእርግጥ ልደብቅ ብትሉም አትችሉም:: ልትደብቁት የምትሞክሩትን ነገር መላው ዓለም ገና ድሮ ያውቀዋል፤ እናንተ ከምታውቁት የበለጠም ስለእናንተ ያውቃል::

ሁለተኛውም ነጥብ ቢሆን የበለጠ ወሳኝነት አለው:: እግዚአብሄር ገና ድሮ ዳኝቷችኋል:: (ዋጋ ሰጥቷችኋል::) ይሄ ወደፊት የሚከሰት ነገር አይደለም:: ገና ድሮ ሆኗል:: እሱ ፍርዱን ሰጥቷል:: ስለዚህ ፍርድን በተመለከተ ያለው ፍርሃት የመነመነ ነው:: እዚህ ላይ ዋናው ጉዳይ በመጨረሻ ላይ የሚመጣው የፍርድ ቀን አይደለም:: በፍርሃት መንዘፍዘፍ አያስፈልጋችሁም:: የፍርዱ ቀን ገና በመጀመሪያው ዕለት ተከናውኗልና:: ገና እንደፈጠራችሁ ወዲያውኑ ፍርዱን ሰጥቷል:: የእሱ ፍጡራን ናችሁና በሚገባ ያውቃችኋል:: አንድ የሆነ ችግር ቢገጥማችሁ ተጠያቂው እናንተ ሳትሆኑ እሱ ነው:: ፈራችሁን





ብትስቱም ተጠያቂው እሱ እንጂ እናንተ አይደላችሁም:: እናንተ እንዴት ተጠያቂ ልትሆኑ ትችላላችሁ? እናንተኮ የገዛ ራሳችሁ ፍጡራን አይደላችሁም:: ስዕል ብትሰሩና የሆነ ነገር ቢበላሽ የብልሽቱ መንስኤ ስዕሉ ነው ለማለት አትችሉም:: መንስኤ የሚሆነው ሰዓሊው ነው::

ስለዚህ ህዝብን ወይም <ይሀን አድርጋችኋል፣ ይህንን አላደረጋችሁም> ብሎ የሚጠይቃችሁን ማህበረሰብ መፍራት አያስፈልጋችሁም:: ነፃ ናችሁ:: አንድ ሰው የገዛ ራሱን ለመሆን ሙሉ ለሙሉ ነፃ መሆኑን ሲያውቅ፣ ህይወት ለእሱ አስደናቂ ለውጥን የምታመጣለት መሆን ትጀምራለች::

ፍርሃት የእግር ብረቶችን ይፈጥራል፤ ነፃነት ክንፎችን ይሰጣችኋል::



# ነፃነት - ከ፡ ነፃነት - ለ

## ማንም ከምንም ነገር ከኃላፊነት ነፃ አይደለም

ከአንድ ነገር ነፃ ስለመሆን በጭራሽ አታስቡ - ሁልጊዜም ለአንድ ነገር ስትሉ ነፃ መሆናችሁን አስቡ እንጂ፡፡ ደግሞም የእነዚህ አስተሳሰቦች ልዩነት እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ከአንድ ነገር ነፃ ከመሆን እንፃር ሳይሆን ለአንድ ነገር ብላችሁ ነፃ ከመሆን አንፃር አስቡ፡፡ ለእግዚአብሄር እና ለእውነት ነፃ ሁኑ እንጂ ከህዝብ፣ ከቤተክርስቲያን ከዚህ ወይም ከዚያ ነገር ነፃ ለመሆን መፈለጋችሁን አታስቡ፡፡ አንድ ቀን ምናልባት ርቃችሁ ልትሄዱ ትችሉ ይሆናል፡፡ ግን በፍፁም ነፃ አትሆኑም፡፡ በጭራሽ! ይህ የሆነ አይነት ልጓም (መግቻ) ነው፡፡

ለምንድነው ህዝብን በጣም የምትፈሩት? እየተጐተታችሁ ከሆነ ፍርሃታችሁ የሚያሳየው መጐተታችሁን፣ እጅ መስጠታችሁን ነው፡፡ የትም ብትሄዱ በህዝብ የበላይነት ሜና ስር ሆናችሁ ትቀራላችሁ፡፡

እያልኩ ያለሁት እውነታዎችን መመልከት እንዳለባችሁ ነው ከህዝብ አንፃር ማሰብ እንደማያስፈልጋችሁ ነው የምገልፀው፡፡ በቃ ከራሳችሁ ተፈጥሮ አንፃር ብቻ አስቡ፡፡ ይህንን ሀሳባችሁን አሁኑኑ እርግፍ አድርጋችሁ ልትተውት ትችላላችሁ፡፡ ትግል ከገጠማችሁ ነፃ ልትሆኑ አትችሉም፡፡ በትግል የሚገኝ ነገር ስለሌለ እርግፍ አድርጋችሁ ልትተውት ትችላላችሁ፡፡

ችግሩ ህዝብ አይደለም፣ እናንተ ራሳችሁ ናችሁ ችግሩ፡፡ ህዝቡ እየጐተታችሁ አይደለም፡፡ እናንተ እራሳችሁ እየተሳባችሁ ነው፡፡ የምትሳቡት በሰው ሳይሆን ሳታውቁት ባደገባችሁ በገዛ ራሳችሁ ፀባይ ነው፡፡ ሁልጊዜም ሀላፊነትን እንድ የሆነ ቦታ በአንድ ሰው ላይ መደፍደፍ እንደሌለባችሁ አስታውሱ - ምክንያቱም በፍፁም ከኃላፊነት ነፃ አትሆኑም፡፡ ዞሮ ዞሮ በውስጣችሁ ኃላፊነቱ አለ፡፡



NIX HOT 8 LITE



አንድ ሰው ህዝብን አብዝቶ የሚቃረነው ለምንድነው? ምስኪን ህዝብ! እናንተስ ለምንድነው ህዝቡን በጣም የምትቃረኑት? ለምንስ ቁስል ትሸከማላችሁ?

እናንተ ካልተባበራችሁ በስተቀር ህዝብ ምንም ሊያደርግ አይችልም፡፡ ዋናው ጉዳይ የእናንተ ትብብር ነው፡፡ አሁኑኑ ትብብሩን እርግፍ አድርጋችሁ ልትተውት ትችላላችሁ፡፡ ይህንን ለማድረግ ከጣራችሁ ችግር ውስጥ ትወድቃላችሁ፡፡ ስለዚህ ከመቅፅበት አድርጉት፡፡ ይህ እንግዲህ በአሁኑ ቅፅበታዊ ግንዛቤያችሁ ውስጥ ያለ ነው፡፡ ትግል ከገጠማችሁ መሸነፋችሁን አውቃችሁ እንደገባችሁበት ማወቅ በመቻላችሁ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚያ ትግል ላይም ዋነኛ ትኩረታችሁ ህዝቡ ነው፡፡

በሚለዮናች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ የሚከሰተውም ይኸው ነው፡፡ አንዳንድ ወንዶች ከሴቶች ለመሸሽ ይፈልጋሉ፡፡ ህንድ ውስጥ የዚህ አይነቱ ነገር ለብዙ ክፍለ ዘመናት ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ከዚያ በሽሹ ቁጥር የበለጠ በሴቶች ይማረካሉ፡፡ ወሲባዊ ግንኙነትን ለማስወገድ ሲፈልጉ፣ መላው አእምሮዋቸው ወሲባዊ ይሆናል፡፡ የሚያስቡት ስለ ወሲብ ብቻ ነው፡፡ ሌላ ምንም የሚያስቡት ነገር አይኖራቸውም፡፡ ይፆማሉ፣ እንቅልፍ አይተኙም፣ ፓራናያማ እና ዮጋ ይሰራሉ፣ ይሄንና ያንን ያደርጋሉ፣ አንድ ሺህ አንድ መንገዶችን ይሞክራሉ፣ ነገር ግን ሁሉም ዋጋ የላቸውም፡፡ ከወሲብ ጋር ትግል በገጠሙ ቁጥር ስሜታቸው እጅግ ስለሚገር የበለጠ ትኩረት ያደርጉበታል፡፡ ይኸው ስሜታቸው ከሁሉ ነገር በላቀ ወሳኝ ይሆንባቸዋል፡፡

### አንድ ሰው ህዝብን አብዝቶ የሚቃረነው ለምንድነው? ምስኪን ህዝብ! እናንተስ ለምንድነው ህዝቡን በጣመ የምትቃረኑት? ለምንስ ቁስል ትሸከማላችሁ?

ህዝብን በጣም የምትፈሩ ከሆነ እናንተንም የሚገጥማችሁ ነገር ይኸው ነው፡፡ እናንተ ካልተባበራችሁ በስተቀር ህዝቡ ምንም ነገር ሊያደርግባችሁ አይችልም፡፡ ስለዚህ ጥያቄው ያለው በእናንተ መንቃት ላይ ነው፡፡ አትተባበሩ!

ምን አስተዋልኩ መሰላችሁ? ማንኛውንም አይነት ነገር ቢያጋጥማችሁ ተጠያቂ እናንተ ራሳችሁ ናችሁ፡፡ ሌላ ማንም ሰው ሊጋጣሚውን

አላመጣባችሁም፡፡ እንዲሆን ፈልጋችሁት ስለነበር የሆነው ነገር ሆነ፡፡ አንድ ሰው የሚጠቀምባችሁ እንዲጠቀምባችሁ ስለፈለጋችሁ ነው፡፡ አንድ ሰው እስር ቤት ውስጥ የሚያስገባችሁ መተስር በመፈለጋችሁ ነው፡፡ ባታውቁትም በሆነ መንገድ ይህንን ሳትፈልጉት አልቀራችሁም፡፡ ምናልባት ይህን የደህንነታችሁ ዋስትና አድርጋችሁ ቆጥራችሁት ይሆናል፡፡ የሰጣችሁት ስም ምናልባት የለየ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለመታሰር ስትመኙ ነበር - ምክንያቱም በእስር ቤት ውስጥ ያለ ሰው የደህንነት ስሜት ይሰማዋልና፡፡ የሚያጋጥመውም ችግር አይኖርም፡፡

እንደዚያም ሆኖ ከእስር ቤቱ ግድግዳዎች ጋር አትታገሉ፡፡ ለደህንነታችሁ ያላችሁን ፅኑ ምኞት እና ህዝቡ እንዴት ሊጠቀምባችሁ እንደሚችል ድረሱበት፡፡ ከህዝቡ አንድ የሆነ ነገር መጠየቅ አለባችሁ እውቅና፡ ዝና፡ ክብር፡ መታመን ሊሆን ይችላል የምትጠይቁት ከጠየቃችሁ ደግሞ ለሰጣችሁ ነገር መልሳችሁ መክፈል ይኖርባችኋል፡፡ ከዚያም ህዝቡ "እሺ ክብርን ሰጠንህ፡ አንተ ደግመ ነፃነትን ስጠን" ይላል፡፡ በቃ ቀላል ድርድር ነው፡፡ ነገር ግን ህዝቡ በጭራሽ ምንም ነገር አላደረጋችሁም፡፡ ከመነሻው ጀምሮ ተጠያቂዎቹ እናንተ ናችሁ፡፡ ስለዚህ ከራሳችሁ መንገድ ላይ ዘወር በሉ!



INFINIX HOT 8 LITE

# ዋናውን ፊታችሁን አግኙ

## "ፈሪ ለመሆን ድፍረቱ የሌለው፡ እሱ ጀግና ነው"

በቃ ራሳችሁን ሁኑ እንጂ ስለ ዓለም በትንሹም እንኳን ግድ አይሰጣችሁ፡፡ ከዚያ በኋላ በልባችሁ ውስጥ አስደናቂ የመዝናናት እና ጥልቅ የሆነ የሰላም ስሜት ይሰማችኋል፡፡ የዜን ሰዎች <ዋናው ፊታችሁ> ብለው የሚጠሩት ይህንን ነው፡፡ ውጥረቶች፡ <ሊታይ ሊተይ> ባይነት፡ ግብዝነት የሌለበት እንዲሁም እንዴት አይነት ባህርይ ሊኖራችሁ እንደሚገባ የሚደነግጉ የስነ - ምግባር ደንብ ተብዬዎች የሌለበት ዘና ያለ ሁኔታም ነው፡፡

ደግሞም <ዋና ፊት> ሲባል እጅግ ውብ ቅኔያዊ አገላለፅ እንጂ የለየ ፊት አላችሁ ማለት አለመሆኑን አስታውሱ፡፡ አሁን ያላችሁ ፊት ራሱ ያለበትን ውጥረቶች ያስወግዳል፡ ይኸው ፊታችሁ ዘና ይላል፡ ይኸው የአሁን ፊታችሁ ሌሎችን የበታች አድርጐ የማያይ ይሆናል፡፡ እንግዲህ በእነዚህ አዳዲስ አሴቶች ስር አሁን ያላችሁ ፊት ዋና ፊታችሁ ይሆናል፡፡

አንድ ጥንታዊ ጥቅስ አለ፡<ፈሪ ለመሆን ድፍረቱ የሌለው - እሱ ታላቅ ጀግና ነው፡፡>

ፈሪ ብትሆኑ ምን ችግር አለው? በቃ ፈሪ ናችሁ፡፡ ይሄ ፍፁም ጥሩ ነው፡፡ ፈሪዎችም አስፈላጊ ናቸው፡፡ አለበለዚያ ጀግኖችን ከየት ልናገኝ እንችላለን? ጀግኖች እንዲፈጠሩ የኋላ መነሻ (መደብ) ይሆኑ ዘንድ ፈሪዎችም የግድ አስፈላጊ ናቸው፡፡

ብቻ ምንም ይሁን ምን ራሳችሁን ሁኑ፡፡

ችግሩ ከዚህ በፊት በፍፁም ራሳችሁን በቻ እንድትሆኑ የነገራችሁ ሰው ያለመኖሩ ነው፡፡ በተራ ነገሮች ላይ ሳይቀር <እንዲህ መሆን ይገባችኋል፡ እንደዚያ መሆን አለባችሁ> እያለ ሁሉም ሰው የማያገባው ነገር ውስጥ ይገባል፡፡

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ትንሽ ልጅ እያለሁ እንዴት መሆን እንዳለብኝ ሲነገረኝ የሰጠላኝ ነበር፡፡ መምህራኖቼም ይህን ጊዜ ሊደልሉኝ ይጀምራሉ፡፡ "በአገባቡ ፀባይህን ካላመርክ ልዩ ተሰጥኦ ያለው ልጅ ልትሆን ትችላለህ" ይሉኛል፡፡

እኔ ግን "ልዩ ተሰጥኦ ገደል ይግባ! በቃ እኔ ራሴን ለመሆን ነው የምፈልገው" እላቸዋለሁ፡፡ እግሮቼን ጠረጴዛ ላይ አድርጌም እቀመጥ ነበር፡፡ በዚህ ሁሉም አስተማሪዎች ይናደዳሉ፡፡ "ምን ዓይነት ፀባይ ነው ያለህ?" ይሉኛል፡፡

እኔም "ጠረጴዛው ምንም ነገር አላለኝም፡፡ ይሄ ደግሞ በእኔና በጠረጴዛው መካከል ያለ ስምምነት ነው፡፡ ስለዚህ ለምን በጣም ትበሳጫላችሁ? እግሮቼን እናንተ ጭንቅላት ላይ አላደረግሁ! ልክ እንደ እኔ ሁሉ ዘና ማለት ይገባችኋል፡፡ በዚህ መልኩ እያስተማራችሁኝ ያለውን የማይረባ ነገር በተሻለ መንገድ ልረዳው የምችል ይመስለኛል፡፡"

የክፍሉ አንደኛው ወገን ግድግዳ ላይ ቀንጆ መስኮት ነበር፡፡ በውጪ በኩል ደግሞ ዛፎች፣ ወፎችና እርግቦች አሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በመስኮቱ በኩል ወደ ውጪ ስለምመለከት አስተማሪዎች ይመጡና "ወደ ትምህርት ቤት የመጣኸው ለምንድነው?" ይሉኛል፡፡

ምን እንደምላቸው ታውቃላችሁ? "ምክንያቱም በቤታችን ውስጥ እዚህ እንዳለው መስኮት ወደ ውጪ ሰማዩን የሚያሳይ መስኮት የለም፡፡ በቤታችን ዙሪያም ወፎችና እርግቦች የሉም፡፡ ቤታችን ከተማ መሀል በመሆኑ፣ በዙሪያው ሌሎች ቤቶች ስላሉና አካባቢው የተጨናነቀ ስለሆነ ወፎች ወደዚያ አይመጡም፡፡ እርግቦችም ቢሆኑ በዝማሬያቸው የዚያ አካባቢ ሰዎች የሚደሰቱ አይመስላቸውም ...."

"እዚህ የምመጣው እናንተን ለማዳመጥ ከመሰላችሁ እርሱት! የወር ሂሳብ እስከከፈልኩ ድረስ እናንተ አገልጋዮቼ መሆናችሁን አስታውሱ፡፡ በፈተና ብወድቅ መጥቼ አቤቱታ አላቀርብባችሁም፡፡ ደግሞም አላዝንም፡፡ ነገር ግን እሙቱን ሙሉ ውጪ ያሉትን እርግቦች እያዳመጥኩ እናንተን የማዳምጥ መስዬ ብታይ ግብዝ ህይወት መኖር ጀመርኩ ማለት ይሆናል፡፡ ግብዝ መሆን ደግሞ አልፈልግም፡፡"

በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ መምህራንና ፕሮፌሰሮች በተወሰነ መልኩ፣ እነሱ ገደብ ባበጁላቸው መንገዶች ብቻ እንድትንቀሳቀሱ ይፈልጋሉ፡፡ በዚያን ዘመን በትምህርት ቤታችን ውስጥ ቆብ ማድረግ አስፈላጊ (ግዴታ) ነበር፡፡ አሁንም ምናልባት እንደዚያ ሊሆን ይችላል፡፡ እኔ ቆብ ማድረግ የምቃወምበት ምንም ምክንያት የለኝም፡፡ ከዩኒቨርሲቲ ከወጣሁ ጀምሮ ቆብ ማድረግ ጀምሬያለሁ፡፡ ነገር ግን ከዩኒቨርሲቲ እስከ ወጣሁበት ጊዜ ድረስ አንድም ቀን ቆብ አጥልቄ አላውቅም



INFINIX HOT 8 LITE
AI TRIPLE CAMERA



ነበር፡፡ በሁኔታዬ ይጨነቅ የነበረው የመጀመሪያው መምህሬ "የትምህርት ቤቱን ደንብ እየተላለፍክ ነው፡፡ ቆብህ የታለ?" አለኝ፡፡

"የትምህርት ቤቱን የስነ-ምግባር ደንብ አምጣና አሳየኝ፡፡ ሁሉም ተማሪ ቆብ ማጥለቅ እንዳለበት የተጠቀሰ ነገር አለ? ከሌለ ከትምህርት ቤቱ ደንብ ውጪ የሆነ ነገር እንዳደርግ እያስገደድከኝ ነው ማለት ነው" አልኩት፡፡

ወደ ትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ ዘንድ ወሰደኝ፡፡ እኔም ለትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ "የተባልኩትን ነገር ለማድረግ ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነኝ፡፡ ብቻ ቆብ ማጥለቅ ግዴታ ስለመሆኑ የት ቦታ ላይ እንደተፃፈ አሳዩኝ፡፡ ግዴታ ከሆነና በዚህ ሳልስማማ ብቀር ሌላው ቀርቶ ትምህርት ቤቱን ለቅቄ መሄድ እችላለሁ፡፡ መጀመሪያ ይህ ደንብ የት ቦታ እንደተፃፈ ብቻ አሳዩኝ" ብዬ ነገርኩት፡፡

ምንም የተፃፈ ደንብ የለም፡፡ እናም ንግግሬን ቀጠልኩ፡፡ "ለምን ቆብ ማጥለቅ እንዳለብኝ ሌላ ምክንያት ልትሰጡኝ ትችላላችሁ? የአእምሮዬን የማሰብ ችሎታ ይጨምርልኛል ወይ? እድሜዬንስ ይጨምርልኛል? ጤናማ ያደርገኛል?" ብዬ ጠየቅኩ፡፡ "እስከማውቀው ድረስ ህንድ ውስጥ ቆብ የማይደረግበት ብቸኛው ግዛት ቤንጋል ነው፡፡ ይሄ ደግሞ አብዛኞቹ የላቀ የማሰብ ችሎታ ያላቸው ብልህ ሰዎች የሚወጡበት የሃገሪቱ ክፍል ነው፡፡ ፑንጃብ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ በዚያ ሰዎች ከቆብ ይልቅ ሰፋፊ ባርኔጣ ያደርጋሉ፡፡ ባርኔጣቸው በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ የማሰብ ችሎታቸው እንዳያመልጣቸው በባርኔጣው ደርተው ሊይዙት የሚሞክሩ ይመስላሉ፡፡ ይህ ቦታ ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ ብዙዎቹ ዝቅተኛ የማሰብ ችሎታ ያላቸው ሰዎች የሚኖሩበት ነው" አልኩ፡፡

የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ "እያልከው ያለኸው ነገር እውነትነት አለው፡፡ ሆኖም ይህ የትምህርት ቤቱ ደንብ ነው፡፡ አንተ ቆብ ማድረግ ካቆምክ ሌሎች ተማሪዎችም ያቆማሉ" አለኝ፡፡

ይህን ጊዜ "ታዲያ ምን የሚያስፈራ ነገር አለ? ማንም ተማ ከልቡ ያልተቀበለው ከሆነ፣ በቃ ይህንን ልምድ ወዲያ ማለት" አልኩ፡፡

ፍፁም አላስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንኳን ሳይቀር ራሳችሁን እንድትሆኑ ማንም ሰው አይፈቅድም፡፡

በልጅነቴ ፀጉሬ ረጅም ነበር፡፡ ቤታችን እና የአባቴ ሱቅ የተያያዙ ስለነበር ሱቁ ውስጥ ወጣ፣ ገባ ማለት እበዛለሁ፡፡ ቤታችን ከሱቁ ኋላ ነበር፡፡ ወደ ቤት ለመግባት በሱቅ በኩል ማለፍ ያስፈልጋል፡፡ ሰዎች ሲያዩኝ "ይህች ልጅ የማናት?" ብለው

ይጠይቃሉ:: ምክንያቱም ፀጉሬ በጣም ረጅም ስለሆነ ወንድ አላመስላቸውም:: ወንድ ልጅ እንደዚያ ረጅም ፀጉር ይኖረዋል ብለው አያስቡም::

አባቴ በጣም ያፍርና እየተሽማቀቀ "የእኔ ልጅ ነው" ይላል::

"እንዴ!" ይላሉ ሰዎቹ:: "ታዲያ ይሄ ሁሉ ፀጉር!"

አንድ ቀን፣ የወትሮው የተለመደ ፀባዩ ባይሆንም በጣም ስላፈረ እና ስለበሳጨ መጣና እሱ ራሱ ፀጉሬን ምድምድ አድርጎ ቆረጠው:: ሱቁ ውስጥ ጨርቅ የሚቆርጥበትን መቀስ አምጥቶ ነበር ፀጉሬን የቆረጠው:: ምንም አላልኩትም:: በዚህም በጣም ተገረመ:: "ምንም የምትለው ነገር የለህም?" ብሎ ጠየቀኝ::

"በራሴ መንገድ ማለት የምፈልገውን ነገር እልሀለሁ" አልኩት::

"ምን ማለትህ ነው?"

"ታየዋለህ" አልኩትና እናም ከቤታችሁን ፊት ለፊት ፀጉር ቤት ወደነበረው የአፕየም ሱሱኛ ወደ ሆነው ፀጉር ቆራጭ ሄድኩ:: በዚያን ጊዜ አከብረው የነበረው ብቸኛው ሰው ነበር:: ከእሱ ፀጉር ቤት አጠገብ በተርታ ፀጉር ቤቶች ነበሩ:: እኔ ግን ሰውየውን በጣም እወደዋለሁ:: የተለየ ባህርይ ያለው ሰው ነው:: ፐሉበት እሱም በጣም ይወደኛል:: አንዳንድ ጊዜ ለረጅም ሰአታት አብረን ሆነን እናወራለን::

ወደ እሱ ሄድኩና "ፀጉሬን ሙሉ በሙሉ ላጭልኝ" አልኩት::

ህንድ ውስጥ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ፀጉራቸውን የሚላጩት አባት ሲሞትባቸው ብቻ ነው:: የአፕየም ሱሰኛ ቢሆንም እንኳን ፀጉር ቆራጩ ለጥቂት ጊዜ ድንግጥ አለና "ምን ተፈጠረ? አባትህ ሞተ እንዴ?" ብሎ ጠየቀኝ::

"ስለዚህ አትጨነቅ:: ያልኩህን ነገር ብቻ አድርግ:: አንተን የሚያስጨንቅህ ነገር የለም! ይልቅ ፀጉሬን እንደም ሳይቀር ሙሉ በሙሉ ላጭልኝ::"

ፀጉር ቆራጩም "ትክክል ነህ:: እኔን የሚመለከተኝ ምንም ነገር የለም:: አባትህ ከሞተም ሞተ ነው:: በቃ!" አለና ስራውን ጀመረ::

ፀጉሬን ሙልጭ አድርጎ ከላጨልኝ በኋላ ወደ ቤት ሄድኩ:: በስቱ በኩል አልፈ ሰገባ አባቴ እና ሁሉም ደንበኞቹ ተመለከቱኝ:: "ምን ሆኖ ነው? የማነው ልጅ? አባቱ [illegible] ጠየቁት::

INFINIX HOT 8 LITE
AI TRIPLE CAMERA



"የእኔ ልጅ ነው:: እኔም በህይወት አለሁ! ነገር ግን አንድ ነገር እንደሚያደርግ አውቅ ነበር:: ተገቢ ምላሽ ነው የሰጠኝ" አለ አባቴ::

በየሄድኩበት ቦታ ሁሉ ሰዎች "ምን ነካህ? አባትህ ሙሉ ጤነኛ አይደለም እንዴ?" ይሉኛል::

"ሰዎች ጊዜያቸው ሲደርስ ይሞታሉ:: የተጨነቃችሁት ለእሱ ነው:: ስለ እኔ ፀጉር አልተጨነቃችሁም" ብዬ እመልስላቸዋለሁ::

አባቴ ለመጨረሻ ጊዜ ከፍቃዴ ውጪ ያደረገብኝ ነገር ይሄ ነበር:: ምክንያቱንም ምላሹ የበለጠ አደገኛ እንደሚሆን ያውቃል! "ይህን ሁሉ ነገር ያመጣኸው አንተ ራስህ ነህ:: ምን ቅሬታን የሚፈጥር ነገር አለ? <የእኔ ልጅ ናት> ብለህ መመለስ ትችል ነበር:: እኔ እንደዚያ ብትል ተቃውሞ የለኝም:: በምርጫዬ ውስጥ ጣልቃ መግባት አልነበረብህም:: እንደዚህያ ማድረግህ እጅግ ኋላ ቀርነት ነው:: ለእኔ የሆነ ነገር ከማለት ይልቅ ከመሬት ተነስተህ ፀጉሬን መቁረጥ ጀመርክ" ብዬው ነበር::

ማንም ሰው ቢሆን ማንንም እራሱን እንዲሆን ገም ብሎ አይተወውም:: በዚህም እነዚያን ሁሉ ሀሳቦች በጣም በጥልቀት ስለተማራችኋቸው የራሳችሁ ሀሳቦች ይመስሉዋችኋል:: አሁን ግን ዘና በሉ:: እነዚያን ሁሉ ያደጋችሁባቸውን ሁኔታዎች እርሱዋቸው:: ከዛፎች ላይ እንደሚረግፉ ደረቅ ቅጠሎች እራግፏቸው:: ከፕላስቲክ የተሰሩ ቅጠሎች፣ ከፕላስቲክ የተሰሩ አበቦች ያሉት ዛፍ ከመሆን የተራቆተ ዛፍ መሆን ይሻላል:: እንደዚያ መሆን እስቀያሚ ነውና::

ዋናው ፊት ማለት የየትኛውም አይነት ግብረ-ገብነት፣ ሀይማኖት፣ ማህበረሰብ፣ ወላጅ፣ መምህር፣ የሀይማኖት አባት እንዲሁም የማንም ሰው አስተሳሰብ ተገዢ አለመሆን ነው:: በቃ ሀይወታችሁን በራሳችሁ ውስጣዊ ስሜት መሰረት መኖር ማለት ነው:: አስተውሎት (የማስተዋል ችሎታ) አላችሁ:: ዋናው ፊታችሁም አብሮዋችሁ አለ::

# አደጋ ውስጥ በመኖር የሚገኝ ደስታ

# 4

## አደገኛ አጋጣሚዎችን መፈለግ

ደፋሮች ያለማወላወል የትም ይሄዳሉ፡፡ አደገኛ አጋጣሚዎችን በሙሉ ይፈልጋሉ፡፡ የህይወት ፍልስፍናቸው እንደ መድህን ኩባንያዎች አይደለም፡፡ የህይወት ፍልስፍናቸው እንደ ተራራ ወጪ፣ ሞተር በሌለው አውሮፕላን እንደ ሚንሳፈፍ እንዲሁም በማዕበል ላይ እንደማንሸራተት ሰው ነው፡፡ የሚንሸራተቱትም በውጪያዊ ባህሮች ላይ ብቻ ሳይሆን በውስጣቸው ባሉት ባህሮች ውስጥም ጭምር ነው፡፡ በአልፕስ እና በሂማሊያስ ተራሮች ላይ የሚወጡት ከወጪ ብቻ አይደለም፣ በውስጣቸውም የተራራ አናቶችንም ይሻሉ፡፡



# ህያው የምትሆኑት በአደጋ ውስጥ ብቻ ነው

በስጋት መኖር ማለት ህይወትን መኖር ነው፡፡ በስጋት ካልኖራችሁ ህይወትን አትኖሩትም፡፡ ህይወት የሚያብበው በአደጋ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ደህንነት ተጠብቆ እያለ ህይወት በጭራሽ አያብብም፡፡ የሚያብበው በስጋት ውስጥ ብቻ ነው፡፡

ደህንነት ሊሰማችሁ ሲጀምር የረጋ ኩሬ ትሆናላችሁ፡፡ ኃይላችሁን አታንቀሳቅሱትም፡፡ ከዚያም ትፈራላችሁ፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው እንዴት ወደማይታወቅ ቦታ እንደሚሄድ አያውቅም፡፡ ታዲያ ለምን ለዚህ ሀላፊነት ትወስዳላችሁ? የሚታወቅ ነገር ለደህንነት የበለጠ አስተማማኝ ነው፡፡ ስለዚህ በለመዳችሁት ነገር ተጠምዳችሁ ትቀራላችሁ፡፡ ይህ የለመዳችሁት ነገር ደግሞ እያንገፈገፋችሁ፣ እያሰለቻችሁ ይሄድና በውስጡ በመሆናችሁ ትቸገራላችሁ፡፡ እንደዚያም ሆኖ የምታውቁት እና የሚመቻችሁ ይመስላችኋል - ቢያንስ ይታወቃልና፡፡ የማታውቁት ነገር ውስጣችሁን ያስረደዋል፡፡ ስለማይታወቅ ነገር ገና ማሰብ ስትጀምሩ የፍርሃት ስሜት ይወራችኋል፡፡

በአለም ላይ ሁለት አይነት ሰዎች ብቻ ናቸው ያሉት፡፡ በምቾት ለመኖር የሚፈልጉት ሞትን ይሻሉ፡፡ ምቹ የሆነ መከን - መቃብር ይፈልጋሉ፡፡ መኖር የሚፈልጉት ደግሞ በስጋት ውስጥ መኖርን ይመርጣሉ - ምክንያቱም ህይወት የሚነፋው አደጋ ሲኖር ብቻ ነው፡፡

ተራራ ላይ ወጥታችሁ ታውቃላችሁ? የምትወጡት ከፍታ በጨመረ ቁጥር የመውደቁ አደጋ የበለጠ አፍላነት፣ የበለጠ ወጣትነት ይሰማችኋል፡፡ በህይወትና በሞት ሲጨምር፣ ከጉን ያለው ገደል የበለጠ ጥልቅ ሲሆን፣ በህይወትና በሞት መካከል ብትሆኑም፣ ነፍሳችሁ በሞትና በህይወት መካከል ተወጥራም፣ ይበልጥ ህያው ትሆናላችሁ፡፡ በዚያን ጊዜ መሰላቸት የለም፡፡ ያን ጊዜ ያለፈ ጊዜ ጭጋግ፣ የወደፊት ጊዜ ጉጉት አይኖሩም፡፡ ያኔን ጊዜ የአሁኑ ቅፅበት እንደነበልባል በጣም የሰላ ይሆናል፡፡

በማዕበል ላይ ስትንሸራተቱ ወይም በበረዶ ላይ ስትንሻረሩ፣ አሊያም በሰገነ አልባ አውሮፕላን ሰማይ ላይ ስትንሳፈፉ (ህይወትን የማጣት አደጋ በተጋረጠበት በየትኛውም ቦታ) አስደናቂ የደስታ ስሜት ይኖራችኋል ምክንያቱም ህይወትን የማጣቱ አደጋ በአስደናቂ ሁኔታ ህያው ያደርጋችኋል፡፡ ስለዚህ ሰዎች በአደገኛ ስፖርቶች ይሳባሉ፡፡

በዓለም ላይ ሁለት አይነት ሰዎች ብቻ ናቸው ያሉት፡፡ በምቾት ለመኖር የሚፈልጉት ሞትን ይሻሉ፡፡ ምቹ የሆነ መካነ- መቃብር ይፈልጋሉ፡፡ መኖር የሚፈልጉት ደግሞ በስጋት ውስጥ መኖርን ይመርጣሉ፡- ምክንያቱም ህይወት የሚፋፋው አደጋ ሲኖር ብቻ ነው፡፡

ሰዎች ተራሮች ላይ ይወጣሉ፡፡ አንድ ሰው ኤድመንድ ሒላሪን "የኤቨረስትን ተራራ ለመውጣት ለምን ሞከርክ?" ብሎ ጠይቆት ነበር፡፡ የመለሰለት፡፡ ድርጊቱ አደገኛ ነበር፡፡ ከዚያ በፊት ብዙ ሰዎች ሞተዋል፡፡ ለሰላሳ፣ ለሰባ አመታት ያህል ሰዎች በቡድን ሆነው ወደዚያ ሲሄዱ ቆይተዋል፡፡ ሞት የማይቀር እጣ ፈንታቸው ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሰዎቹ ይህንን ተራራ ለመውጣት ወደ ስፍራው ይሄዳሉ፡፡ የሚስባቸው ምን ነበር?

ከፍ ወዳለ ስፍራ ላይ ስትደርሱ፣ ከተረጋጋው አለም ርቃችሁ ስትሄዱ፣ ከተለመደው ህይወት ስታፈነግጡ በድጋሚ የዱካ ሰው ትሆናላችሁ፣ የእንስሶች አለም አንድ አካል ትሆናላችሁ፡፡ እንደገና እንደ አንበሳ ወይም እንደ ነብር ትኖራላችሁ፡፡ ወይም እንደ ወንዝ ትሆናላችሁ፡፡ በድጋሚ የበለ እየራቃችሁ እንደወፍ በሰማይ ላይ ትበራላችሁ፡፡ የደህንነት ስሜት በሚሰማችሁ በእያንዳንዱ ቅፅበት የባንክ ሂሳብ፣ ሚስት፣ ባል፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ቤተ - ክርስቲያን፣ ዝና እንዳቸውም ሳይቀሩ እየራቁ .... እየራቁ ... ይደበዝዛሉ፡፡ እናንተም ብቸኛ ትሆናላችሁ፡፡

ለዚህም ነው ሰዎች በስፖርቶች ላይ ዝንባሌ የሚያድርባቸው፡፡ ይህም ቢሆን ታዲያ እውነተኛ አደጋ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በጊዜ ብዛት በስፖርቶቹ በጣም ልትካኑባቸው ትችላላችሁ፡፡ ልትማሩዋቸውና ልትሰለጥኑ ትችላላችሁ፡፡ ይሄ ከወዲሁ በጣም የታሰበበት አደጋ ነው፡፡ (የታሰበበት አደጋ የሚለውን እንደጠቀም እንደምትፈቅዱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡) በተራራ ላይ እየገለፅ እንዳጠተም እንደምትፈቅዱልኝ... መውጣት ስፖርት፣ ስለጠና ልትወስዱ እንዲሁም ተገቢውን ቅድመ - ጥንቃቄ መውጣት ስፖርት ትችላላችሁ፡፡ ወይም ደግሞ በከፍተኛ ፍጥነት እያሽከረከራችሁ ልትወስዱ ትችላላችሁ፡፡ ወይም ደግሞ በከፍተኛ ፍጥነት እያሽከረከራችሁ ለአት መቶ ማይሎች ልትሸፍኑ ትችላላችሁ፡፡ ይሄም አደገኛ እና ልብ - ሰቀላት መቶ ማይሎች ልትሸፍኑ ትችላላችሁ፡፡ ከዚያ አንጠልጣይ ነው፡፡ ነገር ግን በጊዜ ሂደት ልትካኑበት ትችላላችሁ፡፡ ከዚያ የድርጊቱ አደገኛ መሆን የሚታየው ከውጪ ለሚመለከቱዋችሁ እንጂ ለእናንተ አይሆንም፡፡ አደጋው ቢኖርም እንኳን ያን ያህል አይደለም፡፡ ደግሞም እነዚህ አደጋዎች አካላዊ ብቻ ናቸው፡፡ አደጋው ያለው በሰውነት ላይ ብቻ ነው፡፡

‹በስጋት ውስጥ ኑሩ› ስላችሁ በአካላዊ (በሰውነት) አደጋ ብቻ ሳይሆን በስነ ልቦናዊና በመጨረሻም በመንፈሳዊ አደጋ ውስጥ ጭምር ኑሩ ማለቴ ነው፡፡ አደጋው ምናልባትም መመለሻ የሌለበት ከፍታ ላይ ይደርስ ይሆናል፡፡ ቡድሃ ‹አናጋሚን› ብሎ የሚጠራው ቃል ይኸው ሲሆን ትርጉሙም መመለሻ የሌለው ሰው ማለት ነው፡፡ መመለስ ወደማይቻልበት ከፍታ ላይ ይደረሳል፡፡ ከዚያም በተ ጭልጥ ተብሎ ይጠፋል፡፡ በጭራሽ ተመልሶ አይመጣም፡፡

## ሁሉም ነገር ሲሟላላችሁ መሞት ትጀምራላችሁ

‹በስጋት ውስጥ ኑሩ› ስላችሁ የአንድ ከተማ ከንቲባ ወይም የኮርፖሬሽን አባል ሆናችሁ በህይወታችሁ ተራ መልካም ስም (ዝና) ኑሯችሁ እትኑሩ ማለቴ ነው፡፡ የሄ ህይወት አይደለም፡፡ ሚኒስቴር ብትሆኑ ወይም ጥሩ ስራ ይዛችሁ በባንክ ቤት የተትረፈረፈ ገንዘብ ኑሯችሁ ‹ሁሉ በጁ - ሁሉ በደጁ› ብትሆኑ ይሄ ህይወት አይባልም፡፡ ሁሉም ነገር ሲሟላላችሁ እሰኪ እሰቡት፡፡ በቃ እየሞታችሁ እኮ ነው፡፡ ምንም የሚፈጠር ነገር የለም፡፡ ሰዎች ያከብሯችሁ ይሆናል፡፡ ስትሞቱም ብዙ ቁጥር ያለው ህዝብ እስከሬናችሁን በሰልፍ ይከተልም ይሆናል፡፡ ይሄ ሁሉ ጥሩ ነው፡፡ እለቀ፡፡ ፎቶዎቻችሁ በየጋዜጦቹ ላይ ይወጣና በየርዕስ - አንቀፆች ላይ ይፃፍላችኋል፡፡ ከዚያ በኋላ ሰዎች ይረሱዋችኋል፡፡ በቃ ህይወታችሁን ሙሉ የኖራችሁት ለነዚህ ነገሮች ስትሉ ብቻ ነውን?

አስተውሉ - አንድ ሰው ህይወቱን በሙሉ በተራ አለማዊ ነገሮች ሊያባክን ይችላል፡፡ መንፈሳዊ መሆን እነዚህ ጥቃቅን ነገሮች ያን ያህል ብዙ አስፈላጊ ተደርገው መታየት እንደማይገባቸው መገንዘብ ማለት ነው፡፡ እነዚህ ትርጉሙ-

ቢስ ናቸው እያልኩ ግን አይደለም፡፡ እነዚህ ነገሮች ትርጉም- አዘል ናቸው፡፡ ነገር ግን የምታስቡትን ያህል ትርጉም አዘል አይደሉም፡፡

ገንዘብ አስፈላጊ ነገር፡ መሰረታዊ ፍላጎት ነው፡፡ ነገር ግን ገንዘብ ግብ አይደለም፡ ሊሆንም አይችልም፡፡ ቤት በእርግጥም አስፈላጊ፡ መሰረታዊ ፍላጎትም ነው፡፡ እኔ መናኝ አይደለሁም፡፡ ደግሞም ቤታችሁን አጥፍታችሁ ወደ ሂማሊያ ተራራ እንድትሸሹ አልፈልግም፡፡ ቤቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ቤቱ የሚያስፈልገው ለእናንተ ነው፡፡ ሀሳቤን አዛብታችሁ እንዳትረዱት፡፡

ሰዎችን ልብ ብዬ ሳያቸው ሁሉም ነገር መላቅጡ እንደጠፋባቸው እገነዘባለሁ፡፡ የሚኖሩት ለቤቱ መኖር የእነሱ መኖር አስፈላጊ እንደሆነ አድርገው ነው፡፡ ለቤታቸው ሲሉ ነው፡፡ ህይወታቸውን የሚገፉት፡፡ ለባንክ ሂሳባቸው ህልውና እንደሚፈልጉ ሁሉ፡ በቃ ገንዘብ ማጋበሳቸውን ይገፉበትና ከዚያ ይሞታሉ፡፡ በፍፁም ህይወታቸውን ኖረውት አያውቁም፡ በጭራሽ ህይወታቸው <ትር - ትር> የሚልበት እና እንደ ጅረቱ የሚንቀረቀርበት ቅፅበት ኖሮ አያውቅም፡፡ ብቻ በደህንነት ስሜት፡ በሚያውቁት አለም እና በመልካም ዝና ውስጥ ተሸብበዋል፡፡

ከዚያ ብትሰላቹ ምን ይገርማል! ይሄ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ሰዎች ወደ እኔ ይመጡና በጣም መሰላቸታቸውን ይነግሩኛል፡፡ ትክት ብሏቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ጠፍቷቸው አንድ ቦታ ላይ ይቆማሉ፡፡ ተመሳሳይ ነገርን በመደጋገም እንደገና ህያው የሚሆኑም ይመስላቸዋል፡፡ የዚያን ያህል ግን ቀላል አይሆንላቸውም፡፡ መላው የህይወታቸውን ስርአት ቅርፅ መለወጥ ይገባቸዋል፡፡

አፍቅሩ፤ ነገር ግን ያቀራችኋትን ሴት ነገ እንደምታገኙዋት አድርጋችሁ አታስቡ፡፡ ይህ ይሆናል ብላችሁ አትጠብቁ፡፡ ሴቲቱን በሚስትነት ደረጃ ዝቅ አድርጋችሁ አትዩዋት፡፡ እንግዲህ በስጋት ውስጥ እየኖራችሁ ነው፡፡ ያፈቀራችሁትን ወንድ በባልነት ደረጃ ዝቅ አድርጋችሁ አትዩት፡፡ ምክንያቱም ባል አስቀያሚ ነገር ነው፡፡ ወንዱም ወንድ፡ ሴቲቱም ሴት ትሁን፡፡ ደግሞም የነገ ውሎዎቻችሁን ከወዲሁ የሚታወቅ አታድርጉት፡፡ ምንም ነገር ይሆናል ብላችሁ በርግጠኝነት አትጠብቁ - ለማንኛውም ነገር ዝግጁ ሁኑ እንጂ፡፡

<በስጋት ውስጥ ኑሩ> ስል ይህንን ማለቴ ነው፡፡





ምን እናድርግ? ከአንዲት ሴት ጋር በፍቅር እና ... እንሌና ወዲያውኑ ልንጋባ ወደ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ማዘጋጃ ቤት፡ አሊያም ወደ ቤተ-ክርስቲያን መሄድ እንጀምራለን፡፡ አትጋቡ አላልኩም፡፡ ይሄ ተቀባይነት ያለው ስርአት ነው፡፡ ማህበረሰቡን ማስደሰታችሁ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን በአእምሯችሁ ውስጥ በፍፁም ሴቲቱን አዝልቃችሁ አታስገቡዋት፡፡ ለአንዲት ቅፅበት እንኳን ቢሆን በጭራሽ <የእኔ ንብረት ነሽ> አትበሉ - ምክንያቱም አንድ ሰው እንዴት የእናንተ ንብረት ሊሆን ይችላል? ደግሞም ሁለመናዋን በእጃችሁ ማስገባት ስትጀምሩ እሷም ሁለመናችሁን በእጇ ውስጥ ማስገባት ትጀምራለች፡፡ ከዚያ በኋላ ሁለታችሁም በፍቅር አትጠመዱም፡፡ በቃ እርስ በርሳችሁ አንዳችሁ ሌላችሁን እያደቀቃችሁ፡ እየገደላችሁ፡ ሽባ እየተደራረጋችሁ ነው፡፡

አፍቅሩ፡ ነገር ግን ፍቅራችሁ በትዳር ውስጥ አይኮስስ፡፡ ስራ ስሩ፡፡ መስራት ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ስራን ብቸኛው ህይወታችሁ እንዲሆን አታድርጉት፡፡ ጨዋታ በህይወታችሁ ውስጥ ሊኖርና የህይወታችሁም ማዕከል ሆኖ መቅረት ይኖርበታል፡፡ ስራ ወደ ጨዋታ የሚወስዳችሁ መንገድ ብቻ መሆን አለበት፡፡ በቢሮ ውስጥ፡ በፋብሪካ ውስጥ እንዲሁም በሱቅ ውስጥ ስሩ፡፡ ነገር ግን የምትሰሩት ለጨዋታ፡ ጊዜ እና አጋጣሚ እንዲኖራችሁ ብቻ ይሁን፡፡ የህይወታችሁን ደረጃ ወደ ተደጋጋሚ ልማድነት ዝቅ አታድርጉት፡፡ ምክንያቱም የህይወት ግብ ጨዋታ፡ መዝናናት ነውና!

ጨዋታ ማለት አንድን ነገር ለራሱ ሲባል ማድረግ ነው፡፡ ብዙ ነገሮችን ለገዛ ራሳቸው ብለው ማድረግ ከስደሰታችሁ የበለጠ ህያው ትሆናላችሁ፡፡ በእርግጥ ህይወታችሁ ሁልጊዜም በስጋት፡ በአደጋ ውስጥ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ህይወት መሆን ያለበት እንደዚያ ነው፡፡ አደጋ የህይወት አንድ አካል ነው፡፡ አብዛኛው የህይወት ክፍል፡ አብዛኛው ውብ የህይወት ክፍል፡ እያንዳንዱ በህይወት ውስጥ ያለ ቅፅበት አደጋ ነው፡፡ ምናልባት ልብ አላላችሁት ይሆናል፡፡ አየር ወደ ውስጥ ስትምጉም ሆነ ወደ ውጪ ስትተነፍሱ አደጋ አለው፡፡ ሌላው ቀርቶ አየርን ወደ ውጪ ስታወጡ እንኳን ትንፋሻችሁ ተመልሶ ወደ ውስጥ ይግባ፡ አይግባ ማን ያውቃል?! እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡ ማስተማመኛም የለም፡፡

ነገር ግን መላው እምነታቸው ለደህንነታቸው መጨነቅ የሆነ ጥቂት ሰዎች አሉ፡፡ ስለ እግዚአብሄር ቢያወሩም እንኳን እግዚአብሄር ለደህንነታቸው

መጠበቅ ከሁሉ የላቀ ሀይል እንዳለው ብቻ ነው የሚናገሩት፡፡ ስለ እግዚአብሄር ሲያስቡም እሱን የሚያስቡት ስለሚፈሩ ብቻ ነው፡፡ በተመስጦ ማሰላሰልና መፀለይ ካለባቸውም ይህን የሚያደርጉት የቅዱሳን መፅሃፍትን ትዕዛዛት ለመጠበቅና በእግዚአብሄር ቅዱስ መፅሀፍ ስማቸውን ለማስፈር ሲሉ ብቻ ነው፡፡ "እግዚአብሄር የሚባል ነገር ካለ ቢተክርስቲያን ሳግ መሆኔን እንዲሁም ዘወትር እንደማመልከው ያውቅልኛል፡፡ ይህንንም ማስመስከር እችላለሁ" ብለውም ያስባሉ፡፡ ፀሎታቸውም ቢሆን ይህንን ሀሳባቸውን የሚያንፀባርቁበት መንገዳቸው ነው፡፡

በስጋት መኖር ማለት በህይወት ውስጥ እያንዳንዱ ቅፅበት በገዛ ራሱ መጨረሻ እንደሆነ አድርጎ መኖር ነው፡፡ እያንዳንዱ ቅፅበት የራሱ ተፈጥሯዊ ዋጋ ስላለው አትፈሩም፡፡ ሞትም እንዳለ ታውቃላችሁ፡ የሞትን መኖር እውነታም ትቀበሉታላችሁ፡ ከሞት ለመደበቅ እንደማትችሉም ይገባችኋል፡፡ በእካል፡ በስነ-

ልቦና እና በመንፈስ ከሞት ጋር የምትገጣጠሙበትን እነዚያን ቅፅበቶች ትደሰቱባቸዋላችሁ፡፡

<በስጋት ውስጥ ኑሩ> ስላችሁ ሞት እውን የሚሆንባቸውን፡ በቀጥታ ከሞት ጋር የምትገናኙባቸውን እነዚያን ቅፅበቶች በደስታ ተቀበሉዋቸው ማለቴ ነው፡፡

**በስጋት መኖር ማለት በህይወት ውስጥ እያንዳንዱ ቅፅበት በገዛ ራሱ መጨረሻ እንደሆነ አድርጎ መኖር ነው፡፡ እያንዳንዱ ቅፅበት የራሱ ተፈጥራዊ ዋጋ ስላለው አትፈሩም፡፡**

ደፋሮች ያለማወላወል የትም ይሄዳሉ፡፡ አደገኛ አጋጣሚዎችን በሙሉ ይፈልጋሉ፡፡ የሀይወት ፍልስፍናቸው እንደ መድህን ኩባንያዎች አይደለም፡፡ የሀይወት ፍልስፍናቸው እንደ ተራ ወጪ፡ ሞተር በሌለው አውሮፕላን እንደሚንሳፈፍ እንዲሁም በማዕበል ላይ እንደሚንሸራተት ሰው ነው፡፡





የሚንሸራተቱትም በውጪያዊ ባህሮች ላይ ብቻ ሳይሆን በውስጣቸው ባሉት ባህሮች ውስጥም ጭምር ነው፡፡ በአልፕስ እና ሂማሊያስ ተራሮች ላይ የሚወጡት በውጪ ብቻ አይደለም፡ በውስጣቸውም የተራራ እናቶችን ይሻሉ፡፡

ነገር ግን አንድ ነገር አስታውሱ፡፡ በፍፁም በአደጋ ውስጥ የመሆን ጥበብ አትርሱ፡፡ በጭራሽ! ሁልጊዜም በአደጋ ውስጥ ለመሆን የምትችሉ ሆናችሁ ቆዩ፡፡ በአደጋ ውስጥ የመሆን አጋጣሚን ባገኛችሁ ቁጥር በፍፁም አጋጣሚው እንዳያመልጣችሁ፡፡ እናም ተሸናፊ አትሆኑም፡፡እውነተኛ ህያዋን ለመሆን ብቸኛው መተማመኛ አደጋ ነው፡፡

# ምንም ነገር ብታደርጉ ሀይወት ምስጢር ነው

አእምሮ አንድ ሲገለፅ የሚችል ነገር እንዳለ ለመቀበል ይቸገረዋል፡፡ አእምሮዋችን ሁሉም ነገር እንዲገለፅለት ያስቅቅ ይችኩላል፡፡ ካልተገለፀለት እንኳን ቢያንስ ለምን እንደማይገለፅለት ምክንያቱን ይሻል፡፡ ምስጢር ወይም እርስ በእርሱ የሚጋጭ ማንኛውም ነገረ አእምሮን ማስጨነቁን ይቀጥላል፡፡

መላው የፍልስፍና፡ የሀይማኖት፡ የሳይንስ እንዲሁም የሒሳብ ታሪክ ስረ መሰረታቸው አንድ ነው፡፡ የወጡትም ከተመሳሳይ አእምሮዎች ውስጥ ነው፡፡ በአንድ አይነት መንገድ ይከነክናሉ፤ ያሳክካሉ፡፡ እናንተ ራሳችሁን በአንድ መልክ ስትፎክሩ ሌላውም በተለየ መንገድ ያንን ያደርግ ይሆናል፡፡ ነገር ግን እስኩን ልትረዱት ይገባል፡፡ የእከኩ መንስኤ <ህይወት ምስጢር አይደለም> የሚለው እምነት ነው፡፡ አእምሮ ምቾት ሊሰማው የሚችለው በሆነ መንገድ እንቆቅልሹ ሲፈታ እና ሚስጥሩ ይፋ ሲወጣ ብቻ ነው፡፡

ሀይማኖት አብን (እግዚአብሄርን)፡ መንፈስ ቅዱስን፡ ወልድን በመፍጠር ይህንን አድርጓል፡፡ ሌሎች የተለዩ ሀይማኖቶችም የተለያዩ ነገሮችን ፈጥረዋል፡፡ እንግዲህ እነዚህ ሊሸፈን የማይችለውን ቀዳዳ ለመሸፋፈን የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ናቸው፡፡ ምንም አይነት ነገር ብታደርጉ ቀዳዳው በዚያ አለ፡፡ እንዲያውም በሸፈናችሁት ቁጥር የበለጠ ይጎላል፡፡ ቀዳዳውን ለመሸፈን የምታደርጉት እያንዳንዱ ጥረት እንድ ሰው ቀዳዳውን እንዳያየው ያላችሁን ስጋት ያሳያል፡፡ በታሪክ ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች አእምሮ ይህንን ቀዳዳ ለመሸሸግ የተለያዩ የመጣፊያ (የመሸፈኛ) ጨርቆችን

እየተሳደደ ተዳለው ላይ እየለጠፈ ይገኛል፡፡ በተለይም በ <ሂሳብ> ውስጥ ይሄ ጎልቶ ይታያል፡፡ ምክንያቱም ሂሳብ ንፁህ የአእምሮ ጨዋታ ነው፡፡ ሂሳብ የአእምሮ ጨዋታ የማይመስላቸው የሂሳብ ተመራማሪዎች (ሊቃውንት) አሉ፡፡ ልክ እግዚአብሔርን እውን አድርገው እንደሚያስቡት ማለት ነው፡፡

ሁለቱ፣ ህይወት እንቆቅልሽ ሳይሆን የሚከሰቱ ምትኮች ናቸው፡፡ እናም በእውን አለም ሊኖሩ የማይችሉ ክፍተቶችን ታገኛላችሁ፡፡ እነዚያን ክፍተቶች በሀብቶች ትሞሉዋቸዋላችሁ፡፡ ስለዚህ ቢያንስ ህይወትን በአግባቡ የተረዳችሁት እየመሰላችሁ የእርካታ ስሜት ይሰማችሁ ይጀምራል፡፡<መረዳት> የሚለውን ቃል አስባችሁት ታውቃላችሁ? የቃሉ ትርጉም ከስራችሁ (ከቁጥጥራችሁ ስር) ማቆም ማለት ነው፡፡ ይሀ ቃል ቀስ በቀስ ከያዘው ዋና ሀሳብ በጣም የራቀ ትርጉም ሲሰጠው ይገርማል፡፡ ከስራችሁ ሊታወሱት የምትችሉት ማንኛውም ነገር በእጃችሁ ውስጥ ነው፣ በቁጥጥራችሁ ስር ነው፣ ከእግራችሁ በታች ነው፡፡ እናንተም አለቆቹ ናችሁ፡፡

ሰዎችም ህይወትን በዚያ መልኩ ለመረዳት እየሞከሩ ይገኛሉ፡፡ ይህንን የሚያደርጉትም ህይወትን ከእግሮቻቸው ስር አውለው፣ "አለቆቹ እኛ ነን፡፡ አሁን እኛ የማንረዳው (የማናውቀው) ምንም ነገር የለም" ብለው ለማወጅ እንዲችሉ ነው፡፡ይሁንና ይህንን ማድረግ አይቻልም፡፡ ምንም ነገር ብታደርጉ ህይወት ምስጢር ነው! ምስጢርም ሆና ይቀራል፡፡







# ከየትኛውም ስፍራ ባሻገር የሚታይ ሌላ ስፍራ አለ

ዐይኖቻችንን በባሻገሮች ተከበናል፡፡ እግዚአብሄር ማለት ባሻገር የሚታየን ነገር ነው፡፡ ያንን ባሻገር የሚታየንን ስፍራ አልፈን ማየት አለብን፡፡ ይህ ስፍራ በውስጥም ሆነ በውጪ ሁልጊዜም አለ፡፡ ይሁንና ምቹ ስላልሆነ፣ ስለሚከብደኑስ፣ ባሻገር የሚታየውን ነገር አስተውለን እንመለከተውም ..... ቸልታው ልማድ የኖብናል፡፡ ልክ ወደ ገደል ውስጥ እንደማየው ይመስለናል፡፡ አንድ ሰው ወደ ገደል ውስጥ አጮንብሶ ሲመለከት ሰውነቱ በፍርሃት መራድ ይጀምራል፡፡ የተለሸለሸውና <ሸቅብ፣ ሽቅብ> ሊለው ይጀምራል፡፡ ገና የገደሉን መኖር ስናውቅ በፍርሃት መራድ እንጀምራለን፡፡ ማንም ሰው ወደ ገደል ውስጥ አይመለከትም፡፡ በእውን የሚታየንን ነገር ትተን ወደ ሌሎች ነገሮች ማየታችንን እንቀጥላለን፡፡ በእውን የምናየው ነገር እንደ ገደል ነው፡፡ ምክንያቱም በእውን የሚታየውን ቃላት ባዶነት ነው፡፡ ድንበር የሌለው ሰፊ ሰማይ (አድማስ) ነው፡፡ ቡድሃ "ዱራንጋማ" (ባሻገር ከሚታየው ስፍራ ተገኙ) ይላል፡፡ በፍፁም በድንበሮች ተወስናችሁ አትቅሩ፡፡ ሁልጊዜም ድንበሮችን አልፋችሁ ሂዱ፡፡ አስፈላጊ ሆነው ካገኛችኋቸው ድንበሮችን አብጁ፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜም ወጥታችሁ መርገጥ እንዳለባችሁም አስታውሱ፡፡ በፍፁም አንድ ቦታ ላይ አትታሰሩ፡፡

እኛ ግን በብዙ አይነት መንገዶች እንታሰራለን፡፡ በግንኙነት፣ በእምነት፣ በወይማኖት .... በነዚህ ሁሉ እንታሰራለን፡፡ አንዳንድ ሰው ሀይለኛ ንፋስ ባመኖሩ የደስታ ስሜት ይሰማዋል፡፡ ከአደጋ የተጠበቀ ይመስለዋል፡፡ ይሁንና መከላከያው የውሸት ነው፡፡ ምክንያቱም ሞት ይመጣና ባሻገር ወዳለው ስፍራ እየጎተተ ይወስዳችኋል፡፡ ሞት መጥቶ ጉትቶ ሳይወስዳችሁ በፊት በራሳችሁ ሂዱ፡፡

አንድ ታሪክ ላንሳ፡-

አንድ የዜን እምነት ተከታይ መነኩሴ ሊሞት ያጣጥራል፡፡ እድሜው በጣም ገፍቷል፡፡ ዘጠና አመቱ ነበር፡፡ ድንገት አይኖቹን ገልጦ "ጫማዬ የት አለ?" ይላል፡፡

በዚህ ጊዜ ደቀ- መዝሙሩ 'ወደ የት ልትሄድ ነው? አበድክ እንዴ? ልትሞት እኮ ነው። በዚሙ ምንም እድል የለህም ብሏል። ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ናቸው የቀሩህ ይለዋል።

'ታዲያ ለዚህ አይደለም እንዴ ጫማዬን የምጠይቀው። ወደ መካነ - መቃብሩ መሄድ እፈልጋለሁ። በሸክም መሄድ አልፈልግም። ደግሞም እኔን ታውቀኛለህ። ህይወቴን በሙሉ በሰዎች ላይ ሸክም ሆኜ አላውቅም። ይሄ በጣም አስቀያሚ ነገር ነው። አስከሬኔን አራት ሰዎች ሊሸከሙት?! በፍፁም አይደረግም! አይሆንም!' አለና መነኩሴው ከአልጋው ላይ ተነሳ።

በእግሩም ወደ መካነ - መቃብሩ ሄደ። መን ይሄ ብቻ! የገዛ ራሱን መቀበሪያ ጉድጓድ ቆፍሮ ውስጡ ተኛ። ከዚያም ሞተ። እንዲህ ያለው ያልታወቀ ነገርን የመቀበል፣ በገዛ ራስ የመሄድ እንዲሁም ባሻገር ያለውን ነገር (አለም) በፀጋ የመቀበል ድፍረት አስደናቂ ነው። ከዚያ ሞት መልኩ ይለወጣል። <ሞት> ሞት አይሆንም።

የዚህ አይነት ደፋር ሰው በፍፁም አይሞትም፣ ሞት ድል ተነስቷል። የዚህ አይነት ደፋር ሰው ከሞት ባሻገር ይሄዳል - ምክንያቱም ባሻገር ወዳለው ስፍራ በገዛ ራሱ ለሚሄድ፣ ባሻገር ያለው ስፍራ በፍፁም እንደ ሞት ያለ ስፍራ አይደለም። ባሻገር ያለው ስፍራ ሁልጊዜም እንደገደል ማሚቶ ያስተጋባችኋል።

# ህይወት ሁልጊዜም አይጨበጥም

ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት ሁልጊዜ ዙሪያችሁን እንደግድግዳ ከቦታል። በዙሪያችሁ እንደግድግዳ ስለከበባችሁም ከክፉ ነገር የሚከላከላችሁ መሆኑን አሳምኖአችኋል። ይህ እንግዲህ ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት እናንተን የሚያማልልበት መንገድ ነው። በተደጋጋሚ 'እኔ በዙሪያችሁ ከሌለሁ ከክፉ ነገር የሚከላከላችሁ ነገር የለም፣ በቀላሉ ለችግር ትጋለጣላችሁ። ከመጠን ያለፈ አደጋ ይገጥማችኋል። ስለዚህ እኔ ልጠብቃችሁ፣ ዙሪያችሁንም ልከበባችሁ' ማለቱንም ይገፋበታል።

አዎን፣ ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት በተወሰነ መልኩ ከክፉ ነገር ይከላከላችኋል። ነገር ግን ግድግዳው እስር ቤትም ይሆንባችኋል። በተወሰነ



መልኩ ከክፉ ነገር ትጠበቃላችሁ። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት (የራስ ኩራት) በሚያመጣቸው ችግሮች ማንም ሰው አይጎዳም ነበር። በተወሰነ መልኩ ከክፉ ነገር ይጠብቃችኋል፣ ከጠላቶቻችሁ ይጠብቃችኋል፣ ከወዳጆቻችሁም ጭምር እንኳን ይጠብቃችኋል።

በሮቻችሁን ቆልፋችሁ ጠላቶቻችሁ እንዳያገኟችሁ ስትሉ ቤታችሁ ውስጥ እንደመደበቅ ማለት ነው። አንድ ወዳጃችሁ ቢመጣ በሩ ስለተቆለፈ መግባት አይችልም። ለወዳጃችሁ ብላችሁ በሩን ብትከፍቱት ጠላታችሁም ዘልቆ በመግባት አደጋ ላይ ልትወድቁ ትችላላችሁ።

አንድ ሰው ስለዚህ የግድ በጥልቀት ማሰብ ይኖርበታል። ይህ በህይወት ውስጥ ከሚያጋጥሙት ችግሮች ውስጥ አንዱ ነው። ደግሞም ችግሩን በአግባቡ ሊያልፉት የሚችሉት በጣም ጥቂት ቁጥር ያላቸው ደፋሮች ብቻ ናቸው። ሌሎች ፈሪዎች ስለሚሆኑ ይደበቁ እና መላው ህይወታቸው ይባክናል።

ህይወት በአደገኛ ሁኔታዎች ውስጥ ያለ ሂደት ነው። ሞት ግን ምንም ደጋ የለውም። ብትሞቱ የሚገጥማችሁ ምንም ችግር የለም፣ ደግሞም ማንም ሰው አይገድላችሁም - ምክንያቱም ገና ድሮ ሞታችኋልና እንዴት አንድ ሰው ሊገድላችሁ ይችላል? መቃብራችሁ ጉድጓድ ውስጥ ገቡና ያብቃላችሁ?

ህይወት ካላችሁ ግን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግሮች አሉ። ሰው የበለጠ ህያው ሲሆን የበለጠ ችግሮች ይኖሩበታል። ይሁንና በዚህ ውስጥ ምንም ችግር የለበትም - ምክንያቱም ከችግሮች ጋር መጋፈጥ፣ ፈተናን በድል ለማለፍ መሞከር ነው እንድታድጉ የሚያደርጋችሁ።

ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት በዙሪያችሁ የሚገኝ ረቂቅ ግድግዳ ነው። ማንም ሰው ዘልቆ እንዲገባ አይፈቀድለትም። በውስጡ ስትሆኑ ክፉ ነገር የማይገጥማችሁ እና ከአደጋ የተጠበቃችሁ ይመስላችኋል። ነገር ግን ይህ የደህንነት ስሜት እንደሞት ያለ ነው። በዘር ውስጥ ያለ ተክል እንደሚሰማው አይነት የደህንነት ስሜት ነው። ተክሉ ለመብቀል ይፈራል - ምክንያቱም ማን ያውቃል? ዓለም በጣም አደገኛ ይሆን ይሆናል። ተክሉ ደግሞ በጣም ለስላሳ እና ለአደጋ የሚጋለጥ ነው። ከዘሩ ግድግዳ ጀርባ ባለው ህዋስ ውስጥ ተደብቆ ሳለ ሁሉም ነገር ከአደጋ እንደተጠበቀ ነው።

ወይም በእናቱ ማህፀን ውስጥ ያለ ትንሽ ህፃን ልጅን አስቡ፡፡ በዚያ ሁሉም ነገር አለ፡፡ የህፃኑ ፍላጐት ምንም ይሁን ምን ወዲያውኑ ይሟላለታል፡፡ ሲታት፣ ትግል፣ ስለወደፊቱ መጨነቅ የለም፡፡ በቃ ልጁ በተድላና በደስታ ይኖራል፡፡ እያንዳንዱ ፍላጐቱ በእናቱ፣ በእናቱ በኩል ብቻ ይሟላለታል፡፡

እናላ ሁልጊዜም በእናታችሁ ማህፀን ውስጥ መቆየትን ትፈልጋላችሁ? የእናት ማህፀን ከሚገባው በላይ ከእደጋ ይጠብቃል፡፡ ምረጡ ብትባሉ ሁልጊዜም በእናታችሁ ማህፀን ውስጥ መሆንን ትመርጣላችሁ ወይ? በእርግጥ የእናት ማህፀን በጣም ምቹ ነው፡፡ ከዚያ የበለጠ ምን ምቹ ስፍራ አለ? ሳይንቲስቶች አሁንም ድረስ ቢሆን ከእናት ማህፀን የበለጠ ምቹ የመኖሪያ ስፍራ መስራት አለመቻላችንን ይናገራሉ፡፡ የመጨረሻው ምቹ የመኖሪያ ስፍራ የእናት ማህፀን ነው፡፡ በዚያ ያለው ኑሮ ፍፁም ነው፡፡ ሁሉም ነገር ወዲያውኑ ይቀርባል፡፡ ፍላጐቱ ነፍስ ሲዘራ ያለውን ይሟላል፡፡ ሌላው ቀርቶ የአተነፋፈስ ችግር እንኳን የለም፣ እናት ለልጁ ትተነፍስለታለች፡፡ ስለምግብም ቢሆን መጨነቅ አያስፈልግም፣ እናት ለልጁ ወደ ሰራዷ ስትል ምግብ ትመገባለች፡፡

እንደዚያስ ቢሆን ታዲያ እናንተ በእናታችሁ ማህፀን ውስጥ ልትቆዩ ትፈልጋላችሁን? ምቹ ነው፣ ነገር ግን ህይወት በዚያ ውስጥ የለም፡፡ ህይወት ሁልጊዜም ተጨባጭ አይደለም፡፡ ያለውም ውጪ ነው፡፡

<ኤክስታሲ> (ፍንደቃ) የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በጣም በጣም ትልቅ ትርጉም ያለው ነው፡፡ <ኤክስታሲ> (ፍንደቃ) ማለት ነገር መውጣት - ከሽፋኖች፣ ከመከለያዎች፣ ለግዛ ራስ ካሉ አመለካከቶች፣ ከምቾቶች እንዲሁም ሞትን ከመሰሉ ግድግዳዎች ሁሉ መውጣት ነው፡፡ <ፈንዳቂ መሆን> ማለት ደግሞ ንፋስ በውስጣችሁ ያልፍ ዘንድ ወጥቶ መታየት፣ ነፃ መውጣት፣ ሰሚትን መንካት፣ ሂደት መሆንና መጋለጥ ነው፡፡

አንድ አባባል አለ፡፡ እንዳንድ ጊዜ "የዚያ አይነቱ ተሞክሮ ጉልቶ የሚተይ ነበር" እንላለን፡፡ እንግዲህ የፍንደቃ ትርጉም ይኸው ነው - <በጉልህ መታየት፡፡>

አንድ ዘር ተከፍቶ በውስጡ የሸሸገው ብርሃን ሲገለፅ፣ አንድ ህፃን ሲወለድና ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ እነዚያ ሁሉ በዚያ የነበሩ ምቾቶች ወዲሊታወቀው





አለም ውስጥ ይንቀሳቀሳል፡፡ ይህ እንግዲህ ፍንደቃ ነው፡፡ እንዴት ወፍ እንቁላሏዋን ሰብራ በመውጣት ወደ ሰማይ ስትበር ይህ ፍንደቃ ነው፡፡

ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት እንቁላል ነው፡፡ ከውስጥ ወደ ውጪ መውጣት አለባችሁ፡፡ ፈንዳቂ ሁኑ! ከመከለያዎቹ፣ ከሽፋኖቹ፣ ከእጥሮቹ ውስጥ ውጡ፡፡ ከዚያ የበለጠ ሰፊ ወደሆነው ግዙፍና የትየለሌ አለም ትደርሳላችሁ፡፡ ያን ጊዜ ብቻ ነው በተትረፈረፈ ሁኔታ የምትኖሩት፡፡

ነገር ግን ፍርሃት ሽባ አድርጓችኋል፡፡ ህፃን በነበራችሁ ጊዜ፣ ከእናታችሁ ማህፀን ውስጥ ከመውጣታችሁ በፊት መውጣት እንደነበረባችሁ ወይም እንዳልነበረባችሁ ሳታመንቱ አልቀራችሁም፡፡ ለውጥ ወይስ ለቅር? ብላችሁ እያመነታችሁ አንድ ጊዜ ወደፊት ሌላ ጊዜ ወደኋላ ሳትሉ አልቀራችሁም፡፡ ምናልባትም እናታችሁ ስታምጣችሁ ለዚያ ሳይሆን አይቀርም በብዙ መከራ ውስጥ ያለፈችው፡፡ ህፃን ልጅ ሲወለድ ያመነታል፡፡ ህፃኑ ለመፈንደቅ ገና አልተዘጋጀምና፡፡ ያለፈው ጊዜ ወደ ኋላ ይስበዋል፣ የወደፊቱ ጊዜም ይጠራዋል፡፡ እናም ህፃኑ ሁሳቡ ይከፈላል፡፡

ይህ ሁሳብን ለመቁረጥ የሚያስቸግር ጋሬጣ (ግድግዳ) ነው፡፡ ባለፈ ጊዜ ላይ - ለራስ ባለ አመለካከት ላይ የሙጥኝ ማለት ነው፡፡ ይህንን ደግሞ በየቦታው ይላችሁት ትጓዛላችሁ፡፡ እንዳንድ ጊዜ ከስንት አንድ ጊዜ ህያው እና ንቁ ስትሆኑ ይህንን ሊታሰተውሉት ትችላላችሁ፡፡ እለበለዚያ ምንም እንኳን እንደመስታወት ቀለጥ አድርጎ ከውስጥ ያለውን የሚያሳይ ቢሆንም ሊታዩት አትችሉም፡፡ አንድ ሰው መላው የህይወት ዘመኑን በትንሽ የእስር ቤት ክፍል ውስጥ ከየአትጣጫው ተዘግቶበት መስኮት በሌለበት፣ አንድ ብቻ ሳይሆን ብዙ ውስጥ ህይወቱን ሊኖር ይችላል፡፡ በሮች የሉም፣ መስኮቶች የሉም፣ ብቻ ከውስጥ ተዘግቷል፡፡

ነገር ግን በውስጥም ሆነ በውጪ ያለውን ያሳያል - ከመስታወት የተሰራ ግድግዳ ነውና፡፡

የዚህ አይነቱ የራስ አስተሳሰብ ወዲያ መጣል አለበት፡፡ አንድ ሰው ድፍረትን ማሰባሰብና ወለሉ ላይ መበተን አለበት፡፡ ሰዎች የገዛ ራሳቸውን ሊአል ማሰባሰብና እያዳበሩት መሆኑን ሳያውቁ በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ የተለያዩ አይነት መንገዶች ይህንን እያዳበሩ ይገኛሉ፡፡

ሚስዝ ኮችራን ከባሏ የሬሳ ሳጥን አጠገብ ቆማለች፡፡ ወንዱ ልጃቸው ከጉልበቷ አጠገብ ቆሟል፡፡ ለቅሶ ደራሾች አንድ በአንድ በአጠገባቸው ያልፋሉ፡፡

"አሁን ምንም አይነት ህመም አይሰማውም" አለች ሚስዝ ክሮቶ በአጠገባቸው ስታልፍ፡፡ "ለመሆኑ በምንድነው የሞተው?"

"ምስኪን ሰው ነበር" አለች ሚስዝ ኮችራን፡፡ "በጨብጥ ነው የሞተው"

አንዲት ሌላ ሴትም አስከሬኑን ትኩር ብላ እየቸና "አሁን ሁሉም ነገር አልፎለታል" አለች፡፡ "ፊቱ ላይ የተረጋጋ ፈገግታ ይታይበታል፡፡ ለመሆኑ በምንድነው የሞተው?"

"በጨብጥ በሽታ ነው የሞተው!" አለች በሷን በሞት የተነጠቀችው ሴት፡፡

ድንገት ልጁ እናቱን ጉተት አደረጋትና "እማዬ ...." አላት፡፡ "ስለ አባዬ አሟሟት እየተናገርሽው ያለሽው ነገር አስቀያሚ ነው፡፡ በጭብጥ በሽታ አይደለም የሞተው፡፡ የሞተው በተቅማጥ ነው!"

"አውቃለሁ!" አለች ሚስዝ ኮችራን፡፡ "ነገር ግን እንደዚያ በአስቀያሚ ሁኔታ ከመጉሳቆሉ ይልቅ አዝናኝ ስፖርት እየሰራ እንደሞተ እንዲያስቡ ብዬ ነው!"

እስከመጨረሻው ቅፅበት ድረስ በጨዋታቸው ገፍተዋል፡፡

ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት እውነተኛ እንድትሆን አይፈቅድላችሁም፤ እንድትዋሹ ማስገደዱን ይገፋበታል፡፡ ለራስ ያለ አመለካከት ነው ውሸቱ፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ውሳኔ ላይ መድረስ አለበት፡፡ ይሄ ደግሞ ታላቅ ድፍረትን ይጠይቃል፡፡ ያለበለዚያ እስከአሁን ድረስ ስትንከባከቡት የቆያችሁትን ነገር ሁሉ ይበታትነዋል፡፡ እናንተም ሙሉ በሙሉ ይበታትናችኋል፡፡ በዚያ አንድ ሰው ቢኖርም እናንተ ግን ያንን ሰው አትሆኑም፡፡ በውስጣችሁ ዘላቂ ያልሆነ (አፍላ እና ባለፈው ጊዜ ያልተበረዘ አካል) ነፍስ ይዘራል፡፡ ከዚያ ምንም አይነት ግድግዳ አይኖርም፡፡ የትም ቢታ ብትሆኑም ድንበር የሌለውን የትየለሌ ዓለም ታዩታላችሁ፡፡

አንድ በእድሜ የገፋ ሰው ወደሚወደው ቡና ቤት ውስጥ ሲገባ ከዚያ ቀደም የሚያውቃት አስተናጋጅ በአዲስ አስተናጋጅ ተተክታ አገኘ፡፡ መጀመሪያ ተደነጋግሮ የነበረ ቢሆንም በጨዋ ደንብ እንደ እሷ ያለ ቆንጆ ወጣት ለረጅም ጊዜ አለማየቱን ነገራት፡፡





እዳዬ አስተናጋጅ <ጆንን ቢጤ> ነበረች፡፡ ራሷን እንቃንቶች እና ኮምጨጭ ብላ "በጣም አዝናለሁ፡፡ ለዚህ አይነቱ አስተያየት መልስ መስጠት አልችልም" አለችው፡፡

"ኧረ! መልካም ነዋ፤ የኔ ውድ" አላት ሽማግሌው ተረጋግቶ፡፡ "ግን እኔ ያደረግሁትን ማድረግ አትችይም? ውሸት መናገር አትችይም?"

የምንከተላቸው ስርአቶች በሙሉ ለራሳችን ያለንን አመለካከቶች እርስ በርስ የሚያጠናክሩ እንጂ ሌላ ምንም አይደሉም፡፡ በቃ ውሸት ናቸው፡፡ ለአንድ ሰው አንድ ነገር ስትሉት ለአስተያየታችሁ መልስ ይሰጣል፡፡ እናንተም ሆናችሁ እሱ እውነተኛ አይደላችሁም፡፡ ሁላችንም በስነ- ምግባር፣ በስነ - ስርአቶች በስለጠኑ ገፅታዎች እና ጭንብሎች ጨዋታችንን እንገፋታለን፡፡

ከዚያ ግድግዳውን መጋፈጥ ይኖርባችኋል፡፡ እናም ቀስ በቀስ ግድግዳው ይወፍርና ምንም ነገር ለማየት አትችሉም፡፡ ግድግዳው በየእለቱ ውፍረቱ እየጨመረ ስለሚሄድ እዚያው አትቆዩ፡፡ በዙሪያችሁ አንድ ግድግዳ የተሸከማችሁ መስሎ ከተሰማችሁ አሽቀንጥራችሁ ጣሉት! ዘላችሁ ከዚያ ውጡ! ከዚያ ለመውጣት የሚያስፈልጋችሁ መወሰን ብቻ ነው! ሌላ ምንም ነገር የለም፡፡ ለነገ ብላችሁ አታቆዩት፡፡ በድጋሚ የምትገነቡት መስሎ ከታያችሁም አቁሙ፡፡ በጥቂት ቀናት ውስጥ ሲፈራርስ እና ሲያበቃለት ታዩታላችሁ - ምክንያቱም ግድግዳው ለመኖር የሚያቋርጥ የእናንተን እገዛ ይፈልጋል፤ የእናንተን የጡት ወተት ይሻል፡፡

# የመጨረሻው ድፍረት መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ የለውም

ብዙ አይነት ፍርሃቶች አሉ፡፡ ነገር ግን ከመሰረታቸው ሲታዩ ሁሉም የአንድ ፍርሃት ብታዮች - የአንድ ፍርሃት ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ የሚበቅሉበትም ዛፍ ሞት ነው፡፡ ፍርሃት ከሞት ጋር እንደሚያያዝ ላታውቁ ይሆናል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ፍርሃት ከሞት ጋር ይያያዛል፡፡

ፍርሃት በቃ የሞት ጥላ ነው፡፡ ኪሳራ ላይ የመውደቅ ፍርሃት እንዳለባችሁ በግልፅ አይታይ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ገንዘብ ስለሌላችሁ የበለጠ ለሞት



ትርጉም፡-ሀብታሙ ተስፋዬ

የተጋለጣችሁ እንዳትሆን ፈርታችኋል፡፡ ሰዎች ከከፋ ነገር እንዲጠብቃችሁ ብለው ገንዘብ ማከማቸትን ይገፋፏችኋል፡፡ ይሁን እንጂ እራሳችሁን ከሞት የምትከላከሉበት ምንም አይነት መንገድ እንደሌለ በሚገባ ታውቃላችሁ፡፡ እንደዚያም ሆኖ አንድ የሆነ ነገር መደረግ አለበት፡፡ ገንዘብ ቢያንስ ዋስትና ያደርጋል፡፡ እናም ራሳችሁን በስራ የተወጠረ ማድረግና መኖር - ሀሳን እንደመሳት፣ እንደ አደንዛዥ ዕፅ ያለ ነገር ነው፡፡

በመሆኑም የአልካል መጠጥ ሱሰኞች የመኖራቸውን ያህል የስራ ሱሰኞችም አሉ፡፡ ያለማቋረጥ እራሳቸውን በሆነ አይነት ስራ ውስጥ ይጠምዳሉ፡፡ በፀጥታ መቀመጥ አይችሉም፡፡ ጠዋት ላይ ስለት ጊዜ ያነበቡትን ጋዜጣ እንደገና ማንበብ ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ ሁልጊዜም በስራ ተጠምደው መቆየት ይፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም ሥራው በእነሱና በሞት መካከል መጋረጃ ይጋርድላቸዋል፡፡ ነገር ግን ፍርሃታቸው ወደ ዋና ፍሬ ነገሮቹ ቢቀለል፣ ብቸኛው ፍርሃት ሞት ብቻ ነው፡፡

ሌሎች ፍርሃቶች ሁሉ ብቃዮች ብቻ መሆናቸውን መገንዘብ በጣም ጠቃሚ ወሳኝ ነው፡፡ የዚያን ጊዜ ስረ መሰረቶቹ ከታወቁ አንድ የሆነ ነገር ሊደረግ ይችላል፡፡ ዋነኛውና መሰረታዊው ፍርሃት ሞት ከሆነ ፍርሃታችሁን ማጥፋት የሚችለው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ይኸውም በውስጣችሁ ያለውን ሞት አልባ ንቃት - ሀሊዎ የማወቅ ተሞክሮ ነው፡፡ ገንዘብም ሆነ፣ ስልጣንም ሆነ፣ ክብርም ሆነ፣ ሌላም ማንኛውም ነገር ለሞት ዋስትና ሊሆን አይችልም፡፡ ብቸኛው ዋስትናችሁ አካላችሁም ሆነ አእምሯችሁ እንደሚሞት፣ ነገር ግን እናንተ ከአካልና ከአእምሮ (ከአካለ - አእምሮ) ጥንቅር ባሻገር መሆናችሁን የሚያሳየው ጥልቅ የሆነ በተመስጦ ማሰላሰል ነው፡፡

ማዕከላዊ ፍሬ ነገራችሁ፣ የህይወታችሁ ወሳኝ ምንጭ፣ ከእናንተ በፊት እዚህ ነበር፡፡ ከእናንተ በኋላም እዚህ ይቀራል፡፡ ወደ ተለያዩ አይነት ቅርፆች ተተይዟል፡፡ በተለያዩ አይነት ቅርፆችም አሁን ባለበት ሁኔታ መገለጥ ችሏል፡፡ ነገር ግን በጭራሽ ተሰውሮ አያውቅም፡፡ መነሻው የሚባል ነገር ካለ ገና ከመነሻው ጀምሮ አለ፡፡ መጨረሻ የሚባል ነገር ካለም እስከ መጨረሻው ድረስ አይሰወርም፡፡ ምክንያቱም እኔ በየትኛውም አይነት መነሻ እና መጨረሻ አላምንም፡፡





ህይወት መነሻ እና መድረሻ - ቢስ ነው፡፡ ሁልጊዜም እዚህ አለ፣ እናንተም ሁልጊዜም በዚህ ነበራችሁ፡፡ ቅርፆች የለያዩ አይነት ሆነው ቆይተዋል፡፡ በዚህ ህይወት እንኳን ቢሆን ቅርፆች የተለያዩ ናቸው፡፡

**ማዕከላዊ ፍሬ ነገራችሁ፣ የህይወታችሁ ወሳኙ ምንጭ፣ ከእናንተ በፊት እዚህ ነበር፡፡ ከእናንተ በኋላም እዚህ ይቀራል፡፡ በጭራሽ ተሰውሮ አያውቅም፡፡ መነሻ የሚባል ነገር ካለ ገና ከመነሻው ጀምሮ አለ፡፡ መጨረሻ የሚባል ነገር ካለም እስከ መጨረሻው ድረስ አይሰወርም፡፡ ምክንያቱም እኔ በየትኛውም አይነት መነሻ እና መጨረሻ አላምንም፡፡**

ወደ እናታችሁ ማህፀን ውስጥ የገባችሁበት የመጀመሪያው ቀን በጥያቄ ምልክት ስር ከምታደርጉዋት ነጥብ ያልበለጣችሁ ነበራችሁ፡፡ አንድ ፎቶግራፍ ብታዩ ያ ነጥብ (ሀዋስ) እናንተ መሆናችሁን ለይታችሁ አታውቁም፡፡ ከዚያ በፊትም እንደዚያው ......

አንድ ፎቶግራፍ ሊተዩ ትችላላችሁ፡፡ ፎቶግራፉ መልካችሁን በጣም አይናችሁ ለማየት እስከምትችሉበት ጊዜ ድረስ እንዲያድግ ለማድረግ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ለይታችሁ ልታውቁት አትችሉም? በእውነ ጊዜ በውስጣችሁ <ትር - ትር> የሚለው የህይወት ቅርፅ፣ የህይወት ምንጭ ግን እሱ ራሱ ነው፡፡

በየቀኑ እየተለወጣችሁ ነው፡፡ እና እንደተወለዳችሁ - የአንድ ቀን ዕድሜ እያላችሁ እንኳን ራሳችሁን ለይታችሁ አታውቁም፡፡ የዚያን ጊዜውን ሁኔታችሁን በፎቶግራፍ ብታዩት "ወይ አምላኬ! ይሄ እኔ ነኝ? ትላላችሁ፡፡ የልጅነት ሁሉም ነገር ይለወጣል፡፡ ታረጃላችሁ፣ ወጣትነት ያልፋል፡፡ ሆኖም ሞት ዘመናችሁን ገና ድሮ አልፋችሁበታል፡፡ እናም ሞት ይመጣል፡፡ ደግሞም ህይወታችሁን ቅርፁን ቀይሮ ብቻ እንጂ በአካል አይመጣም፡፡ በሙሉ ሲተየር የኖረው ሌላ ሳይሆን ቅርፅ ብቻ ነው፡፡

ቅርፃችሁ በእያንዳንዱ ቅፅበት እየተቀየረ ይገኛል፡፡ ከልጅነት እስከ ወጣትነታችሁ ..... ልጅነት አልፎ ወጣትነት ሊመጣ አሌታወቃችሁም፡፡ ከወጣትነት እስከ እርጅና ዘመናችሁ ነገሮች በቀስታ ስለሚሄዱ በየትኛው ቀን፣ በየትኛው እለት፣ በየትኛው አመት ወጣትነታችሁ እንዳለፈበት በጭራሽ አታውቁትም፡፡

ሞት ከአንድ አካል፥ ከአንድ ቅርፅ ወደ ሌላኛው የሚደረግ መን - ሴፈ ዝዓይ ነው፡፡ ነገር ግን መጨረሻችሁ አይደለም፡፡

በጭራሽ ተወልዳችሁ አልነበረምና በፍፁም አትሞቱም፡፡

ሁልጊዜም ከእዚህ አሳችሁ፡፡ አንዱ ቅርፅ ሲሄድ ሌላው ይመጣል፤ የህይወት ጅረት ፍሰቱን ይቀጥላል፡፡ ይህንን ተሞክሮ ካላለፋችሁበት ለሞት ያላችሁ ፍራቻ ትቷችሁ አይሄድም፡፡ ለዚህ ደግሞ ሊያግዛችሁ የሚችለው በተመስጦ ማሰላሰል - በተመስጦ ማሰላሰል ብቻ ነው፡፡

**ሞት ከአንድ አካል፥ ከአንድ ቅርፅ ወደ ሌላኛው የሚደረግ መን . ሰፈ ዝዓይ ነው፡፡ ነገር ግን መጨሻችሁ አይደለም፡፡ በጭራሽ ተወልዳችሁ አልነበረምና በፍፁም አትሞቱም፡፡**

ይህንን እኔም ልለው እችላለሁ፤ ቅዱሳን ሰዎቹ ሊሉትም ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይሄ ምንም እገዛ አያደርግም፡፡ አሁንም ቢሆን ጥርጣሬ ይኖር ይሆናል፡፡ ማን ያውቃል? እነዚህ ሰዎች እየዋሹ ይሆናል፡፡ ወይም ደግሞ ሰዎቹ በሌሎች ሰዎቹ፤ በሌሎች መምህራን ተታለው ይሆናል፡፡ እናም ጥርጣሬ ካለ ፍርሃትም ይኖራል፡፡

በተመስጦ ማሰላሰል ከእውነታ ጋር ፊት ለፊት ያገናኛል፡፡ በገዛ ራሳችሁ የህይወትን ምንነት ካወቃችሁት በፍፁም ስለሞት አትጨነቁም፡፡ ባሻገር ልትሄዱ ትችላላችሁ፡፡ ይህ የራሳችሁ ስልጣን ነው፡፡ ደግሞም መብታችሁ ነው፡፡ ነገር ግን ከእእምሮ ወደ አእምሮ-አልባ ያልሆነ ሀሳብ ለመንቀሳቀስ ትንሽ ጥረት ማድረግ አለባችሁ፡፡

አንድ ህፃን በተወለደበት ቅፅበት የህይወቱ መጀመሪያ ይመስላችኋል፡- ይህ እውነት አይደለም፣ ይህ እውነት አይደለም፡፡ አንድ በእድሜ የገፋ ሰው በሞተበት ቅፅበት የህይወቱ መጨረሻ ይመስላችኋል፡፡ እንደዚያ ግን አይደለም፡፡ ህይወት ከመወለድና ከመሞት የበለጠ ሩቅ ነው፡፡ መወለድ እና ሞት የህይወት ሁለቱ ጫፎች አይደሉም፡፡ በህይወት ውስጥ ብዙ ልደቶች እና ብዙ ሞቶች ይከሰታሉ፡፡ ህይወት ራሱ መነሻ እና መጨረሻ የለውም፡፡ ህይወት እና ዘላለማዊነት እኩል ናቸው፡፡ ነገር ግን ህይወት



ህያውነት እኛ

እንዴት ወደ ሞት እንደሚለወጥ በቀላሉ መገንዘብ አትችሉም፡፡ ሌላው ቀርቶ ያን ለማመን እንኳን አይቻልም፡፡

በአለም ላይ ጥቂት ለመገንዘብ የማንችላቸው ነገሮች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ህይወትን ወደ ሞት ሲለወጥ መገንዘብ አለመቻላችን ነው፡፡ ህይወት በየትኛው ቅፅበት ነው ህይወትንነቱ አብቅቶ ሞት የሚሆነው? የት ቦታ ላይ ነው በህይወትና በሞት መካከል መስመር ማስመር የምትችሉት? ለልደትም (ለመወለድም) መስመር ማስመር አትችሉም፡፡ ህይወት የሚጀምረው ህፃኑ ሲወለድ ነው ወይስ ሲፀነስ? ግን እኮ ከፅንሰት በፊትም ቢሆን የእናትየው እንቁላል እንዲሁም የአባትየው የወንድ ዘር ህዋስ (ስፐርም) ህያው ነበሩ፤ አልሞቱም ነበር፡፡ ምክንያቱም የሁለት የሞቱ ነገሮች ውህደት ህይወትን ሊፈጥር አይችልም፡፡ ህፃን የሚወለደው የትኛው ቦታ ላይ ነው? ይህንን ሳይንስ ሊደርስበት አልቻለም፡፡ ይህንን ለማወቅ የሚቻልበት መንገድ የለም፡፡ ምክንያቱም እናቲቱ የተሸከመችው እንቁላል ከተወለደችበት ቀን ጀምሮ በውስጧ የያዘችውን ነው፡፡

አንድ ተቀባይነት ማግኘት ያለበት ነገር አለ፡፡ ይኸውም ሌላው ቀርቶ ከመፀነሳችሁ በፊት እንኳን በከፊል ህይወታችሁ ህያው መሆኑ ነው፡፡ ከፊሉን እናንተንታችሁን ደግሞ አባታችሁ ያዋጣል፡፡ ይህኛውም ቢሆን ህያው ሆኖ የቀጣ ነው፡፡ የአባታችሁ የወንድ ዘር ህዋሶች ከሰውነቱ ውስጥ ሲወጡ ህያው ናቸው፡፡ ነገር ግን ረጅም የህይወት ዘመን የላቸውም፡፡ የህይወት ዘመናቸው ሁለት ሰአታት ብቻ ናቸው፡፡ በሁለት ሰአታት ጊዜ ውስጥ ከእናታችሁ እንቁላል ጋር መገናኘት አለባቸው፡፡ በሁለት ሰአታት ጊዜ ውስጥ ሳይገናኙ ቀርተው እዚህም፣ እዚያም ከባዙ ቦታ እናንተም የላችሁም፡፡

እያንዳንዱ የወንድ ዘር ህዋስ የየራሱን የሰብዕና ባህርያት መያዙ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ነው፡፡ ጥቂቶቹ ሰነፎች ሲሆኑ ሌሎቹ ወደ እንቁላሏ በጭራሽ ሊጣደፉ እነሱ የጠዋት የእግር ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መልኩ ባህሪያቶ ገና ሊደርሱ አይችሉም፡፡ ነገር ግን ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? እነዚህ ባህሪያቶ ሞትን ከመወለዳቸው ጀምሮ ያሉ ናቸው፡፡ መሮጥ አይችሉም፡፡ ከዚያ ይልቅ ይመርጣሉ፤ ደግሞም ምን ሊፈጠር እንደሆነ እንኳን አያውቁም፡፡

ይሁንና ጥቂቶቹ ልክ እንደ ኦሎምፒክ ተወዳዳሪዎች ናቸው፡፡ ወዲያውኑ ፈጥነው መሮጥ ይጀምራሉ፡፡ እናም ታላቅ ውድድር ይኖራል፡፡ ምክንያቱም

ዋናው ነገር ወደ እናቲቱ እንቁላል የሚሮጡት በጥቂት መቶዎች የሚቆጠሩ ሀዋሳት አይደሉም፡፡ እናቲቱ የእንቁላሎች ማጠራቀሚያ ጋን እሳት፡፡ የእንቁላሎች መጠን ውስን በመሆኑ በየወሩ አንድ እንቁላል ይለቀቃል፡፡ ስለዚህ ቁጥራቸው በሚልዮኖች ከሚቆጠረው ከነዚያ ሁሉ ሀያው ሀዋሳት ውስጥ አንድ ብቻ እድለኛ ይሆናል ..... በእውነቱ ይሄ ትልቅ ፍልስፍናዊ ችግር ነው!

ይሄ ሌላ ምንም ሳይሆን የስነ - ሀይወት ሳይንስ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ችግሩ በብዙ ሚልዮኖች ከሚቆጠሩት ሰዎች መካከል አንድ ሰው ብቻ ነው መወለድ የሚችለው፡፡ ታዲያ እነዚያ በሚሊዮን የሚቆጠሩት ሌሎቹ ወደ እናትየው እንቁላል ውስጥ መግባት ያልቻሉት እነማን ናቸው? ይህ እንግዲህ ህንድ ውስጥ ስለወሊድ መከላከያ ሲነሳ የሂንዱ ሊቀውንት፣ ፓንዲትስ፣ <ሻንካራቻሪያዎች> የሚጠቀሙበት አንዱ መከራከሪያ ነው፡፡

ሀንዳዊያን ክርክር ላይ ብልህ ናቸው፡፡ ጳጳሱ ስለ ወሊድ መከላከያ ማውራታቸውን ቀጥለዋል፡፡ ነገር ግን አንድም የመከራከሪያ ነጥብ አላነሱም፡፡ ቢሆንስ የሀንዱ እቾቸው በጣም ጥቂት ተቀባይነት ያላቸው መከራከሪያ ሀሳቦችን አንስተዋል፡፡ አንደኛው የመከራከሪያ ነጥባቸው ልጅ መውለድ ማቆሚያው የት ላይ ነው? ሁለት ልጆች ከተወለዱ በኋላ ነው ወይስ ሶስት? ራቢንድራናዝ ታጎሬ ለወላጆቹ አስራ ሦስተኛው ልጅ ነው ይባላል፡፡ የወሊድ ቁጥጥር ተግባራዊ ሆኖ ቢሆን ራቢንድራናዝ የሚባል ሰው ባልኖረ ነበር፡፡

የመከራከሪያ ነጥቡ ተቀባይነት ያለው ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ወሊድን መቆጣጠር ማለት ከሁለተ ቢበዛ ከሦስት ልጅ በኋላ መውለድን ማቆም ነው፡፡ እንዲ ሊመት ወይም ሌላ ነገር ሊፈጠር ስለሚችል እድል አይሰጥም፡፡ የእናንተን እና የሚስታችሁን ዘር ለማብዛት ሁለት ልጆች ልትወልዱ ትችላላችሁ፡፡ ስለዚህም የህዝብ ብዛት ያንን ያህል አይጨምርም፡፡ ነገር ግን ራቢንድራናዝ ለወላጆቹ አስራ ሶስተኛ ልጅ ነበር፡፡ ወላጆቹ ደርዘን ልጅ ከወለዱ በኋላ አቁመው ቢሆን ኖሮ ራቢንድራናዝ ባቡሩ አምልጦት ነበር፡፡ አሁን እንግዲህ ምን ያህል ራቢንድራናዞች ናቸው ባቡሩ ያመለጣቸው? ከሻንካራቻሪያዎቹ መካከል አንዱን አዋራሁት፡፡ "በጣም ትክክል ነህ፡፡ ከክርክር አንፃር ሀሳቡ እውነት መሆኑን እቀበላለሁ፡፡ የወሊድ መከላከያ ጥቅም ላይ በመዋሉ የተነሳ አንድ ራቢንድራናዝ ታጎሬ ልናጣ እንችላለን፡፡ እኔ ግን እሱን ለማጣት ፍላጎት አለኝ፡፡ መላው የሀገሪቱ ህዝብ በሰላም ሊኖር





ከቻለ፣ በቂ ምግብ ካገኘ፣ በቂ ልብሶች ካገኘ፣ መሰረታዊ ፍላጎቶቹ ሁሉ ከተሟሉ፣ ይሁና ምን አለበት? በበኩሌ አንድ ራቢንድራናዝ ለማጣት ዝግጁ ነኝ፡፡ ምንም አይደለም፡፡ ሚዛናዊነቱን ማየት አለብህ፡፡ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ከሞቱ እና ከተራቡ አንድ ራቢንድራናዝ ታጎሬን ለማግኘት ሲባል ብዙ ልጅ መውለዱ ምን ይጠቅማል? ታዲያ ሁሉም ወላጆች አስራ ሦስት ልጅ መውለድ አለባቸው? በዚህ አይነት አስራ አራተኛውስ ልጅ? አስራ አምስተኛውስ ልጅ?" አልኩት፡፡

ደግሞም እነዚህን አነስተኛ ቁጥሮች እርሷቸው፡፡ ሰዎች ፍቅር በሚሰሩበት በእያንዳንዷ ቅፅበት በሚልዮኖች የሚቆጠሩ የወንድ ዘረ ሀዋሶች ይለቀቃሉ፡፡ ግን ሰዎች ፍቅር በሰሩ ቁጥር ልጅ አይወለንም፡፡ ፍቅር በሚሰራበት በእያንዳንዱ ቅፅበት በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ይጠፋሉ፡፡ ምን ያህል ቁጥር ያላቸው የኖቤል ሽልማት ተሸላሚዎች፣ ፕሬዝዳንቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ወይም ሌሎች ሰዎች በዚያ ውስጥ እንዳሉ ለማወቅ አንችልም፡፡

እንግዲህ ስሌቱ ምን መሰላችሁ? ከአስራ አራት እስከ አርባ ሁለት አመት እድሜ አንድ ሰው በጤናማ ሁኔታ ፍቅር የሚሰራ ከሆነ ከመላው የአለም ህዝብ ጋር እኩል መጠን ያለው የወንድ የዘር ፍሬ ሀዋስ ያስወግዳል፡፡ አንድ ሰው የመላውን አለም ህዝብ ያህል ልጆች ሊወልድና ከልክ በላይ አለምን ሊያጨናንቅ ይችላል! ይታያችሁ አለም ገና ድሮ ተጨናንቃለች! እናም እነዚህ ሁሉ ሰዎች ከሰብእዊነታቸው በስተቀር ከሌሎች ጋር ምንም የሚጋሩት ነገር የሌላቸው የተለያዩ ሰዎች ይሆናሉ፡፡

የለም - የለም! ህይወት እዚያ ላይ አይጀምርም፡፡ ህይወት የሚጀምረው ከወደኋላ ነው፡፡ ይህ ለእናንተ ተራ ንድፈ - ሀሳብ ብቻ ነው፡፡ ለእኔ ግን ተሞክሮ ነው፡፡ ህይወት የሚጀምረው ያለፈው ህይወታችሁ በሞተበት ቅፅበት ላይ ነው፡፡ ስትሞቱ በህይወት ምዕራፍ በአንዱ ወገን ሰዎች መላው የህይወታችሁ ገፅታ አድርገው የሚያስቡት ገፅታ ይዘጋል፡፡ ይህ የተየለሌ ምዕራፎች ባሉት አንድ መፅሀፍ ውስጥ ያለ አንድ ምዕራፍ ብቻ ነው፡፡ አንዱ ምዕራፍ ይዘጋል፡፡ ነገር ግን መፅሀፉ አይዘጋም፡፡ በቃ ገፁን ስትገልጡት ሌላኛው ምዕራፍ ይጀምራል፡፡

በሞት ላይ የሚገኝ ሰው ቀጣይ ህይወቱን በአይነ ህሊናው ያያል፡፡ ይህ ደግሞ የሚታወቅ እውነታ ነው፡፡ ምክንያቱም ምዕራፉ ከመዘጋቱ በፊት

ይከሰታል፡፡ እልፍ እልፍ አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው ከመጨረሻው ተመልሶ ይመጣል፡፡ ለምሳሌ ውሃ ውስጥ እየሰጠመ ይሆን ይሆናል፡፡ ነገሩ በሆነ መንገድ ይድናል፡፡ ራሱን ስቷል - <ኮማ> ውስጥ ነው ሊባል ይችላል፡፡ እናም ውሃው ከውስጡ መውጣት አለበት፡፡ ሰው ሰራሽ ትንፋሽም ሊሰጠው ይገባል፡፡ እናም በሆነ መንገድ ይድናል፡፡ ብቻ ምዕራፉን ለመዝጋት ጫፍ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ እንደዚህ አይነቶቹ ሰዎች አስደናቂ እውነታዎችን ተናግረዋል፡፡

ከእነዚህ አንዱ እየሞቱ መሆናቸው እየተሰማቸው ባለበት ቅፅበት፣ ሁሉ ነገር ባበቃበት ጊዜ፣ መላውን ህይወታቸውን የመጨረሻው ከፊታቸው ያዩታል፡፡ ከልደታቸው ጀምሮ እስከዚያ ቅፅበት ያለው እንደ ብልጭታ ይታያቸዋል፡፡ በሴኮንድ ክፍልፋዮች ውስጥ ያንጠማቸውን ነገር የማታወሳቸው ነገር በሙሉ እንዲሁም የማያስታውሷቸውም በሙሉ ይታዩዋቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ትኩረት ያልሰጧቸው እና ያላወቋቸው ጭምር በሙሉ የትውስታቸው አካል ይሆናሉ፡፡ መላው የትውስታቸው ምስል እንደ ብልጭታ ሆኖ በፍጥነት ይታያቸዋል፡፡ ይህ ሁሉ የሚሆነው በሴኮንድ ክፍልፋይ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ምክንያቱም እየሞቱ ስለሆነ ጊዜ የላቸውም፡፡

በተጨማሪም መላውን ትዕይንት ብታዩትም የአንድን ሰው ሙሉ ታሪክ ከትንሽ <እዚህ ግባ> ከማይባሉ ዝርዝሮች ጋር ማዛመድ አትችሉም፡፡ ነገር ግን ሁሉም ነገር ታይቶታል፡፡ ይሄ እርግጥ ነው፡፡ ደግሞም በጣም አስፈላጊ የሆነ ክስተት ነው፡፡ ምዕራፉን ከመጨረሱ በፊት ሁሉንም ተሞክሮዎቹን፣ ያልተሟሉ ጉጉቶቹን፣ የወደፊት ሀሳቦቹን፣ ቅሬታዎቹን፣ ጭንቀቶቹን፣ ስቃዮቹን፣ ደስታውን .... ሁሉንም ነገር በድንገት ያስታውሳል፡፡

**ህይወት የሚጀምረው የለፈው ህይወታችሁ በሞተበት ቅፅበት ላይ ነው፡፡ ስትሞቱ በህይወት ምዕራፍ በአንዲ ወገን ሰዎች መላው የህይወታችሁ ገፅታ አድርገው የሚያስቡት ገፅታ ይዘጋል፡፡ ይህ የትየለሌ ምዕራፎች ባሉት አንድ መፅሀፍ ውስጥ ያለ አንድ ምዕራፍ ብቻ ነው፡፡ አንዱ ምዕራፍ ይዘጋል፡፡ ነገር ግን መፅሀፉ አይዘጋም፡፡ በቃ ገፁን ስትገልጡት ሌላኛው ምዕራፍ ይጀምራል፡፡**

ቡድሃ ይህንን ክስተት የሚጠራበት ቃል አለው፣ <ታንሀ> ብሎ ይጠራዋል፡፡ ቃል በቃል ሲተረጉም ፅኑ ፍላጎት (ጉጉት) ማለት ሲሆን ፍካሬያዊ ፍቺው





ግን <የመላው ህይወት ፅኑ ፍላጎት> ማለት ይሆናል፡፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች - ፍንቶች፣ እርካታ፣ ቅሬታ፣ ስኬት፣ ውድቀት ይከሰታሉ፡፡ ነገር ግን የሚከሰቱት ፅኑ ፍላጎት (ጉጉት) ብላችሁ በምትጠሩት መድረክ ውስጥ ነው፡፡

እየሞተ ያለ ሰው ይበልጥ ርቆ ከመንዙ በፊት ይህንን ማየት አለበት፡፡ ምክንያቱም ይህ አካሉ አብሮት ይሄዳል፡፡ አእምሮው፣ አንጎሉ ግን አብሮት አይሄድም፡፡ ከእዚህ አለም አዕምሮው ውስጥ የሚለቀቀው ፅኑ ፍላጎት ከነፍሱ ጋር ይጣበቃል፡፡ ይህ ፅኑ ፍላጎት የወደፊት ህይወቱን ይወስናል፡፡ ሳይሳካ የቀረውን ማንኛውም ነገር ለማሳካትም ወደ ኢላማው ያመራል፡፡

ህይወታችሁ የሚጀምረው ከመወለዳችሁ በፊት፣ ገና እናታችሁ ሳትፀንስ በፊት፣ ገና ድሮ ያለፈው ህይወታችሁ ፍፃሜ ባገኘ ጊዜ ነው፡፡ ያ ፍፃሜ የዚህ ህይወት መጀመሪያ ነው፡፡ አንዱ ምዕራፍ ሲዘጋ ሌላው ይከፈታል፡፡ አሁን ይህ አዲስ ህይወታችሁ ዘጠና ዘጠኝ ከመቶ የሚወሰነው የምትሞቱበት የመጨረሻ ቅፅበት ይሆናል፡፡ ስብስባችሁት የነበረ፣ እንደ ዘር ያመጣችሁት ፍሬ ዛሬ ይሆንና ዘሮችን፣ ፍሬዎችን ወይም አብረውት የነበሩትን ነገሮች ይዛ ይመጣል፡፡ ይህንን ደግሞ ከዘሩ ውስጥ ማንበብ አትችሉም፡፡ ነገር ግን ዘሩ ሁሉንም ንድፍ ይዟል፡፡

ምናልባት አንድ ቀን ሳይንስ ከዘሩ ውስጥ መላውን መርሃ - ግብር ማንበብ የሚቻልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ዛፉ ምን አይነት ቅርንጫፎች እንዳሉት፣ ለምን ያህል ጊዜ በህይወት እንደሚኖር፣ በመጨረሻም ምን ሊሆን እንደሚችል ይታወቅ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ንድፉ አለ፡፡ የማናውቀው ቋንቋውን ነው፡፡ እያንዳንዱ የሚፈጠረው ነገር ወደፊት ሊደረስበት በሚችልበት መንገድ ተቀምጧል፡፡

**እየሞተ ያለ ሰው አካሉ አብሮት ይሄዳል፡፡ አእምሮው፣ አንጎሉ ግን አብሮት አይሄድም፡፡ ከእዚህ ዓለም አዕምሮው ውስጥ የሚለቀቀው ፅኑ ፍላጎት ከነፍሱ ጎር ይጣበቃል፡፡ ይህ ፅኑ ፍላጎት የወደፊት ህይወቱን ይወስናል፡፡ ሳይሳካ የቀረውን ማንኛውም ነገር ለማሳካትም ወደ ኢላማው ያመራል፡፡**

ስለዚህ በምትሞቱበት ጊዜ የምታደርጉት ነገር እንዴት እንደምትወስዱ ይወስናል፡፡ ብዙ ሰዎች የሙዋች እንዳሉ ይሞታሉ፡፡ መሞት እንደምትወለዱ ደግሞም ለምን ለመሞት እንዳልፈለጉ አንድ ሰው ሊገባው አይፈልጉም፡፡ በሚሞቱበት ቅፅበት ነው የአለመኖራቸውን እውነታነት የሚገነዘቡት፡፡ ህይወት ልክ እንደ ህልም ሆኖ አልፏል፡፡ ሞት መጥቷል፡፡ አሁን ተጨማሪ ጊዜ የለም፡፡ ሞት በሩን እያንኳኳ ነው፡፡ እናም ለመኖር የሚቻልበት ጊዜ ሲኖር ህይወትን ከመኖር ይልቅ አንድ ሺህ አንድ የማይረቡ ነገሮችን እያደረጋችሁ ጊዜያችሁን ታባክናላችሁ፡፡

ካርታ እና ቼዝ የሚጫወቱ ሰዎችን "ምን እያደረጋችሁ ነው?" ብዬ እጠይቃቸዋለሁ፡፡

"ጊዜን እየገደልን ነው" ይላሉ፡፡

ገና ከልጅነቴ ጀምሮ ይህንን <ጊዜን መግደል> የሚለውን እንደተቃወምኩት ነው፡፡ አያቴ ታላቅ የቼዝ ተጫዋች ነበር፡፡ "አሁን አገላለፅ እየገፋ ነው፡፡ አንተ ግን ጊዜን ትገድላለህ፡፡ ጊዜ እየገደለህ መሆኑን አታስተውልም? ስለማታስተውልም አንተ ጊዜን እየገደልክ መሆኑን ትናገራለ፡፡ ጊዜ ምን እንደሆነ እንኳን አታውቅም፡፡ የት እንዳለም አታውቅም፡፡ እስኪ ያዘውና አሳየኝ" እለዋለሁ፡፡

እነዚህ <ጊዜ በረረ፤ ጊዜ አለፈ፤ ጊዜ ሄደ> የሚሉ አገላለፆች በሙሉ መፅናኛ ናቸው፡፡ እውነቱን ካየነው እያለፋችሁ፤ በየጊዜው ቀልቀል እየፈሰሳችሁ የላችሁት እናንተ ራሳችሁ ናችሁ፡፡ ነገር ግን ጊዜ እንደሚያልፍ፤ እናንተ ደግሞ እንደምትቆዩ ሁሉ <ጊዜ ያልፋል> እያላችሁ ማሰባችሁን ተያይዛችሁታል! ጊዜ አያልፍም፤ ባለበት ቦታ ላይ ነው፡፡ የእጅ ሰአቶች እና የግድግዳ ሰአቶች በጭራሽ የማያልፈውን ጊዜን ለመለካት ሰዎች የፈለሰፉዋቸው ነገሮች ናቸው፡፡

በህንድ ሀገር ፑንጃብ ውስጥ በፑንጃብ ግዛት እየተጓዛችሁ ከሆነ ማንንም ሰው ቢሆን "ስንት ሰአት ነው?" ብላችሁ እንዳትጠይቁ፡፡ ምክንያቱም ይህንን ጥያቄ የጠየቃችሁት አስራ ሁለት ሰአት ላይ ከሆነ ትደበደባላችሁ፡፡ ምናልባት በህይወት ማምለጥ ከቻላችሁ በሆነ ተአምር መሆን አለበት፡፡ ይህ የሚሆነው አንድ የፍልስፍና ምክንያት ስላላቸው ነው፡፡ ፍልስፍና በቂሎች እጅ ላይ ከወደቀ የሚፈጠረው ነገር ይኸው ነው፡፡





የሲክሂዝም መስራች ናናክ "ሁሉም ነገር ብሩህ የሚሆንበት ቅጽበት <የሳማድሂ ጊዜ> - ልክ በአስራ ሁለት ሰአት ላይ እንደሚታዩት የሰአትና የደቂቃ ቆጣሪ እጆታዎች ነው፡፡ በዚያን ጊዜ እጆታዎቹ አንድ ይሆናሉ፡፡" የደቂቃ ቆጣሪ እጆታዎች ነው፡፡ በዚያን ጊዜ እጆታዎቹ አንድ ይሆናሉ፡፡" (አንድ በሌላው ላይ ይሆናል) ብሎ ነበር፡፡ እንግዲህ ይህንን ሲል በ<ሳምሃዲ> ጊዜ የተፈጥሯችሁ ሁለትነት እንደሚጠፋና አንድ ወደ መሆን ደረጃ ላይ መድረሳችሁን ምሳሌ መስጠቱ ነው፡፡ በምንሞትም ጊዜ የሚፈጠረው ይኸው ነው፡፡ በኋላ ላይ ሰው ሲሞት የሚፈጠረው ይኸው መሆኑን ገልጿል፡፡ እንደገና ለየብቻ ይንቀሳቀሱ የነበሩት እጆታዎች አንድ ላይ በመሆን ይቆማሉ፤ አንድ ይሆናሉ፡፡ እናንተም ከህይወት ጋር አንድ ትሆናላችሁ፡፡

ስለዚህ ፑንጃብ ውስጥ አስራ ሁለት ሰአት የሞት ምልክት ሆኗል፡፡ "ሰአት ስንት ነው?" ብላችሁ ማንኛውንም <ሳርዳርጅ> (የፑንጃብ ሰው) ብትጠይቁት እና ሰአቱ አስራ ሁለት ሰአት ከሆነ እናንተን መግታት ይጀምራል - እያበሸቃችሁት እና እንዲሞት እየረገማችሁት ነውና፡፡ ፑንጃብ ውስጥ ስለ አንድ ረጅም ፊት ስላለው የተከፋና የተጨነቀ ሰው ሲናገሩ "ፊቱ ላይ አስራ ሁለት ሰአት ሆኗል" ይላሉ፡፡ ሳርዶርጆች ሰአታቸውን ሲቀይሩ አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን ቶሎ ብለው አምስት ደቂቃ ወደፊት አይቻለሁ፡፡ አስራ ሁለት ሰአት ላይ አይተውትም፡፡ የገዛ ሰአታቸው ያስኬዱታል፤ አስራ ሁለት ሰአት ላይ አይተውትም፡፡ የገዛ ሰአታቸው ሊያታልላቸው ደስ አይላቸውም፡፡ አስራ ሁለት ቁጥር የሚያስታውሳቸው መከራ፤ ሀዘንና ሞትን ብቻ ነው፡፡ ስለ <ሳምሃድኒ> ሙሉ በሙሉ ረስተዋል፡፡ ናናክ ሊገልፅላቸው የሞከረውን ቁም ነገር በንግተውታል፡፡

እነዚህ <ጊዜ በረረ፤ ጊዜ አለፈ፤ ጊዜ ሄደ> የሚሉ አገላለፆች በሙሉ መፅናኛ ናቸው፡፡ እውነቱን ካየነው እያለፋችሁ፤ በየጊዜው ቁልቁል እየፈሰሳችሁ ያላችሁት እናንተ ራሳችሁ ናችሁ፡፡ ነገር ግን ጊዜ እንደሚያልፍ፤ እናንተ ደግሞ እንደምትቆዩ ሁሉ፤ <ጊዜ ያልፋል> እያላችሁ ማሰባችሁን ተያይዛችሁታል!

አንድ ሰው ሲሞት - ለእሱ አስራ ሁለተ ሰአት ሲሞላበት ህይወትን የሙጥኝ ይላል፡፡ መላው ህይወቱን ጊዜ እያለፈ መሆኑን ሲያስብ ቆይቷልና፡፡ አሁን ደግሞ እሱ ሊሄድ ነው! ሊያልፍ ትንሽ ነው የቀረው፡፡ የቱንም ያህል የሙጥኝ ቢል የሚጠቅመው ነገር የለም፡፡ መከራ ላይ ይወድቃል፡፡ መከ...

ለመቋቋም የማይቻል በመሆኑ ብዙ ሰዎች ከመሞታቸው በፊት ራሳቸውን ስተው <ኮማ> ውስጥ ይገባሉ:: ስለዚህ መላውን ህይወታቸውን መልሰው የማስታወሱን አጋጣሚ ያጡታል::

ህይወትን የሙጥኝ ካላላችሁ፣ ስትሞቱ ከዚያ በኋላ ለጥቂት ቅፅበት ያህል እንኳን ህያው ሆኖ የመቆየት ፍላጐት ከሌለ፣ ንቁ እንደሆናችሁ ትሞተላችሁ:: ምክንያቱም ተፈጥሮ ራሳችሁን የምታስታችሁ፣ የግድ ኮማ ውስጥ የምታስገባችሁ ምክንያት አይኖራትም፣ እንደነቃችሁ ትሞታላችሁ፣ እናም ያለፈውን ጊዜ በሙሉ ታስታውሳላችሁ:: ስታደርጉት የቆያችሁት ነገር በሙሉ የማይረባ እንደነበረም ለማወቅ ትችላላችሁ::

ፅኑ ፍላጐታችሁ ተሟልተዋል - ታዲያ ምን አገኛችሁ? ፅኑ ፍላጐቶቻችሁ ሳይሟሉ ቀርተው ተሰቃይታችኋል:: ነገር ግን በመሟላታቸው የተነሳ ምን አገኛችኋል? ይህ እንግዲህ ሁልጊዜም የምትሸነፉበት አስገራሚ ጨዋታ ነው:: ደግሞም አሸነፋችሁም - ተሸነፋችሁ ምንም ልዩነት የለውም::

ደስታዎቻችሁ ውሃ ላይ ያረፉ ፊርማዎች እንጂ ሌላ ምንም አልነበሩም:: ህመማችሁም በአለቶች ላይ ተቀርፀው ታትመዋል:: ህይወታችሁም በሙሉ በዚያ ሁሉ ህመም የተሰቃያችሁት በእነዚህ በውሃ ላይ ላረፉት ፊርማዎች ብላችሁ ነው:: በዚህ ደረጃ ህይወታችሁን ሙሉ የተጉዳችሁት - ከዚህ ከፍታ፣ የመላው ህይወታችሁን ገደል ለማየት ከምትችሉበት ከዚህ ነጥብ ላይ ከአሻንጉሊቶች ያልበለጡ መሰለው ለሚታዩዋችሁ ለነዚህ ትናንሽ ደስታዎች ብላችሁ ነበር:: ስኬቶቹ ውድቀቶችም ነበሩ:: ውድቀቶቹ በእርግጥም ውድቀቶች ነበሩ:: እናም ደስታዎች በህመም ለመሰቃየት የሚገፉ ማበረታቻዎች እንጂ ሌላ ምንም ነገር አልነበሩም::

ያ ሁሉ ያለምክንያት የተደሰታችሁበት ነገር የህልማችሁ ውጤት ነበር:: ባዶ እጃችሁን ልትሄዱ ነው:: ይህ ሁሉ ህይወት የማያቋርጥ ኡደት ሆኖ ቆይቷል:: አሁንም፣ አሁንም ያለማቋረጥ በአንድ አይነት ኡደት ውስጥ ዙሪያውን መሄዳችሁን ገፍታችሁበታል:: ግን የትም ቦታ አልደረሳችሁም:: ምክንያቱም በኡደት ውስጥ በመንቀሳቀስ የትም ቦታ ላይ ልትደርሱ ትችላላችሁን? በኡደቱ ውስጥ የትኛውም ቦታ ላይ ብትሆኑ ማዕከሉ ሁልጊዜም በተመሳሳይ ርቀት ላይ ሆኖ ይቀራል::





ስሌት መጣ፣ ውድቀት መጣ፣ ደስታ መጣ፣ ስቃይ መጣ፣ ሁልጊዜም ቢሆን መከራም አለ፣ ደስታም አለ:: በኡደቱ ውስጥ ሁሉም ነገር መከሰቱን ገፋብኗታል:: ነገር ግን የተፈጥሯችሁ ማዕከል ከእያንዳንዱ ቦታ ያለው ርቀት ሁልጊዜም እኩል እንደሆነ ነው:: በኡደቱ ውስጥ ሆናችሁ ይህንን ማየት ይከብዳችኋል:: ከልክ በላይ በውስጡ ናችሁና፣ ከመጠን በላይ የኡደቱ አካልም ሆናችኋል:: ሆኖም አሁን ድንገት ሁሉም ነገር ከእጃችሁ ላይ ወድቋል፣ ባዶ እጃችሁን ነው የቆማችሁት::

ካሊል ጂብራን <ዘ ፕሮፌት> (ነብዩ) በሚለው ዘመን የማይሽረው ምርጥ ስራው አንድ ምርጥ ዓረፍተ ነገር አለው ... ነብዩ አል - ሙስጣፋ በማሳዎቻቸው ላይ በስራ ተጠምደው ወደነበሩት ሰዎች እየተጣደፈ ይሄድና "መርከቡ ከዚህ ደርሳለች:: የመሄጃዬ ጊዜ ደርሷል:: እዚህ የመጣሁት በዚህ የሰተውን እንዲሁም በዚህ ያልተከሰተውን ነገር በሙሉ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ለማየት ብቻ ነው:: መርከብ ላይ ከመሳፈሬ በፊት እዚህ ያለው ህይወቴን ምን ይመስል እንደነበር ለማየት በጣም ናፍቅያለሁ" አላቸው::

እኔም ላስታውሳችሁ የነበረው ዓረፍተ ነገር ... "እኔ ልክ ወደ ውቅያኖስ ውስጥ እንደሚገባ ወንዝ ነኝ:: ወንዙ ያለፈበትን ሸንተረር፣ ሜካዎቹን፣ ተራሮቹን እና ሰዎቹን መለስ ብሎ ለመመልከት ለጥቂት ጊዜ ያህል ቆም ይላል:: በሺዎች የሚቆጠሩ ማይሎችን አቋርጦ ሲመጣ በህይወት የበለፀገ ነበር:: አሁን ግን በአንዲት ትንሽ ቅፅበት ውስጥ ሁሉም ነገር ሟሙቶ ሊቀር ነው:: ስለዚህ በውቅያኖስ ውስጥ ሊገባ ጫፍ ላይ የደረሰ ወንዝ ወደ ኋላው እንደሚመለከተው ሁሉ እኔም ወደ ኋላ መመልከትን ፈለግሁ" ይላል::

ይሁንና እንደዚህ ወደ ኋላ ለመመልከት የሚችለው፣ ያለፈ ጊዜ ላይ የሙጥኝ ካላላችሁ ብቻ ነው አለበለዚያ እንዲታጡት ሲጥት ስለሚኖርባችሁ እስተውሉ ለመመልከት፣ ለማየት ጊዜ የላችሁም:: ደግሞም ጊዜ የጨከንድ ሽራፊ ነው:: አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ንቁ ሆኖ ያለፈበትን መላውን ሸንተረርና ሜዳ እያየ፣ የማይረባ መሆኑን እያስተዋለ ከሞተ፣ በሰላ አእምሮ፣ በእውቀት፣ በድፍረት ተሞልቶ ወዲያውኑ ይወለዳል:: ታዲያ ይህን ነገር ያደረገው እሱ ራሱ አይደለም::

ሰዎች ግብዝነትህ ሳይቀር አእምሮህ የሰላ፣ ደፋርና ብልህ ነበርክ:: እኔ ግን አሁንም እንኳን ያንን ያህል ደፋር አይደለሁም .... " ይሉኛል:: የዚህ

ምክንያቱ ባለፈው ህይወቴ ስሞት ከእናንተ በተለየ ሁኔታ መሞቴ ነው፡፡ ይህ እንግዲህ ትልቅ ለውጥ ያመጣል፡፡ ምክንያቱም እንደ እሟሟታችሁ ትወለዳላችሁ፡፡ እሟሟታችሁ የሳንቲሙ አንዱ ገፅታ ነው፡፡ አወላለዳችሁ ደግሞ የዚያው ሳንቲም ሌላው ገፅታ ነው፡፡

በሌላኛው ወገን መደናገር፣ መከራ፣ ጭንቀት፣ ግትርነትና ሰኑ ፍላጐት ካለ በዚህኛው የሳንቲሙ ገፅታ የአእምሮን መስላት፣ ድፍረት፣ ንስሀና እና እውቀት (ግንዛቤን) መጠበቅ አትችሉም፡፡ ይሄ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ሊታሰቡት አትችሉም፡፡

ለዚህም ነው በጣም ቀላል፣ ነገር ግን ለእናንተ ለመግለፅ የማያስቸግር የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ሀይወት ውስጥ ገና ከመነሻው ጀምሮ ደፋር ወይም አእምሮው የሰላ ብልህ ሰው ለመሆን ያደረግሁት ነገር የለም፡፡ ደግሞም ስለ ድፍረት ወይም የአእምሮ ብሩህነት አሊያም ብልህነት በተመለከተ በጭራሽ አስቤው አላውቅም፡፡

እያደግኩ ስሄድ፣ ያለፈው ሀይወቴን እና ሞቴን መገንዘብ ጀመርኩ፡፡ ፍላጐቴ ካየሁትና ከማውቀው ነገር በበለጠ ከፊት ለፊቴ ያለውን ያልታወቀውን ነገር በማወቅ ላይ ነበር፡፡ በፍፁም ወደ ኋላ ተመልክቼ አላውቅም፡፡ ይሃ ደግሞ ሀይወቴን በሙሉ አብሮኝ ያለ ባህሪዬ ነው፡፡ በፍፁም ወደ ኋላ አልመለከትም፡፡ ይህ ምንም ጠቀሜታ የለውም፡፡ ወደ ኋላ ተመልሳችሁ ለመሄድ አትችሉም፡፡ ታዲያ ለምን ጊዜያችሁን ታባክናላችሁ? እኔ ሁልጊዜም ወደ ፊት እመለከታለሁ፡፡ ሌሎች ሰዎች አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርጉ የሚከለክለውን ፍሬን አጥቼ የቆየሁት ለምን እንደሆነ ግልፅ ያደረገልኝ ይኸው ነው፡፡

እነዚህን ፍሬኖች የሚሰጣችሁ ላልተወቁ ነገሮች ያላችሁ ፍርሃት ነው፡፡ ያለፈውን ጊዜ የሙጥኝ ስላላችሁ በማይታወቀው ጊዜ ውስጥ ለመንቀሳቀስ ትፈራላችሁ፡፡ የሚታወቀውን፣ ግልፅ የሆነላችሁን ነገር የሙጥኝ ብላችሁታል፡፡ ምናልባት ጐጂ ወይም አስቀያሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቢያንስ ታውቂታላችሁ፡፡ ከእዚህ ሁኔታ ጋርም የሆነ አይነት ወዳጅነት (ባልንጀርነት) አዳብራችኋል፡፡

በጣም ይገርማችሁ ይሆናል፡፡ በሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ያየሁት ተሞክሮ ግን ይኸው ነው፣ ከመከራ ጋር ወዳጅነታቸውን በማዳበራቸው ብቻ





የደረሰባቸውን መከራ የሙጥኝ ይላሉ፡፡ ለረጅም ጊዜ አብረውት ስለኖሩ አሁን እሱን መተው ከትዳር ጓደኛቸው ጋር መፋታት ያህል ይሆንባቸዋል፡፡

ቢጋቡቻ እና በፍቺ ውስጥም ያለው ሁኔታ ከዚህ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ሰውዬው ቢያንስ በቀን አስራ ሁለት ጊዜ ስለፍቺ ያስባል፣ ሴትየዋም እንደ እሱ፡፡ ቢያንስ እንጂ በሆነ መልኩ ሁለቱም የማያውቁትን መጪውን ጊዜ በመፍራት ይሁን እንጂ አብረው ተቻችለው መኖሩን ይገፉበታል፡፡ ይህ ሰውዬ መጥፎ ነው፡፡ ብቻ አብረው ተቻችለው መኖሩን ይገፉበታል፡፡ እውን ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን ሌላውን ሰውዬ ማን ያውቀዋል? ምናልባት የባሰ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ቢያንስ የዚህን ሰውዬ መጥፎነትና አፍቃሪ ያለመሆን ለምዳችሁታል እና ታግሳችሁ ልታሳልፉት ትችላላችሁ፡፡ ደግሞም በትዕግስት ችላችሁ ስታልፉት ቆይታችኋል፡፡ አጥንት - ብርቱ ሆናችኋል፡፡ በጭራሽ ከማታውቁት ከአዲስ ሰውዬ ጋር ከመጀመሪያው እንደገና መጀመር ይኖርባችኋል፡፡ በመሆኑም ሰዎች የሚያውቁት ላይ የሙጥኝ ብለው እንደተጣበቁ ይቀራሉ፡፡ እስቲ ሰዎችን በሚሞቱበት ቅፅበት ልብ ብላችሁ እይዋቸው፡፡ ስቃያቸው ሞት አይደለም፡፡ ሞት በውስጡ ምንም አይነት ስቃይ የለውም፣ ፍፁም ስቃይ - አልባ ነው፣ እንዲያውም በርግጠኝነት ደስ ያሰኛል፡፡ ልክ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ እንደመግባት ነው፡፡ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ መሆን ስቃይ ያለው ይመስላችኋል? የሚሞቱ ሰዎች ስለሞት እና ስለ ጥልቅ እንቅልፍ እንዲሁም ስለደስታ አይጨነቁም፡፡ የሚጨነቁት ከእጃቸው እያፈተለከ ስላለው ስለሚያውቁት አለም ነው፡፡ ፍርሃት ማለት እንድ ትርጉም ብቻ ነው ያለው፡፡ ይኸውም የሚያውቁትን ነገር ማጣትና ወዳልታወቀው ዓለም ውስጥ መዝለት ነው፡፡

ሁልጊዜም የምታውቁትን ነገር አሽቀንጥራችሁ ለመጣል ተዘጋጁ፡፡ የታወቀን ነገር ለማሽቀንጠር ከፍላጐት የበለጠ ነገር ይኑራችሁ፡፡ እስኪበስል እንኳን አትጠብቁ፡፡ በቃ ዘላችሁ አዲስ የሆነ ነገር ላይ ጉብ በሉበት፡፡ አዲስነቱ አፍላነቱ በጣም ይማርካል፡፡ ከዚያ ድፍረት ይኖራል፡፡

ሞትን መፍራት በእርግጥም ታላቁ እና ከሁሉ በበለጠ ድፍረታችሁን የማጉዳ ፍርሃት ነው፡፡

ስለዚህ አንድ ነገር ላይ ብቻ ሀሳቤን ልሰነዝር እችላለሁ፡፡ አሁን ተመልሳችሁ ወደኋላ ወደ ቀድሞው ሞታችሁ መሄድ አትችሉም፡፡ ይሁንና አንድ ነገር

ማድረግ ልትጀምሩ ትችላላችሁ፡፡ በማንኛውም ነገር ሁልጊዜም ከሚታወቀው ወደ ማይታወቀው ለመንቀሳቀስ ተዘጋጁ፡፡

እንደዚያ ማድረጉ ነው የተሻለ የሚሆነው፡፡ እውን ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን ሌላውን ሰውዬ ማን ያውቀዋል? ምናልባት የባሰ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ቢያንስ የዚህን ሰውዬ መጥፎነትና አፍቃሪ ያለመሆን ለምዳችሁታል፡፡ ስለዚህ ታግላችሁ ልታሳልፉት ትችላላችሁ፡፡ ደግሞም በትዕግስት ችላችሁ ስታልፉት ቆይታችኋል፡፡ እጥንት - ብርቱ ሆናችኋል፡፡ በጭራሽ ከማታውቁት ከአዲስ ሰውዬ ጋር ከመጀመሪያው እንደገና መጀመር ይኖርባችኋል፡፡ ከአዲስ ሰዎች የሚያውቁት ላይ የሙጥኝ ብለው እንደተጣበቁ ይቀራሉ፡፡ በመሆኑም ሰዎችን የሚያውቁት ላይ የሙጥኝ ብለው እንደተጣበቁ ይቀራሉ፡፡ እስቲ ሰዎችን በሚሞቱበት ቅፅበት ልብ ብላችሁ እዩዋቸው፡፡ ስቃያቸው ሞት አይደለም፡፡ ሞት በውስጡ ምንም አይነት ስቃይ የለውም፤ ፍፁም ስቃይ እልባ ነው! እንዲያውም በርግጠኝነት ደስ ያሰኛል፡፡ ልክ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ እንደመግባት ነው፡፡ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ መሆን ስቃይ ይመስላችኋል? የሚሞቱ ሰዎች ስለሞት እና ስለ ጥልቅ እንቅልፍ እንዲሁም ስለደስታ አይጨነቁም፡፡ የሚጨነቁት ከእጃቸው እያፈተለከ ስላለው ስለሚያውቁት አለም ነው፡፡ ፍርሃት ማለት አንድ ትርጉም ብቻ ነው ያለው፡፡ ይኸውም የሚያውቁትን ነገር ማጣትና ወዳልታወቀው ዓለም ውስጥ መዝለት ነው፡፡

ሁልጊዜም የምታውቁትን ነገር እሽቀንጥራችሁ ለመጣል ተዘጋጁ፡፡ የታወቀን ነገር ለማሽቀንጠር ከፍላጐት የበለጠ ነገር ይኑራችሁ፡፡ እስኪበስል እንኳን አትጠብቁ፡፡ በቃ ዘላችሁ አዲስ የሆነ ነገር ላይ ጉብ በሉበት፡፡ አዲስነቱ እፍላነቱ በጣም ይማርካል፡፡ ከዚያ ድፍረት ይኖራል፡፡

ሞትን መፍራት በእርግጥም ታላቁ እና ከሁሉ በበለጠ ድፍረታችሁን የሚጉዳ ፍርሃት ነው፡፡

ስለዚህ አንድ ነገር ላይ ብቻ ሀሳቤን ልሰነዝር እችላለሁ፡፡ እሁን ተመልሳችሁ ወደኋላ ወደ ቀድሞው ሞታችሁ መሄድ አትችሉም፡፡ ይሁንና አንድ ነገር ማድረግ ልትጀምሩ ትችላላችሁ፡፡ በማንኛውም ነገር ሁልጊዜም ከሚታወቀው ወደ ማይታወቀው ለመንቀሳቀስ ተዘጋጁ፡፡







እንደዚያ ማድረጉ ነው የተሻለ የሚሆነው፡፡ የማይታወቀው ከሚታወቀው የባሰ ሆኖ ቢገኝ እንኳ ዋናው ነጥብ ይሄ አይደለም፡፡ ዋናው ነገር ከታወቀው ወደማይታወቀው የምታደርጉት ለውጥና ከሚታወቀው ወደማይታወቀው ለመሄድ ያላችሁ ዝግጁነት ነው፡፡ ይህ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ ዋጋ አለው፡፡ እናም ሁሉም አይነት ተሞክሮዎች ውስጥ ያንን ማድረጋችሁን ግፉበት፡፡ ይህን ማድረጋችሁ ለሞት ዝግጁ ያደርጋችኋል፡፡ ምክንያቱም ሞት ሲመጣ ድንገት ሞትን በመምረጥ ህይወትን እተዋለሁ" ብላችሁ ለመወሰን አትችሉም፡፡ የዚህ አይነቱ ውሳኔ ላይ ድንገት ተነስቶ አይደረስም፡፡

እያንዳንዷን ቅፅበት እየኖራችሁበት እና እየተዘጋጃችሁ እያንዳንዱን ኢንች እያንዳንዷን አለፋችሁ መሄድ አለባችሁ፡፡ የማይታወቀውን አለም ውበት እያወቃችሁት ስትሄዱ በውስጣችሁ አዲስ ባህርይ ማቆጥቆጥ ይጀምራል፡፡ ይህ ባህርይ በዚያ ያለ ነው፡፡ ብቻ በጭራሽ ተጠቅማችሁበት አታውቁም፡፡ ሞት ከመምጣቱ በፊት ከሚታወቀው ወደማይታወቀው አለም መሄዳችሁን ግፉበት፡፡ ሁልጊዜም አዲሱ ከአሮጌው እንደሚሻል አስታውሱ፡፡

እርጌ ነገር ሁሉ ወርቅ ያለመሆኑን ሲነገር ይሰማል፡፡ እኔ ግን እርጌ ነገር ሁሉ ወርቅ ቢሆንም እንኳን እርጌን ነገር እርሱት እላችኋለሁ፡፡ ወርቅ ሆኖም አልሆን ግድ ሳይሰጣችሁ አዲስ ነገርን ምረጡ፡፡ ዋናው ቁምነገር ምርጫችሁ ነው፡፡ ዋናው ጉዳይ የመማር፡ ወደ ጨለማ ውስጥ የመግባት እንዲሁም ለማወቅ ያላችሁ ምርጫ ነው፡፡ ቀስ በቀስ ድፍረታችሁ መስራት ይጀምራል፡፡ ደግሞም የአስተሳሰብ መስላት ከድፍረት ተነጥሎ የሚቆይ ነገር አይደለም፡፡ ሁለቱም አንድ አይነት የውስጥ አካል አላቸው ሊባል ይችላል፡፡

ከፍርሃት ጋር አብሮ ፈሪነት አለ፡፡ እናም የአእምሮ ዝግመት - <እስከዚህም> መሆን ይኖራል፡፡ እነዚህ ሁለቱ አንድ ላይ በመሆን እርስ በርስ ይደጋገፋሉ፡፡

የአእምሮ መስላት፣ ብልጥነት፣ ግልፅነት፣ ሚዛናዊ አስተሳሰብ እንዲሁም አዲስ ነገርን የመማር ችሎታ ከድፍረት ጋር አንድ ሆነው ይመጣሉ፡፡

በአንድ ተላል ልምምድ ጀምሩ፡፡ እግራቹ በሚኖርበት በማንኛውም ጊዜ ሁልጊዜም ቢሆን ያልታወቀውን፣ አደገኛውን፣ አስጊውንና የደህንነት ስሜት እንዲሰማን የማያደርገውን መምረጥ እንዳለባችሁ አስታውሱ፡፡ ከዚህ በኋላ ተሸናፊዎች አትሆኑም፡፡

በዚያን ጊዜ ብቻ ነው ሞት በአስገራሚ ሁኔታ ነገሮችን ግልጥልጥ አድርጎ የሚያሳይ ተሞክሮ የሚሆነው እና አዲሱን ውልደታችሁን አርቃችሁ የምታዩበትን አእምሮ ሊሰጣችሁ የሚችለው:: (ልደታችሁን) አረቃችሁ ከማስባችሁ በተጨማ አንድ የሆነ አማራጭ ይኖራችኋል:: በዚህ አይነት በኋላ በተሻለ ግንዛቤ እንዴት የሆነች እናትን ወይም አንድ የሆነ መምረጥ ትችላላችሁ:: በተለምዶ ሲታሰብ ሁሉም ነገር ሆነ አባትን የማይደረግ በቃ ድንገተኛ የሆነ ይመስላል:: ይሁንና እውቀቱ (ግንዛቤው) ተብሎ ኖሮት እየሞተ ያለ ሰው ግንዛቤ ኖሮት ይወለዳል::

እናቴን አንድ የሆነ ነገር ልትጠይቋት ትችላላችሁ:: ምክንያቱም እሷ በዚያ ነበረች:: ከተወለድኩ በኋላ ለሦስት ቀናት ምንም ወተት አልጠጣሁም:: ሁሉም ተጨንቀው ግራ ገባቸው:: ሀኪሞቹ "ይህ ልጅ ወተት አልጠጣ ካለ እንዴት በህይወት ሊቆይ ይችላል?" ብለው ተጨነቁ:: ነገር ግን ችግሬን አያውቁትም:: ምን አይነት ችግር እየፈጠሩብኝ እንዳሉም የሚያውቁት ነገር የላቸውም:: በተቻላቸው መንገድ ሁሉ ሊያስገድዱኝ ይሞክራሉ:: እኔ ደግሞ ይህንን ልገልፅላቸው የምችልበት: ወይም እነሱ ችግሬን በገባ ራሳቸው ሊደርሱበት የሚችሉበት መንገድ የለም::

ባለፈው ህይወቴ ከመሞቴ በፊት ፆም ላይ ነበርኩ:: ለሃያ አንድ ቀናት ለመፆም ወቶቹ ስለበር ፆሜን ማጠናቀት ፈልጌ ነበር:: ነገር ግን ፆሜን ሳጠናቅቅ ሦስት ቀናት ሲቀሩኝ ተገደልኩ:: እነዚያ ሦስት ቀናት ሲላው ቀርቶ በዚህ አለም ስወለድ እንኳ ግንዛቤዬ (አእምሮዬ) ውስጥ ቀርተዋል:: ስለዚህ ፆሜን መጨረስ ነበረብኝ:: በእውነቱ ግትር ነኝ! አለበለዚያ መቼም ሰዎች ነገሮችን ከአንዷ ህይወታቸው ወደ ሊላኛው ይዘው አይሄዱም:: አንድ ምዕራፍ ከተዘጋ በቃ ተዘጋ ነው::

ታዲያ ለሦስት ቀናት ያህል ምንም ነገር በአፌ ውስጥ ሊያስገቡ አልቻሉም:: በቃ ተቃወምኩዋቸው:: ከሰስት ቀን በኋላ ፍፁም ጤነኛ ሆኜ ሲያዩ: ሁሉም ተደነቁ:: "ለሦስት ቀናት ምግብ እምቢ ያለው ለምንድነው? ህመም ወይም ሌላ ችግር የለትም:: ከሦስት ቀናት በኋላ አሁንም ሙሉ ጤናማ ነው" አሉ:: ነገሩ እንቆቅልሽ እንደሆነባቸው ቀረ::

እርግጥ እነዚህን ነገሮች ባላወራ እመርጣለሁ:: ምክንያቱም ማረጋገጫ የሌላቸው ንድፈ ሀሳቦች ይሆኑባችኋል:: እኔም ብሆን በሳይንሳዊ መንገድ





ማረጋገጫ ልሰጥባቸው አልችልም:: ደግሞም በኔ ግፊት የመጣ ማንኛውንም አይነት እምነት እንዲኖራችሁ ማድረግ አልፈልግም:: ስለዚህ አእምሯችሁ ወስጥ እምነት ሊፈጥርባችሁ የሚችለውን ነገር ሁሉ ቆርጣችሁ ማውጣትን ግቱበት::

ትወዱኛላችሁ: ታምኑኛላችሁ:: ስለዚህ የምላችሁን ማንኛውንም ነገር ታምኑበት ይሆናል:: እኔ ግን ደግሜ ደጋግሜ የምነግራችሁ በእናንተ ተሞክሮ ላይ ያልተመሰረተ ማንኛውንም ነገር በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ብቻ እንድትቀበሉት ነው:: የምነግራችሁን እምነታችሁ አታድርጉት:: አንዳንድ ጊዜ ምሳሌ ስሰጣችሁ ይህን ማድረጉ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ስለማገኘው ነው:: ምክንያቱም ሰዎች "በልጅነትህ አእምሮህ የሰላና በጣም ደፋር ለመሆን የቻልከው እንዴት ነው?" ብለው ይጠይቁኛል::

እኔም ምንም ያደረግሁት ነገር የለም:: ብቻ ያለፈው የህይወት ዘመኔ ሳደርግ የነበረውን ማድረጌን ነው የቀጠልኩበት::

ድፍረት ወደ እናንተ ይመጣል::

ብቻ በቀላል ቀመር ጀምሩ: የማይታወቅ ነገር በፍፁም እያምልጣችሁ!

ብትጎዱ ሁልጊዜም የማይታወቀውን ነገር ምረጡ እና ወደፊት ገስግሱ:: ሁልጊዜም የምትከፍሉት መስዋዕትነት እንኳን መጐዳት የግድ ይሆናል: ሁልጊዜም የበለጠ አድጋችሁ: የበለጠ ጉልምሳችሁ አሉ:: ይህንን ካለፋችሁ በኋላ ግን የበለጠ ብልህ ሆናችሁ ትመጣላችሁ::



# ድፍረትን ፍለጋ

# 5

## ሰዎች ደፋሮች የሚሆኑት ጀግና በመሆን አይደለም

*ሁሉም ሰው ይፈራል፤ መፍራትም አለበት፡፡ ሀይወት ማለት አንድ ሰው መሆን የማገባውን ሲሆን ነው፡፡ እናም ደፋር የሚሆኑ ሰዎች ደፋሮች የሚሆኑት ጀግና በመሆን አይደለም - ምክንያቱም ጀግና ፍርሃቱን ገታ እንጂ በእርግጠኛነት ደፋር አልሆነም፡፡ አንድ ሰው ደፋር የሚሆነው ፍርሃቱን በመቀበል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የጀግንነት ጉዳይ አይደለም፡፡ ብቻ በቀላሉ የሀይወትን እውነታዎች ማየትና ፍርሃት ተፈጥሯዊ መሆኑን መገንዘብ ነው፡፡ በዚህም ሰው ፍርሃት የሚያስከትሉበትን ነገሮች ይቀበላቸዋል!*





# በተመስጦ የማሰላሰል ዘዴዎችና ለጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች

## ማንኛውም የታገተ ነገር ፀፀትን ይፈጥራል

### ፍርሃትና ፀፀት አንድ ናቸውን?

ፍርሃትና ፀፀት አንድ አይደሉም፡፡ የተቀበልነው ፍርሃት ነፃነት ሲሆን ያስተባበልነው፣ ውድቅ ያደረግነው እና የከነንነው ፍርሃት ፀፀት ይሆናል፡፡ ፍርሃትን የሁኔታዎች አንድ አካል አድርጋችሁ ብትቀበሉት ....

ፍርሃት የሁኔታዎች አካል ነው፡፡ ሰው አንድ በጣም ትንሽ ደቃቅ አካል ሲሆን መላው አለም ግን ሰፊ ነው፤ ሰው ጠብታ - በጣም ትንሽ ጠብታ ሲሆን መላው አለም ደግሞ የውቅያኖስ ያህል ሰፊ ነው፡፡ እናም "ምናልባት በመላው አለም ውስጥ ጠፍቼ እቀራለሁ፡፡ እኔነቴም ጠፍቶ ይቀራል" የሚል ብርክ ነፍስ ይዘራብናል፡፡ ይህ ደግሞ ሞትን ከመፍራት ጋር ይያያዛል፡፡ ሞትን መፍራት ደግሞ <አለም ድምጥማጧ ይጠፋል> ብሎ ከመፍራት የሚመጣ ነው፡፡

የሰው ልጅ መፍራቱና መብረክረኩ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ይህንን ከተቀበላችሁት፣ <ሀይወት እንዲህ ናት> ብላችሁ ካመናችሁ፣ ይህን ሙሉ በሙሉ ከተቀበላችሁት ወዲያውኑ መብረክረኩ ይቆማል፡፡ ፍርሃት - ፍርሃት እየሆነ የሄደው ያው ሀይል - ይተረተርና ነፃነት ይሆናል፡፡ ከዚያም ጠብታው ውቅያኖስ ውስጥ ገብቶ ቢሰወርም በዚያ እንደሚኖር ታውቃላችሁ፡፡ ከዚያም ውቅያኖስ ትሆናላችሁ፡፡ ከዚህ በኋላ "ህይወታችሁን ብታድኑት ታጡታላችሁ፡፡ ህይወታችሁን ብታጡትም ታድኑታላችሁ" የሚለውን የኢየሱስን አባባል ትረዱታላችሁ፡፡

ከሞት ባሻገር የመሄጃው ብቸኛው መንገድ ሞትን መቀበል ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ሞት ይሰወራል፡፡ ደፋር የመሆኛው ብቸኛው መንገድም ፍርሃትን መቀበል ነው፡፡ ከዚያ ሀይል ይወጣና ነፃነት ይሆናል፡፡ ነገር ግን ፍርሃትን

ከሆናችሁት፣ ከሆታችሁት፣ መፍራታችሁን ከደበቃችሁ እንዲሁም ራሳችሁን ለመከላከል የብረት ልብስ ብትለብሱ እና ወታደሮች ብታሰልፉ ዐዐት ነፍስ ይዘራል፡፡

ማንኛውም የታገተ ነገር ዐዐትን ይፈጥራል፡፡ እንዲወጣ ያልተፈቀደለት ማንኛውም ነገር ዐዐትን ያመጣል፡፡ ከተፈጥሮ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ፍርሃትን ያስከትላል፡፡ በዚያን ጊዜ ለሌሎችንም ሆነ ለራሳችሁ ስትዋሹ ነገር በመቆየታችሁ የዐዐት ስሜት ያድርባችኋል፡፡ ይህ ሀሰተኛነት ዐዐት ነው፡፡

"ፍርሃትና ዐዐት አንድ ናቸው?" ብላችሁ ብትጠይቁ መልሱ <አይደለም> ይሆናል፡፡ ፍርሃት ዐዐት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ፍርሃት ዐዐት ላይሆንም ይችላል፡፡ ይህ እንግዲህ ከፍርሃት ጋር ባላችሁ ግንኙነት ላይ ይመሰረታል፡፡ ከፍርሃት ጋር ያላችሁን ግንኙነት የተሳሳተ ከሆነ ዐዐት ይሆናል፡፡ ፍርሃትን በቀላሉ ከተቀበላችሁት እና ስለ ፍርሃት ምንም ነገር ካላደረጋችሁ - ምንም ሊደረግ የሚቻል ነገር የለም! ፍርሃት ንፃነት ይሆናል፣ ድፍረትም ይሆናል፡፡

የገዛ ራሳችሁን አስጠሊታ፣ የተሳሳተ ወይም ሀጢአተኛ አታድርጉ፡፡ ራሳችሁን አትዐዐቱ፡፡ ምንም ሆናችሁ ምን እናንተ ያው የሆናችሁትን ናችሁ፡፡ የሆነ የተበላሸ (የተሳሳተ) ነገር ቢኖር እንኳን እናንተ አልተሳሳታችሁም፡፡ ምናልባት የተሳሳተ ነገር ፈፅማችሁ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በዚያ የተነሳ የእናንተ ተፈጥሮ የተሳሳተ ሊሆን አይችልም፡፡ አንዳንድ ድርጊቶቻችሁ የተሳሳቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የእናንተ ተፈጥሮ ሁልጊዜም ትክክል ነው፡፡







# መፍራት ማለት ፍርሃትን መቃረን ነው

**እኔ ሁልጊዜም አስፈሳጊ እና ሀያል እንደሆንኩ፣ ሌሎችን ለማሳመን እየሞከርኩ እንዳለሁ አስተውያለሁ፡፡ የዚህን ምክንያት ለማወቅ እንድችልም በተመሰጦ ለሰላስያለሁ፡፡ እናም የዚህ ምክንያት ፍርሃት ይመስለኛል፡፡ አይደል?**

ለራስ ያለ አመለካከት (እኔነት) ሁልጊዜም ከፍርሃት ይመነጫል፡፡ እውነተኛ ደፋር ሰው የራስ አመለካከት የለውም፡፡ ለራስ የሚኖር አመለካከት መከላከያ የብረት ልብስ ነው፡፡ ምክንያቱም ትፈራላችሁ፡፡ በዙሪያችሁ "እኔ እንዲህ ..... እንዲህ ..... ነኝ፡፡ እኔ እንደዚህ ..... እንደዚህ ..... ነኝ" የሚል ሀሳብ ትፈጥራላችሁ፡፡ አይደለም እንዴ? ታዲያ ማንም ሰው ሊጎዳችሁ አይደፍርም፡፡ ያው ገና ከመሰረቱ ፍርሃት ስላለባችሁ እንጂ፡፡ ይሄ መልካም ነው! እንግዲህ ይህንን በአግባቡ እና በጥልቀት ተመልከታችሁታል፡፡ አንድ ጊዜ መሰረታዊውን መንስኤ ካያችሁት በኋላ ነገሮች በጣም ቀላል ሆነዋል፡፡ እለበለዚያ ሰዎች ለራሳቸው ካላቸው አመለካከት ጋር መጣላታቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ደግሞም እውነተኛው ችግር ለራስ ያለ አመለካከት አይደለም፡፡ ስለዚህ እየተጣላችሁ ያላችሁት ከእውነተኛው በሽታ ሳይሆን ከበሽታው ምልክት ጋር ነው፡፡ እውነተኛው በሽታ ፍርሃት ነው፡፡ ለራሳችሁ ካላችሁ አመለካከት ጋር መጣላቱን ልትገፉበት ትችላላችሁ፡፡ እናም ኢላማችሁን መሳቱን ትቀጥላላችሁ፡፡ ምክንያቱም ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት ማሳሳቻው እንጂ እውነተኛው ጠላት አይደለም፡፡ ብታሸንፉ እንኳን ምንም የምታሸንፉት ነገር አይኖርም፡፡ ደግሞም ማሸነፍ አትችሉም፡፡ ሊሸነፍ የሚችለው እውነተኛ ጠላት ብቻ ነው፡፡ ሀሰተኛ ጠላት ሊሸነፍ አይችልም፡፡ ምክንያቱም በጭራሽ የለማ! ይሄ የላይ ወብት ነው፡፡ ቁስል እንዳለባችሁ እና እስቀያሚ መስሎ ስለታያችሁ በላዩ ላይ የሆነ ጌጥ እንደማድረግ ይቆጠራል፡፡

አንድ ጊዜ ምን ሆነ መሰላችሁ? በአንድ ከተብ የፊልም ተዋናይ ቤት ውስጥ እርፌ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎችን ከቤቱ መጥተው ከእኔ ጋር እንዲገናኙ ጠየቁ፡፡ እንዲት የፊልም አክተርም በዚያ ተገኘች፡፡ ሴትየዋ የሚያምር ትልቅ ማሰሪያ

ያለው ቁንጆ ስእት አስራለች፡፡ አንድ ከአጠገቧ ተቀምጦ የነበረ ሰው ስለሰዓቷ ሊጠይቃት ትንሽ ተጨንቀች፡፡ እኔ እያስተዋልኳት ነበር፡፡ ሰውየው ሰአቱን ለማየት ፈልጓል፡፡ እሷ ደግሞ ሰአቱን ለማውለት አልፈለገችም፡፡ ሰውየው ግን አጥብቆ ጠየቃት፡፡ ይህን ጊዜ ሴትየዋ ውትውታው ስለከበዳት ልትሰጠው ግድ ሆነባት፡፡ ከዚያም በኋላ ችግሯ ምን እንደነበር ለማየት ቻልኩ፡፡ ሴትየዋ አንድ ትልቅ ነጭ የስጋ ደዌ በሽታ ጠባሳ ነበረባት፡፡ ያንን ጠባሳዋን በቆንጆው ሰአት ማሰሪያ ደብቃው ነበር፡፡ አሁን ተጋለጠች፡፡ እናም ላብ ያስምጣት ጀመር፡፡ በጣም ደንግጣለችም ......

ለራሳችን ያለን አመለካከት እንደዚህ ነው፡፡ ፍርሃት አለ፡፡ ነገር ግን ማንም ሰው ፍርሃቱን ማሳየት አይችልም - ምክንያቱም መፍራታችሁን ካሳያችሁ የበለጠ እንድትፈሩ የሚያደርጓችሁ ብዙ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ በሀይል መፍራታችሁን አንድ ጊዜ ካወቁባችሁ ሁሉም እየተነሱ በሃይል ይሰፍሩባችኋል፡፡ እናንተን ማዋረድ ያስደስታቸዋል፡፡ አንድን ሰው ደካማ ሆኖ ሲሳገኙት ይደሰታሉ፡፡ ሰዎች የዚህን አይነት ሰው መጠቀሚያቸው ማድረግና መጉሸም ደስ ይላቸዋል፡፡

ስለዚህ የፈራ ሰው ሁሉ በውስጡ በፍርሃቱ ዙሪያ ለራሱ ትልቅ አመለካከትን ይፈጥራል፡፡ እንደ ፊኛ በተነፋው ለራሱ ባው አመለካከት ውስጥ የበለጠ አየር ያስገባል፡፡ ከልክ በላይ ትልቅ ይሆናል፡፡ አዶልፍ ሒትለር፡ የኡጋንዳው ኢዲ አሚን ... ስዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው፡፡ እንዲህ ያሉት ሰዎች በጣም ይጠማጠራሉ፡፡ ከዚያ ሌሎችን ማስፈራራት ይጀምራሉ፡፡ ማንንም ሰው ለማስፈራራት የሚሞክር የትኛውም ሰው በውስጡ እሱ ራሱ በጣም መፍራቱን በሚገባ ማወቅ አለባችሁ፡፡ አለበለዚያ ለምን እንደዚያ ያደርጋል? ጥቅሙ ምንድን ነው? እሱ ራሱ ፈርቶ ካልሆነ በስተቀር እናንተን ለማስፈራራት የሚጨነቀው ማነው?

ውስጣቸው በፍርሃት የተሞላ ሰዎች ዘና ብለው እረፍት ለማግኘት እንዲችሉ በማለት ሌሎችን ያስፈራራሉ፡፡ እናንተ ከፈራችሁ እነሱን እንደማትነኩዋቸው በሚገባ ያውቃሉ፡፡ እናንተም ደፍራችሁ የእነሱን ጠረፍ አታልፉም፡፡

ደህና መስላችሁ ትታያላችሁ - በትክክል ጉዳዩም ይኸው ነው፡፡ ስለዚህ ለራሳችሁ ካላችሁ አመለካከት ጋር አትጣሉ፡፡ ከዚያ ይልቅ ፍርሃትን አስተውላችሁ ተመልከቱት እና ልትቀበሉት ሞክሩ፡፡ ፍርሃት ተፈጥሯዊ ነው፣



INFINIX HOT 8 LITE



ህይወት አንድ አካልም ነው፡፡ ፍርሃትን መደበቅ አያስፈልግም፡፡ ያለፉ መስሎ መታየትም አስፈላጊ አይደለም፡፡ ያለ ነገር ነው - ሁሉም የሰው ልጅ በፍርሃት የተሞላ ነው፡፡ የሰብአዊነት አንድ አካል ነው፡፡ ተቀበሉት፣ ፍርሃትን በተቀበላችሁበት ቅፅበት ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት ደብዛው ይጠፋል፡፡ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ለራሳችሁ ያላችሁ አመለካከት በውስጣችሁ ለዚያ ሲል የሚኖርበት ምክንያት አይኖረውም፡፡ ለራሳችሁ ካላችሁ አመለካከት ጋር መጣላቱ የሚፈይድላችሁ ነገር የለውም፡፡ ፍርሃትን መቀበል ወዲያውኑ እገዛ ያደርጋል፡፡ የዚያን ጊዜ በዚህ ሰፊ አለም ውስጥ በእርግጥም ኢምንት መሆናችንን ታውቃላችሁ፡፡ ደግሞስ እንዴት አለመፍራት ይቻላል? ህይወት እኮ በሞት የተከበበች ናት፡፡ ታዲያ እንዴት አለመፍራት ይቻላል? ህይወት እኮ በሞት የተከበበች ናት፡፡ ታዲያ እንዴት አለመፍራት ይቻላል? በማንኛውም ቅፅበት ደብዛችን ሊጠፋ ይችላል፣ እንዴት ትንሽ ነገር ብትበላሽ ያበቃልናል - ስለዚህ እንዴት አለመፍራት እንችላለን? ይህንን አምናችሁ ስትቀበሉ ቀስ በቀስ ፍርሃታችሁ ይጠፋል፡፡ ምክንያቱም አሁን መፍራቱ ምንም ጠቀሜታ የለውም፡፡ በሚገባ ተቀብላችሁታል፣ እንደዚህ አሁን ፍርሃትን ተቀብላችሁታል፣ ነው መሆን ያለበት!

ስለዚህ ፍርሃታችሁን ለመደበቅ ስትሉ አንድ የሆነ ነገር አትፍጠሩ፡፡ ደግሞም ለፍርሃታችሁ መሸሸጊያ የሚሆን ነገር ካልፈጠራችሁ በቀ እርፍ ውስጣችሁ ይኖራል፡፡ እኔ ምንም አይነት ፍርሃት አይኖራችሁ <አትፈሩም> ነው፡፡ ፍርሃት እያልኳችሁ አይደለም፡፡ እያልኩት ያለሁት ይኖራል፡፡ ነገር ግን እናንተ አትፈሩም፡፡ እየተከታተላችሁኝ ነው? መፍራት ማለት ፍርሃትን መቃረን ነው - ፍርሃት እንዲኖር አትፈልጉም፣ እሱ ግን አለ፡፡

ፍርሃትን ስትቀበሉት .... ብሮች እረንኀዶ እንደሆኑት ሁሉ ሰብአዊነትም በፍርሃት የተሞላ ነው፡፡ ታዲያ ምን ይደረጋል? ብሮች አይደበቁም፡፡ ሁሉም ሰው ለሞት የተጋለጠ ነው፡፡ ፍርሃት የሞት ጥላ ነው፡፡ ተቀበሉት!

# የተቀበልነው ፍርሃት ነፃነት ነው!

**ለብቻዬ ስሆን የወሰኑ ነገሮችን በማለፍ ሰዎችን ለማፍቀር የምችል ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን ከሰዎች ጋር ስሆን ወዲያውኑ ያሰብኩት ሁሉ ይጠፋብኛል፡፡ ለምንድነው?**

በገሃዱ አለም ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማፍቀር ይቸግራል፡፡ ምክንያቱም በገሀዱ አለም ያለ አንድ ሰው ሀሳባችሁን ሁሉ አያሟላላችሁም፡፡ አፈጣጠሩም እንደዚያ አይደለም፡፡ አንድ ሰው ወደዚህች ምድር የመጣው የማንንም ሰው ሀሳቦች ሊያሟላ አይደለም - የገዛ ራሱን ህይወት ለመኖር እንጂ፡፡ ስለዚህ ሰውየው ለእናንተ ወደማይስማማችሁ ወይም ከእናንተ ስሜቶችና ተፈጥሮ ጋር ወደማይጣጣም አቅጣጫ በሄደ ቁጥር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

ስለ ፍቅር ማሰብ በጣም ቀላል ነው፡፡ ለማፍቀርም በጣም ቀላል ነው፡፡ መላውን አለም ማፍቀር በጣም ቀላል ነው፡፡ ዋነኛው ችግር ያለው አንድን የሰው ልጅ ማፍቀሩ ላይ ነው፡፡ እግዚአብሄርን ወይም የሰው ዘርን (ሰብአዊ ፍጡርን) ማፍቀር በጣም ቀላል ነው፡፡ ዋናው ችግር የሚፈጠረው በገሃዱ አለም ካ አንድ ሰው ጋር ስትጠላለፉ እና ስትገጣጠሙ ነው፡፡ ከገሃዱ አለም ሰው ጋር መገጣጠም ማለት በታላቅ ለውጥ እና በታላቅ ፈተና ውስጥ ማለፍ ነው፡፡

ሰውየው የእናንተ ባሪያ አይሆንም፤ እናንተም እንደዚያው የእሱ ባሪያ አትሆኑም፡፡ እንግዲህ ትልቁ ችግር የሚነሳው እዚህ ላይ ነው፡፡ እናንተ ባሪያው ከሆናችሁ ወይም እሱ ባርያችሁ ከሆነላችሁ ችግር የለም፡፡ ችግር የሚነሳው ማንም ሰው ባሪያ ስለማይሆን እና ማንም ሰው ባሪያ ሊሆን ስለማይችል ነው፡፡ ሁሉም ሰው ነፃ ነው፡፡ መላ አለም በውስጡ ነፃነትን ይዟል፡፡ ሰውም ነፃነት ነው፡፡

**በገሃዱ ዓለም ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማፍቀር ይቸግራል፡፡ ምክንያቱም በገሀዱ ዓለም ያለ አንድ ሰው ሀሳባችሁን ሁሉ አያሟላላችሁም፡፡ አፈጣጠሩም እንደዚያ አይደለም፡፡ አንድ ሰው ወደዚህች ምድር የመጣው የማንንም ሰው ሀሳቦች ሊያሟላ አይደለም - የገዛ ራሱን ህይወት ለመኖር እንጂ፡፡**

INFINIX HOT 8 LITE





ችግሩ ሁልጊዜም የሚኖር መሆኑን አስታወሱ፡፡ ከእናንተ ጋር በግል የሚያያዝበት ነገር የለም፡፡ ችግሩ ያለው ከመላው የፍቅር ክስተት ጋር ነው፡፡ የግል ችግራችሁ አታድርጉት፡፡ አለበለዚያ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ትወድቃላችሁ፡፡ ሁሉም ሰው እነሰም በዛ ተመሳሳይ ከሆነ ችግር ጋር መጋፈጥ ይኖርበታል፡፡ በፍፁም በፍቅር ላይ ምንም ችግር የሌለበት ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ ሁሉም ሰው ከፍቅር ጋር፣ ከራሱ ከፍቅር አለም ጋር የተያያዘ ችግር አለበት፡፡

አንድ ግንኙነት ስትጀምሩ ገና ከመነሻው ችግሮች ወደሚነሱበት ሁኔታ ያመጣችኋል፡፡ ደግሞም በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ በራሱ መልካም ነገር ነው፡፡ በምስራቁ አለም በውስጡ ያለውን ችግር በማየት ብቻ ሰዎች ሸሽተዋል፡፡ ከዚያ ፍቅራቸውን መካድ፣ ለዚያ አለም ያላቸውን ፍቅር ውድቅ ማድረግ ጀመሩ፤ ፍቅር አልባዎች ሆኑ፡፡ ያንንም አለም <መፈታተር የሌለበት አለም> ብለው ጠሩት፡፡ ቀስ በቀስ ሙታን ሆኑ፡፡ ከምስራቁ አለም ፍቅር ድራሹ ጠፋ ማለት ይቻላል፡፡ እናም በተመስጦ ማሰላሰል ብቻ ቀረ፡፡

በተመስጦ ማሰላሰል ማለት በብቸኝነታችሁ ውስጥ ጥሩ ስሜት ሊሰማችሁ ነው፡፡ በተመስጦ ማሰላሰል ማለት ከራሳችሁ ጋር ብቻ መተሳሰር ነው፡፡ ከዚያ ውጪ አደታችሁ መላ የሚሆነው ከራሳችሁ ጋር ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን አትሄዱም፡፡ በእርግጥ በጠና በጠኝ ከመቶ ችግሮቻችሁ ይፈታል፡፡ አሁን ብዙም ችግር በጣም ብዙ የምትከፍሉት ነገር ይኖራል፡፡ አይደርባችሁም፡፡ የምስራቁ አለም ሰው ብዙም አይጓጓም፤ ብዙም ውጥረት የለበትም፡፡ የሚኖረው በገዛ ራሱ ዋሻ ውስጥ ተከልሎና አይኖቹን ጨፍኖ ነው ሊባል ይቻላል፡፡ ህይሉን እንዲንቀሳቀስ አይፈቅድለትም፡፡ የሁዳት መስመሩ አጭር ነው፡፡ በውስጡ ያለው በትንሹም ቢሆን የሞተ ይሆናል፡፡ ደስታው የእሸናፊነት ደስታ፣ ፍስሃ አይደለም፡፡

በአብዛኛው ያንን ደስታ አይደለም ለትሉት ትችላላችሁ፡፡ ምንም አይነት በሽታ ስለሌለባችሁ ጤነኛ መሆናችሁን እንደምትናገሩት ሁሉ በአብዛኛው ስለዚያ የሆነ አሉታዊ ነገር መናገር ትችላላችሁ፡፡ ይህ ግን ብዙም የጤና ስሜት አይደለም፡፡ ጤና፣ የሆነ አዎንታዊ ነገር ሊኖረው ይገባል፤ በገዛ ራሱ ድምቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ የበሽታ አለመኖር ብቻውን ጤና አይሆንም፡፡ በዚያ መልኩ ከታየማ ሊባው ቀርቶ የሞተ ሰው እስከሬን ራሱ ጤነኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም ህመም የለበትም፡፡

በመሆኑም በምስራቁ አለም ያለፍቅር ለመኖር፣ አለምን ለመካድ ሰንዋከር ቆይተናል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ፍቅርን መካድ - ሴትን፣ ወንድን ፍቅር ሊያብብባቸው የሚችልባቸውን ሁሉንም አጋጣሚዎች መካድ ነው፡፡ የሂንዱ እና የቡድሂስት መነኩሳት ብቻቸውን ሲሆኑ ሴትን እይፈቀድላቸውም፣ ሴትን መንካትም ሆነ ሲላው ቀርቶ ፊት ለፊት ማየት ሳይቀር አይፈቀድላቸውም፡፡ እንዴት ሴት አንድ የሆነ ነገር ለመጠየቅ ስትመጣ አይኖቻቸውን መስበር ይኖርባቸዋል፡፡ ሴቲቱን በስህተትም እንኳ ቢሆን እንዳያይዋት የአፍንጫቸውን ጫፍ ማየት አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ማን ያውቃል? የሆነ ነገር ሊደውልባቸው ይችላል … ደግሞም አንድ ሰው በፍቅር እጅ ላይ ከወደቀ ረዳት አልባ ይሆናል፡፡

በሰዎች ቤት ውስጥ አይቆዩም፣ በአንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ አይቆዩም፡፡ ምክንያቱም መዋደድ፣ መፈቀር ሊከሰት ይችል ይሆናል፡፡ ስለዚህ ከቦታ ቦታ መሄዳቸውን፣ መንገላወዳቸውን እንዲሁም የትኛውንም አይነት ግንኙነቶችን ማስወገድን ይገፋበታል፡፡ አንድ የሆነ አይነት የመርጋት ባህርይ ማዳበር ችለዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች የማይረበሹ፣ ስለአለም የማይጨነቁ ናቸው፡፡ ነገር ግን ደስተኞች አይደሉም፡፡ ደስታንም አያጣጥሙም፡፡

በምዕራብ አለም የተከሰተው ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡ ሰዎች ደስታን በፍቅር በኩል ለማግኘት ሲሞክሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህም ሁ ችግሮችን ፈጥረዋል፡፡ ከራሳቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሙሉ አጥተዋል፡፡ ከራሳቸው ርቀው ብዙ ሄደዋል፡፡ እንዴት አድርገው ወደራሳቸው ተመልሰው እንደሚመጡም አያውቁም፣ ቤታቸው የት እንዳለ መንገዱን አያውቁትም፡፡ በመሆኑም ሁሉም ነገር ትርጉመ - ቢስ ሆኖ ይታያቸዋል፡፡ ቤት አልባ የሆኑ ይመስላቸዋል፡፡ ስለዚህ ከዚህች ሴት፣ ከዚያ ወንድ ጋር እያሉ ፍቅርን ለማግኘት ጥረታቸውን ገፍተውበታል፡፡ በዚህ የነሳ ከተለያዩ ተቃራኒ ፆታ ካላቸው ሰዎች ጋር፣ ተመሳሳይ ፆታ ካላቸው ሰዎች ጋር እንዲሁም ከግብ ራሳቸው ጋር ፍቅር ይሰራሉ፣ በተገኘው መንገድ ሙከራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ይሁንና እንደገና ባዶ የመሆን ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ ምክንያቱም ፍቅር ብቻውን ደስታን ሊሰጣችሁ ቢችልም በውስጡ ምንም አይነት ፀጥታ አይኖረውም፡፡ ደግሞም ደስታ ሲኖርና ፀጥታ ሳይኖር ሲቀር አሁንም የሆነ ነገር ይጎድላል፡፡



IX HOT 8 LITE



ፀጥታ ሳይኖር ደስተኞች ብትሆኑ ደስታችሁ ልክ እንደ ትኩሳት፣ እንደ ግርግር ይሆናል … ምንም ነገር በሌለበት ብዙ ትርምስ፡፡ ይህ ትኩሳት በውስጣችሁ ብዙ ውጥረትን ይፈጥራል፡፡ ከውስጡ ግን ምንም የሚወጣ ነገር አይኖርም፡፡ ቤታ ፋሚ - ማሳደድ ብቻ እናም አንድ ቀን ያ ሁሉ ጥረት መስረቱ - ቢስ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ምክንያቱም ሊላኛውን ነገር ለማግኘት ስትሞክሩ ቆይታችኋል፡፡ ራሳችሁን ግን ገና አላገኛችሁትም፡፡

እነዚህ ሁለቱም መንገዶች ውድቅ ሆነዋል፡፡ የምስራቁ አለም ሰዎች ፍቅር ሳይኖር በተመስጦ ማሰላሰልን ስለሞከሩት አልተሳካላቸውም፡፡ የምዕራብ አለም ሰዎች ደግሞ በተመስጦ ማሰላሰል በሌለበት ፍቅርን በመሞከራቸው ከሽፎባቸዋል፡፡ መላው ጥረቴ አንድ መዋቅር ልሰጣችሁ ነው፡፡ ይህ መዋቅር ምሉዕ ነው፣ ማለትም በውስጡ ፍቅርን እና በተመስጦ ማሰላሰልን ይዟል፡፡ አንድ ሰው ለብቻው ሲሆን ደስተኛ ሊሆን ይገባዋል፡፡ አንድ ሰው ከሰዎች ጋር ሆኖም ደስተኛ መሆን አለበት፣ አንድ ሰው በውስጡ ደስተኛ መሆን ይገባዋል፣ ከሰዎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ውስጥም መደሰት አለበት፡፡ አንድ ሰው ከውስጥም ሆነ ከውጪ ውብ የሆነ ቤት መስራት አለበት፡፡ በቤታችሁ ዙሪያ ቆንጆ የአትክልት ስፍራ ሊኖራችሁ ይገባል፡፡ የመኝታ ክፍላችሁም እንደዚያው ውብ መሆን አለበት፡፡

ስለዚህ በተመስጦ ማሰላሰል ውስጣዊ መጠለያ -ውስጣዊ ቅዱስ ስፍራ መሆን አለበት፡፡ አለም ለእናንተ ከመጠን በላይ የሚበዛባችሁ ሲመስላችሁ ወደ ቅዱስ ስፍራችሁ ልትመለሱ ትችላላችሁ፡፡ በውስጣዊ ማንነታችሁ ውስጥ ስሎታችሁን መትጠብ ትችላላችሁ፡፡ ራሳችሁን ዳግም ማደስ ትችላላችሁ፡፡ ዳግም ተፈጥራችሁ፣ ለመኖር እንደገና ህያው፣ አዲስ፣ ወጣት ሆናችሁ፣ በድጋሚ ታድሳችሁ … ለመኖር ወደ ውጪ ለመውጣት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ሰዎችን የፈለጋችሁትን ለመሆን ወደ ውጪ ለመውጣት ትችላላችሁ፡፡ ለማፍቀር እና ችግሬችን ለመጋፈጥ አቅም ያላችሁ መሆንም ይገባችኋል፡፡ ምክንያቱም የማያስተማምን እና ችግሬችን መጋፈጥ የማይችል ፀጥታ ብዙም ፀጥታ አይባልም፣ ብዙም ጠቀሜታ የለውም፡፡

የሚያስፈልጉ የሚናፈቀው ችግሮችን ፊት ለፊት መጋፈጥ የሚችል እና በፀጥታ የሚዘልቅ ፀጥታ ብቻ ነው፡፡

በመሆኑም እነዚህን ሁለት ነገሮች ልነግራችሁ እወዳለሁ- እንደኛ በመስጦ ማሰላሰልን ተግባራዊ ማድረግ ጀምሩ፡፡ ምክንያቱም ሁልጊዜም በአቅራቢያችሁ ካለው የተፈጥሮዋችሁ ማዕከል መጀመሩ መልካም ነው፡፡ ይህ በአቅራቢያችሁ

ያለው የተፈጥሮዎቻችሁ ማዕከል ደግሞ በተመስጦ ማሰላሰል ነው፡፡ ነገር ግን በፍፁም በውስጡ ተሰንትራችሁ እንዳትቀሩ፡፡ በተመስጦ ማሰላሰል መንቀሳቀስ፣ ማበብ፣ መተርተር እንዲሁም ፍቅር መሆን አለበት፡፡

ደግሞም አትጨነቁ፡፡ በተመስጦ ማሰላሰልን ችግር አታድርጉት፣ ችግር አይደለም፡፡ በቀ ሰብአዊ ነው - ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ሁሉም ሰው ይፈራል፤ መፍራትም አለበት፡፡ ህይወት ማለት ሰው መሆን የሚገባውን ሲሆን ነው፡፡ ደፋር የሚሆኑ ሰዎች ደፋሮች የሚሆኑት ጀግና በመሆን አይደለም፡፡ ምክንያቱም ጀግና ፍርሃቱን ጉታ እንጂ በእርግጠኛነት ደፋር አልሆነም፡፡ አንድ ሰው ደፋር የሚሆነው ፍርሃቱን በመቀበል ነው፡፡ ይሄ ደግሞ የጀግንነት ጉዳይ አይደለም፡፡ በቀላሉ የህይወትን እውነታዎች የማየትና ፍርሃት ተፈጥሯዊ መሆኑን መንዘብ ነው፡፡ በዚህም ሰው ፍርሃትን የማየስከትሉበትን ነገሮች ይቀበላቸዋል!

ችግሩ የሚነሳው እናንተ የሚያስፈሩዋችሁን ነገሮች ለማጣጣል ስለምትፈልጉ ነው፡፡ በጣም ለራስ ከሚሰጥ አመለካከት ጋር የዛመዱ (የተጣጣሙ) አባባሎችን ሲታጠኑ ቆይታችኋል፡፡ "ጀግኖች ሁኑ!" ስትባሉ ነው ያደጋችሁት፡፡ ምን አይነት የማይረባ አባባል ነው! ቂልነት ነው! እንዴት አድርጉ ነደው እንድ ብልህ ሰው ፍርሃትን የማየስወግደው? ምንም የማታውቁ ደደቦች ከሆናችሁ ምንም የምትፈሩት ነገር አይኖራችሁም፡፡ በዚያን ጊዜ የአውቶቡስ ሾፌሩ ጠሩንባውን መንፋቱን ቢቀጥልም እናንተ ግን ምንም ሳትፈሩ ከመንገዱ መሀከል ትቆማላችሁ፡፡ ወይ ደግሞ አንድ ኮርማ እናንተን ለመውጋት ቀንዶቹን አሾሎ እየመጣ ያለምንም ፈርሃት ቆማችሁ ትጠብቁታላችሁ፡፡ ግን ይህን በማድረጋችሁ እላዋቂ ደደቦች ናችሁ! ብልህ ሰው ዘሎ ከመንገዱ መውጣት አለበት፡፡

ሱሰኞች ሆናችሁ በየጫካው ያለውን እባብ በየቦታው መፈለግ ከጀመራችሁ የዚያን ጊዜ አንድ ችግር አለ፡፡ መንገዱ ላይ ምንም ሰው ሳይኖር ፈርታችሁ መሮጥ ከጀመራችሁም አንድ ችግር ይኖራል አለበለዚያ ፍርሃት ተፈጥሯዊ ነው፡፡

ስለዚህ ፍርሃታችሁን ታስወግዳላችሁ ስል በህይወታችሁ ውስጥ ምንም አይነት ፍርሃት አይኖርም ማለቴ አይደለም፡፡ ዘጠና ከመቶው ፍርሃታችሁ አእምሮዋችሁ የወለደው ሀሳብ መሆኑን ታውቃላችሁ ማለቴ ነው፡፡ አስር ከመቶው ፍርሃታችሁ በእውነታው አለም ያለ በመሆኑ የግድ ልትቀበሉት ይገባችኋል፡፡ እኔ ሰዎችን ጀግና አላደርግም፡፡ ከዚያ ይልቅ የበለጠ ቀልጣፎች፣ ሀይለኞች እና ንቁዎች ነው የማደርጋቸው፡፡ ደግሞም ንቃታቸው በቂ ነው፡፡ ፍርሃታቸውን እንደመወጣጫ ድንጋይ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉም ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ አትጨነቁ፡፡





# ራስን ማጋለጥ ማለት ባዶነትን ማጋለጥ ነው

## እሁንም ድረስ ራሴን ለማጋለጥ በጣም የምፈራው ለምንድነው?

ራሱን ለማጋለጥ የማይፈራ ማን አለ? ራስን ማጋለጥ ታላቅ ፍርሃትን ይፈጥራል፡፡ ይሄ ደግሞ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ምክንያቱም ራስን ማጋለጥ ማለት በአእምሯችሁ ውስጥ የሸከማችሁትን ቆሻሻ በሙሉ ማጋለጥ ነው፡፡ ያ በብዙ የህይወት ዘመናችሁ ለክፍለ ዘመናት ያከማቻችሁት ቆሻሻ ይጋለጣል፡፡ ራስን ማጋለጥ ማለት ድክመትን፣ ገደቦችን እንዲሁም ጥፋቶችን ሁሉ ማጋለጥ ነው፡፡ እራስን እስከ መጨረሻው ማጋለጥ ማለት ስስነትን (ስስ ብልትን) ማጋለጥ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ሞት ነው ... ራስን ማጋለጥ ማለት ባዶነትን ማጋለጥ ነው፡፡

ከዚህ ሁሉ የአእምሮ ቆሻሻ እና የአእምሮ ጩኸት በስተጀርባ ፍፁም ባዶ የሆነ ስፍራ አለ፡፡ ያለ እግዚአብሄር አንድ ሰው ባዶ ስፍራ ነው፡፡ በቃ ያለ እግዚአብሄር አንድ ሰው ባዶ እና ምንም ነው፡፡ ሰዎች ይህን እርቃን፣ ይህን ባዶነት፣ ይህን አስተያሚኒት መሸሸግ ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ በሚያማምሩ አበቦች ይሸፍኑታል፤ ሸፋኖቹንም ያስጌጡዋቸዋል፡፡ አንድ ሰው ቢያገስ አንድ የሆነ ሰው፣ አንድ የሆነ ነገር መሆኑን ያስመስላል፡፡ ይሄ ደግሞ የገለ ባህሪያችሁ ብቻ አይደለም፡፡ ይህ አለም አቀፋዊ ባህርይ ነው፡፡ ሁሉም ሰው እንደዚህ ነው፡፡

ማንም ሰው ቢሆን ራሱን እንደ መፅሀፍ ሊገልጥ አይችልም፡፡ ፍርሃት ፈጥርቆ ይይዛችኋል፡፡ "ሰዎች ምን ይሉኛል?" ትላላችሁ፡፡ ገና ከልጅነታችሁ ጀምሮ ጭምብሎችን - ቆንጆ ጭምብሎችን ማጥለት እንዳለባችሁ ስትማሩ ቆይታችኋል፡፡ የግድ ቆንጆ ፊት ሊኖራችሁ አያስፈልግም፡፡ በቃ ቆንጆ ጭምብል ካላችሁ በቂ ነው፡፡ ደግሞም ጭምብሉ ርካሽ ነው፡፡ ፊታችሁን መቀየር አድካሚ ስራ ነው፡፡ ፊታችሁን ቀለም መቀባት ግን በጣም ይቀላል፡፡

እሁን ድንገት ተነስታችሁ እውነተኛ ፊታችሁን ብታጋልጡት ጥልቁ የስብዕናችሁ ማዕከል ይርበተበታል፤ በፍርሃት ትርዳላችሁ፡፡ ሰዎች ፊታችሁን ይወዱት ይሆን? እናንተንስ ይቀበሏችሁ ይሆን? ሰዎች ያከብሯችሁ

ያፌትራችሁ ይሆን? ምክንያቱም ሰዎች ሊያፌትሩት የነበረው ጭንብላችሁን ነበር፤ አሁን ፍርሃት ይነሳል፡፡ "ድንገት እርቃኔን ብቀር ሰዎች ያፌትሩኝ ይሆን? ያከብሩኝ ይሆን? ያደንቁኝስ ይሆን? ወይስ ሁሉም ከእኔ ይሸሻሉ? ምናልባት እኮ ፊታቸውን ያዞሩብኝ እና ብቻዬን እቀር ይሆናል" ትላላችሁ፡፡

በመሆኑም ሰዎች በማስመሰላቸው ይበልቁበታል፡፡ ከፍርሃት ውጪ ሰበብ አለ፡፡ ከፍርሃት ውጪ ያ ሁሉ ቅጥፈት አለ፡፡ እውነተኛ ለመሆን አንድ ሰው ደፋር መሆን አለበት፡፡

**ማንም ሰው ቢሆን ራሱን እንደ መፅሀፍ ሊገልጥ አይችልም፡፡ ፍርሃት ፈጥርቆ ይይዛችኋል፡፡ "ሰዎች ምን ይሉኛል?" ትላላችሁ፡፡ ገና ከልጅነታችሁ ጀምሮ ጭንብሎችን - ቆንጆ ጭንብሎችን ማጥለቅ እንዳለባችሁ ስትማሩ ቆይታችኋልና፡፡**

ከህይወት መሰረታዊ ህጎች አንዱ ይህ ነው፤ የደበቃችሁት የትኛውም ነገር ማደጉን ይቀጥላል፡፡ ነገር ግን በይፋ ያጋለጣችሁት የትኛውም ነገር፣ የተሳሳተ ከሆነ ብን ብሎ ይጠፋል - በፀሀይ ይተናል፤ ትክክል ከሆነ ደግሞ ይፋፋል፡፡ አንድን ነገር ስትሸሽጉት ተቃራኒው ነው የሚከሰተው፤ ትክክለኛው ነገር መሞት ይጀምራል - ምክንያቱም እንዲፋፋ አልተደረገም፡፡ ንፋስ፣ ፀሀይ፣ ዝናብ ያስፈልገዋል፤ ሊያገኝ የሚገባው ተፈጥሯዊ ነገር በሙሉ ያስፈልገዋል፡፡ ሊያድግ የሚችለው በእውነት ብቻ ነው፡፡ የሚመገበውም እውነትን ነው፡፡ ምግቡን መስጠታችሁን ካቆማችሁበት እየቀጨጨ፤ እየቀጨጨ መሄድ ይጀምራል፡፡ እናም ሰዎች እውነታቸውን በማቀጨጭ ተጨባጭነት የሌለውን ነገራቸውን በማደለብ ላይ ይገኛሉ፡፡

እውነተኛ ያልሆነው ፊታችሁ ቀላሉ ቅጥፈት ነው፡፡ ስለዚህ የበለጠ ቅጥፈቶችን መፈልሰፍ ይኖርባችኋል፡፡ አንድን ቅጥፈት ለመደገፍ መቶ ጊዜ መዋሸት አለባችሁ፡፡ ምክንያቱም አንድ ቅጥፈት ሊደገፍ የሚችለው የበለጠ ትላልቅ በሆኑ ሌሎች ቅጥፈቶች ነው፡፡ ስለዚህ በ <ላይ ጌጦች> ስትሸሸጉ እውነታው መሞት ይጀምርና እውነት ያልሆነው እየደለበ ይሄዳል፡፡ እራሳችሁን በይፋ ብታጋልጡ ሀሰተኛው ፊታችሁ ይሞታል - እውነት ያልሆነ ነገር በገላጣ ስፍራ መቆየት አይችልምና፡፡ መቆየት የሚችለው በሚስጥር ብቻ ነው፤ በጨለማ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ሀሰተኛው ፊታችሁ ሊቆይ የሚችለው ንቁ ባልሆነው አእምሯችሁ ውስጥ ባሉት ጥሻዎች ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ወደ ንቁው የአእምሯችሁ ክፍል ካመጣችሁት መትነን ይጀምራል፡፡





እንግዲህ በውይይት የሚሰጥ የአእምሮ ህክምና (የሳይኮአናሊስስ) ስልት መላው ሚስጥር ይኸው ነው፡፡ ይህ ቀላል ሚስጥር ነው፡፡ ነገር ግን በውይይት የሚሰጥ ህክምና መላው ሚስጥር ነው፡፡ ሀኪሙ ንቁ ባልሆነው የአእምሯችሁ ክፍል (በውስጣችሁ ባው ጨለማ ግዛት) ውስጥ ያለውን ነገር በሙሉ ወደ ንቁው የአእምሯችሁ ክፍል ለማምጣት እገዛ ያደርጋል፡፡ በዚያ ያለውን ነገር በሙሉ እናንተ ራሳችሁም ሆናችሁ ሌሎች ሰዎች ለማየት ወደሚችሉበት ስፍራ ያመጣዋል፡፡ እናም ተአምር ይፈጠራል፡፡ ገና ሲታዩት መሞት ይጀምራል፡፡ ይህንን ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ሊታዛምዱት ትችላላችሁ፡፡ በውይይት በሚሰጥ የአእምሮ ህክምና የምታደርጉት ይህንን ነው፡፡ ራሳችሁን ለሀኪሙ ገልጣችሁ ታሳዩታላችሁ፡፡ ለአንድ ሰውም እንኳን ቢሆን ራስን እጋልጦ ማሳየት በህይወታችሁ ውስጥ ታላላቅ ለውጦችን ለማምጣት በቂ ነው፡፡ ነገር ግን ለሀኪም ራስን ገልጦ ማሳየት ውስን ነው፡፡ ራሳችሁን ገልጣችሁ ያሳያችሁት ለአንድ ሰው ብቻ ነው፤ ያውም ለብቻችሁ ሆናችሁ እሱም የነገራችሁትን ነገር ይፋ ላያደርግ ቃል ገብቶላችሁ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የእንደ ሀኪም የሥራው አንዱ አካል ነው፡፡ የነገራችሁትን ነገር ለሌላ ሳይናገር በሚስጥር የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ ይሄ ሙያውን ሲጀምር የፈፀመው ቃለ መሃላ አንድ አካል ነው፡፡ ስለዚህ ራሳችሁን በይፋ ያጋለጣችሁና ያሳያችሁትም በጣም ውስን በሆነ ሁኔታ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ደግሞም ራሳችሁን ገልጣችሁ የምታሳዩት ከሙያ አንፃር ነው፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን ብዙ ረድቷችኋል፡፡ በውይይት በሚሰጥ የአእምሮ ህክምና በጥቂት ቀናት ውስጥ ሊፈፀም የሚችል ነገር አመታትን - አራት ወይም አምስት አመታትን ሊፈጅ ይችላል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ታዲያ ህክምናው በፍፁም አይጠናቀቅም፡፡ በህክምናው አጠቃላይ ሂደት ከተከናወኑት ነገሮች መካከል በተጠናቀቀው፣ በተደረገው ወይም ባለቀው ሂደት ውስጥ ከተነሱት ጉዳዮች መካከል ... አለም ገና አንዱንም ነገር አላወቀም፡፡ ገና ነው፡፡ ሀኪሞቻችሁም ቢሆኑ ታዲያ ሙሉ በሙሉ ከእናንተ ጋር ተወያይተው በውስጣችሁ ያለውን ነገር ሁሉ አላወቁም፡፡ ምክንያቱም ራሳችሁን ገልጣችሁ የምታሳዩዋቸው በጣም በተወሰነ መልኩ፣ ከተወሰኑ ሁኔታዎች አንፃር ነው፡፡ ሀኪሙ የማያደምጥ መስሎ ያዳምጣችኋል፡፡ የምትነግሩትን ነገር ለማንም ሰው መናገር አይናገርበትምና ነው፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን ይጠቅማችኋል፤ ሸክማችሁን ለማቃለል በአስገራሚ ሁኔታ ይረዳችኋል፡፡

እራሳችሁን በመደበኛ ሁኔታ እጋልጣችሁ ማሳየት ብትችሉ፣ በሚስጥር ወይም ለባሙያ ሳይሆን ከሁሉም ሰው ጋር በሚኖራችሁ ግንኙነት ራሳችሁን በይፋ ገልጣችሁ ብታሳዩ - <ሳንያስ> ማለት እንግዲህ ይኸው ነው፡፡ ይህ ሂደት በገዛ ራስ በውይይት የሚደረግ የአእምሮ ህክምናን ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል፡፡ ይህ በየቀኑ ለሃያ አራት ሰአታት የሚከናወን የአእምሮ ህክምና ነው፡፡ በማንኛውም አይነት ሁኔታ

ከሚስት፣ ከጓደኛ፣ ከዘመድ፣ ከጠላት፣ የማይታወቅ ሰው፣ ከአለቃ እንዲሁም ከሰራተኛ ጋር በመሆን የሚከናወን የአእምሮ ህክምና ነው፡፡ በቀን ውስጥ ባሉት ሀያ አራት ሰአታት በሙሉ ከሰዎች ጋር እየተገናኛችሁ ነው፡፡

ራሳችሁን ማጋለጡን ከገፋችሁበት (መጀመሪያ ላይ በእርግጥም በጣም ያስፈራችኋል) ነገር ግን ወዲያውኑ ጥንካሬ ማግኘት ትጀምራላችሁ ምክንያቱም እውነታው አንድ ጊዜ ከተጋለጠ ይጠናከርና እውነት ያልሆነው ይሞታል፡፡ እናም እውነቱ ሲጠናከር ከልምዱ ጋር ተጣጥማችሁ ማለስለሱ ትሆናላችሁ፡፡ አንድ ግለሰብ መሆን ትጀምራላችሁ ስብዕናው ጠፍቶ ግላዊ ባህርያችሁ ይታያል፡፡

ስብዕና ማላላቻ ነው፤ ግላዊ ባህርይ ግን ተጨባጭ ነው፡፡ ስብዕና የላይ ሽፋን ሲሆን የግል ባህርይ እውነታችሁ ነው፡፡ ስብዕና ከውጪ በመገደዳችሁ የያዛችሁት ፀባይ፣ ጭንብል ነው፡፡ ግላዊ ባህርይ ግን እውነተኛ ባህርይ ነው፡፡ የግል ሲሰራችሁ የሰጣችሁ ባህርይ ነው፡፡ እግዚአብሄር ስብዕናችሁን ማህበረሰብ ያወሳሰበው፣ ማህበረሰብ የወለወለው ሲሆን ግላዊ ባህርይ ግን አስደናቂ ሀይል ያለው ጥሩ፣ ያልተገራና ጠንካራ ነው፡፡

ይሁንና ፍርሃቱ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ምክንያቱም ገና ከልጅነታችሁ ጀምሮ ትጥፈቶችን ስትማሩ ቆይታችኋል፡፡ ስለዚህ ከውሸቱ ጋር በጣም ተለይታችሁ ታውቆችኋልና ውሸቱን አሽቀንጥሮ መጣል ልክ ራስን በራስ እንደመግደል ነው፡፡ ደግሞም ፍርሃቱ የመጣው ታላቅ የማንነት ቀውስ በመነሳቱ ነው፡፡

ለምሳሌ፡ ለስልሳ አመታት አንድ የሆነ አይነት ሰው ሆናችሁ ቆይታችኋል፡፡ አሁን ግን ስልሳ አመታችሁን ሊታከብሩ ተቃርባችሁ ይሆናል፡፡ ለስልሳ አመታት አንድ የሆነ አይነት ሰው ነበራችሁ፡፡ አሁን በዚህ የህይወታችሁ ደረጃ ላይ ያንን ስብዕናችሁን አሽቀንጥራችሁ ስለራሳችሁ እንደ አዲስ <ሀ - ሁ - ሂ .....> እያላችሁ መማር ያስፈራል፡፡ ሞት በየእለቱ እየቀረበ፣ እየመጣ ይገኛል፡፡ ታዲያ አዲስ ትምህርት የመጀመሪያው ጊዜ አሁን ነው? ትምህርቱን መጨረስ ወይም አለመጨረሳችሁን ማን ያውቃል? ምናልባት የቀድሞውን ማንነታችሁን ካጣችሁ በኋላ አዲስ ማንነት ለማዳበር በቂ ጊዜ፣ በቂ ጉልበት እንዲሁም በቂ ድፍረት አይኖራችሁ ይሆናል፡፡ ታዲያ ማንነት ሳይኖራችሁ ልትሞቱ ነውን? የመጨረሻውን የእድሜ ዘመናችሁንስ ማንነት ሳይኖራችሁ ልትኖሩ ነውን? ይሄ መቼም እብደት ነው፡፡ ያለ አንድ ማንነት መኖር ልብን ያስጥማል፣ ልብን ያኮማትራል፡፡ አንድ ሰው "አሁን ያለኝ ጥቂት ቀናት ስለሆኑ በዚሁ ብቀጥል መልካም ነው፡፡ ከቀድሞው፣ ከማውቀው፣ ከሚያስተማምነው፣ ከምቹው ማንነቴ ጋር ብኖር ይሻለኛል" ብሎ ያስባል፡፡ በዚያ በኩል ዘዴኛ ሆናችኋል፡፡ ደግሞም ታላቅ የመዋዕለ - ንዋይ ፈሰስ





ም ቆይቷል፡፡ የህይወታችሁን ስልሳ አመታት አፍስሳችሁበታል፡፡ በሆነ መልኩ ማንነታችሁን በተመለከተ አንድ ሀሳብ ፈጥራችሁ ያንን በማመን ተተብትባችሁ መኖር ችላችኋል፡፡ አሁን እኔ ግን ያንን ሀሳብ አሽቀንጥራችሁ እንድትጠሉት እነግራችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም እናንተ ያንን አይደላችሁም!

ራሳችሁን ለማወቅ ምንም ማሰብ አያስፈልግም፡፡ ሁሉም ሀሳቦች ወዲያ መጣል አለባቸው፡፡ የዚያን ጊዜ ብቻ ነው ማን እንደሆናችሁ ሊታወቁ የምትችሉት፡፡

ፍርሃት ተፈጥሯዊ ነው፡፡ አትኮንኑት፣ የተሳሳተ ነገር አድርጋችሁም አትውሰዱት፡፡ የመሆን ማህበራዊ አስተዳደግ አካል ነው፡፡ የግድ ልንቀበለው ይገባናል፡፡ ከእሱ ባሻገር መሄድም አለብን፡፡ ሳንኮንነው (ለማጥፋት ሳንሞክር) ከእሱ ባሻገር መሄድ ይኖርብናል፡፡

ቀስ እያላችሁ ራሳችሁን አጋልጡ፡፡ ቀስ በቀስ! ልትቆጣጠሩት ወደማትችሉት ነገር ውስጥ ዘላችሁ አትግቡ፡፡ ቀስ እያላችሁ ደግሞ በደረጃ ሂዱ፡፡ ነገር ግን በቅርቡ የእውነትን ጣዕም ትማሩታላችሁ፡፡ የዚያኔ እነዚያን ስልሳ አመታት ያለጥርጥር ሲታባክኑዋቸው መቆየታችሁን ስታዩ ትደነቃላችሁ፡፡ የድሮው ማንነታችሁ ይጠፋል፣ ሙሉ በሙሉ አዲስ አስተሳሰብ ይኖራችኋል፡፡ በእርግጥም አዲስ ማንነት ሳይሆን አዲስ ራዕይ፣ ነገሮችን የምታዩበት አዲስ መንገድ፣ አዲስ አስተሳሰብ ነው፡፡ በድጋሚ <እኔ> ማለት የምትችሉት ከኋላው አንድ የሆነ ነገር ኖሮት አይደለም፡፡ ቃሉን የምትጠቀሙት ጠቃሚ በመሆኑ ብቻ ይሆናል፡፡ ይሁንና ሁልጊዜም ቢሆን ቃሉ ምንም ትርጉም እንደሌለው፣ ምንም ፍሬ - ነገር እንደሌለው እንዲሁም ዘላቂ ነገር እንዳልያዘ ታውቃላችሁ፡፡ <እኔ> ከሚለው ቃል ጀርባ ያለው ነገር በአንድ የትየለሌ፣ ሰፊ እና መለኮታዊ ውቅያኖስ ውስጥ ይሸሸጋል፡፡

በፍፁም አንድ ሌላ ማንነት አታዳብሩም፡፡ አሮጌው ማንነታችሁም ይሰወራል፡፡ ከዚያ ለመጀመሪያ ጊዜ እራሳችሁን በእግዚአብሄር ውቅያኖስ ውስጥ እንዳለ የባህር ሞገድ አድርጋችሁ ትቆጥራላችሁ፡፡ ያ ደግሞ ማንነት አይደለም፡፡ ምክንያቱም እናንተ በውስጡ አይደላችሁም፤ እናንተ ጠፍታችኋል፡፡ እግዚአብሄር አጥለቅልቋችኋል፡፡

ሀሰተኛውን ነገር አደጋ ላይ ማጋለጥ ከቻላችሁ እውነታው የእናንተ ሊሆን ይችላል፡፡ ደግሞም እንደዚያ መሆን አለበት - አደጋ ላይ የጣላችሁት ሀሰትን ነውና፡፡ እውነቱንም አገኛችሁታል፡፡ ምንም ነገራችሁን ለአደጋ ሳታጋልጡ ሁሉንም ነገር በእጃችሁ አስገብታችኋል፡፡

# የመሰላቸት ስሜት የሚሰማን የተሰጠንን ስርዓት ተከትለን ስለምንኖር ነው

**ራሴን እንደጠላሁት ደርሰበታለሁ፡፡ ደግሞም ደስ የሚል ስሜት አይሰማኝም፡፡ አንተ ምንም ብትሆን የገዛ ራሳችንን እሜን መቀበል እንደሚገባን ትናገራለህ፡፡ እኔ በውስጤ የሆነ ከደስታ ጋር የተያያዘ ነገር ማጣቴን እያወቅሁ ህይወትን መቀበል አልቻልኩም፡፡ ምን ላድርግ?**

ሊያዝናናህ ያልቻለ ከዚያ ይልቅ ውጥረት ውስጥ መግባትህን የበለጠ እንድታሰላስል የሚያደርግህ አዲስ አይነት የህመም ማስታገሻ መኖሩን ሰምቻለሁ፡፡

መድሃኒቱን ሞክረው! አሁንም፣ አሁንም፣ አሁንም ሞክረው፡፡ እንደ አንድ አሜሪካዊ ሁን! ነገር ግን ከሦስት ጊዜ በላይ አትሞክረው፡፡ ሞክረው፣ አሁንም ሞክረው፣ እንደገናም ሞክረው፡፡ ከዚያ አቁም፡፡ ምክንያቱም ጅል መሆን ጠቀሜታ የለውም፡፡

"ራሴን እንደጠላሁት ደርሼበታለሁ ....." ብለሀል፡፡ ይህ ትልቅ ግኝት ነው፡፡ አዎን፣ የምሬን ነው! መሰላቸታቸውን የሚያውቁ በጣም ጥቂት ሰዎች ናቸው፡፡ እናም ተሰላችተዋል - ፍፁም ተሰላችተዋል፡፡ ይህንን ደግሞ ከእነሱ ከራሳቸው በስተቀር ሁሉም ሰው ያውቀዋል፡፡ አንድ ሰው መሰላቸቱን (ራሱን መጥላቱን) ካወቀ ይሄ ትልቅ ጅምር ነው፡፡ አሁን የወሰኑ ጥቂት እንድምታዎችን መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የመሰላቸት ስሜት የሚሰማው ብቸኛው እንስሳ ሰው ነው፡፡ ይህ ትልቅ ፀጋ ነው፣ የሰው ልጅ ክቡርነት አንድ አካልም ነው፡፡ አንድ ጎሽ ወይም አንድ አህያ ሲሰላች አይታችሁ ታውቃላችሁ? በፍፁም አይሰላቹም፡፡ መሰላቸት ማለት የአኗኗር መንገዳችሁን መሳሳት የሚያመለክት ቀይ መብራት ነው፡፡ በመሆኑም ታላቅ ክስተት ይሆናል፡፡ "ተሰላችቻለሁ፣ ስለዚህ የሆነ ነገር ማድረግ አለብኝ፣ አንድ የሆነ ለውጥ ያስፈልገኛል" ማለት በእውነቱ ትልቅ ነገር ነው፡፡ የመሰላቸት ስሜት መኖሩን መጥፎ አድርጋችሁ አትዩት፡፡ ጥሩ ምልክት ነው፣ መልካም የሆነ ለለውጥ በጣም ዕገዛ የሚያደርግ ጅማሮ ነው፡፡ ነገር ግን በዚያ ብቻ አታቁሙ፡፡





እንደ ሰው ለምን የመሰላቸት ስሜት ይሰማዋል? እንደ ሰው የመሰላቸት ስሜት የሚሰማው ከሌሎች ለእሱ የተሰጠውን ስርዓት ተከትሎ ሲኖር ነው፡፡ ይህንን ስርአት እርሱት፡፡ ከዚህ ስርአት ውስጥ ውጡ! በገዛ ራሳችሁ መንገድ መኖር ጀምሩ፡፡

ይህ ደግሞ የገንዘብ፣ የስልጣን እንዲሁም የዝና ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ በተፈጥሮ በውስጣችሁ ከምትፈልጉት ነገር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን አድርጉት፡፡ የመሰላቸቱ ስሜት ደብዛው ይጠፋል፡፡ የሌሎችን ሀሳብ እየተከተላችሁ መሆን አለበት፣ ነገሮችን በ <ትክክለኛው> መንገድ እያደረጋችሁ መሆን አለበት፣ እንግዲህ የመሰላቸት ስሜት የመሰረት ድንጋዮች እነዚህ ናቸው፡፡

መላው የሰው ልጅ ተሰላችቶ ራሱን ጠልቷል፡፡ ምክንያቱም የሀይማኖት ሊቅ መሆን የማይገባው ሰው ሀይማኖተኛ፣ የሂሳብ ሊቅ መሆን የሚገባው ፖለቲከኛ፣ ባለቅኔ መሆን የሚገባው ደግሞ ነጋዴ ሆኗል፡፡ ሁሉም ሰው በማይገባው ቦታ ላይ ነው ያለው፡፡ ማንም ሰው መሆን የሚገባው ቦታ ላይ አይደለም፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው አደጋ ውስጥ መግባት አለበት፡፡ እራሳችሁን አደጋ ውስጥ ለማስገባት ዝግጁ ካደረጋችሁ ከመቅፅበት የመሰላቸት ስሜት ሊጠፋ ይችላል፡፡

"የገዛ ራሴ እንዳስጠላኝ ደርሼበታለሁ ....." ብለኸኛል፡፡ በገዛ ራስህ ተሰላችተሀል፡፡ ምክንያቱም ከራስህ ጋር ልባዊ ጥምረት የለህም፡፡ ለራስህ አልታመንክም፡፡ የገዛ ራስህን ተፈጥሮ አላከበርከውም፡፡

ደግሞም "ህይወትን መቀበል አልቻልኩም" ብለሃል፡፡ እንዴት ህይወትን ትቀበላለህ? ህይወትን መቀበል የምትችለው ማድረግ የፈለግከውን ነገር ምንም ይሁን ምን ስታደርግ ብቻ ነው፡፡

ቪንሰንት ቫን ጎህ፣ ስዕል መሳል ከልቡ በላይ ያስደስተው ነበር፡፡ አንዲን አንኳን ስዕሉን አልሸጠም፣ ማንም ሰው አድንቆትም አያውቅም እናም በረሀብ ተቆራምዶ ነበር፣ ረሃብ እየገደለው ነበር፡፡ ወንድሙ ቢያንስ በህይወት ለመቆየት እንዲችል ብቻ በጣም አነስተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ይሰጠው ነበር፡፡ በሳምንት ለሦስት ቀናት ብቻ እየተመገበ በተቀሩት አራት ቀናት ፆሙን ያድራል፡፡ በእነዚህ አራት ቀናት የግድ ፆሙን ማደር ነበረበት፡፡ አለበለዚያ ስዕል የሚሰራበትን ሸራ፣ ቀለም እና ብሩሽ ከየት ያመጣል? ነገር ግን ከልቡ በላይ ደስተኛ ነበር፡፡ ህይወትን ተቀብሎት ነበር፡፡

**ህይወትን መቀበል የምትችለው ማድረግ የፈለግከውን ነገር ምንም ይሁን ምን ስታደርግ ብቻ ነው፡፡**



INFINIX HOT 8
AI TRIPLE CAMERA

የሞተው ገና የሰላሳ ሦስት አመት ጕልማሳ ሰው እያለ ሲሆን፣ ራሱን ነበር ያጠፋው፡፡ ነገር ግን ራሱን በራሱ ማጥፋቱ ከአንተ አይነቱ ህይወት በጣም ይሻላል፡፡ ምክንያቱም ራሱን ያጠፋው መሳል የፈለገውን ስዕል ከሳለ በኋላ ነበር፡፡ ለረጅም ጊዜ ለመሳል ይመኝ የነበረውን ፀሃይ ስትጠልቅ የሚያሳይ ስዕል ስርቶ በጨረሰበት ቀን አንድ ደብዳቤ ፅፏል፡፡ ደብዳቤው፡- "ስራዬ ተጠናቀቀ፡፡ አሁን ረክቻለሁ፡፡ ይህንን አለም ለቅቄ የምሄደው ከልክ በላይ ተደስቼ ነው" ይላል፡፡ ራሱን በራሱ አጥፍቷል፡፡ እኔ ግን ይህንን ራስን በራስ መግደል አልለውም - ህይወትን ሙሉ በሙሉ ኖሯታልና፣ የህይወትን ኛ ሁለቱንም ጫፎች በድምቀት አብርቷቸዋልና፡፡

ለመቶ አመታት ልትኖሩ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ህይወታችሁ በቀ ደረቅ አጥንት፣ ሽክም፣ የሞተ ሽክም ይሆናል፡፡ "ምንም ብንሆን ምን ራሳችንን እሚን ብለን መቀበል" እንዳለብን ተናግረሃል፡፡ "እኔ በውስጤ የሆነ ከደስታ ጋር የያያዘ ነገር ማጣቴን እያወቅኩ ህይወትን መቀበል አልቻልኩም" ብለሃል፡፡

እኔ <ራሳችሁን እሚን ብላችሁ ተቀበሉ> ስል <የህይወት ስርአታችሁን ተቀበሉት> ማለቴ አይደለም፡፡ እባብታችሁ አትረዱኝ፡፡ እራሳችሁን ተቀበሉት ስል ሌላኛውን ነገር በሙሉ ውድቅ አድርጋችሁ ራሳችሁን ተቀበሉት ማለቴ ነው፡፡ አንተ ግን ይህንን በገዛ ራስህ መንገድ ሳትተረጉመው አልቀረህም፡፡ ነገሮች መሆን ያለባቸው እንደዚያ ነው ....

አንድ ከማርስ የመጣ ፍጡር (ማርሳዊ) መንኮራኩሩን ማንሀተን ውስጥ አሳረፈ፡፡ ወዲያውኑ ብቅ ከማለቱ አንድ ለማኝ ተጠጋው፡፡ "ጋሼ" አለውና "አስር ሳንቲም ስጠኝ?" ብሎ ጠየቀው፡፡

ማርሳዊው "አስር ሳንቲም ምንድነው?" ብሎ ጠየቀው

ለማኙ ለአንድ ደቂቃ አሰበና "ትክክል ነህ፡፡ ሰሙኒ ስጠኝ፣ እሺ" አለው፡፡

**እኔ <ራሳችሁን እሚን ብላችሁ ተቀበሉ> ስል <የህይወት ስርአታችሁን ተቀበሉት> ማለቴ አይደለም፡፡ እባብታችሁ አትረዱኝ፡፡ እራሳችሁን ተቀበሉት ስል ሌላኛውን ነገር በሙሉ ውድቅ አድርጋችሁ ራሳችሁን ተቀበሉት ማለቴ ነው፡፡**





እኔ ያልኩትን አንተ አልተረዳኸውም፡፡ የግድ የተጫኑብህን ነገሮች በሙሉ አሽቀንጥረህ ጣላቸው፡፡ ተቀበላቸው እያልኩህ አይደለም፡፡ በውስጣዊው ማዕከልህ ውስጥ ያለውን ከባሻገር ይዘኸው የመጣኸውን ነገር በሙሉ ተቀበለው፡፡ የዚያን ጊዜ የሆነ ነገር ያጣህ መስሎ አይሰማህም፡፡ ያለምንም ቅድመ - ሁኔታ ራስህን በተቀበልክበት ቅፅበት ድንገት በውስጥህ የሆነ የደስታ ስሜት ይፈነዳል፡፡ ህይወትህ በቅጡ መፍሰስ ትጀምራለች፡፡ ከዚያም በእርግጠኝነት አስደሳች፣ አስፈንዳቂ ትሆናለች፡፡

የአንድ ወጣት ጓደኞች እሱ እንደሞ ያስባሉ፡፡ እሱ ግን ራሱን ስቶ ‹ኮማ› ውስጥ ገብቷል፡፡ የሆነ ጊዜ ላይ ሊቀብሩት ሲዘጋጁ በህይወት የመኖር ምልክት አሳየ፡፡ ከዚያ በኋላ መሞት ምን እንደሚመስል ተጠየቀ፡፡

"ሞት!" አለና ጮኸ፡፡ "እኔ እኮ አልሞትኩም፡፡ ሁልጊዜም መን እየተደረገ እንደሆነ አውቅ ነበር፡፡ ደግሞም እንዳልሞትኩም አውቅ ነበር፡፡ ምክንያቱም እግሮቼ ተዝቅዘው ነበር፡፡ በዚህ ላይ በጣም ርቦኝ ነበር፡፡"

"ታዲ ግን፣ እንደዚያ አይነት ስሜት እንዴት በህይወት እንደለህ ሆና እንዲሰማህ አደረገህ?" ብሎ ጠየቀው፣ ግራ ከተጋቡት ጓደኞቹ መካከል አንዱ፡፡

"እንግዲህ መንግስተ ሰማያት ውስጥ ብሆን ኖሮ እንደማይርበኝ አውቅ ነበሩ፡፡ ሲኦል ወርጄ ብሆን ኖሮም እግሮቼን አይቀዘቅዙኝም ነበር" አለ፡፡

አንድ ሰው አለመሞታችሁን በእርግጠኝነት መናገር ይችላል፡፡ ርቧችኋል፣ እግሮቻችሁም ቀዝቅዘዋል፡፡ በቃ ተነሱና ትንሽ በእግራችሁ ዞር ዞር በሉ፡፡

አንድ ያልተማረ እና በማህበረሰቡ ዘንድ ክብሬት የሌለው ሰው በአንዲት አንድ ያልተማረ እና በማህበረሰቡ ዘንድ ክብሬት የሌለው ሰው በአንዲት የሚሊየነር ልጅ ፍቅር ተያዘ፡፡ እሷም ከወላጆችዋ ጋር እንዲገናኝ በሚማርከው ቤታቸው ውስጥ ጋበዘችው፡፡ ሰውዬው ውድ ዋጋ ባላቸው የቤት እቃዎች፣ በሰራተኞቹ እንዲሁም በሌሎቹ የሀብት ምልክቶች ፍርሃት አደረበት፡፡ ነገር ግን እስከ እራት ሰአት ድረስ ዘና ብሎ ለመታየት ችሎ ነበር፡፡ እራት በቀረበበት ግዙፍ ጠረጴዛ አጠገብ እንደተቀመጠ የጠጣው ወይን ጠጅ ሞቅታ ስለፈጠረበት ፈሱን ሳጥ አደረገ፡፡

የልጅቷ አባት ቀና ብሎ ተመለከተና ከምስኪኑ ሰውዬ እግር ስር የተጋደመው ውሻ ላይ አፈጠጠ፡፡ "ሮቨር!" አለ በስጋት ድምፅ፡፡

ምስኪኑ ሰውዬ ውሻው ተወቶሽ በመሆኑ እፎይታ ተሰማው፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም ተረጋግቶ እንደገና ፈሳ፡፡

የልጅቷ አባት እንደገና ወደ ውሻው ተመለከተና "ሮቨር!" አለ ሎክ ባ ድምፅ፡፡

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ምስኪኑ ሰውዬ ለሦስተኛ ጊዜ ፈሳ፡፡ ይሄኔ የባ ዐጋው ሰው ፊት በንዴት ተሸበሸበ፡፡ "ሮቨር፣ ሰውዬው ሰቶ ሁላችንንም ሳያበላሽህ በፊት ከዚህ ውጣና ሂድ!" አለ፡፡

አሁንም ቢሆን ገና ጊዜ አለ - እስከአሁን ድረስ ከኖራችሁበት እስር ቤት ውስጥ አሁኑኑ ውጡ! ለዚህ ደግሞ ትንሽ ድፍረት ብቻ ነው የሚያስፈልገው፡፡ ቢቃ ትንሽ የቁማርተኛነት አይነት ልብ ብቻ! ደግሞም ምንም የሚተጣ ነገር አለመኖሩን አስታውሱ፡፡ የምታጡት የታሰራችሁበትን ሰንሰለት ብቻ ነው፡፡ የሆነ ነገር ያጣችሁ እየመሰላችሁ የሚሰማችሁን ስሜት ብቻ ነው ልታጡ የምትችሉት፡፡ ሌላ ምን የምታጡት ነገር አለ? ከአስልቺው ሁኔታ ውስጥ አሁኑኑ ውጡና እንደ ሙሴ፣ እንደ ኢየሱስ፣ እንደ ቡድሃ፣ እንደ ማሃቪራ፣ ለዛራቱስትራ፣ ለካቢር ወይም ለናናክ አይደለም፡፡ ኃላፊነታችሁ ለራሳችሁ ብቻ ነው፡፡ እንደ ክሪሽና የገዛ ራሳችሁን ተቀበሉት፡፡ ኃላፊነት ያለባችሁ ለቡድሃ፣

ኃላፊነት የማስማችሁ ሁኑ፡፡ <ሃላፊነት ይሰማችሁ> ስል አባቢታችሁ አባባሉን እንዳትተረጉሙት አደራ እላለሁ፡፡ የማወራው ስለ ግዴታ እና ሀላፊነት አይደለም፣ ቃሉን የምጠቀመው በቀጥታ ትርጉሙ ነው፡፡ ለገሀዱ አለም ምላሽ ስጡ፡፡ ለዚህም ሀላፊነት ይሰማችሁ፡፡

እስካሁን የኖራችሁት ህይወት ሀላፊነት የጐደለው መሆን አለበት፡፡ ሌሎች እንድታሟሏቸው የሚጠብቁባችሁን ሀላፊነቶች ሁሉ ሲታሟሉ ነው የከረማችሁት፡፡ ታዲያ ምን የምታጡት ነገር አለ? አሁን ተሰላችታችሁታል፡፡ ከእስር ቤቱ ለመውጣት ምን ማድረግ ያስፈልጋችኋል? ቤቱ በላችሁ ውጡ፡፡ ደግሞም ወደ ኋላ አትመልከቱ!

"ከመዝለላችሁ በፊት ሁለት ጊዜ አስቡ" ሲባል ሰምታችሁ ይሆናል፡፡ እኔ ግን "መጀመሪያ ዝለሉና ከዚያ የፈለጋችሁትን ያህል አስቡ" እላችኋለሁ፡፡







# በተመስጦ ማሰላሰል ለባዶነት ፍራቻ

ሁሉጊዜ ማታ ላይ ከመተኛታችሁ በፊት አይኖቻችሁን ጨፍናችሁ ለሀያ ደቂቃ ወደ ባዶነታችሁ በልቀታችሁ መግባትን አስታውሱ፡ ተቀበሉት፡፡ ባዶነታችሁን በዚያ እንዲሆን ተውት፡፡ የፍርሃት ስሜት ይሰማችኋል፡ ይህም ስሜት በዚያ ይኑር፡፡ በፍርሃት ራዱ፡፡ ነገር ግን በዚያ እየተወለደ ያለውን ፍርሃት አትግፉት፡፡ በሁለት እና በሦስት ሳምንታት ውስጥ ውበቱን ልታዩት ትችላላችሁ፣ ቡራኬውም ሊደርሳችሁ ይችላል፡፡ ያንን ቡራኬ አንድ ጊዜ ካያችሁት ፍርሃት በገዛ ራሱ ፍቃደኝነት ይሰወራል፡፡ ከፍርሃት ጋር ትግል መግጠም አያስፈልጋችሁም፡፡

በጉልበታችሁ ወለሉ ላይ ተንበርክካችሁ ወይም እንደሚመቻችሁ ሆናችሁ ተቀመጡ፡፡ ጭንቅላታችሁ ወደፊት ማጐንበስ ከጀመረ (ይጀምራልም) ተውት፡፡ ከዚያ በኋላ ልክ እንደ ህፃን ልጅ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሲቆይ እንደሚቀመጠው ያለ አቀማመጥ ይኖራችኋል፡፡ ጭንቅላታችሁ ጉልበታችሁን ወይም ወለሉን መንካትም ይጀምራል፡፡ በቃ እንደዚያ እንዲሆን ተውት፡፡ በገዛ ራሳችሁ ማህፀን ውስጥ ዘልቃችሁ ግቡና በዚያው ሁኑ፡፡ ለዚህ ደግሞ ምንም አይነት ዘዴ ወይም ጥረት አያስፈልግም፡፡ ብቻ እዚያው ሁኑ፡፡ በዚያ ውስጥ ከሚሰማችሁ ስሜት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት መስርቱ፡፡ ከዚያ በፊት ተሰምቶአችሁ የማያውቅ ስሜት ይሰማችኋል፡፡ አእምሯችሁ ነገሮችን መዳት ይችላል፡፡ ምክንያቱም የሚመጣው በጣም ልዩ ከሆነና ካልታወቀ ስፍራ ነው፡፡ ነገር ግን አእምሮ ከዚህ ጋር መሮካከር አይችልም፡፡ ከዚህ በፊት የዚህ አይነት ነገር በጭራሽ አጋጥሞት አያውቅምና፡፡ ስለዚህ በተሳሳተ ሁኔታ ያጋባል፡፡ ሊመድበውና የለየ ምልክት ሊሰጠው ይፈልጋል፡፡

ነገር ግን የሚተቀው አእምሮ ሲሆን የማይታወቀው ደግሞ እግዚአብሄር ነው፡፡ የማይታተቀው በፍንም የሚተቀውን አካል አይሆንም፡፡ አንድ ጊዜ የሚተቀው ነገር አካል ከሆነ ከዚያ በኋላ የማይታወቀው እግዚአብሄር አይደለም፡፡ የማይታወው የማይታወቅ ሆኖ ይቀራል፡፡ ሌላው ቀርቶ እያወቃችሁት እንኳን የማይታወቅ ሆኖ ይቀራል፡፡ ምስጢሩ በፍፁም አይፈታም፡፡ ምስጢሩ በተፈጥሮ ሊፈታ የማይችል ነው፡፡

ስለዚህ ሁልጊዜ ማታ ወደ እዚያ ስፍራ ዘልቃችሁ ግቡ፡፡ በዚያ ውስጥ ፍርሃት ይኖራል፡፡ መርበትበትም ይኖራል፡፡ ያም ቢሆን መልካም ነው፡፡ ቀስ በቀስ ፍርሃቱ እያነሰ ደስታው ይበረክታል፡፡ በሦስት ሳምንታት ውስጥ አንድ ቀን ድንገት የሆነ አይነት ቡራኬ፣ የሆነ አይነት ከፍተኛ የእንቅስቃሴ ሀይል ይነሳል፡፡ ሌሊቱ አልቆ ፀሃይ ከአድማሱ በላይ እንደታየች ሁሉ መላው ተፈጥሯችሁ በደስታ ይሞላል፡፡

**የማይታወቀው በፍፁም የሚተወውን አካል አይሆንም፡፡ አንድ ጊዜ የሚታወው ነገር አካል ከሆነ ከዚያ በኋላ የማይታወው እግዚአብሄር አይደለም፡፡ የማይታወው የማይታወቅ ሆኖ ይቀራል፡፡ ሌላው ቀርቶ እያወቃችሁት እንኳን የማይታወቅ ሆኖ ይቀራል፡፡ ምስጢሩ በፍፁም አይፈታም፡፡ ምስጢሩ በተፈጥሮ ሊፈታ የማይችል ነው፡፡**





# በተመስጦ ማሰላሰል የቀድሞ የፍርሃት ስርዓቶችን ለማሟላት

በልጅነቴ ያዳበርኩትን ስርአት አሁን ድረስ እየደጋገምኩት መሆኔን አውቂያለሁ፡፡ ወላጆቼ ሲያንጓጥጡኝ ወይም እኔ አለቃዊ የሚመስለኝን ነገር ሲናገሩ አኮርፍና በመሸሽ ያለሰዎች ሁሉንም ነገር ለማድረግ እና ለብቻዬ ሆኜ ለመኖር እንደምችል በማሰብ እፅናናለሁ፡፡ አሁን ለጓደኞቼም ተመሳሳይ ባህርይ እያሳየሁ መሆኔን መረዳት እየጀመርኩ ነው፡፡

ይህ እንዲህ አልለወጥ ያለ የድሮ ልማድ ነው፡፡ የዚህን ተቃራኒ ለማድረግ ሞክሩ፡፡ መዘጋትን የወደዳችሁ ሲመስላችሁ ራሳችሁን ክፍት አድርጉ፣ ለመሄድ ስትፈልጉ አትሂዱ፣ ለማውራት ሳትፈልጉ ስትቀሩ አውሩ፣ ክርክሩን ለማቆም ስትፈልጉ አታቁሙ፡፡ ከዚያ ይልቅ በተቻላችሁ መጠን በጋለ ስሜት ዘላችሁ ግቡበት፡፡

ፍርሀትን የሚፈጥር ሁኔታ በተነሳ ቁጥር ሁት አማራጮች አሉ፡፡ ከፍርሃት ጋር ግብግብ ትግጥማላችሁ፣ ወይም ትሸሻላችሁ፡፡ በተለይ በኋላ ቀር አገሮች ውስጥ አንድ ህፃን በተለምዶ ከፍርሃት ጋር ግብግብ ለመግጠም አይችልም፡፡ በአሜሪካ ውስጥ አንድ ህፃን በጣም ግብግብ ስለሚገጥም ወላጆቹ ይሸሻሉ! ነገር ግን በጥንታዊያን ሀገሮች በባህል በታሰሩ ሀገሮች ወይም ደግሞ ይሸሻሉ! ነገር ግን በጥንታዊያን ሀገሮች በባህል በታሰሩ ሀገሮች ወይም ደግሞ ባህላዊ እሴቶች አሁንም ድረስ ጠንካራ በሆኑባቸው ቤተሰቦች ውስጥ አንድ ህፃን ግብግብ ሊገጥም አይችልም፡፡ ብቸኛው አማራጭ መሸሽ ነው፡፡ ህፃኑ ራሱን ለመከላከል ሲል የገዛ ራሱን በገዛ ራሱ ይጠቀልላል፡፡ እንግዲህ እንዴት እንደሚሸሽ ጥበቡን ተምራችኋል፡፡

አሁን ብቸኛው አማራጭ ለመሸሽ እየሞከራችሁ መስሎ ሲሰማችሁ እዚያው ቀጥ ብላችሁ ቁሙ፤ ግትር ሁኑ እና በጥሩ ሁኔታ ተፋለሙ፡፡

ለሌላአንድ ወር ያህል ብቻ ተቃራኒውን ለማድረግ ሞክሩ እና ከዚያ የሚመጣውን እናያለን:: አንድ ጊዜ ተቃራኒውን ነገር ማድረግ ከቻላችሁ እንዴት ሁለቱንም በጣል እንዳለባችሁ ይገባችኋል:: ሁለቱም መጣል ይገባችኋል:: የዚያን ጊዜ ብቻ ነውና አንድ ሰው ደፋር የሚሆነው ምክንያቱም ሁለቱም የተሳሳቱ ናቸው:: አንደኛው የተሳሳተ መንገድ በውስጣችሁ ዘልቆ ስለገባበሌላኛው አማካኝነት ሚዛን መጠበቅ አለበት:: እንግዲህ ለአንድ ወር ያህል ለማንኛውም ነገር እውነተኛ ወረኛ ትሆናላችሁ:: በጣም ጥሩ ስሜትም ይሰማችኋል ምክንያቱም አንድ ሰው በሸሸ ቁጥር መጥፎ የሆነ የበታችነት ስሜት ይሰማዋል:: አንድ ሰው ራሱን ዝግ በማድረጉ የፍርሃት አካሄድ ነው:: ጀግኖች ሁኑ:: ከዚያ ሁለቱንም እንጥላቸዋለን ጀግና መሆንም በራሱ ወደ ውስጥ ሲዘልቅ ፍርሃት ነውና:: ጀግንነት እና ፍርሃት ሲሰወሩ አንድ ሰው ደፋር ይሆናል:: ይህንን ሞክሩ.








# በተመስጦ ማሰላሰል ለማመን

ለማመን ከተቸገራችሁ ወደ ኋላ መመለስ አለባችሁ:: ወደ ውስጥ ዘልቃችሁ ትውስታዎቻችሁን መቆፈር አለባችሁ፣ ወደ ኋላ ታሪካችሁ መመለስ አለባችሁ:: ከእምሯችሁን ካለፉት ጊዜያት አሻራዎች ማፅዳት አለባችሁ:: ካለፈው ጊዜ ጋር በተያያዘ የከመራችሁትን ቆሻሻ ስለሚሆር ሸክማችሁን አቃሉት::

ይህንን የማድረጊያው ቁልፍ ይኸውላችሁ፣ በትዝታ መልክ ሳይሆን እፎይታ ለማግኘት ብላችሁ ወደ ኋላ መመለስ ቻሉ:: ይህንን ለማድረግ በተመስጦ አሰላስሉ:: በልጅነታችሁ የተከናወኑትን ነገሮች በሙሉ ለማወቅ ሞክሩ:: የበለጠ ጥልቅ የሆነ ሰማት ይሰማችኋል:: መጀመሪያ በአራት ወይም በአምስት አመታችሁ የሆነ ቦታ ላይ የተከናወነውን ነገር ታስታውሳላችሁ:: እናም ከዚያ ባሻገር መሄድ አትችሉም:: ድንገት የቻይና ግንብ ፊታችሁ ይጋረጣል:: ቢሆንም ሂዱ:: ቀስ በቀስ የበለጠ ጠልቃችሁ እየሄዳችሁ መሆን ይሰማችኋል:: ወደሶስትና ሁለት አመታችሁ ትሄዳላችሁ:: ሰዎች ከእናታቸው ማህፀን በነበሩ ጊዜ የነበሩትን ሁኔታዎች የሚያስታውሱበት ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች አሉ:: ከዚያ ባሻገር ሄደው በሌላኛው ህይወታቸው የሞቱበት ጊዜ ላይ የደረሱም አሉ:: ነገር ግን ወደ ተወለዳችሁበት ጊዜ መድረስ ከቻላችሁ እና ያንን ቅፅበት መልሳችሁ ከኖራችሁበት ጥልቅ የሆነ ስቃይ እና ህመም ይሆንባችኋል:: በድጋሚ የተወለዳችሁ ያህል ይመስላችኋል:: ምናልባትም አንድ ህፃን ሲወለድ እንደሚያደርገው ሁሉ ጮሃችሁ ታለቅሱም ይሆናል፣ ህፃን ለመጀመሪያ ጊዜ ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ እንደሚታፈነው ሁሉ ትታፈኑም ይሆናል:: ህፃን የታፈነ የሚመስለው ለጥቂት ሰከንዶች መተንፈስ ባለመቻሉ ነው:: ታዲያ እናንተም በኃይል ትታፈናላችሁ:: ህፃን ስለሚታፈን ጮክ ብሎ ያለቅስና ትንፋሹን ይመጣል:: የአየር መተላለፊያ

ቧንቧዎቹም ይከፈታሉ፡፡ ሳንባውም ስራውን ማከናወን ይጀምራል፡፡ እናንተም እንደዚያ መሆን ይኖርባችሁ ይሆናል፡፡ ከዚያ ተመልሳችሁ ትመጣላችሁ፡፡ ሁልጊዜ ማታ፡ ማታ እንደገና ሂዱ ተመልሳችሁም ኑ፡፡ ይህ ምናልባት ቢያንስ ከሶስት እስከ ዘጠኝ ወር ይፈጃል፡፡ እናም በየቀኑ የበለጠ ጭንቀታችሁን እያራገፋችሁ እየቀለላችሁ ይሄዳል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ ከዚህ ጉን ለጉን ማመን ይመጣል፡፡ ያለፈው ጊዜ አንድ ጊዜ ከፀዳ እና የተከሰተውን ነገር ሁሉ ካያችሁት ከዚያ ነፃ ትሆናላችሁ፡፡ ቁልፉ እንግዲህ ይህ ነው፡ በትውስታችሁ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ነገር ካወቃችሁት ከዚያ ነፃ ትሆናላችሁ፡ ማወቅ ነፃ ያወጣል፡፡ ራስን መሳት ባርነት ይፈጥራል፡፡ ከዚያም ማመን ይቻላል፡፡

# በተመስጦ ማሰላሰል ፍርሃትን ወደ ፍቅር ለመቀየር

ወንበራችሁ ላይ ወይም የተመቻችሁ ነገር ላይ እንደተመቻችሁ ሆናችሁ መቀመጥ ትችላላችሁ፡፡ ከዚያ በኋላ እጆቻችሁን አንድ ላይ አጣምራችሁ ታፋችሁ ላይ አድርጉ፡፡ የቀኝ እጃችሁ ከግራ እጃችሁ በታች ይሁን፡፡ ይህ አቀማመጥ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀኝ እጅ ከግራ አእምሮ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሁልጊዜም ፍርሃት የሚመጣው ከግራ አንጎል በኩል ነው፡፡ ግራ እጅ ደግሞ ከቀኝ አንጎል ጋር ይያያዛል፡፡ ድፍረት የሚመጣው ከቀኝ ጉን ነው፡፡

ግራ አንጎል የምክንያት መቀመጫ ነው፡፡ ምክንያት ደግሞ ፍርሃት ነው፡፡ ለዚህም ነው አንድን ሰው ጀግናም ምሁርም ሆኖ የማታገኙት፡፡ አንድን ሰው ጀግና ሆኖ ባገኛችሁት ቁጥር ምሁር ሆኖ አታገኙትም፡፡ ምክንያት የሌለው ይሆናል፡፡ የቀኝ አንጎል የማስተዋል ችሎታ አለው፡፡ . . .





ይህ ተምሳሌታዊ ነው፡ ተምሳሌታዊ ብቻም አይደለም፡፡ ሀይልን የሆነ አቀማመጥ ያስይዘዋል፡፡ የሆነ አይነት ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

ስለዚህ ቀኝ እጅ ከግራ እጅ በታች ይሆንና ሁለቱ አውራ ጣቶች እርስ በርስ ይገናኛሉ፡፡ ከዚያ ዘና ብላችሁ አይኖቻችሁን ጨፍኑና የታችኛውን መንጋጋችሁን ዘና አድርጉት፡፡ ከዚያ ዘና ብላችሁ አይኖቻችሁን ጨፍኑና የታችኛውን መንጋጋትሁን ዘና አድርጉት፡፡ በአፋችሁ መተንፈስ እንድትጀምሩ ሳታስገድዱት መንጋጋችሁን በትንሹ ዘና አድርጉት፡፡ በአፍንጫችሁ አትተንፍሱ፡ በአፋችሁ መተንፈስ ጀምሩ፡፡ ይሄ ዘና ያደርጋችኋል፡፡ በአፍንጫችሁ ካልተነፈሳችሁ የአእምሯችሁ የቀደሞ ስርአት ከዚህ በኋላ ተግባራዊ አይሆንም፡፡ ይህ አዲስ ነገር ይሆናል፡፡ ደግሞም በአዲስ የአተነፋፈስ ስርአት በቀላሉ አዲስ ልማድ ሊፈጠር ይችላል፡፡

ግራ አንጎል የምክንያት መቀመጫ ነው፡፡ ምክንያቱም ደግሞ ፍርሃት ነው፡፡ ለዚህም ነው አንድን ሰው ጀግናም-ምሁርም ሆኖ የማታገኙት፡፡ አንድ ሰው ደግና ሆኖ ባገኛችሁት ቁጥር ምሁር ሆኖ አታገኙትም፡፡

ሁለተኛ በአፍንጫችሁ ካልተነፈሳችሁ አንጎላችሁን አያንቃቃውም፡፡ በቀጥታ ወደ ደረታችሁ ትንፋሻችሁ ወደ አንጎላችሁ አይሄድም፡፡ ደረታችሁ ይሄዳል፡፡ አለበለዚያ የማያቋርጥ መንቃቃት እና መታሸት ይኖራል፡፡ ለዚህም ነው በአፍንጫችን ቀዳዶች ውስጥ አተነፋፈስ አሁንም፡ አሁንም የሚቀያየረው፡፡ በአንድ የአፍንጫ ቀዳዳ መተንፈስ የአንጎልን አንዱን ጉን ያሸዋል፡፡ በሌላኛው ቀዳዳ መተንፈስ እንደዚሁ ሌላውን የአንጎል ጉን ያሸዋል፡፡

ጉራ ያሸዋለ፡፡ በእያንዳንዱ አርባ ደቂቃ ውስጥ አተነፋፈስ ይቀያየራል፡፡

ስለዚህ በአፋችሁ እየተነፈሳችሁ በዚህ መልኩ ተተመጡ፡፡ አፍንጫ ሁለት ቀዳዳ አለው፡፡ አፍ ግን አንድ ቀዳዳ ብቻ ነው ያለው፡፡ በአፋችሁ ስትተነፍሱ ምንም ለውጥ የለም፡፡ለአንድ ሰአት የህል እንኳን ብትቀመጡ በተመሳሳይ መንገድ ነው የምትተነፍሱት፡፡ በአፍንጫችሁ ስትተነፍሱ በአንድ አይነት ሁኔታ ውስጥ ብቻ አትሆኑም፡፡ ሁኔታው ወዲያውኑ ይቀያየራል፡ ለውጡንም ታውቁታላችሁ

ስለዚህ ይህ በጣም ፀጥተኛ፡ ሁለትዮሻዊ ያልሆነ፡ አዲስ አይነት የመዝናናት ሁኔታ ይፈጥርና ሀይላችሁ በአዲስ መልክ መፍሰስ ይጀምራል፡፡ ለአርባ ደቂቃ ያህል ይህንን ማድረግ ከቻላችሁ ትልቅ እገዛ ይኖረዋል፡፡ እናም መጀመሪያ ለአርባ ደቂቃ ያህል እየተቀመጣችሁ ዳምሩት፡፡ ከዚህየ ቀስ በቀስ ወደ ስልሳ ደቂቃ ትሄዳላችሁ፡፡ በየቀኑ ይህንን አድርጉ፡፡

ታዲያ በመሀሉ ማንኛውንም አጋጣሚ እያምልጣችሁ፡፡ የፈለገው አጋጣሚ ቢመጣ ዘሊቃችሁ ግቡበት፡፡ ሁልጊዜም ሀይወትን ምረጡ፡ ሁልጊዜም ማድረግን ምረጡ፡፡ በፍፁም አታፈግፍጉ፡ በጭሽ አትሽሹ፡፡ የፈጠራ ችሎታችሁን እንድትጠቀሙ የሚያደርጋችሁ ማንኛውም አጋጣሚ ካገኛችሁ አጋጣሚውን ተጠቀሙበት፡፡


HOT 8 LITE
AI TRIPLE CAMERA



# የመጨረሻው ጥያቄ - ፈሪሀ-እግዚአብሔር

የሚያስብልን የግላችን እግዚአብሔር እንዳለን ማሰብ በንድፈ ሀሳብ ደረጃም እንኳን ቢሆን በማንኛውም መልኩ ጠቀሜታ የለውም? ይህን የጠየኩበት ምክንያት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ውድቅ ማድረግን ገና ሳስበው ክልክ በላይ ስለምፈራ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ሀሳብ ውድቅ በማድረግህ ለምን የፍርሃት ስሜት ይሰማሀል? በእርግጥም እግዚአብሄርን ማሰብ በሆነ መልኩ ከመፍራት እያዳነህ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ሀሳብ ውድቅ እንዳደረግከው ወዲያውኑ መፍራት ትጀምራለህ፡፡ ይሄ ስነ-ልቦናዊ መከላከያ ነው በቃ ይኸው ነው፡፡

ህፃን ልጅ የግድ ይፈራል፡፡ እናቱ ማህፀን ውስጥ አይፈራም ነበር፡፡ ማንኛውም ህፃን ልጅ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሳለ ወደ ቤተመቅደስ ወይም ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ወይመ መፅሀፍ ቅዱስ፡ ቅዱስ ቁርዓን፡ ጊታ. . . ለማንበብ ስለመፈለጉ፡ አለያም እግዚአብሄር አለ ወይም የለም ብሎ ስለመጨነቁ የሰማሁት ነገር የለም፡፡ አንድ ህፃን በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሳለ በምንም አይነት ስለ እግዚአብሄር ስለ ሰይጣን፡ ስለ መንግስተ ሰማያት ወይም ስለ ሱኦል

ይጨኒቃል ብዬ አላስብም፡፡ ለምን እንደዚያ ያስባል? ገና ድሮ በገነት እየኖረ ነው፡፡ ነገሮች ከዚያ በተሻለ የተሻሉ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

በሞቃትና ደስ በሚል ቤት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ደህንነቱ ተጠብቆ ለሰውነቱ እድገት ጠቀሜታ በሆኑ ኬሚካሎች ውስጥ እየተንሳፈፈ ነው፡፡ ደግሞም የሚገርማችሁ ነገር በአንፃራዊነት ሲታይ ህፃኑ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ በህይወት ዘመኑ ማደግ ከሚችለው በበለጠ ያድጋል፡፡ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ በህይወት ዘመኑ ማደግ ከሚችለው በበለጠ ያድጋል፡፡ በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጥ በጣም ረጅም ጉዞ ነው የሚጓዘው፡፡ ‹ምንም› ከመሆን ተነስቶ አንድ ፍጡር ይሆናል፡፡ በዘጠኝ ወራት ውስጥ የሚቆጠሩ አመታት በሚፈጅ አዝጋሚ ለውጥ ውስጥ ያልፋል፡፡ ከፍጥረታት መጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያሉትን የእድገት ደረጃዎች ያልፋል፡፡ ከፍጥረታት መጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያሉትን የእድገት ደረጃዎች ያልፋቸዋል፡፡ በነዚህ ሁሉ የእድገት ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል፡፡

ህይወቱም ፍፁም አስተማማኝ ናት፡፡ ስራ መቆጠር አያስፈልገውም፣ አታረዛለሁ፣ እራባለሁ ብሎ አይፈራም፡፡ ሁሉም ነገር የሚደረገው በእናቱ አካል ውስጥ ነው፡፡ ለዘጠኝ ወራት በእናቱ ማህፀን ውስጥ ሙሉ በሙሉ ደህንነት ተጠብቆ መኖር ሀይማኖት የምትሉትን ነገር ያመጣውን ችግር ይፈጥራል፡፡

ልጅ ከእናቱ ማህፀን ውስጥ ሲወጣ የሚፈጠርበት የመጀመሪያው ስሜት ፍርሃት ነው፡፡ ቤቱን እና ደህንነቱን አጥቷል፣ ሙቀቱን፣ አካባቢውን፣ የሚያውቀውን ዓለም ሙሉ በሙሉ አጥቷል፡፡ እናም ወደ አዲስ እንግዳ ዓለም፣ ምንንም ወደማያውቀው ዓለም ተወርውሯል፡፡

ህፃኑ የእናቱ መተንፈስ ሊረዳው እንደማይችል እና አሁን በራሱ መተንፈስ እንዳለበት እስከሚገባው ድረስ ጥቂት ሴኮንዶችን





ይፈጅበታል፡፡ ሀኪሙ ህፃኑን እንዲነቃ ለማድረግ ዘቅዝቆ ይይዘውና ቂጡን በሀይል ይመታዋል፡፡ ምን አይነት አጀማመር ነው ምን አይነት አቀባበል ነው፡፡

እናም በዚያ ምት የተነሳ መተንፈስ ይጀምራል፡፡ በምትፈሩ ጊዜ አተነፋፈሳችሁ እንደሚቀየር አስተውላችሁ ማየት ትችላላችሁ፡፡ በፈራችሁ ቁጥር ወዲያውኑ አተነፋፈሳችሁ ይቀየራል፡፡ ቀለል ሲላችሁ፣ የምቾት ስሜት ሲሰማችሁ እንዲሁም ምንም የሚያስፈራችሁ ነገር ሳይኖር ሲቀር አተነፋፈሳችሁ ኩታ ገጠም ሆኖ በጥልቀት ተጣጥሞ የበለጠ ፀጥተኛ ሲሆን ይታወቃችኋል፡፡ ጥልቅ በሆነ በተመስጦ የማሰላሰል ሂደት ወቅት አንዳንድ ጊዜ መተንፈስ ያቆማችሁ መስሎ ይሰማችኋል፡፡ መተንፈስ አላቆማችሁም፣ ነገር ግን እንዳቆማችሁ ያህል መስሎ ይሰማችኋል፡፡

ለአንድ ህፃን መጀመሪያው ሁሉንም ነገር መፍራት ነው፡፡ለዘጠኝ ወራት ጨለማ ውስጥ ነበር፡፡ በሚወለድበት ዘመናዊ ሆስፒታል ውስጥ ግን በዙሪያው ደማቅ ብርሃን ያላቸው መብራቶች አሉ፡፡ ብርሃን የሚባል ነገር አይተው ለማያውቁት አይኖቹ፣ የሻማ ብርሃን እንኳን አርፎበት ለማያውቀው ‹ሬቲናው› ይሄ በጣም ብዙ ነው፡፡ ይህ ብርሃን አይኖቹን ክፉኛ ያስደነግጣቸዋል፡፡

ሀኪም ደግሞ የጥቂት ሴኮንዶች ያህል እንኳን እድል አይሰጠውም፡፡ ለደህንነቱ የመጨረሻ ተስፋው የነበረውን ከእናቱ ጋር የሚያገናኘው ያንን ቀጭን እትብት ቶሎ ይቆርጥበታል፡፡ ታዲያ ይህንን ስታስቡት ከመላው ፍጥረታት በሙሉ እንደ ትንሽ ህፃን ልጅ ያለ አሳዛኝ ፍጡር አለመኖሩን ያለጥርጥር ትገነዘባላችሁ፡፡፡

ለዚህም ነው እንግዲህ ፈረሶች የእግዚአብሔር ፅንሰ ሀሳብ የሌላቸው፡፡ ዝሆኖች ስለ እግዚአብሔር አስበው አያውቁም፡፡ ደግሞም

ማሰቡ አያስፈልጋቸውም:: ገና የተወለደ ህፃን ዝሆን ወዲያውኑ መራመድ፣ ዙሪያውን መመልከት እንዲሁም ዓለምን መቃኘት ይጀምራል፤ እንደ ትንሽ ህፃን ልጅ ያህል ረዳት አልባ ምስኪን አይደለም:: በእርግጥ በሰው ልጅ እረዳት አልባ መሆን ላይ የተመሰረቱ ብዙ ነገሮች እንዳሉ ስትረዱ ይገርማችኋል:: ቤተሰባችሁ፣ ማህበረሰባችሁ፣ ባህላችሁ፣ ሀይማኖታችሁ፣ ፍልስፍናችሁ . . . ሁሉም ነገር ማለት ይቻላል በትንሽ ህፃን ረዳት አልባነት ላይ የተመሰረተ ነው::

በእንስሳት ዘንድ የቤተሰብ መኖር አስፈላጊነት ከህፃኑ ወላጆች የግድ መገኘት ያለባቸውን ነገሮች እንዲያገኙ ብቻ ነው:: የሰው ልጅ ቤተሰብ ግን ከተወሰኑ ስርአቶች ላይ የግድ መወሰን አለበት:: እናት እና አባት ልጃቸውን ለመንከባከብ አብረው መሆን አለባቸው:: ልጅ የፍቅር ግዴታቸው ውጤት ነው:: የፈጠሩትም እነሱ ናቸው:: አሁን እንግዲህ ልክ እንደብዙዎች እንስሳት ለብቻው ቢተው በህይወት ይኖራል ብላችሁ አታስቡ አይቻልም ምግቡን የት ሊያገኝ ነው? ማንን ምግብ ስጡኝ ብሎ ይጠይቃል? ምንስ ብሎ ነው የሚጠይቀው?

ታዲያ ምናልባት ቀደም ብሎ መጥቶ ይሆን? ደግሞ የሰው ልጅ የሚወልደው ያለ ጊዜው እንደሆነና ዘጠኝ ወር በቂ እንዳልሆነ የሚያስቡ ጥቂት የስነ ህይወት ሳይንስ ባለሙያዎች አሉ:: ምክንያቱም ህፃኑ በጣም ምስኪንና ረዳት አልባ ነው:: ነገር ግን የሰው ልጅ አካል የተሰራው እናትየው በዘጠኝ ወራት በላይ ህፃኑን መሸከም እንዳትችል ሆኖ ነው:: አለበለዚያ እናቱ ትሞታለች:: እሷ ሞተች ማለት ልጁም አብሮ ይሞታል ማለት ነው:: ህፃኑ ልጅ በእናቱ ማህፀን ውስጥ ቢያንስ ሶስት አመታት ሊኖር ቢችል ኖሮ ምናልባት አባቱ፣ እናቱ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰቡ፣ ባህል፣ እግዚብሔር እንዲሁም ቄስ እንደሚያስፈልጉት





ታለሏል:: ነገር ግን ህፃን ልጅ በእናቱ ማህፀን ለሶስት አመታት ሊኖር አይችልም:: ይህ ያልተለመደ የስነ ህይወት ክስተት መላውን የሰው ልጅ ባህሪ፣ አስተሳሰብ እንዲሁም የቤተሰብና የማህበረሰብን መዋቅር ጭምር ፈጥሮበታል፤ ይህ ሁኔታ ፍርሀትንም ፈጥሮበታል::

የህፃን ልጅ የመጀመሪያ ተሞክሮ ፍርሃቱ ነው:: መውለድም ቢሆን የሞት አይነት ነው:: ይሄንን ማስታወስ ይገባችኋል:: እስኪ ከህፃኑ እግር እንፃር ተመልከቱት :: አንድ የሆነ አይነት አለም ውስጥ እየኖረ ነበር:: ይሄ ደግሞ ሙሉ በሙሉ አመርቂ አለመ ነበር:: ምንም የሚፈለገው ነገር አልነበረውም ለምንም ነገር አይሳሳም (አይስገበገብም) ነበር:: መኖሩ፣ መፈጠሩ ያስደስተዋል:: እናም ድንገት ተወርውሮ ወደ ውጭ ተጣለ:: ለህፃኑ ይህ አጋጣሚ የሞት ተሞክሮ ነው:: መላው አለሙ ደህንነቱ፣ የሚሞቀው ቤቱ ሞተውበታል:: ሳይንቲስቶች አሁንም ድረስ የእንድ እናት ማህፀን ምቹና ሞቃት የሆነ ቤት ገና መፍጠር አለመቻሉን ይናገራሉ:: ነገር ግን እየሞከርን ነው:: ቤቶቻች ሁሉ እኮ ሞቃተና ምቹ መኖሪያ ለመፍጠር የምናደርገውን ጥረት ያሳያሉ:: ሌላው ቀርቶ የዚያን አይነት ስሌት ለመፍጠር ብለን የውኃ አልጋ ለመስራት ሞክረናል:: ሙቅ ውኃ የተሞላባቸውን ገንዳዎችም አሉን:: በዚያ ውስጥ ጋደም ስትሉ የህፃኑን አይነት ስሜት ይሰማችኋል:: በሙቅ ውኃ መዘፍዘፍን ጠንትተው የሚያውቁ ሰዎች ውሀው ውስጥ ጨው ሳይቀር ይጨምራሉ ምክንያቱም በእናት ማህፀን ውስጥ ያለው ፈሳሽ(?)ቋማ ነው:: የጨው መጠን ባህር ውስጥ ካለው ጨው ጋር ትክክል አንድ አይነት ነው:: ነገር ግን ለምን ያህል ጊዜ በሙቅ ውኃ ገንዳ ውስጥ መዘፍዘፍ ትችላላችሁ? ለብቻችን ገለል ብለን የምንቆይባቸው በርሜሎችም አሉን:: እነዚህም ቢሆኑ ያጣችሁትን ያንን ማህፀን መፈለጋችሁን እንጂ ሌላ የሚያሳዩት ነገር የለም::

## የህፃን ልጅ የተሞከረ ፍርሃት ነው፡፡ የመጨረሻው የሰው ልጅ ተሞክሮ ያው ፍርሃት ነው፡፡

ሲግመንድ ፍሩድ ሁሉን ነገር የተገለፀለት ጠቢብ አይደለም፡፡ በርግጥ ትንሽ ወፍ ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ትንሽ ወፎችም ቢሆኑ ውብ መዝሙር ይዘምራሉ፡፡ አንድ ጊዜ ወሳኝ እና ጠቃሚ ሃሳቦች ይኖሩዋቸዋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ወንድ ከሴት ጋር ፍቅር የሚሰራው እንደገና ወደማህፀን ለመግባት ስለሚጥር እንጂ ለሌላ አይደለም ብሎ ያስባል፡፡ ምናልባት ሀሳቡ አንድ ነገር ይኖረው ይሆናል፡፡ ይህ ሰውዬ ወፈፌ ነው፤ ሀሳቡ በጣም ከእውነት የራቀም ይመስላል፡፡ ሆኖም እንደ ሲግመንድ ፍርድ ያለው ሰው ወፈፌ ቢሆንም በጥንቃቄ መደመጥ አለበት፡፡

እኔ በበኩሌ በዚህ ላይ የሆነ እውነት ያለው ይመስለኛል፡፡ ሰው ማህፀንን ፈልጐ ያው የወጣበትን ያንኑ ፈልጐ ለማግኘት መሻቱ እውነት ይመስለኛል፡፡ ወደዚያ ማህፀን አይደርስም፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ ስለዚህ ብዙ አይነት ነገሮችን ፈጥሯል፡፡ ዋሻዎችን፣ ቤቶች፣ አውሮፕላኖችን መስራት ይጀምራል፡፡ የአውሮፕላንን ውስጠኛውን ክፍል አይታችኋል? አንድ ቀን በአውሮፕላን ውስጥ ሰዎች ጨው በተጨመረባቸው የሙቅ ውኃ ገንዳዎች ውስጥ ቢንሳፈፉ ተአምር አይሆንም፡፡ አውሮፕላኑን በትክክል በተመሳሳይ ሁኔታ ሊሰጣችሁ ይችላል፡፡ ነገር ግን እመርቂ አይሆንም፡፡

ህፃኑ ሌላ ነገር አያውቅም፡፡ እኛ ምቹና ሞቃት ልናደርገው እንሞክራለን፡፡ አንዲት ቁልፍ ስንጫን የአየር ላይ አስተናጋጅዋ በዚያ አለች በተቻለ መጠን ምቹ አድርገነዋል፡፡ የእናት ማህፀንን ያህል ምቹ ልናደርገው አንችልም እንጂ፡፡ በዚያ ቁልፍ መጠን መጫን



እያስፈልጋችሁም ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ ሳይርባችሁ በፊት ትመግባላችሁ፤ አየር ከመፈለጋችሁ በፊት ይቀርብላችኋል፡፡ ምንም አይነት ኃላፊነት የለባችሁም ነበር፡፡ ስለዚህ እናቱ ማህፀን እየወጣ ያለ ህፃን የሚሰማው ስሜት ካለ ይህ ስሜት ሞት መሆን አለበት፡፡ የመወለድ ስሜት ሊሰማው አይችልም፡፡ ይህ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ የኛ ሃሳብ ነው፤ ይህ ከውጪ ቆመን ያለነው የእኛ ሃሳብ ነው፡፡ እኛ ይህንን መውለድ እንለዋለን፡፡

እናም ለሁለተኛ ጊዜ እንደገና አንድ ቀን መላው የሕይወት ዘመኑን ሲለፉ ከቆየ በኋላ . . አንድ ነገር ማድረግ ችሏል፡፡ አንዲት ትንሽ ቤት፣ ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ ትንሽ ምቾት እንዲሁም በአለም ላይ ሊዝናኑበት እና እራሱን ሊሆን የሚችልበት ትንሽ ጥግ ይኖረዋል፡፡ በዚያም ተቀባይነት ያኛል፡፡ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ ህይወትን ሙሉ መታገል ይጠይቃል፡፡ እናም ድንገት አንድ ቀን ወለ ውጭ ይወጣል፡፡

እንደገና ሀኪምም ይመጣል፡፡ ይህ እንግዲህ የተወለደ ጊዜ በሀይል የመታው ሀኪም ነው፤ ነገር ግን ያን ጊዜ መንፈስ እንዲጀምር ነበር፡፡ አሁን ግን እስከምናውቀው ድረስ. . . አሁን በዚያኛው ወገን ነን፤ ሌላኛውን ወገን አናውቀውም፡፡ ሌላው ወገን ለሀሳባችን ተትቷል፡፡ ለዚያም ነው ሲኦልና ገነትን የምናስበው፡፡ ደግሞም ሁሉሉም ሀሳብ መላትው ጠፍቷል፡፡

እኛ በዚህኛው ወገን ነን፡፡ ይህ ሰው ደግሞ እየሞተ ነው፤ ለእኛ እየሞተ ይመስላል፡፡ ምናልባት እንደገና ዳግም እየተወለደም ይሆናል፡፡ ያንን የሚያውቀው ግን እሱ ብቻ ነው፡፡ እናም ፊቱን ወደ እኛ መልስ አድርጐ፤ «አትጨነቁ፡፡ አልሞትኩም፡፡ በህይወት አለሁ» ብሎ ሊነግረን አይችልም፡፡ ለመጨረሻ ጊዜ ሊያየንና ሁሉንም ሰው ሊሰናበት

ተመልሶ ወደ እናቱ ማህፀን ውስጥ ለመግባት አልቻለም ነበር፡፡ አሁንም ወደ ኋላ ተመልሶ አይኖቹን በመግለጥ ሊሰናበተን ፡፡ እትጨነቁ፡፡ እየሞትኩ አይደለም፡፡ ዳግም እየተወለድኩ ነው፡፡ ሊለን አይችልም፡፡

የሂንዱዎች የዳግም ልደት ሀሳብ ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን የተወለደው አይነተ ውልደት ቅጣይ ነው፡፡ ለማህፀኑ ማህፀኑ ካሰበ ህፃኑ ሞቷል፡፡ ሂንዱዎች ይህንኑ ሀሳብ ሞት ላይ ተጥለውበታል፡፡ ከዚህ ወገን እየሞተ ይመስለናል፡፡ ነገር ግን ከሌላ ወገን . . . ነገር ግን ሌላው ወገን የእኛ ሀሳብ ነው፡፡ እንደፈለግነው ልናደርገው እንችላለን፡፡

ሁሉም ሀይማኖት ሌላኛውን ወገን የተለየ መንገድ ያደርገዋል፡፡ ምክንየቱም እያንዳንዱ ማህበረሰብ፡ እያንዳንዱ ባህል በተለየ የቦታ አቀማመጥ፡ በተለያየ ታሪክ ላይ ስለሚመሰረት፡፡ ለምሳሌ ቲቢያዊያን ሌላኛውን ወገን ቀዝቃዛ አድርገው እያስቡትም፡፡ ቅዝቃዜ አስፈሪ ነው፡፡ በጣም ደሞ ሊቀዘቅዝ አይችልም፡፡ ቲቢታዊያን የሞተ ሰው ሞቃት እንደሆን እና ሁልጊዜም ሞቃት ሆኖ በሚዘልቅ አዲስ አለመ ውስጥ እንደሚሆን ያስባሉ፡፡

ህንዳዊያን ሁሊም ሙቅ ሆኖ እንደሚቆይ ሊያስቡ አይችሉም፡፡ በህንድ ውስጥ የሶስት ወራት ሙቀት እንኳን በጣም ብዙ ተደርጐ ይቆጠራል፡፡ ታዲያ ለዘለአለም ሙቅ ሆናችሁ ብትቆዩ ትቀቀላላችሁ! ስለ አየር ሙቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያ የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ሂንዱዎች ገነትን የሚገልፁት ሙቅም ቀዝቃዛም ያልሆነ የተመጣጠነ አየረ እንዳለው አድርገው ነው፡፡ በዚየ ሁሌ ወቅቱ ፀደይ ነው፡፡ በህንዶች የፀደይ ወራት ሁሉም አበቦተ ይጐመራሉ፤ ንፋሱ መአዛቸውን ይዞ ሲነፍስ ያውዳል፤ ወፎች ይዘምራሉ፤ ሁሉም ነገር ህያው ነው፡፡ ግን አየሩ ሙቅ አይደለም ያልሞቀም፤ ያልተዘቀዘም





ለስላሳ አየር ይኖራል፡፡ ደግመው ደጋግመው የሚያስታውሱት ይህንን ነው የተመጣጠነ ሙቀት የለው አየር በገነት የለማቋረጥ እንደሚነፍስ፡፡

ሀሳቡን የሚቀጣጥለው እንግዲህ የእናንተ አእምሮ ነው፡፡ አለበለዚያ በወዲያኛው አለም ለቲቢታዊያን፡ ወይም ለህንዳዊያን አሊያም ለሙስሊሞች የተለያየ ሊሆን አይችልም፡፡ ሙስሊሞች ሌላኛው አለም በርሃ እንደሚሆን ሊያስቡ አይችሉም፡፡ ምክንያቱ እነሱ በአረቢያን በረሀ ውስጥ ብዙ

ስቃዮችን አሳልፈዋል፡፡ ለእነሱ ሌላው ዓለም የበረሃ ገነት ነው፤ በየቦታው የበረሃ ገነት አለ፡፡ በየመቶ ማይል ርቀቶች ትንሽ ውሀና ጥቂት ዛፎች ያሉት የበረሃ ገነት የምታገኙበት ቦታ ሳይሆን በየቦታው የበረሃ ገነት አለ፤ በረሀ ብሎ ነገር አታገኙም፡፡

እኛ የየራሳችንን ሀሳብ እናስባለን፡፡ ግን ሂደቱ እየሞተ ላለ ሰውዬ አሁንም ከዚህ ቀደም በገጠመው ተሞክሮ ውስጥ ማለፍ ነው አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ አእምሮው እንስቶ ቀማ ውስጥ ካልገባ ሙሉውን የህይወቱን ኡደት ማስታወስ መጀመሩ በሚገባ ይታወቃል፤ በተወለደበት ጊዜ ወደነበረው ቅፅበት ወደ ኋላ ተመልሶ ይሄዳል፡፡ ይህንን አለም ትቶ ሲሄድ የተከሰቱትን ነገሮች በሙሉ መመልከቱ አስፈላጊ መስሎ ይታያል፡፡ በቃ በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ በህይወት የቆየባቸው ቀናት በሙሉ ልክ በፊልም እንደሚታዩ ሆነው ይንቀሳቀሳሉ፡፡

የአመቱ ቀናት መንቀሳቀሳቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ምክንያቱም ሁለት የአመቱ ቀናት መንቀሳቀሻን እለባቸው፡፡ የአመቱ ስአት በሚፈፈው ፊልም ብዙ አመታት መሸፈን አለባቸው፡፡ ቀናት በተለመደው ፍጥነት ከተንቀሳቀሱ በፊልም ቤቱ ውስጥ ለሁለት አመታት ያህል ልትቀመጡ ነው፡፡ ታዲያ ያንን ያህል ጊዜ ችሎ

የሚቀመጠው ማን ነው? ማንም? ብቻ የእሙቱ ቀናት መንቀሳቀሳቸውን ይቀጥላሉ፡፡ በቀናቱ ፍጥነት

ይለዋወጣሉ፡፡ በምንሞትበት ጊዜ መላው ሀይወት በልጭልጭታ መልክ አልፎ ይሄድና መጨረሻው ትዕበት ላዩ ይቆማል፡፡ እንደገና የሚከሰተው ይኸው ሂደት ነው፡፡ ሀይወት ሙሉውን ክብ ተጉዛ ወደነበረችበት ተመለሳ መጣች፡፡

ይህንን እንድታስታውሱ ለምን ፈለግሁ? ምክንያቱም እግዚአበሔራችሁ እያደገ እያደገ እስከመጨረሻው ትዕበት ድረስ የተጠለውን የመጀመሪያውን ቀን ፍርሃታችሁ እንጂ ሌላ ምንም አይደለም፡፡ ለዚህም ነው አንድ ሰው በወጣትነቱ ሀይማኖት የለሽ የሚሆነው፡፡ ለመሆንም ደግሞ ይቻለዋል፡፡ ነገር ግን እያረጁ ሲሄዱ ሀይማኖት የለሽ መሆን ይከብዳል፡፡ ወደመቃብሩ እየቀረበ እየመጣ ከሆነ እና አንድ እግሩን ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ ‹‹አሁንም ሀይማኖት የለም?›› ብላችሁ ብትጠይቁት ‹‹ሌላ ሀሳብ እየተከሰተልኝ ነው›› ይላችኋል ምክንያቱም ይፈራል፡፡ ‹‹ይፈጠር ይሆን?›› ብሎ ይሰጋል፡፡ መላው አለሙሙ ደብዛው እየጠፋ ነው፡፡

‹‹ የእግዚአብሔር ነገር ውድቅ ሳደርግ ከመቅዕበት የፍርሀት ስሜት ይሰማኛል›› ተብሎ ተነግሮኛል፡፡ ይህ በተጻለ ለእግዚአብሔር ያለህን ሀሳብ ለመተበል ፍርሃትህን እየገታህ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ ሀሳቡን ስታስወግድ ከመቅዕበት ፍርሃት ያቆጠቁጣል፡፡ ፍርሃት ከተመጣ ደግሞ የግድ ልትጋፈጡት ይገባችኋል፡፡ ፍርሃታችሁን ስለእግዚአብሔር በማሰብ መሸፈን ምንም የሚረዳችሁ ነገር የለውም፡፡ እንደገና እምነት ሊኖራችሁ አይችልም፡፡ እምነታችሁን አጥፍታችሁታል፡፡ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ሊኖራችሁ አይችልም ምክንያቱም ጥርጣሬያችሁ እውን ሆኗል፡፡ ስለዚህ እምነታችሁ





ለብወለድ ነው፡፡ ደግሞም የትኛው የፈጠራ ሀሳብ ከአንድ እውነት ፊት መቆም ይችላል፡፡ አሁን እግዚአብሔር ለእናንተ ንድፈ ሀሳብ ሆኖ መቅረቱ ነው ፀሎታችሁ ዋጋ አይኖረውም፡፡ ንድፈ ሀሳብ መሆኑን ታውቃላችሁ፡፡ ንድፈ ሀሳብ መሆኑን መርሳት አትችሉም፡፡

አንድ እውነታ አንድ ጊዜ ከሰማችሁ ለመርሳት አትችሉም፡፡ ይህ እንግዲህ የእውነት አንዱ ባህሪ ነው፡፡ ሀሰት ያለማቋረጥ መታወስ የለበትም፡፡ ምናልባትም ትረሱታላችሁ፡፡ ውሸት የለመደበት ሰው እውነትን ከሚናገር ሰው በተሻለ የማስታወስ ችሎታ ሊኖረው ይገባል፡፡ ምክንያቱም እውነትን የሚናገር ሰው ማስታወስ አያስፈልገውም ፡ የምትናገሩት እውነትን ብቻ ከሆነ ማስታወስ አያስፈልጋችሁም፡፡ የምትናገሩት ነገር ሀሰት ከሆነ ነው ያለማቋረጥ ማስታወስ የሚኖርባችሁ፡፡ ለአንዱ አንድ ውሸት፣ ለሌላኛው ሌላ ውሸት፣ ለአንድ ሌላ ሰው ደግሞ ሌላ ነገር ተናግራችኋል፡፡ ለእያንዳንዱ ሰው የነገራችሁትን ነገር በአእምሯችሁ ነገር ጥያቄ በተነሳ ቁጥር እንደገና የወለድ መዋሸት አለባችሁ፡፡ ስለዚህ በተከታታይ ትዋሻላችሁ፡፡ ውሸት የወለድ ቁጥጥርን አያምንም፡፡

እውነት ድንግል ናት፡፡ በፍፁም ልጅ የሏትም፡፡ በእርግጥም ደግሞ ሳጤ ናት

ይህንን ከተረዳችሁ እግዚአብሔር በቄሶች፣ በፖለቲከኞች፣ በባለስልጣናት፣ በተሳውስት እንዲሁም እናንተን የስነ ልቦና ባሪያ ሊያደርጉዋችሁ በሚፈልጉ ሰዎች የተፈጠረ ንድፈ ሀሳብ እንጂ ሌላ ምንም አይደለም፡፡ እነዚህ ሁሉ ደግሞ ሁልጊዜም እንድትፈሩ፣ በውስጣችሁ በፍርሃት እንድትርዱ አድርገው ሊያቆዩዋችሁ ይፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም ካልፈራችሁ አደገኛች ናችሁ፡፡

## እውነት ድንግል ናት፡፡ በፍፁም ልጆች የሉዋትም፡፡ በእርግጥም ደግሞ ሳጤ ናት

ፈሪ፣ ቦቅቧቃ፣ ለመሸነፍና እጁን ለመስጠት የተዘጋጀ እንዲሁም ለራሱ እና ለስብዕናው ክብር የሌለው ልትሆን ትችላላችሁ አሊያም ደፋሮች ልትሆን ትችላላችሁ፡፡ ደፋሮች ከሆናችሁ እንግዲህ ታምፃላችሁ፡፡

ይሄንን ማስተረት አትችሉም፡፡ የእምነት ሰዎች ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ አለበለዚየ ደግሞ አመፀኛ ነፍስ ትሆናላችሁ፡፡ ስለዚህ አመፀኞች እንድትሆኑ የማይፈልጉት ሰዎች፣ አመፀኛ መሆናችሁ ጥቅማቸውን ስለሚነካ፡አእምሯችሁ ላይ ክርስትና፣ አይሁድነት፣ ሙስሊማዊነት፣ ሂንዱዝም . . የሚሉ ሀሳቦችን እየተረው ውስጣችሁን በፍርሃት ያርዱታል፡፡ ይህ ለእነርሱ ጉልበት ነው፡፡ ስልጣን ለመያዝ ዝንባሌ ያለው የትኛውም ሰው፣ መላው ህይወቱን የስልጣን ፍላጐት ያለበት ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር ንድፈ ሀሳብ አስገራሚ ጠቀሜታን ያገኛል፡፡

እግዚአብሔርን ከፈራችሁ እና በእግዚአብሔር ካመናችሁ መፍራት አለባችሁ፡፡ትዕዛዞቹን ቅዱስ መፅሀፉን፣ ወሲሁን፣ ስጋ ለብሶ ዳግም መወለዱን አምናችሁ እምነቱን መከተል አለባችሁ፣ እሱንና ወኪሎቹንም መከተል ይኖርባችኋል፡፡

መሠረቱ ግን እሱ የለም፡፡ ወኪሎቹ ብቻ ነው ያሉት፡፡ ይሄ እንግዲህ ያልተለመደ ነገር ነው፡፡ ሀይማኖት ከምንም በላይ አስገራሚ ነገር ነው፡፡ አለቃ የሚባል ነገር የለም፡፡ ነገር ግን በመሃል ሆነው ስራውን የሚያቀላጥፉ ወኪሎተ . . . ቄሶች፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሶች፣ ሊቀ ጳጳሳት፣ መሲሆች በተዋረድ አሉ፡፡





ይሁንና ኢየሱስ ስልጣኑንና ሀይሉን ከእግዚአብሔር አግኝቷል፡፡ ብቸኛው ልጁም ነው፡፡ ሊቀጳጳሱ ስልጣናቸውን ከኢየሱስ አግኝተዋል፡፡ ብቸኛ እውነተኛ እና የማይሳሳቱ ወኪልም ናቸው፡፡ እንደዚህ እያለ እስከ ታችኛው ቄስ ድረስ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ በየቦታው ቅጥረኞች አሉ፡፡ ከናንተ ትጠይቃላችሁ፣ እነሱ ደግሞ የጠየቃችሁትን ያደርጉላችኋል፡፡

ፈሪ ሆናችሁ እንድትቀሩ የረዳችሁት ይህንን ሀሳብ ወዲያ መጣል አለባችሁ፡፡ በፍርሃት ውስጥ ዘልቃችሁ ማለፍ እና እንደ ሰብአዊ እውነታ ልትቀበሉት ይገባል፡፡ የሚያስፈልገው ወደ ውስጥ ዘልቆ መሄድ ነው፡፡ ወደ ፍርሃታችሁ ውስጥ የበለጠ ጠልቃችሁ ስትረቡ ብዙም አታገኙትም፡፡

የፍርሃትን የታችኛውን የእለት ወለል ስትዳስሱት በሳቅ ትፈርሳላችሁ፡፡ ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም፡፡

እናም ፍርሃት ደብዛው ሲጠፋ የዋህነት አለ፡፡ ይህ የዋህነት የአንድ ሀይማኖተኛ ሰው ዋና ፍሬ ነገሩ ነው፡፡

ያየዋህነት በዓለም ላይ ያለው ብቸኛው ተአምር ነው፡፡

በየዋህነት ማንኛውም ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉም ነገር በውስጥም በውጪም በዙሪያችሁ ይገኛል፡፡ ፍፁም የዋህ በጥልቀት የምትመሰገኑ ስትሆኑ እኔ ይህንን እልለውም፡፡ ምክንያቱም ስትፀልዩ የሆነ ነገር እየጠየቃችሁ ነው፡፡ እኔ ይህንን ጥልቅ አመስረኝነት ነ... የምለው፣ ነገር ግን ገና ድሮ ለተሰጣችሁ ነገር እያመሰገናችሁ ነው

የበለጠ ነገር መጠየቅ ደግሞ ያስጠላል፡፡ የተቀበላችሁን ... ይገባችሁ ማመስገን ይገባችኋል፡፡ ከሁሉ የበለጠ ቆንጆ ... አመስጋኞች ስትሆኑ እሁንም፣ እሁንም ህይወት ያሽርጉደጉድላችኋል፡፡ በ... ኡደት ይሆናል፡፡ ባገኛችሁ ቁጥር ጠበለጠ አመስጋኝ ትሆና... ባገኛችሁ ቁጥር ታገኛላችሁ ማለቂየ የለውም፡፡ የትየለሌ ሂደት ...



CAMERA

***እሁን የቀራችሁ ብቸኛ መንገድ ወደ ፍርሃታችሁ ውስጥ መሄድ ነው፡፡ በፀጥታ ወደውስጡ ዝለቁ፡፡ ስትዘልቁ ጥልቀቱን ግወቅ ትችላላችሁ፡፡ እናም እንዳንድ ጊዜ በጣም ጥልቀት የሌለው ሆኖ ይገኛል***

## አንድ ታሪክ ልንገራችሁ፡-

በሌሊት በእግሩ እየተጓዘ ያለ አንድ ሰው ድንጋይ አዳለጠው ቦታው ጥልቀት የለው ገደል መሆኑን ስለሚያውቅ በብዙ ሺህ ጫማ ርቀት ቁልቁል እንዳይወድቅ ፈራ፡፡ ከዚየ ድንጋዩ ላየ የተንጠለጠለውን ቅርንጫፍ ያዘ፡፡ ሌሊቱን በሙሉ ሲያየው የነበረው ታዲያ መጨረሻ የሌለው ገደል ነበር፡፡ ሲሶክ የገዛ ራሱ ድምን ነጥሮ ይመለሳል፡፡

ያንን ሰውዬ ሙሉ ሌሊት ያሳለፈውን ሰቃይ እስቡት፡፡፡ በእያንዳንዷ ቅፅበት ሞት እብሮት ነበር፡፡ እጆቹ እንደበረዶ እየቀዘቀዙ ቁልቁል ተመለከተና ሳቀ፡፡ ምንም ገደል አልነበረም፡፡ ከስድስተ ኢንች ርቀት በኋላ አንድ እለት ነበር፡፡ ሌሊቱን በሙሉ እንቅልፉን ተኝቶ በእረፍት ማሳለፍ ይችል ነበር፡፡ እለቱ በቂው ነበር፡፡ ነገር ግን ሌሊቱን በእሰቀያሚ ሁኔታ አሳለፈ፡፡

ከገዛ ራሴ ተሞክሮ በመነሳት ምን ልላችሁ እችላለሁ መሰላችሁ? ፍርሃት ከስድስት ኢንች ያልበለጠ ጥልቀት ነው ያለው፡፡ እሁን እንግዲህ የዛፉን ቅርንጫፍ የሙጥኝ ብላችሁ ህይወታችሁ በእግራችሁ መቆም የእናንተ ፈንታ ነው፡፡ ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም፡፡







# ስለ ደራሲው

የኦሾ ትምህርቶች ለእመዳደብ አይመቹም፡፡ ከግላዊ የፍቺ ፍለጋ ጀምሮ እጅግ አንገብጋቢ እስከሆኑ የዘመኑ ማህበረሰብ የተጋፈጣቸውን ጉዳዮች ይሸፍናሉ፡፡ መፅሀፎቹ ለመፅሀፍ እንባቢ ተብለው የተፃፉ ሳይሆን በሰላሳ እምስተ እመታት ጊዜ ውስጥ ለእለም እተፍ ታዳሚዎች ከቀረባቸው ያልተዘጋጀባቸው የድምፅና የቪዲዮ ንግግሮች በፅሁፍ የተገለበጡ ናቸው፡፡ ኦሾ በለንደኑ ሰንደይ ታይምስ ከ1000ዎቹ የ20ኛው ክ/ዘመን ተጽእኖ ፈጣሪዎች አንዱ፣ እንዲሁም በአሜሪካዊው

ደራሲ በቶም ሮቢንስ ሐክርስቶስ በኋላ የተፈጠረ በጣም አደገኛ ሰው ተብሎ ተንግሮለታል፡፡

እሾ ስለ ገዛ ራሱ ሲናገር ለአዲስ የሰው ልጅ መወለድ አመቺ ሁኔታዎችን እየፈጠረ መሆኑን ይናገራል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይህንን አዲስ የሰው ልጅ ፡ ዞብራ ዘ ቡድሃ፡ ብሎ ይገልፀዋል፡፡ ትርጉሙም የግሪኩን የዞብራን ዓለማዊ ደስታና የጉተማ ቡድሃን ፀጥ ያለ የመንፈስ እርጋታ አጣምሮ የሚደሰት ማለት ነው፡፡ በእሾ ስራዎች አጠቃላይ ገፅታ ላይ ጊዜ የማይሽረውን የምስራቁን ዓለም ጥበብ እና በምዕራብ አለም ሳይንስና ቴክኖሎጂ አምት ሀይል ያተፈ ራዕይ እንደክር ተጠምዋቸ ይታያል፡፡

እሾ በተጨማሪም ለውስጣዊ ለውጥ ባበረከታቸው አብዮታዊ አስተዋፅዎችም ይታወቃል፡፡ በዚህ አስተዋፅኦው በተመስጦ ማሰላሰልን በፈጣን ለውጥ ላይ የሚገኘው ተዛማጅ ህይወት ላይ ጠቀሜታ እንዲኖረው አስችሎታል፡፡ በአይነት ልዩ የሆኑት የአክቲቭ ሜዲቴሽንስ (ብርቱ የሆነ በተመስጦ የማሰላሰል) አሳቤዎቹ በመጀመሪያ ደረጃ የተከማቹትን የአካልና የአእምሮን ውጥረቶች በማስወጣት ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡ በዚህም የተንሳ ከሀሳብ ነፃ የሆነ እና ዘና ያለ በተመስጦ የማሰላሰል ተግባርን ለመለማመድ ቀላል ይሆናል፡፡

በደራሲው የተጻፉ ሁለት የግለ ታሪክ ስራዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህም፡-

- አውቶባዮግራፊ ኦፍ ኤ ስፒሪችዋል ኢንኮሬክት ሚስቲክ፡ ሴይንት ማርቲንስ ፕሬስ፡ አይ.ኤስ.ቢ.ኤን 0-312-28071-8
- ግሊምሰስ ኦፍ ኤ ጎልደን ቻይልድ ሁድ፡ ዘ ሬቤል ፐበሊሺንግ ሀውስ፡ ኢንድያ፡ አይ- ኤስ.ቢ.ኤን. 8172610726

‹‹ልጆች ከክርስቶስ በኋላ የተፈጠረ በጣም [illegible] ››

አሜሪካዊው ደራሲ ቶም ሮቢንሰን

‹‹ልጆች ከጊዜዎቹ የጊዜ መንገድ ፈጣሪዎች ናቸው፡፡››

የለንደኑ ለንዴይ ታይምስ

[illegible] መንገዱን ስጀምረው ብቻዬን ነበርኩ [illegible] መንገዴን የሚከተሉ ሰዎች በዝተው [illegible] ሆኗል፡፡እኔ ማንንም ወደ መንገዴ [illegible] ልቤ የፈቀደውን አደረግሁ

እንጂ፡፡የእኔ [illegible] በዓለም የሚኖርን የማንንም [illegible] ማድመጥ አይደለም...

‹‹ሰዎች ‹በልጅነትህ ሳይቀር አዕምሮህ የበሳና በጣም ደፋር [illegible] የቻልከው እንዴት ነው›› ብለው ይጠይቁኛል፡፡ የዚህ ምክንያቱ ባለፈው ህይወቴ ሰዎች ከአናንቶ በተለየ ሁኔታ መምጣቴ ነው፡፡ [illegible] እንወለዳለን!

እኔም ከዚህ የተለየ ያደረግሁት ነገር የለም...

[illegible] የምትቀበሉት ነገር እርግጠኛ ነገር በመሆኑ [illegible]

[illegible]

[illegible] በቀላሉ [illegible]

[illegible]

[illegible] እንድትማሩ አደርጋችኋለሁ...

እሾ

@shuktus_books